# የፕራክቲከም፣ የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥን አተገባበር በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሰርተፍኬት (10+1) መርሃ ግብር

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ
ት/ቤት የቀረበ ጥናት

ለአማርኛ ማስተማር (TeAm) ኤም. ኤ. ዲግሪ
ከፊል ማሟያነት የተሰናዳ

ተሰጠ አሰፋ

ሰኔ፥ 1997 ዓ.ም

# በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

## የፕራክቲከም፣ የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥን አተገባበር በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሰርተፍኬት (10+1) መርሃ ግብር

በ

ተሰጠ አሰፋ

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |

# ምስጋና

በቅድሚያ ይህ ጥናት ተወጥኖ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አቅጣጫ ያመላከተኝ፣ ገንቢ የሆኑ ምክሮችን የለገሰኝና የጥናቱን ረቂቅ ደጋግሞ በማረም ሙያዊ ድጋፉ ላልተለየኝ አማካሪዬ አቶ ዓለም እሸቱ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ባለቤቴ ስርጉት ታደሰ የእኔን እዚህ ደረጃ መድረስ አጥብቃ በመሻት ሙሉ የትምህርት ወጪዬን በመሸፈንና በሐሳብ ከጎኔ በመሆን ለስኬት አብቅታኛለችና ውጤቱ የሁለታችንም በመሆኑ እንኳን ደስ አለን፡፡

ለዚህ ጥናት እውን መሆን የአቶ ሰለሞን ተሰማ ገንቢ አስተያየትና የሥራ ባልደረባዬ ዜና ነጋሽ እገዛ አስተዋፅኦ ስለነበረው አመሰግናቸዋለሁ፡፡

ለጥናቱ የሚያስፈልጉኝን መረጃዎች በማሰባስብበት ወቅት አቶ ዳምጠው ብዙነህ እና ወንድወሰን ሙሉጌታ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ቤተ መጻሕፍት ባልደረቦች፣ አቶ ቦንሳ ባይሳ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የፕራክቲከምና ፕሮግራም አስተባባሪ፣ አቶ ሰለሞን ገላው በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ መምህር፣ የ1997 ዓ.ም ሰርተፍኬት መርሃ ግብር ሱፐርቫይዘሮችና ሰልጣኝ መምህራን፣ እንዲሁም የተባባሪ ት/ቤቶች ርዕሳነ መምህራን ያደረጉልኝ እገዛ ላቅ ያለ በመሆኑ ላመሰግናቸው እወዳለሁ፡፡

የሥራ ባልደረቦቼ ወ/ት ርብቃ ሽንቁጤ፣ ገነት ከበደና ትዕግስት አየለ ከድህረ ገጽ ያገኘኋቸውን መረጃዎች በማተምና የጥናቱን ረቂቅ በኮምፒውተር በማረም ቀና ትብብራቸው ስላልተለየኝ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

በመጨረሻም ይህን ጥናት በመተየብ አሁን ያለውን መልክ እንዲይዝ ያደረገችው ወ/ት ሰብለ ተሰማ ባለውለታዬ ናት፡፡

# ማውጫ

| | ገጽ |
|---|---|
| አርዕስት | |
| ምስጋና | III |
| ማውጫ | IV |
| የሠንጠረዥ ዝርዝር | VII |
| የአባሪዎች ዝርዝር | IX |
| አጠቃሎ | X |
| ምዕራፍ አንድ:- መግቢያ | 1 |
| 1.1 የቃላትና ሐረጋት ፍቺ | 1 |
| 1.2 የጥናቱ ዳራ | 2 |
| 1.3 የጥናቱ ዓላማ | 6 |
| 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ/አስፈላጊነት | 6 |
| 1.5 የጥናቱ ክልልና ገደብ | 7 |
| 1.6 ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ | 8 |
| ምዕራፍ ሁለት:- የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት | 9 |
| 2.1 የመምህራን ሥልጠና ምንነት | 9 |
| 2.2 የመምህራን ሥልጠና ታሪካዊ ዳራ | 11 |
| 2.3 መምህራን እንዴት ይሰልጥኑ? | 12 |
| 2.4 በመምህራን ስልጠና የፕራክቲከም፣የማስተማር ልምምድ፣ የሱፐርቪዥንና የምልከታ አተገባበር | 15 |
| 2.4.1 የፕራክቲከም ምንነትና አተገባበር | 15 |
| 2.4.2 የማስተማር ልምምድ ምንነትና አተገባበር | 18 |
| 2.4.3 የማስተማር ልምምድ አስፈላጊነት | 22 |
| 2.4.4 የሱፐርቪዥን ምንነትና አቀራረብ | 25 |
| 2.4.4.1 የሱፐርቪዥን ምንነት፣ ተግባርና ዓላማ | 25 |
| 2.4.4.2 የሱፐርቪዥን አቀራረቦች | 26 |
| 2.4.5 ምልከታ | 30 |
| 2.4.5.1 ምልከታ ምንድነው ? | 30 |
| 2.4.5.2 የክፍል ምልከታ ለምን? | 30 |
| 2.4.5.3 የክፍል ምልከታ እንዴት? | 32 |

2.4.5.4 ድህረ ምልከታ የምግበ መረጃ አቀራረብ 36
2.5 በመምህራን ስልጠና የማስልጠኛ ተቋማት፣ የሱፐርቫይዘሮች፣ የተባባሪ ትምህርት ቤቶች፣ የነባር መምህራንና የተማሪ አስተማሪዎች ተግባርና ኃላፊነት 37
2.5.1 የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት 37
2.5.2 የሱፐርቫይዘሮች ተግባርና ኃላፊነት 38
2.5.3 የተባባሪ ት/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት 38
2.5.4 የነባር መምህራን ተግባርና ኃላፊነት 39
2.5.5 የተማሪ አስተማሪዎች ተግባርና ኃላፊነት 41
2.6 በማስተማር ልምምድና ሱፐርቪዥን ላይ የተካሄዱ ቀደምት ሐገራዊ ጥናቶች ቅኝት 42

ምዕራፍ ሦስት:- የጥናቱ ዘዴና የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች.........................46
3.1 የጥናቱ ተተኳሪዎች 46
3.2 የጥናቱ መረጃ አሰባሰብ ዘዴ 48
3.2.1 የተማሪ አስተማሪዎች ማስታወሻ 48
3.2.2 ተከታታይ ምልከታ 49
3.2.3 የጽሁፍ መጠይቅ 49
3.2.4 የመገምገሚያ ቅጽ 50

ምዕራፍ አራት:- የመረጃ ትንተናና የተገኘው ውጤት 52
4.1 የሱፐርቫይዘሮች የትምህርት ደረጃና የአገልግሎት ዘመን 52
4.2 የጥናቱ ተተኳሪ የተማሪ አስተማሪዎች ዕድሜ፣ የ10ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ውጤትና ወደ ኮሌጅ አገባባቸው 53
4.3 የፕራክቲከም፣ የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥን አተገባበር በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ 54
4.3.1 የፕራክቲከም ሂደትና አተገባበር 54
4.3.1.1 የፕራክቲከም ሂደት 55
4.3.1.2 የፕራክቲከም አተገባበር 60
4.3.1.2.1 ነባር መምህራን በፕራክቲከም ትግበራ 63
4.3.1.2.2 የፕራክቲከምና የማስተማር ልምምድ ተደጋጋፊነት 64

4.3.1.2.3 የተማሪ አስተማሪዎችና ሱፐርቫይዘሮች
ስለ ፕራክቲክም ያላቸው አስተያየት 66
4.3.2 የማስተማር ልምምድ ሂደትና አተገባበር 68
4.3.2.1 ቅድመ ማስተማር ልምምድ ውይይት 70
4.3.2.2 በማስተማር ልምምድ ሂደት
የሱፐርቫይዘሮች ክትትል 74
4.3.2.3 በማስተማር ልምምድ የመደበኛ መምህሩን
ክትትል 76
4.3.2.4 የተማሪ አስተማሪዎችና ሱፐርቫይዘሮች
ለማስተማር ልምምድ ያላቸው አስተያየት 80
4.3.3 የሱፐርቪዥን አቀራረብና አተገባበር 81
4.3.3.1 ሱፐርቪዥኑ እንዴት እየተተገበረ ነው? 81
4.3.3.2 የምግበ መረጃ አቀራረብ 83
4.3.3.2.1 በምግበ መረጃ ልውውጥ የተማሪ
አስተማሪዎችና የሱፐርቫይዘሮች ሚና 86
4.3.3.2.2 የምግበ መረጃ ውይይቱ የትኩረት
አቅጣጫና የሱፐርቫይዘሮች ሃሳብ
ተቀባይነት 87
4.3.3.2.3 የምግበ መረጃው አጠቃላይ ትኩረት 88
4.3.3.3 የተማሪ አስተማሪዎችና ሱፐርቫይዘሮች ሱፐርቪዥኑን
በሚመለከት ያላቸው አስተያየት 90
4.3.3.3.1 የተማሪ አስተማሪዎች አስተያየት 90
4.3.3.3.2 የሱፐርቫይዘሮች አስተያየት 91
ምዕራፍ አምስት፡- ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳብ 93
5.1 ማጠቃለያ 93
5.2 የመፍትሄ ሃሣብ 95
ዋቢ ጽሁፎች 97
አባሪዎች 101

# የሰንጠረዥ ዝርዝር


| ሠንጠረዥ | ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|
| አንድ | በሱፐርቫይዘሮችና በተማሪ አስተማሪዎች መካከል ሊኖር የሚችል ግንኙነት | 13 |
| ሁለት | ባለ ሦስት ደረጃ የማስተማር ልምምድ | 23 |
| ሦስት | ሱፐርቫይዘራዊ አቀራረቦች | 29 |
| አራት | የተተኳሪዎች ሴክሽንና ቁጥር | 46 |
| አምስት | የተመረጡ ተተኳሪዎች የፕራክቲከምና የማስተማር ልምምድ ፕሮግራም | 47 |
| ስድስት | የተተኳሪ ሱፐርቫይዘሮች የትምህርት ደረጃና የአገልግሎት ዘመን | 52 |
| ሰባት | የተተኳሪ ተማሪ አስተማሪዎች ዕድሜ፣ የ10ኛ ክፍል ውጤትና ወደ ተቋም አገባብ | 54 |
| ስምንት | የንድፈ ሐሳብ ትምህርትና ፕራክቲከም መጣጣም | 55 |
| ዘጠኝ | የንድፈ ሐሳብ ትምህርትና ፕራክቲከም ተደጋጋፊነት | 56 |
| አስር | ቅድመ ፕራክቲከም ውይይትን በተመለከተ የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ | 57 |
| አስራ አንድ | ቅድመ ፕራክቲከም ውይይትን በተመለከተ የሱፐርቫይዘሮች ምላሽ | 58 |
| አስራ ሁለት | የፕራክቲከም ሪፖርት አዘገጃጀት | 58 |
| አስራ ሶስት | የሱፐርቫይዘሮች እገዛ | 59 |
| አስራ አራት | በፕራክቲከም ሪፖርት ላይ የተደረገ ውይይት ስለመኖሩ | 60 |
| አስራ አምስት | በፕራክቲከም ሪፖርት ላይ ውይይት ስለመደረጉ | 61 |
| አስራ ስድስት | በፕራክቲከም አራት ተግባራት መገባደጃ ላይ የተ∝ሄደ ውይይት ስለመኖሩ | 62 |
| አስራ ሰባት | የመደበኛ (ነባር) መምህራን ፈቃደኝነት | 64 |
| አስራ ስምንት | የፕራክቲከምና የማስተማር ልምምድ ተደጋጋፊነት | 64 |
| አስራ ዘጠኝ | በኮሌጁ የቀሰሙት የንድፈ ሐሳብ ትምህርት ለማስተማር ልምምዱ የነበረው ፋይዳ | 69 |
| ሃያ | ለማስተማር ልምምድ መሳካት የፕራክቲከም ምልከታ ያለው ፋይዳ | 70 |

| | | |
|---|---|---|
| ሃያ አንድ | ቅድመ ማስተማር ልምምድ ውይይት | 70 |
| ሃያ ሁለት | ቅድመ ማስተማር ልምምድ ገለፃ | 71 |
| ሃያ ሦስት | ሱፐርቫይዘሮች የሚገኙበትን ጊዜ ስለማሳወቃቸው | 72 |
| ሃያ አራት | ሱፐርቫይዘሮች የጉብኝት ጊዜን ስለማሳወቃቸው | 73 |
| ሃያ አምስት | የሱፐርቫይዘሮች ድጋፍ | 73 |
| ሃያ ስድስት | በማስተማር ልምምድ የሱፐርቫይዘሮች ክትትል | 74 |
| ሃያ ሰባት | ሱፐርቫይዘሮች የማስተማር ልምምድን በዕቅድና ፕሮግራም ስለመከታተላቸው | 74 |
| ሃያ ስምንት | የሱፐርቫይዘሮች ተጨማሪ የስራ ጫና | 75 |
| ሃያ ዘጠኝ | የተባባሪ ት/ቤት መደበኛ መምህራን እገዛ | 77 |
| ሰላሳ | ሱፐርቫይዘሮችና መደበኛ መምህራን በጋራ ስለመስራታቸው | 79 |
| ሰላሳ አንድ | የሱፐርቫይዘሮችና መደበኛ መምህራን በጋራ መስራት | 79 |
| ሰላሳ ሁለት | ለማስተማር ልምምዱ ስለተመደበው ጊዜ | 80 |
| ሰላሳ ሦስት | የሱፐርቫይዘሮች ምግበ መረጃ አቀራረብ | 84 |
| ሰላሳ አራት | በድህረ ማስተማር ልምምድ ውይይት ወቅት የተማሪ አስተማሪዎች ስሜት | 84 |
| ሰላሳ አምስት | የውይይቱ መንፈስ | 85 |
| ሰላሳ ስድስት | የተማሪ አስተማሪዎችን ስብዕና ላለመንካት የተደረገ ጥንቃቄ | 85 |
| ሰላሳ ሰባት | የተማሪ አስተማሪዎች ለሱፐርቫይዘሮቻቸው ያላቸው አመለካከት | 86 |
| ሰላሳ ስምንት | የምግበ መረጃ ውይይቱ ትኩረት | 87 |
| ሰላሳ ዘጠኝ | የሱፐርቫይዘሮች ሐሳብ ተቀባይነት | 88 |
| አርባ | የምግበ መረጃው ፋይዳ | 90 |

# የአባሪዎች ዝርዝር


| የአባሪ ቁጥር | ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | የማስታወሻ አያያዝ መመሪያ | 101 |
| ፪ | የተማሪ አስተማሪዎች ማስታወሻ ናሙናዊ ጥንቅር | 103 |
| ፫ | የሱፐርቫይዘሮችና የተማሪ አስተማሪዎች ውይይት ምልከታ ናሙናዊ ጥንቅር | 115 |
| ፬ | በተማሪ አስተማሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ | 128 |
| ፭ | በሱፐርቫይዘሮች የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ | 133 |
| ፮ | የክፍል ምልከታ መከታተያ ቅጽ ናሙና | 136 |

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ላይ የተመሠረተ ነው:: የጥናቱ ዋና ዓላማም በኮሌጁ መምህራንን የማሰልጠን ሂደት የፕራክቲከም፣ የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥንን አተገባበሩን በመመርመር ያለውን ድክመትና ጥንካሬ ማሳየት ላይ ያተኩራል:: ጥናቱ በተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝቱ ስለ መምህራን ስልጠና ምንነትና ታሪካዊ ዳራ፣ የፕራክቲከምና የማስተማር ልምምድ ምንነት አስፈላጊነትና አተገባበር እንዲሁም የሱፐርቪዥንና የምግበ መረጃ አቀራረብን ለመዳሰስ ሞክሯል:: ይህ ጥናት ይዟቸው የተነሳቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተማሪ አስተማሪዎች ማስታወሻ፣ ተከታታይ ምልከታ፣የጽሁፍ መጠይቅና የመገምገሚያ ቅጽ የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች ሥራ ላይ ውለዋል::

በነዚህ መሳሪያዎች አማካይነት የተሰበሰቡት መረጃዎች ትንተና እንደሚያመለክተው በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በ1997 ዓ.ም የመጀመሪያ ደረጃ የአንደኛ ሳይክል (1ኛ–4ኛ) መምህራንን በማሰልጠኑ ሂደት በርካታ የአተገባበር ችግሮች እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል:: ከችግሮቹ መካከል በኮሌጁ የቅድመ ፕራክቲከምና የማስተማር ልምምድ ውይይት አለመካሄድ፣ ሱፐርቫይዘሮችና የተባባሪ ት/ቤት መደበኛ መምህራን ስለፕራክቲከም ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ በመሆኑ ፕራክቲከሙን በአግባቡ ለመከታተል አለመቻላቸው፣ ኮሌጁ ከተባባሪ ት/ቤቶች ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለመመስረቱ፣ በሱፐርቫይዘርነት የሚመደቡ የኮሌጁ መምህራን የስራ ጫና ከግንዛቤ ውስጥ ሳይገባ በኮሌጁ መመደባቸው፣ ሱፐርቪዥኑን እንደ መገምገሚያና መመዘኛ መቁጠር፣ በድህረ ማስተማር ውይይት በተማሪዎች ደካማ ጎን ላይ ብቻ እንዲያተኩር ማድረግ የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል::

በአጠቃላይ በኮሌጁ የሚካሄደው የመምህራን ስልጠና በብዙ ችግሮች ውስጥ ያለ ሂደት መሆኑ ግልጽ ነው:: ስለዚህ ስልጠናው ከችግሮቹ ተላቆ አተገባበሩ የተሳካ ይሆን ዘንድ ኮሌጁ፣ ሱፐርቫይዘሮች፣ የተባባሪ ት/ቤቶች መደበኛ መምህራንና የተማሪ አስተማሪዎች የተቀናጀ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል::

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የቃላትና ሐረጋት ፍቺ

በዚህ ጥናት ውስጥ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጉመው አገልግሎት ላይ የዋሉ ቃላትና ሐረጋት በጣም በርካታ ናቸው:: አብዛኛዎቹ የእንግሊዝኛ ቃላትና ሐረጋት ይዘው የሚገኙት ጽንሰ ሐሳብ የተለመደ ነው:: ይሁን እንጂ አንዳንዶቹ ቃላትና ሐረጋት የሚገልጹት ጽንሰ ሐሳብ በጣም ሰፊ ሊሆን እንደሚችል ይታወቃል:: ስለዚህ እንዲህ ያሉትን ቃላትና ሐረጋት ሊይዙ የሚችሉትን ጽንሰ ሐሳብ በቅድሚያ ማሳወቁ የዚህ ጥናት አንባቢዎች ግር እንዳይሰኙ ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል:: በመሆኑም የእንግሊዝኛ ስያሜ ቃላቱን ከአማርኛ አቻቸው ጋር እንደሚከተለው ማቅረቡ ተገቢ ይሆናል::

| | |
|---|---|
| ፕራክቲከም | Practicum (School experience) |
| የማስተማር ልምምድ | Teaching practice or practice teaching |
| አዎንታዊ ግንኙነት | Orientation that help |
| አሉታዊ ግንኙነት | Orientation that hinder |
| ጥያቄና መልስ | Elicitation |
| የቡድን ውይይት | Plenary discussion |
| ቅድመ ፕራክቲከም | Pre-practicum |
| ሙሉ ፕራክቲከም | Full-practicum |
| ክሊኒካል ልምድ | Clinical experience |
| ፍዝ ምልከታ | Sitting with Nellie |
| ንቁ ምልከታ | Pure observation |
| ሙሉ ጥልቀት | Total immersion |
| ተግባራዊ ትንታኔ | Task analysis |
| ንዑስ ማስተማር | Micro-teaching |
| የቡድን ማስተማር ልምምድ | Group instructional practice |
| ባለ ሁለት ትኩረት ስልት | Double focus technique |
| ልይይታዊ ሞዴል | Separatist model |
| አጋጣሚያዊ ሞዴል | The coincidental model |

| | |
|---|---|
| አዛማጅዊ ሞዴል | The relationist model |
| የግላውያን ሞዴል | The individualist model |
| ትዕዛዛዊ/ሱፐርቫይዘሪ/ አቀራረብ | Supervisory approach |
| አማራጫዊ አቀራረብ | Alternative approach |
| ኢ.ትዕዛዛዊ አቀራረብ | Non-directive approach |
| ትዕዛዛዊ ባህሪ | Behavior prescription |
| ሀሳብ ገላጭ | Idea interpretation |
| ድጋፍ ሰጭ | Person supporter |
| መራሄ ሱፐርቪዥን | Directive supervision |
| ባለአማራጭ ሱፐርቪዥን | Alternative supervision |
| ቅንጅታዊ ሱፐርቪዥን | Collaborative supervision |
| ኢ.አማራጫዊ ሱፐርቪዥን | Non-altetnative supervision |
| ፈጠራዊ ሱፐርቪዥን | Creative supervision |
| ራስ አገዝ ሱፐርቪዥን | Self help-explorative supervision |
| ትዕዛዛዊ አቀራረብ | Classic prescriptive approach |
| ትብብራዊ አቀራረብ | Classic collaborative approach |
| ምግበ መረጃ | Feedback |
| የመገምገሚያ ቅጽ | Evaluation sheet |
| የተባባሪ ት/ቤት መምህራን | Cooperative school teachers |
| የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት | TGE (Tranistional Government of Ethiopia) |
| ትምህርት ሚኒስቴር | MOE (Ministry of Education) |

## 1.2 የጥናቱ ዳራ

ለአንድ ሀገር ዕድገት መፋጠን ትምህርት የሚጫወተው ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ምክንያቱም ግለሰቦችም ሆኑ በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ለሀገር ዕድገት እውን መሆን ሁሉን አቀፍ እንቅስቃሴና ተሳትፎ የሚያደርጉት በትምህርት ያገኙትን ዕውቀት፣ ችሎታ፣ ክሂልና አመለካከት በመጠቀም ነው (TGE 1994:1)፡፡ ለዚህም ነው ትምህርት በአንድ ሀገር ግንባታ ማዕከላዊው አንቀሳቃሽ ሞተር ስለሆነ የትኛውም ሀገር ያለትምህርት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እመርታ ሊያሳይ የማይችለው፡፡

የትምህርት ዋነኛ ዓላማም በየትኛውም ደረጃ ችግርን የመፍታት አቅም ያለው ማህበረሰብን ማፍራት ነው፡፡ የሰው ልጅ ጎጂና ጠቃሚ ልምዶችን ለመለየት የሚችለው በቀሰመው ትምህርት አማካይነት ነው፡፡ ዕውቀትን የመቅሰሙና የመገብየቱ አይነተኛ ዓላማም በሳይንስና ቴክኖሎጂ እየታገዘ የሚኖርበትን አካባቢ በዘላቂነት ለኑሮው እንዲመቸው ለማድረግ፣ ለማስተካከል፣ ለመለወጥና ሁለንተናዊ የሆነ ዕድገት ለማምጣት ነው (Omotoso 1986:1)፡፡

ሀገርን ለማሳደግ ሲታሰብ ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት አስፈላጊ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ጥራቱን ስለጠበቀ ትምህርት ሲነሳ ደግሞ በርካታ ነጥቦች አብረው መነሳታቸው አይቀርም፡፡ ከነዚህም ውስጥ የመጀመሪያውን ስፍራ የሚይዘው የመምህራን ስልጠና ጉዳይ ይሆናል፡፡ የማስተማር ሥራ የማንኛውም ሙያ መሠረት ነውና፡፡ ስለዚህ የማስተማር ሙያ ተወዳጅና ተፈላጊ ይሆን ዘንድ የመምህራን አሰለጣጠን ጥልቅና ጥራት ያለው መሆን ይኖርበታል (Hailom 1997)፡፡ ለተማሪዎቻቸው የተለያዩ ተግባራትን የሚያቀርቡ፣ ተማሪዎቻቸውን የሚያበረታቱና ለትምህርት ያላቸውን ፍላጎት የሚያነቃቁ፣ ተማሪዎቻቸው በክፍል ውስጥ የቀሰሙትን ዕውቀት ከነባራዊው ዓለም ገጠመኞቻቸውና ከወደፊት ራዕያቸው ጋር ማገናዘብ እንዲችሉ የሚያደርጉ በሚገባ የሰለጠኑ መምህራን ናቸው (Dobbyn 1979:1)፡፡

Abraham and et al. (1999:5-6) ትምህርት ሚኒስቴር (1986)ን በመጥቀስ እንደገለጹት እነዚህ በአግባቡ የሰለጠኑ መምህራን ደግሞ፡-

- የትምህርት ኃላፊነትን በአግባቡ የሚወጡ፣ ለሙያው ፍቅርና ክብር ያላቸው፣
- በራሳቸው የሚተማመኑና በትክክል የማስተማሩን ሥራ የሚያካሄዱ፣
- ሙያቸውን ለማሳደግ በግላቸው የሚጥሩ፣
- ሥራቸውን በስርዓት መምራት የሚችሉ ፣ በእኩልነት የሚያምኑ
- ኃላፊነታቸውን የሚያውቁና የሚቀበሉ፣
- ለትምህርት ዕድገት፣ ጥራትና ጥልቀት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማድረግ የሚጥሩ፣
- ከህዝባዊ አመለካከት፣ አስተሳሰብና እምነት ጋር መራመድ የሚችሉ፣
- ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

በሀገራችን ዘመናዊ ትምህርት ታሪክ መምህራንን ማሰልጠን የተጀመረው በ1944/45 ዓ.ም በዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት ተከፍቶ በነበረው የመጀመሪያው መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ነበር (Abraham and et al. 1999, Hailom 1997)፡፡ በዚያን ወቅት በመምህርነት ሙያ ይሰለጥኑ የነበሩት በትምህርታቸው ላቅ ያለ ውጤት የነበራቸው ተማሪዎች ነበሩ፡፡ ኮሌጁ በ1949 የመምህራን ማሰልጠኛ ት/ቤት ተብሎ መጠራት የጀመረ ሲሆን በ1952 ዓ.ም ወደ ሀረር እንዲዛወር ተደርጎ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎችን በመቀበል ለአራት ዓመታት ማሰልጠን እንደጀመረ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ብዙም ሳይቆይ ለአራት ዓመታት ይሰጥ የነበረው ትምህርት ወደ ሦስት

ዓመት እንዲያጥር ሲደረግ ቅበላውም ከ9ኛ ክፍል ሆነ (Abraham and et al. 1999:10-11)። ቀስ በቀስ ሌሎችም የመምህራን ማሰልጠኛ ት/ቤቶች የተከፈቱ ሲሆን ከእነሱም ውስጥ በ1956 ዓ.ም የማጀቴና ደብረ ብርሃን ማህበረሰብ መምህራን ት/ቤቶች ይገኙባቸዋል። የማጀቴ ት/ቤት በ1966 ዓ.ም ቀደማዊ ኃይለሥላሴ የቀን ት/ቤት ተብሎ መደበኛ መምህራን ማሰልጠኛ ሲሆን የደብረ ብርሃን መምህራን ማሰልጠኛ ት/ቤት ደግሞ ከ1963 ዓ.ም ጀምሮ ወደ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋምነት ከፍ ለማለት በቅቷል። በሁለቱም ት/ቤቶች ለአንድ ዓመት ብቻ ይሰጥ የነበረው ስልጠናም ወደ ሁለት ዓመት ከፍ እንዲል ተደርጎ ነበር። ለማስተማር ልምምዱም ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እንደነበር ይታወቃል (Hailom 1997)።

በመጨረሻም የመምህራን ስልጠና በፕራክቲክም መታገዝ እንዳለበት በአዲሱ የመምህራን ስልጠና ፖሊሲ በመጠቆሙ ቀደም ሲል የነበረው የአሰለጣጠን ሂደት መቀየሩ ይታወቃል። MOE (2003:44) ቀደም ሲል የነበረውን የመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር መቀየር አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያት እንደሚከተለው በአስራ ሁለት ነጥቦች ጠቅለል አድርጎ አስቀምጦት እናገኘዋለን።

1. ቀደም ሲል በነበረው የመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር ይሰለጥኑ የነበሩ መምህራን ብቃት አናሳ ስለነበር፣
2. አሰለጣጠኑ ለመምህራን አመርቂ የሆነ ዕውቀት ሲያስጨብጥ ያልቻለ ስለነበረ፣
3. መምህራን በመሠረታዊ የማስተማር ክሂልና ስልት የታነፁ ስላልነበሩ፣
4. ሰልጥነው በስራ ላይ ከሚሰማሩ መምህራን የሚጠበቀው ሙያዊ ብቃት ደረጃ ዝቅተኛ ስለነበር፣
5. ከትምህርት ስልጠና ፖሊሲ እውቀት ማነስ የተነሳና ተገቢውን የአሰራር መዋቅር ባለመከተል በት/ቤቶች የአስተዳደር ችግር እየተከሰተ ስለሆነ፣
6. በመምህራን አሰለጣጠንና በት/ቤት ትምህርት አሰጣጥ ሂደት መካከል የሰፋ ልዩነት ይታይ ስለነበር፣
7. በነበረው የመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር ስነ ምግባራዊ እሴቶች ባለመካተታቸው የሙያ ክብር እንዳይኖር ስላደረገ፣
8. መምህራንን ለማሰልጠን ይረዳሉ ተብለው የተዘጋጁ ኮርሶችና የማስተማር ዘዴዎች በንድፈ ሐሳብ ላይ ብቻ ያተኮሩ ከመሆናቸውም በላይ መምህር ተኮር ስለነበሩ፣
9. በሁሉም ደረጃ ሊያስተምህሩ የሚችሉ መምህራንን በማሰልጠኑ ሂደት ለማስተማር ልምምድ ይሰጠው የነበረው ትኩረት አነስተኛ ስለነበር፣
10. መምህራን ተማሪዎችን በመገምገም ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን መለየት የማይችሉ ስለነበሩ፣

11. በሁሉም ደረጃ የሚያስተምሩ መምህራንን በማሰልጠኑ ሂደት ለተግባራዊ ልምምድ ይሰጠው የነበረው ትኩረት አናሳ ስለነበር ወይም ከነጭራሹ ትኩረት የተነፈገው ስለነበር፣

12. በመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት፣ በት/ቤቶች እና በህብረተሰቡ መካከል የነበረው ግንኙ ነት የላላ ስለነበር ነው::

ከ1966 ዓ.ም የሥርዓት ለውጥ ጀምሮ እስከ 1970 ዓ.ም ድረስ በመደበኛነት መምህራንን የማሰልጠኑ እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ ተቋርጦ የነበረ ቢሆንም ከ1971 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ 12ኛ ክፍልን የጨረሱ ተማሪዎችን በመቀበል ለአንድ ሴሚስተር ብቻ ማሰልጠን ተጀምሮ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ:: ከ1972 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የመምህራን ስልጠና ቆይታ ወደ አንድ አመት ለመራዘም በቅቷል (Abraham and et al. 1999:11)::

ትምህርት ሚኒስቴር በ1984 ዓ.ም ብቃት ያላቸውን መምህራን በተፈለገው መጠን ለማፍራት ያስችላል ያለውን የመምህራን ስልጠና ፖሊሲ ሲያዘጋጅ ወደየ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋማቱ ገብተው መሠልጠን የሚገባቸው 10ኛ ክፍልን ያጠናቀቁ ተማሪዎች እንዲሆኑ አድርጓል::

ከላይ እንደተመለከትነው ብዙም ትኩረት ሳይሰጠው የቆየው የመምህራን ስልጠና በአሁኑ ወቅት ከመዋዕለ ሕፃናት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሊያስተምሩ የሚችሉ መምህራንን የማሰልጠኑ እንቅስቃሴ እየተጠናከረ ይመስላል:: በሀገራችን የትምህርት ፖሊሲም ለመምህራን ስልጠና ልዩ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ተገልፆ ይገኛል:: መምህራን ለየደረጃው የሚመጥነውን ዕውቀት፣ ችሎታና የማስተማር ብቃት በስልጠናው ወቅት መካን ይኖርባቸዋል:: ስልጠናውም በመሠረታዊ ዕውቀት፣ ሙያዊ ስነ ምግባር፣ በማስተማር ስነ ዘዴ፣ በፕራክቲከም (የት/ቤት ልምድ) እና በማስተማር ልምምድ የታገዘ መሆን አለበት (Freeman 1990:103, McIntyre and et al. 1994:9, Fidler 1994:22)::

ይሁን እንጂ ዓለም (1988:2) እንደገለፀው እስካሁን ድረስ መምህራንን የማሰልጠኑ እንቅስቃሴና ሂደት ሙሉ በሙሉ ከችግር የፀዳ መስሎ አይታይም:: ከሚታዩት ችግሮች መካከል በዋነኛነት ሊጠቀሱ የሚችሉት የሚከተሉት ናቸው::

- በፍላጎት ላይ ያልተመሠረተ የዕጩ መምህራን ምልመላ
- ለንድፈ ሐሳብ እንጂ ለፕራክቲከምና ለማስተማር ልምምድ ትኩረት አለመስጠቱ
- በስልጠናው ማጠናቀቂያ ላይ የማስተማር ልምምድ እንዲካሄድ መደረጉ
- የማስተማር ልምምድን እንደ መገምገሚያ መስፈርት መቁጠር
- በሱፐርቫይዘርነት የሚመደቡ የተቋሙ መምህራን ብቃት ማነስ
- በሱፐርቫይዘሮችና በሰልጣኞች መካከል የመረዳዳት መንፈስ አለመኖር ናቸው::

አዲሱ የመምህራን አሰለጣጠን ኘሮግራም እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ያቃልላል ተብሎ ይታሰባል:: የዚህ ጥናት ትኩረትም እውን በተለያዩ ችግሮች ተተብትቦ የነበረው

የመምህራን ሥልጠና በፕራክቲከም አማካይነት ከችግሮቹ ይላቀቅ እንደሆነ መፈተሽ ነው:: በዚህ ጥናት በፕራክቲከም በታገዘው መምህራንን የማስልጠኑ ሂደት ማስልጠኛ ተቋማት፣ ሱፐርቫይዘሮች፣ ነባር መምህራንና ተባባሪ ት/ቤቶች የተጣለባቸውን ኃላፊነት በብቃት መወጣት አለመወጣታቸውን ለመቃኘት ጥረት ይደረጋል::

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አጠቃላይ ዓላማ በአዲሱ የመምህራን አሰለጣጠን ሂደት የፕራክቲከም፣ የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥን አተገባበር በመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት በተለይም በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ምን እንደሚመስል በመቃኘት መተንተን ነው:: ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው:: እነሱም:

- በሰርተፍኬት (10+1) ፕሮግራም የአሃዳዊ ትምህርት መምህራንን በማሰልጠን ሂደት ፕራክቲከም፣ የማስተማር ልምምድና ሱፐርቪዥን እንዴት እየተተገበረ ነው?
- ሱፐርቫይዘሮች ፕራክቲከሙን፣ የማስተማር ልምምዱንና ሱፐርቪዥኑን ለመከታተል ምን ዓይነት ስልት እየተጠቀሙ ነው?
- ድህረ ፕራክቲከምና የማስተማር ልምምድ ውይይት በምን ላይ ያተኩር ነበር≡
- በፕራክቲከም፣ በማስተማር ልምምድና በሱፐርቪዥን ሂደት የተባባሪ ት/ቤት መደበኛ መምህራን ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ነውን≡
- ሱፐርቫይዘሮችና የተማሪ አስተማሪዎች ስለፕራክቲከም፣ ማስተማር ልምምድና ሱፐርቪዥን ያላቸው አስተያየት ምን ይመስላል≡
- የተማሪ አስተማሪዎች ከፕራክቲከም፣ ከማስተማር ልምምድና ከምግበ መረጃ ውይይት ግንዛቤ አግኝተዋልን≡ ወዘተ የሚሉት ናቸው::

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

መምህራንን በማሰልጠን ሂደት ፕራክቲከም፣ የማስተማር ልምምድና ሱፐርቪዥን የሚኖራቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው:: ለመርሃ ግብሩ ከተዘጋጁት ኮርሶች ከንድፈ ሐሳብ ትምህርት፣ ከፕራክቲከም፣ ከማስተማር ልምምድና ከሱፐርቪዥን የሚገኘው ሙያዊ ዕውቀት፣ ልምድና ክሂል የትምህርት ጥራት መሠረት እንደሆነም ይታወቃል::

ስለዚህ ይህ ጥናት በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ያለውን የፕራክቲከም፣ የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥኑን ሂደት በመከታተል አጥንቶ ውጤት ላይ ሲደርስ ከዚህ የሚከተሉት ጥቅሞች ይኖሩታል የሚል እምነት አለ::

- መሠረታዊ የንድፈ ሐሳብ ትምህርቱ፣ ፕራክቲከሙ፣ የማስተማር ልምምዱና ሱፐርቪዥኑ ተጣጥመውና ተጠናክረው ሊከናወኑ የሚችሉበትን መንገድ ይጠቁማል::

- የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማትን፣ የሱፐርቫይዘሮችን፣ የተባባሪ ት/ቤት ነባር መምህራንና የተማሪ አስተማሪዎችን ሚና ለይቶ ያሳያል፡፡
- በፕራክቲከምና በማስተማር ልምምድ ሂደት የሱፐርቪዥንን ምግበ መረጃ ልውውጥ በምን ዓይነት መንገድ መከናወን እንዳለበትና በምን ላይ ማተኮር እንዳለበት ፍንጭ ይሰጣል፡፡
- የፕራክቲከሙ፣ የማስተማር ልምምዱና የሱፐርቪዥኑን አካሄድና አፈፃፀምን በተመለከተ ሊሻሻሉ የሚገባቸው ነጥቦች ካሉ የሚሻሻሉበትን መንገድ ይጠቁማል፡፡
- በመምህራን ስልጠና በተለይም የፕራክቲከምን አተገባበር በሚመለከት ሌሎች ጥናቶች እንዲካሄዱ በመነሻነት ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ክልልና ገደብ

በአሁኑ ወቅት በርካታ የመንግሥትና የግል መምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት መምህራንን እያሰለጠኑ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት ግን ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ነው፡፡ ኮሌጁ የአፀደ ሕፃናት፣ የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል (1–4) በሰርተፊኬትና ሁለተኛ (5–8) ሳይክል መምህራንን ደግሞ በዲፕሎማ በማሰልጠን ላይ ቢሆንም ለዚህ ጥናት የተመረጡት በመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል (1–4) አሃዳዊ ትምህርት መምህርነት በ1997 ዓ.ም በሰርተፍኬት የሚመረቁ ዕጩ መምህራን ናቸው፡፡ ምንም እንኳን የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህርነት የሚሰለጥኑ መምህራን ላይ አነጣጥሮ የነበረ ቢሆንም የሰርተፊኬት መርሃ ግብሩ  አሃዳዊ የትምህርት አሰጣጥን መሠረት ያደረገ በመሆኑ በታሰበው መንገድ መቀጠል አልተቻለም፡፡ በአጠቃላይ MOE (2003: 62-64) እንዳስቀመጠው በኮሌጁ በሰርተፍኬት መርሃ ግብር ለሚሰለጥኑ እጩ መምህራን የሚሰጡ ኮርሶች

1. Practicum: I, II, III & IV (ፕራክቲከም አንድ፣ ሁለት፣ ሦስትና አራት)
2. Teaching Languages ቋንቋን /አማርኛና እንግሊዝኛ/ ማስተማር
3. Teaching Mathematics ሂሳብን ማስተማር
4. Profesional Studies (PSI = Teaching in Ethiopian context, PSII= General Methods of Teaching, PSIII= Child development and support, PSIV= Special Educational needs, PSV= Professional and Topical Issues) ሞያዊ የጥናት ዘርፎችን ማስተማር
5. Teaching Environmental Science የአካባቢ ሳይንስን ማስተማር
6. Civics and Ethical Education የሥነ ዜጋና ሥነ ምግባር ትምህርት
7. Teaching Aesthetics and Physical Educaion የሥነ ውበትንና የሰውነት ማጐልመሻ ትምህርትን ማስተማር ሲሆኑ ይህ ጥናት ፕራክቲከም ሦስት እና አራት ላይ እንዲወሰን በመደረጉ ሁሉንም ኮርሶች፣ የጥናት ዘርፎች፣ ፕራክቲከም አንድና ሁለትን አይቃኝም፡፡

## 1.6. ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ

በ1952 ዓ.ም አገልግሎት መስጠት የጀመረው የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ መምህራንን የማሰልጠኑን እንቅስቃሴ ያዝ ለቀቅ ሲያደረግ እንደነበር ለመረዳት ይቻላል:: ሜክሲኮ ተግባረድ ዕድ ት/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ የተመሠረተው ይህ ኮሌጅ በመጀመሪያ በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዩኒቨርስቲ፣ ቀጥሎ በትምህርት ሚኒስቴር እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን ስር ሲተዳደር ቆይቶ በአሁኑ ሰዓት በአዲስ አበባ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ በመተዳደር ላይ ይገኛል::

ዓለም (1988) የኮሌጁ ታሪክ የተፃፈባቸውን ሰነዶች ጠቅሶ እንደገለፀው ኮሌጁ ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ በ9ኛና 10ኛ ክፍል ገብተው ሊያስተምሩ የሚችሉ መምህራንን በዲግሪ መርሃ ግብር ማሰልጠን ጀምሮ ነበር::

ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ በ2ኛ ደረጃ የ11ኛና የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችን ማስተማር የሚችሉ መምህራንን በዲግሪ ያሰለጥን የነበረው ይህ ኮሌጅ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ ከጤናና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት በስተቀር በሌሎች የትምህርት ዘርፎች ይሰጥ የነበረውን የዲግሪ መርሃ ግብር አቋርጧል:: በአንፃሩ ግን ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ (1-4 ክፍል) እና ሁለተኛ (5-8 ክፍል) ሳይክል መምህራንን በሰርተፍኬትና በዲፕሎማ ፕሮግራም ማሰልጠን ጀምሯል:: ኮሌጁ በየካቲት 12 ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የነበረውን የአፀደ ሕፃናት መምህራን ማሰልጠኛ ተቋምን በመረከብና ኃላፊነቱን በመውሰድ የአፀደ ሕፃናት መምህራንንም በማሰልጠን ላይ ይገኛል::

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

## 2.1 የመምህራን ስልጠና ምንነት

መምህራን በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ አዎንታዊ የሆነ ማህበራዊ ለውጥ በማምጣት የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው:: እነዚህ የለውጥ ሀዋርያት የሆኑ መምህራን በሚገባ የሰለጠኑ መሆን ይጠበቅባቸዋል:: ምክንያቱም የተጣለባቸውን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ይችሉ ዘንድ በመምህርነት ሙያ ስልጠና በቂ የሆነ የንድፈ ሐሳብ እውቀት ቀስመው ከዘመኑ የማስተማር ስነ ዘዴ ጋር ተዋውቀውና በመልካም ስነ ምግባር ታንፀው መገኘት ይኖርባቸዋል:: Schon (1983) እንደሚገልጹት የመምህርነት ሙያ ለማንኛውም ማህበረሰብ አስፈላጊ ነው:: ማስተማር በመምህራንና በተማሪዎች መካከል የሚከናወን የየትኛውም ሙያ እናት ነው (Freeman 1990:103):: ይህ እናት ሙያ ደግሞ በሰለጠኑ መምህራን ቢያዝ ውጤቱ አመርቂ ይሆናል::

የሰለጠኑ መምህራን የሚያስተምሩትን የትምህርት ይዘት ጠንቅቀው ስለሚያውቁ፣ በትምህርት ስርዓቱና በትምህርት ቤቶች መካከል ያለውን ዝምድና ስለሚረዱ፣የሙያውን ስነ ምግባር ስለሚያከብሩ፣ በምን አይነት መንገድ ትምህርቱን ማቅረብ እንደሚኖርባቸውና የመማር ማስተማሩን እንቅስቃሴ እንዴት መቆጣጠር እንደሚገባቸው ስለሚገነዘቡ ኃላፊነት የሚሰማው ዜጋን በመፍጠሩ ሂደት ጉልህ ሚና ይኖራቸዋል::

ይህንን ትልቅ ኃላፊነት የሚሸከሙ መምህራንን ለማሰልጠን ተብለው የሚቀረጹ ኮርሶች ደግሞ ዕጩ መምህራን ምን፣ ለምን ፣ መቼ እና እንዴት ሊያስተምሩ እንደሚገባቸው በቂ ግንዛቤ ሊያስጨብጧቸው የሚችሉ መሆን ይጠበቅባቸዋል (Brown 1990:87)::

የመምህራን ስልጠና ከስያሜው እንደምንረዳው አንድን የትምህርት ይዘት በሚገባ ማስተማር የሚችሉ ዕጩ መምህራን እንዴት እንደሚያስተምሩ በንድፈ ሐሳብና በልዩ ልዩ ሥልጠና እውቀትና የማስተማር ስነ ዘዴን የማስጨበጫ መንገድ ነው (Nettle 1988):: ምንም እንኳን አንዳንድ ሰዎች ዕውቀታቸውን፣ ችሎታቸውንና ልምዳቸውን ለሌሎች ለማስተላለፍ ተፈጥሮአዊ ብቃት ቢኖራቸውም ተሰጥኦአቸውን በስልጠና ቢያዳብሩት የተሻለ ዕውቀትን የማስተላለፍ ችሎታ እንዲኖራቸው ያደርጋል::

የማስተማር ስራ ጥበብ ነው ወይስ ሳይንስ የሚለው ጥያቄ የሚመነጨውም ከዚሁ ሐሳብ ነው:: አንዳንድ ሰዎች መምህራን ለተማሪዎቻቸው አስፈላጊውን እውቀት በጥበብ ማስጨበጥ ከቻሉ የመምህርነት ሙያ ስልጠና ምን ይፈይድላቸዋል? የሚል ሐሳብ ይሰነዝራሉ:: እንደነዚህ ዓይነቶቹ መምህራን የማስተማር ተሰጥኦ ስላላቸው እማሰልጠኛ ተቋም ገብተው ባይሰለጥኑም ከተማሪዎቻቸው የሚሰነዘርላቸውን አስተያየት እየተቀበሉ የማስተማር ብቃታቸውን ማዳበር ይችላሉ የሚል አመለካከትም አላቸው:: ይሁን እንጂ ተሰጥኦ ያላቸውም

ሆኑ የሌላቸው መምህራን ስልጠና መውሰዳቸው ሊኖረው የሚችለው ጥቅም አጠያያቂ ሊሆን አይገባውም:: ስልጠናው በፕራክቲከምና በማስተማር ልምምድ የታገዘ ስለሚሆን የተማሪ አስተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተመለከቱትን የመማር ማስተማር ሂደት መነሻ በማድረግ የራሳቸውን የማስተማር ዘዴ በመቀየስ ከተማሪዎቻቸው ፍላጎት ጋር አጣጥመው ለማቅረብ ትልቅ እገዛ ያደርግላቸዋል:: በተለይ በስልጠናው ጥሩ የማስተማር ሂደትና እንቅስቃሴ ምን እንደሚስል ተመልክተውና እንዴት ቢያስተምሩ የተሻለ ሊሆን እንደሚችል የሚያመለክታቸውን ዕውቀትና ክሂል ቀስመው ያዩትንና የቀሰሙትን ዕውቀት ወደ ተግባር እንዲለውጡ ቢደረግ ውጤቱ አስደሳች ይሆናል (Dobbyn 1979:1):: በእርግጥ ስልጠና በአንድ ጥርት ያለ ዓላማ ላይ ተመስርቶ አንድን ውስን ሙያ ማስጨበጫ መንገድ መሆኑ ግልጽ ነው:: በአንድ ሙያ ለማሰልጠን ሲታሰብ ደግሞ ቀጥሎ ለተመለከቱት ጥያቄዎች መልስ መሻት አስፈላጊ ይሆናል:: ጥያቄዎቹም:-

1. የስልጠናው ዓላማ ምንድነው?
2. ስልጠናው የሚያነጣጥረው ምን ላይ ነው?
3. ኮርሶቹ በይዘትና በማስተማር ዘዴ መካከል ያለውን መወሳሰብ ሊያስወግዱ ይችላሉን?
4. ከትምህርት ቤት ስርዓት አኳያ ለኮርሶቹ ያለ አመለካከት ምን ይመስላል?
5. የንድፈ ሐሳብና የትግበራ ግንኙነት ምን ይመስላል?
6. ስልጣኞች የራሳቸው የመማር ስልት አላቸው ወይስ የሌሎችን ስልት ተከትለው ይማራሉ የሚሉት ናቸው (Fish 1989: 53-54)::

ብዙ የተማሪ አስተማሪዎች ስለ ስልጠና ከሚኖራቸው አነስተኛ ግንዛቤና አሉታዊ አመለካከት የተነሳ ስልጠናው በንድፈ ሐሳብ ላይ ብቻ የተመሰረተ በመሆኑ እንዴት ማስተማር እንዳለብን በሚገባ አልተማርንም ሲሉ ይደመጣሉ::ከዚህ የምንረዳው በአሰለጣጠኑ ሂደት ንድፈ ሐሳብን ከተግባር ጋር በማቀናጀት የማቅረብ ልምድ እንደሌለ ነው:: አሰልጣኞች ወደ ክፍል ይዘውት የሚገቡትን ሁሉ ያለምንም ማንገራገር የተማሪ አስተማሪዎች እንዲቀበሉዋቸው እንጂ በሁሉም አቅጣጫ ምን፣ ለምን ፣ እንዴት፣ የት እና መቼ ማከናወን እንዳለባቸው ሁኔታዎችን ሲያመቻቹላቸው አይታዩም (Ur 1996:3):: ዕጩ መምህራን ደግሞ ትዕዛዛዊ በሆነ መልኩ የሚቀርብላቸውን ንድፈ ሐሳብ የመቀበል ፍላጎት ስለማይኖራቸው ተግባራዊ የማድረግ ብቃት ሊኖራቸው አይችልም:: ስለዚህ አሰልጣኝ መምህራን ጥሩ የትምህርት አሰጣጥ መልካም መምህራንን ለማፍራት እንደሚያስችል በመገንዘብ በቂ ዕውቀት ለማስጨበጥ ይችሉ ዘንድ ገና ከመነሻው ቀጥሎ የተመለከቱትን ነጥቦች ለተማሪ አስተማሪዎች ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል::

1. ሰዎች እንዴት ባለ መንገድ ትምህርት ቀስመው ጥሩ መምህር ሊሆኑ እንደሚችሉ መጠቆም፣

2. አሰልጣኞች ሁልጊዜ ራሳቸው እንደ ባለሙያና ሞዴል አድርገው በማየት የሚበጀውን አዋቂና አድራጊ፣ መልስና መፍትሄ አፈላላጊ አድርገው ሳይቆጥሩ የተማሪ አስተማሪዎች በራሳቸው ለማወቅ የሚጥሩበትን መንገድ ማመቻቸት፣

3. የተማሪ አስተማሪዎችን እንደ አላዋቂና አቀመቢስ በመቁጠር ከማስፈራራት ይልቅ ቀረብ በማለት ለማወያየት ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል (Fish 1989:56-57)::

በተለይ አዳዲስ የማስተማር ሞዴሎች ተግባራዊ እንዲሆኑ በሚፈለግበት ጊዜ የስራ ላይ ስልጠና የሚወስዱ መምህራን ሳይቀሩ ለሞዴሎቹ ባይተዋር የሚሆኑት የተሟላ ስልጠና ካለማግኘታቸው የተነሳ ነው:: Britten (1988:3) እንደሚገልፁት ትዕዛዛዊ የሆነ የመምህራን ሥልጠና ዕጩ መምህራን ለመርሃ ግብሩ የሚኖራቸውን አመለካከት እየቀየረው እንደሚመጣ ግልጽ ነው::

ይሁን እንጂ ባለፉት አስራ አምስት ዓመታት ውስጥ ይህ የዕጩ መምህራን አመለካከት እየተለወጠ መጥቶ በስልጠናው ወቅት ትንንሽ ቡድኖችን እየመሠረቱ የማስተማር ዕቅድ በጋራ እያወጡ፣ የብጤና ንዑስ የማስተማር ልምምድ እያደረጉ ራሳቸውን የሚገመግሙበትና ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች መፍትሄ የሚያፈላልጉበት፣ ስለማስተማር ዘዴው እየተወያዩ የሚሰለጥኑበት ሁኔታ ተመቻችቶላቸዋል (Britten 1988:5):: የአሰለጣጠኑ ሂደትም እየተጠናከረና እየተስፋፋ ለመምጣቱ ጥሩ ማስረጃ የሚሆነው በተናጠል ይሰጥ ከነበረው የመምህራን ስልጠና ወደ ቡድን፣ አጭርና ውስን ይዘቶችን ከማስተማር ልምምድ ወደ ሙሉ የትምህርት ይዘትና የረጅም ጊዜ የክፍል ውስጥ ልምምድ፣ ከተበጣጠሱ የክሂል ትምህርት ዓላማዎች ወደ ቅንጅታዊ የመማር ዓላማዎች፣ ከአሰልጣኝ ወይም ብጤ ግምገማ ወደ ተናጠላዊና ራስን ወደ መመዘን ደረጃ ላይ መደረሱ ነው::

## 2.2 የመምህራን ስልጠና ታሪካዊ ዳራ

የመምህራን ስልጠና እንደዛሬ ከፍተኛ ትኩረት አይሰጠው እንጂ ተግባራዊ መሆን ከጀመረ ረጅም ዘመን አስቆጥሯል:: ይሁን እንጂ የማስተማር ጥበብን ስለማስተማር የነበረው ግንዛቤ በጣም ዝቅተኛ ከመሆኑም በላይ ዕጩ መምህራንን ለማሰልጠን ይደረግ የነበረው ጥረት ውስን በመሆኑ ስልጠናው ችግር ሲገጥመው እንደነበር አንዳንድ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: ለምሳሌ ዓለም (1988፣9) Flanders (1976)ን በመጥቀስ እንደገለፀው እስከ 1965 ዓ.ም ድረስ የነበረው የመምህራን ስልጠና ለለውጥ ራሱን ባለማዘጋጀቱ ስልጠናው ቀላልና በማንኛውም ሰው ሊሰጥ የሚችል ተደርጎ ይታሰብ ነበር:: ይሁን እንጂ በመምህራን ስልጠና ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን በመረዳት ለችግሮቹ መፍትሄ በማፈላለግ ጠንከር ያለ ስልጠና በመስጠትና መምህራን እንዴት እንደሚያስተምሩ መማር እንደሚገባቸው በመገንዘብ ስልጠናውን መስጠቱ ተገቢ እንደሆነ እንረዳለን:: Breen (1989:113) የመምህራን ስልጠና ዕውቀትን እንደ ማስተላለፊያ፣

ለችግር መፍትሄ እንደመፈለጊያ፣ በክፍል ውስጥ ውሳኔ እንደመስጫና የምርምር ሥራን እንደማከናወኛ መንገድ እየታየ መምጣት አለበት የሚሉት ለዚህ ነው፡፡

ዕጩ መምህራን ከተግባራዊ የማስተማር ስነ ዘዴዎችና ከአዳዲስ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ጋር መተዋወቅ እንዳለባቸው ይታወቃል፡፡ ትውውቁ ከአጠቃላይ የማስተማር መርሆዎችና በመሳሪያዎቹ ሊካተቱ ከሚገባቸው የትምህርት ይዘቶች ጋር ሲሆን ተግባራዊ የሚሆነው ግን በስልጠናው ሂደት ነው፡፡

ቀደም ሲል በከፍተኛ ትምህርትና በመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ይሰጥ የነበረው ስልጠና ማስተማርን እንደተግባራዊ ሳይንስ በመቁጠር ዕጩ መምህራን በትምህርት ቆይታቸው አጠቃላይ የማስተማር ንድፈ ሐሳብን፣ ዓላማና መርህን በመቅሰም ወደ ተግባር የመለወጥ ብቃታቸውን አዳብረው ይወጣሉ የሚል እሳቤ የያዘ ነበር፡፡ ነገር ግን የማስተማር ሙያ በአንድ የተወሰነ ጊዜ ውስጥ ተምረው የሚያጠናቅቁት ሳይሆን ዘለግ ባለ ጊዜ የሚቀሰም ሙያ ነው፡፡ የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት እየተጠናከሩ ሲመጡ ይህን ሁኔታ በመገንዘብ ዓይነተኛ ዓላማቸው ዕጩ መምህራንን ተቀብለው በአጭር ጊዜ የማስተማርን ንድፈ ሐሳብና ስነ ዘዴ ከተግባር ጋር አጣምረው ለማስጨበጥ ሳይሆን ማስተማርን መማር ማስጀመር ነበር፡፡ በማሰልጠኛ ተቋማቱ የሚጀመረው ማስተማርን መማር ከመምህሩ ህይወት ጋር ዘላቂና እያደገ የሚሄድ መሆን ይጠበቅበታል (ዓለም **1988፣11**)፡፡

## 2.3 መምህራን እንዴት ይሰልጥኑ?

መምህራንን ለማሰልጠን ሲታሰብ ንድፈ ሐሳባዊ መሠረትን መነሻ ማድረግ የግድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ንድፈ ሐሳብ ብቻውን አንድ ጥሩ መምህር ሊፈጥር አይችልም፡፡ ንድፈ ሐሳብ በተግባራዊ ልምምድ መታገዝ ይኖርበታል፡፡ ይሁንና ዓለም (**1988፣10**) Matehur (1987) እና Wragg (1970)ን ጠቅሶ እንደገለፀው በመምህራን አሰለጣጠን ሂደት ንድፈ ሐሳብን ከተግባራዊ ልምምድ የሚለይ አንድ ትልቅ ሸለቆ አለ፡፡ ይህ በንድፈ ሐሳብና በተግባራዊ ልምምድ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያላላ ሸለቆ መጥበብ አለበት፡፡ Freeman (1990:105-108) ለዚህ ሸለቆ መፈጠር ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረገው በአሰልጣኞች ወይም በሱፐርቫይዘሮችና በተማሪ አስተማሪዎች መካከል የሰመረ ግንኙነት አለመኖሩ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ በተለይ በተማሪ አስተማሪዎች ፍላጎት ላይ ያልተመሰረተ የመምህራን ስልጠና ችግሩን የበለጠ ያጎላዋል፡፡ በመምህራን አሰለጣጠን ሂደት በአሰልጣኝ መምህራንና በተማሪ አስተማሪዎች መካከል ያለው ግንኙነት አጋዥ ወይም እንቅፋት ፈጣሪ ሊሆን እንደሚችልም ይታመናል፡፡

Freeman (1990:106) Gibb (1964:25)ን በመጥቀስ በአሰልጣኞች ወይም በሱፐርቫይዘሮችና በዕጩ መምህራን መካከል ያለው ግንኙነት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መሆኑን ለመረዳት በሚያመች መልኩ እንደሚከተለው አስቀምጠውታል፡፡

## ሠንጠረዥ አንድ

## በሱፐርቫይዘሮችና በተማሪ አስተማሪዎች መካከል ሊኖር የሚችል ግንኙነት

| አዎንታዊ (Orientation that help) | አሉታዊ (Orientation that hinder) |
|---|---|
| 1. መተማመን ፣ አንዱ ያለውን አንዱ መቀበል | 1. አለመተማመን፣ መፈራራት፣ መከራከር |
| 2. በመተባበር መማማር | 2. አንዱ አስተማሪ ሌላው ተቀባይ ወይም መካሪና ተመካሪ መሆን |
| 3. በጋራ ማደግ | 3. መገምገም፣ ማስተካከል፣ መፍትሄ መፈለግ |
| 4. በግልፅ መቀራረብ | 4. በተለያየ ስልት መቅረብ |
| 5. በጋር መፍትሔ መሻት | 5. እኔን በመመልከት መፍትሔ ለመፈለግ ሞክር ማለት |
| 6. ነፃነት፣ ራስን መቻል፣ እኩልነት | 6. መቆጣጠር፣ መምራት፣ መቅረጽ |
| 7. መከራን መሠረት ማድረግ | 7. ቅደም ተከተልን መሠረት ማድረግ ቋሚ፣ ወጥና አይለወጤ አካሄድን መከተል |

ከዝርዝሩ እንደምንረዳው መምህራንን በማሰልጠን ሂደት በትምህርት ባለሙያዎችና በተማሪ አስተማሪዎች መካከል ያለው ግንኙነት አዎንታዊ እንዲሆን ካስፈለገ ግንኙነቱ በተማሪ አስተማሪዎቹ ፍላጎት ላይ መመስረት ይኖርበታል። እያንዳንዱ ግንኙነትም የግዴታ ከትምህርቱ ይዘትና ከስልጠና ሂደቱ ጋር የተቀናጀ ቢሆን ይመረጣል። በሚቀርበው የትምህርት ይዘትና የአቀራረብ ስልት ላይ ያላተኮረ ግንኙነት በመካከላቸው ያለውን ልዩነት (ሽለቆ) ማጥበብ አይችልም።

በመምህራን አሰለጣጠን ሂደት በአሰልጣኝ መምህራን ወይም ሱፐርቫይዘሮችና በተማሪ አስተማሪዎች መካከል ያለው ግንኙነት በሦስት መንገድ ሊፈጠር ይችላል (Freeman 1990:107-114)።

1. ትዕዛዛዊ (አሰልጣኝ መር) ስልጠና:- ስልጠናው ሙሉ በሙሉ በአሰልጣኞች ይመራል። አሰልጣኞች በተማሪ አስተማሪዎች እንቅስቃሴ ላይ አስተያየት ይሰጣሉ። የተማሪ አስተማሪዎች የሚሻሻሉበትን አማራጭ መንገድ በመንደፍ ያቀርባሉ። ከዚህ የተነሳ ይህ አካሄድ አሰልጣኞች መሪ የተማሪ አስተማሪዎች ተመሪ ሆነው የሚታዩበት የአሰለጣጠን ሂደት ነው። አሰልጣኞቹ እኛ ለእናንተ የሚበጀውንና የሚጠቅመውን ሁሉ እናውቅላችኋለን የምንነግራችሁን ሁሉ ተቀበሉን፣ ተማሩ፣ ከዚያ በኋላ ደግሞ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተግባራዊ ስታደርጉት እንመዝናችኋለን ይላሉ (ዓለም **1988:11**)።

Stone and Morris (1972:6-7) በበኩላቸው በዚህ ስልጠና አሰልጣኝ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ምን መስራት እንዳለባቸው ይነግሯቸዋል፣ ያሳዩዋቸዋል

ያዘጋጁላቸዋል። ሕግና ደንብ ተከትለው እንዲሰማሩም ያስገድዷቸዋል በማለት ያስረዳሉ። ይህ ዓይነቱ የመምህራን አሰለጣጠን ሂደት በአሁኑ ወቅት እምብዛም አገልግሎት ላይ የለም።

2. አማራጫዊ ስልጠና፦ በዚህ የአሰለጣጠን ሂደት አሰልጣኞች የተማሪ አስተማሪዎች በማስተማር ልምምድ ወቅት የሚያነሱዋቸውን ነጥቦች መነሻ በማድረግ የራሳቸውን አማራጭ ሐሳብ ያቀርቡላቸዋል። ያቀረቡላቸውን አማራጭ ሐሳብ ሊቀበሉት ወይም ላይቀበሉት ይችላሉ። ሳይቀበሉት ቢቀሩ እንዲቀበሏቸው ግፊት አያደርጉም። እንዲያውም ተጨማሪ ስነ ትምህርታዊ ጉዳዮችን እያቀረቡ የተማሪ አስተማሪዎቹ የበለጠ ኃላፊነትን እንዲወስዱ ለማድረግ ይጥራሉ።

3. ኢትዕዛዛዊ (አሰልጣኝ መር ያልሆነ) ስልጠና፦ የተማሪ አስተማሪዎች አሰልጣኞቻቸው ያስተማሯቸውን ንድፈ ሐሳብ መነሻ አድርገው ወደ ተግባር ለመለወጥ በነፃነት የሚንቀሳቀሱበት የአሰለጣጠን ሂደት ነው። በዚህ የስልጠና ሂደት የአሰልጣኞች ድርሻ የተማሪ አስተማሪዎችን መርዳት እንጂ መምራት አይደለም። ይህ ዓይነት ግንኙነት ያለው የአሰለጣጠን ሂደት ለስኬታማ የመምህራን ስልጠና አስፈላጊ ነው።

እንደ Ellis (1986:95) አገላለጽ ከሆነ የተዋጣለት የመምህራን አሰለጣጠን ሂደት በሚከተለው ቅደም ተከተል ሊከናወን ይገባዋል።

1. ገለፃ፦ አሰልጣኝ መምህራን የተለያዩ አማራጭ የመማሪያ መሳሪያዎችን በመጠቀም በቀጥታ ለተማሪ አስተማሪዎቻቸው በመግለጽ ያስረዳሉ።
2. በቡድን /በብጤ ውይይት፦ አሰልጣኝ መምህራን የተለያዩ መልመጃዎችን ወደ ክፍል ይዘው በመምጣት ሰልጣኞች በቡድን/በብጤ ሆነው በመወያየት ይማማራሉ።
3. ወርክሾፕ፦ የተማሪ አስተማሪዎች በግል ወይም በቡድን ያዘጋጁትን ይዘት በትምህርት ዕቅድና በመርጃ መሳሪያዎች ታግዘው ያቀርባሉ።
4. በግል መስራት፦ የሚሰጣቸውን የቤት ስራ በየግላቸው ሰርተው በመምጣት ዕውቀትና ችሎታቸውን ያዳብራሉ።
5. በማሳየት፦አሰልጣኞች መደበኛ ተማሪዎችን ወይም የተማሪ አስተማሪዎቹን ተጠቅመው አንድን ውስን ስልት ወይም ቴክኒክ እንዴት መተግበር እንደሚቻል በማሳየት ያስለጥናሉ።
6. በጥያቄና መልስ (Elicitation)፦ አሰልጣኞች የተለያዩ ጥያቄዎችን እያቀረቡ ከተማሪ አስተማሪዎች ጋር እየተጠያየቁ ያስለጥናሉ።
7. የቡድን ውይይት (Plenary discussion)፦ በመማር ማስተማሩ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ላይ ሰልጣኞችን በሙሉ በማወያየት የማስተማር ስልት ነው።

8. የፓናል ውይይት፡- አሰልጣኞች የተለያዩ የፓናል ውይይቶችን ማዘጋጀት ይችላሉ፡፡ ሰልጣኞችን በመጋበዝ ፓናሉን ማዘጋጀት ወይም በተመረጡ ነጥቦች ዙሪያ ጥያቄዎችን አዘጋጅተው በሚመጡ ተጋሪዎች አማካይነት የፓናል ውይይት ማካሄድ ይቻላል፡፡ በዚህን ጊዜ አሰልጣኞች የፓናል ውይይቱን በሊቀመንበርነት ይመራሉ፡፡

## 2.4 የመምህራን አሰለጣጠን ስላቶችና አተገባበር

### 2.4.1 የፕራክቲከም ምንነትና አተገባበሩ

ፕራክቲከም (የት/ቤት ልምድ) የተማሪ አስተማሪዎች በመምህርነት ሙያ ተመርቀው ወደ ክፍል በመግባት ከማስተማራቸው በፊት ከመምህርነት ሙያ ጋር የሚተዋወቁበት መንገድ ነው፡፡ በማስተማር ሙያ ዋነኛና መሠረታዊ አላባ በመባል የሚታወቀው ፕራክቲከም የአንድን እውናዊ ት/ቤት ልምድ በሚገባ ለማወቅ ያስችላል፡፡ በት/ቤት ውስጥ እየተከናወነ ያለውን የመማር ማስተማር እንቅስቃሴ፣ የተማሪዎችን ባህሪና እውነተኛው የመምህርነት ሙያ ምን እንደሚመስል በመመልከት ዕውቀትና ክሂልን ለማሳደግ ያግዛል(Richards and Nunan 1990:101)፡፡ ሰልጣኝ መምህራን የት/ቤቶች መርሃ ግብር ሙሉ ተሳታፊዎች እንዲሆኑም ይረዳቸዋል፡፡

ለፕራክቲከም ወደ ተባባሪ ት/ቤቶች የሚወጡ የተማሪ አስተማሪዎች በተቻለ መጠን የት/ቤቶቹ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ተሳታፊዎች መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ተሳትፎአቸው ተጠየቃዊ አካሄድን የተከተለና የራሱን ቅደም ተከተል ጠብቆ እያደገ መሄድ ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም ፕራክቲከም የራሱ የሆነ ቅደም ተከተላዊ አፈፃፀም አለውና፡፡

የመጀመሪያው የፕራክቲከም ክፍል ቅድመ ፕራክቲከም (Pre-Practicum) የሚባለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሙሉ ፕራክቲከም (Full-Practicum) በመባል ይታወቃል፡፡ በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ የሚመጣው ክሊኒካል ልምድ (Clinical Experience) ነው (http://www.bc.edu/bc-org/avp/soe/acadamics/practicam/roles.html)፡፡ የተማሪ አስተማሪዎች እነዚህ ደረጃዎችን ለይተው በማወቅ በየደረጃው መፈፀም ያለባቸውን ጉዳይ ማከናወን ይገባቸዋል፡፡ ለምሳሌ በቅድመ ፕራክቲከም ሱፐርቫይዘራቸው በምን በምን ላይ ማተኮር እንዳለባቸውና ከፕራክቲከሙ በኋላ ከእነሱ ምን እንደሚጠበቅ ይነግራቸዋል፡፡ ከዚያ የትኩረት አቅጣጫቸውን በተመደቡበት ት/ቤት፡-

- አጠቃላይ ሁኔታ (ት/ቤቱ የሚገኝበትን ቦታ)
- አስተዳደራዊ መዋቅርና አደረጃጀት
- የመማሪያ ክፍል አውድ
- የመማሪያ ማስተማሪያ መሳሪያዎችና

- በትምህርት ቤቱ በሚታዩ ችግሮችና እየተወሰዱ ባሉ እርምጃዎች ላይ በማተኮር ምልከታ ያደርጋሉ፣ የጽሁፍና የቃል ሪፖርት በማዘጋጀት ለሱፐርቫይዘራቸው ያቀርባሉ፡፡ የሚሰጣቸውንም ምጋቤ ምላሽ ያዳምጣሉ፡፡ በመጨረሻ የተሰጣቸውን አስተያየት መነሻ በማድረግ ወደ ፕራክቲከም ዋናውና ጠቀሚው ክፍል ይሸጋገራሉ፡፡ በብጤ ማስተማርና በንዑስ ማስተማር የጀመሩትን ልምምድ በእውነተኛው የመማሪያ ክፍል አጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡ ልምምዳቸውም በተመደቡላቸው ሱፐርቫይዘሮች እየተገመገመ ድክመትና ጥንካሬያቸው ይገለፅላቸዋል፡፡

በመምህራን ስልጠና ፕራክቲከም የተጠበቀውን ውጤት ሊያስገኝ የሚችለው በአግባቡ የተተገበረ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ የተማሪ አስተማሪዎች ለፕራክቲከም በሚወጡበት ጊዜ ከት/ቤቱ አውድ ማለትም ከት/ቤቱና ከተማሪዎች ባህሪያት፣ የመማር ማስተማር ሂደትና ደረጃ፣ የተማሪዎች የመማርና የመቀበል አቅም፣ በት/ቤቱ በማገልገል ላይ ካለው የማስተማር ዘዴ ጋር ተዋውቀው በንዑስና በማስተማር ልምምድ አዳብረው የተዋጣላቸው መምህራን እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ ያገኙትን እውቀትና ልምድ ለክፍል ጓደኞቻቸው፣ ለሱፐርቫይዘራቸው፣ ለተባባሪ ት/ቤት መምህራን ማንፀባረቅ ይኖርባቸዋል (Moore 1994:39-40, Bartlett 1990:102-106, Fish 1989:32, Fidler 1994:17-18 , MOE 2003:65)፡፡

ይህ ደግሞ በአንድ ት/ቤት መቼት በንድፈ ሐሳብ እና በልምምድ መካከል የጠበቀ ግንኘነት መፍጠር ያስችላል፡፡ ግንኙነቱም የሚፈጠረው ቀጥሎ በተመለከተው መንገድ ይሆናል (MOE 2003:65)፡፡

ሀ. ፕራክቲከም አንድ

ይህ ፕራክቲከም አንድ በመባል የሚታወቀው በመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት ለ13 ሳምንታት የሚዘልቅ ነው፡፡ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ሳምንታት የተማሪ አስተማሪዎች ወደ ተባባሪ ት/ቤቶች በመሄድ በሳምንት ለአራት ጊዜ ያህል ምልከታ ያደርጋሉ፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ሳምንታት ከተመደቡባቸው ትምህርት ቤቶች ጋር የመተዋወቂያ ጊዜያት ናቸው፡፡ ከሦስት እስከ አስራ ሦስት ሳምንታት ደግሞ ተማሪዎች በአሰልጣኞቻቸው እየታገዙና በቡድን በቡድን እየሆኑ ምልከታ በማድረግ ያጠናሉ፡፡ ሁሉንም የክፍል ደረጃዎች ተዘዋውረው የመጎብኘት እድልም ያገኛሉ፡፡ በተባባሪ ት/ቤቶች ለሚቆዩበት ለእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ ከአሰልጣኞቻቸው ጋር በመሆን የሚሰሩትን የስራ እቅድ ያወጣሉ፣ ዓላማቸውን ይነድፋሉ፣ የአሰራር ስልታቸውን ይወስናሉ፡፡ ስለተመደቡበት ት/ቤትና የመማሪያ ክፍሎች በምልከታ ወቅት የሰበሰቡትን መረጃ በማቀናጀት ዝግበ ጥናት (Portfolio) አዘጋጅተው ያቀርባሉ፡፡ ወደ ማሰልጠኛ ተቋማቸው ከተመለሱ በኋላ ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር ሃሳብ ይለዋወጣሉ፣ የየራሳቸውን ገጠመኝ ያንፀባርቃሉ፡፡ በክፍል ውስጥ የቀሰሙዋቸው ኮርሶች (Ps I, Ps II እና Ps IV) የጀመሪያውን ፕራክቲከም በጥሩ ሁኔታ ለማከናወን ማገዝ ያለማገዙን ያስረዳሉ፡፡ እነዚህ ኮርሶች

በምልከታቸው ወቅት የልጆችን ባህሪ ማድነቅ እንዲጀምሩ፣ የእድገት ደረጃቸውንና የመማር ስልታቸውን ለመለየት እንዲችሉ ያግዙዋቸዋል:: የሚገመገሙትም በምልከታ ወቅት ስለ ተባባሪ ት/ቤት ተማሪዎች፣ ስለት/ቤቱ አጠቃላይ ሁኔታ (አደረጃጀት፣ አስተዳደርና ለማስተማር ያለው ምቹነት) በመማሪያ ክፍሎችና በአጠቃላይ በት/ቤቱ ማህበረሰብ የሚታየው የመማር ማስተማር እንቅስቀሴ ምን እንደሚመስል ሰብስበው ባመጡት መረጃ ላይ ተመስርተው በሚያቀርቡት የጽሁፍና የቃል ሪፖርት ይሆናል:: ተባባሪ ነባር መምህራን የመጀመሪያው ዙር ፕራክቲከም መጠናቀቂያ ላይ በአፈፃፀማቸው ዙሪያ ምግበ መረጃ ይሰጡዋቸዋል:: ጥሩ የሰሩት በምን በምን ዙሪያ እንደሆነና ድክመት የታየባቸው በምን በምን ላይ እንደሆነ ይገልፁላቸዋል::

ለ. ፕራክቲከም ሁለት

ይህ ክፍል የመጀመሪያው ፕራክቲከም ቀጣይ ነው:: እንደቀጣይነቱም ከአስራ አራተኛው ሳምንት እስከ 18ኛው ሳምንት ይዘልቃል:: በነዚህ ሳምንታት የተማሪ አስተማሪዎች አንድን ውስን ነገር ለመመልከት ዝግጅት የሚያደርጉበት ነው:: ከዚያ የህፃናትን ባህሪያት በጥልቀት ያጠናሉ፣ ት/ቤቶች ከአካባቢው ማህበረሰብና ከወላጆች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለመመልከት ይጥራሉ፣ ዝግበ ጥናትም ያዘጋጃሉ:: በመጨረሻም ምን እንደተማሩ በቃል ይገልፃሉ::

በዚህ ወቅት በንደፈ ሐሳብ ደረጃ የተማሩትን ኮርስ መነሻ በማድረግ ህፃናት በክፍል ውስጥ እንዴት እየተማሩ እንደሆነ ያጠናሉ፣ ህፃናትን በማስተማር የት/ቤቶችንና የወላጆችን ተግባር ሁሉ ይመለከታሉ::

ሐ. ፕራክቲከም ሦስት

ይህ ክፍል በሁለተኛው መንፈቀ ዓመት ከ1-10 ሳምንታት ይከናወናል:: መዋቅሩ እንደ ፕራክቲከም አንድ ነው:: ይሁን እንጂ ከምልከታ ይልቅ ለማስተማር ልምምድ ትኩረት የሚሰጥበት የፕራክቲከም ክፍል ነው:: አንድን ሕፃን ቀርቦ ከማጥናቱ ጎን ለጎን የተጓዳኝ ክበባትን እንቅስቃሴም ይቃኛል::

መ. ፕራክቲከም አራት

ይህ ክፍል ደግሞ በሁለተኛው መንፈቀ ዓመት ከ10-16 ባሉት ሳምንታት ይከናወናል:: ተማሪዎች በመጀመሪያው አንድ ሳምንት (ከ10-11) ለአራት ሳምንታት ለሚቆየው ፕራክቲከም ይዘጋጃሉ:: ከ12-16ኛው ሳምንት ከተመረጡ ትምህርት ቤቶች ጋር በቅንጅት ይሰራሉ፣ ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እየተረዳዱ የት/ቤቶቹ ስርዓተ ትምህርት መነሻ በማድረግ በተገቢው ርዕስ ዙሪያ የትምህርት እቅድ ያዘጋጃሉ፣ የሁሉንም ህፃናት የመማር ልምድ ለመቃኘትም ጥረት ያደርጋሉ::

በአጠቃላይ የመምህራን ስልጠና በፕራክቲከም የተደገፈ እንዲሆን የተመረጠበት ምክንያትና ዓላማ ለሰልጣኝ መምህራን የመማር ማስተማር መርሆችን በአንድ ት/ቤት የመማሪያ ክፍል መቼት ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ አጋጣሚዎችን ለመፍጠር ነው:: ይህም እውን የሚሆነው ነባር መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ጥበባዊ ምልከታ እያደረጉ ሰልጣኞቹን የመሯቸው፣ ያማከሯቸውና የረዷቸው እንደሆነ ብቻ ነው:: ይህ ከሆነ ደግሞ የተማሪ

አስተማሪዎቹ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ያላቸውን ችሎታና ልምድ ያዳብራሉ፣ ከእውናዊው የማስተማር ስራ ጋር ይተዋወቃሉ፣ ስለ ህፃናትና ወጣቶች ባህሪያት ተገንዝበው፡ እንደየፍላጎታቸው መልስ የመስጠት ችሎታቸውን ያዳብራሉ፣ ውሳኔ የመስጠት ችሎታቸውንና ሐሳብን በማንፀባረቅ የመማርና እራስን የመገምገም ብቃታቸውን ያሳድጋሉ፣ ለት/ቤቶችና ለሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ያላቸውን ስሜትና አመለካከት ለማሻሻልም ይችላሉ።

## 2.4.2 የማስተማር ልምምድ ምንነትና አተገባበሩ

የማስተማር ልምምድ በመምህራን አሰለጣጠን ሂደት የተማሪ አስተማሪዎች በንድፈ ሐሳብ ደረጃ የቀሰሙትን ዕውቀት፣ የማስተማር ዘዴና መርህ በአንድ የመማሪያ ክፍል አውድ ውስጥ በሱፐርቫይዘሮች ወይም በሌላ ሰዎች እየተጎበኙ ወይም እየተገመገሙ የሚያከናውኑት ተግባር ነው (Tann 1994:94)። ይህ ተግባር የተማሪ አስተማሪዎች ሁለንተናዊ ስብዕናቸውንና ብቃታቸውን በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ አለው። እንደ ዓለም (1988፣14) አገላለጽ ከሆነ የማስተማር ልምምድ በመምህራን ስልጠና ውስጥ ዓቢይ ተተኪሪ ጉዳይ በመሆኑ በማስተማር ልምምድ ወቅት የተማሪ አስተማሪዎች ለልምምድ ከተመደቡበት ት/ቤት መምህራን፣ ከአሰልጣኞች፣ ከሱፐርቫይዘሮችና ከብጤዎቻቸው ድጋፍና እርዳታ ማግኘት ይኖርባቸዋል።

ማስተማርን የመማሩ ጉዳይ ሙሉ በሙሉም ባይሆን ቢያንስ በከፊል በማስተማር ልምምድ ሂደት ሊገኝ ይችላል (ዓለም 1988:13)። ከማስተማር ልምምድ የሚገኘው ዕውቀትና ችሎታ ከፊል ነው ያሰኘው የማስተማር ልምምድ በብዙ ችግሮች የተተበተበ ስለሆነ የታሰበውን ውጤት ሳያስገኝ የሚቀርበት አጋጣሚ ብዙ ስለሆነ ነው። ይሁን እንጂ የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ለማስተማር ልምምዱ በቂ ጊዜ መድበው፣ ሰፊ ቅድመ ዝግጅት አድርገው፣ የልምምዱን ሂደት በቅርበት ተከታትለው ውጤቱ የሰመረ እንዲሆን የማድረግ ፍላጎትና አቅም ካላቸው ችግሩ ሊቃለል ይችላል። ብዙዎቹ የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ግን ይህን ጉዳይ ችላ በማለታቸው እንዲያውም የማስተማር ልምምዱ የስልጠናው አንዱ ክፍል መሆኑን እስከመዘንጋት የደረሱበት ሁኔታ እንዳለ እንረዳለን (Abraham and et al 1999:248-249)።

በማስተማር ልምምድ የሚደረገው እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ንድፈ ሐሳብን ከተግባር ለማዛመድ የሚደረግ ጥረትን ሊያካትት እንደሚገባ ዓለም (1988) Greis (1984)ን ጠቅሶ ገልጿል። አንዳንድ የተማሪ አስተማሪዎች ለልምምድ ወደ ተመረጡ ት/ቤቶች በሚሄዱበት ጊዜ ቀደም ሲል በመምህራን ማሰልጠኛ ተቋሙ የማስተማር ኮርሶችን ሲሰጣቸው የነበረውን የትምህርት አቀራረብ ስልት ለመተግበር ሲሞክሩ ይታያሉ (Dobbyn 1979:1)። ይህ ሊሆን የሚችለው አንድም በራስ የመተማመን መንፈስ ካለመኖር አልያም የአሰልጣኝ መምህራኑን የማስተማር ዘዴ እንደሞዴል በመውሰዳቸው ነው። በመጽሐፍ ላይ የተመሰረተ የማስተማር ስልትን ወይም መምህር መር የማስተማር ዘዴ የሚከተል መምህር ካጋጠማቸው በማስተማር ልምምዳቸው ላይ ተጽእኖ ያደርግባቸዋል። እንዲህ ያለ የማስተማር ዘዴ ትርጉም ያለውና

አስደሳች ካለመሆኑ የተነሳ በክፍል ውስጥ ጥሩ መስተጋብርን የመፍጠር አቅም የለውም:: በዚህን ጊዜ የተማሪ አስተማሪዎቹ በራስ የመተማመን ብቃታቸውን ለማጠናከር ከመፍጨርጨር ይልቅ ወኔ ሲከዳቸው ይታያሉ (Jarvis 1987:18):: ከማሰልጠኛ ተቋማቱ የሚቀስሙት በንድፈ ሐሳብ ትንታኔ ላይ ብቻ የሚያተኩር ከሆነም ተመሳሳይ ችግር መከሰቱ አይቀርም (ዓለም 1988:14)::

Fish (1989:98-100) የተለያዩ የማስተማር ሞዴሎች እንዳሉ በመግለጽ ንድፈ ሐሳብን ከተግባር ለማዛመድ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳላቸው አመልክተዋል:: ሞዴሎቹ በሁለት ሲከፈሉ የመጀመሪያው ማስተማርን የመማር ሞዴል ነው:: ሰባት ያህል የአሰለጣጠን ሂደትን ያካትታል:: ሁለተኛው ደግሞ ንድፈ ሐሳብን ከተግባር የማዛመጃ ሞዴል ነው:: አራት ያህል ንዑስ ሞዴሎችን አካቷል:: ቀጥለን ማስተማርን የመማር ሞዴል ሰባት ንዑስ ክፍሎችን ለመመልከት እንሞክራለን::

1. ፍዝ ምልከታ (**Sitting with Nellie**):– ይህ የልምምድ ሞዴል ከአንድ ሰው አጠገብ በመቀመጥ የሚሰራውን ሥራ በመመልከት የመቅዳት ስልት ነው:: በመሠረቱ ይህ በፋብሪካ ውስጥ ለመስራት እንጂ ማስተማርን ለመማር የሚረዳ ሞዴል አይደለም::
2. ንቁ ምልከታ (**Pure Observation**) :–ይህ ቀለል ያለ ሞዴል ነው:: የማስተማር ተግባር በማንኛውም ሁኔታ ቢከናወን ተመሳሳይነት ያለውና በግልጽ የሚታይ በመሆኑ በምልከታ የማስተማር ስራን መቅዳት ይቻላል::
3. ሙሉ ጥልቀት (**Total immersion**) :– በዚህ ሞዴል አንዱና አማራጭ የሌለው የመማሪያ መንገድ አስቸጋሪ በሆኑ ተግባራት ውስጥም ቢሆን ሙሉ በሙሉ መግባትና ችግሩን ተቋቁሞ ትምህርት መቅሰም ወይም ውድቀትን በፀጋ መቀበል ነው:: በዚህ መንገድ ማንኛ ውም ሰው ማስተማርን መማር አይችልም::
4. ተግባራዊ ትንታኔ (**Task analysis**) :– ይህ ሞዴል ማስተማር ክሂላዊ መሠረት ባላቸው ተግባራት ላይ የሚያተኩር መሆኑን ያመለክታል:: መምህራን የሚያስተምሩትን ነገር መተንተን ይጠበቅባቸዋል:: የተማሪ አስተማሪዎችም ተግባር እየተነተኑ ዕውቀትን ይቀስማሉ:::
5. ንዑስ ማስተማር (**Micro-teaching**) :– ይህ ከሌሎቹ ሞዴሎች ለየት ያለ ሞዴል ነው:: ምክንያቱም በቀጥታ ማስተማርን በመማር ላይ ያተኮረ ነው:: ብዙውን ጊዜ ንዑስ ማስተማር በአንድ አነስተኛ ክፍል በቪዲዮ ካሜራ በመታገዝ ሲከናወን ይችላል::
6. የቡድን ማስተማር ልምምድ (**Group Instructional Practice**):- የቡድን አባላት በት/ቤት የመማሪያ ክፍል ውስጥ ከሱፐርቫይዘራቸው ጋር ሆነው በማየት ወይም በመስራት ማስተማርን የሚማሩበት ሞዴል ነው::

7. ባለ ሁለት ትኩረት ስልት (Double focus Technique) :-በመደበኛ የመማሪያ ክፍል መምህር፣ ሱፐርቫይዘር፣ የተማሪ አስተማሪዎች፣ የክፍል ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት እርስ በርሳቸው ሊማማሩበት የሚችሉበት ሞዴል ነው፡፡ ባለሁለት ትኩረት ስልት የተባለውም መደበኛ ተማሪዎች ትምህርታቸውን እየተከታተሉ የተማሪ አስተማሪዎች ማስተማርን መማር በመቻላቸው ምክንያት ነው፡፡

ከላይ በዝርዝር ለማየት እንደተሞከረው ከመጀመሪያው ሞዴል በስተቀር ማስተማርን ለመማር የሚያስችሉ ሞዴሎች መሆናቸውን ነው፡፡ ስለዚህ በመምህራን አሰለጣጠን ሂደት እንደ አስፈላጊነቱ ሞዴሎቹን እየመረጡ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

ሁለተኛው የFish (1989) ንድፈ ሐሳብን ከተግባር ጋር የማዛመጃ ሞዴል በውስጡ አራት ንዑሳን ሞዴሎችን ይዟል፡፡

1. ልይይታዊ ሞዴል (Separatist model):- ንድፈ ሐሳብና ተግባር ምንም ዓይነት ዝምድና የሌላቸው ሁለት የተለያዩ ነገሮች እንደሆኑ የሚያሳይ ሞዴል ነው፡፡ የንድፈ ሐሳብም ሆነ የተግባር ጠቀሜታ ላቅ ያለ ቢሆንም መሠረታዊ የሆነ ግንኙነት ግን የላቸውም የሚል ሞዴል ነው፡፡
2. አጋጣሚያዊ ሞዴል (The Coincidental model):- ንድፈ ሐሳብ የተግባር መሠረት ነው፡፡ በክፍል ውስጥ የሚደረግ ማንኛውንም እንቅስቃሴ የሚመራው ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀት ነው፡፡ ተግባር ወደ ንድፈ ሐሳብ ይመራል የሚለው ሐሳብ በዚህ ሞዴል ተቀባይነት የለውም፡፡
3. አዛማጅ ሞዴል (The relationist model):- ንድፈ ሐሳብና ተግባር ሊነጣጠሉ የማይችሉ ነገሮች ናቸው፡፡ የንድፈ ሐሳብ አካል በመማሪያ ክፍል ውስጥ ያለና ቀጥተኛ የሆነ ተጽእኖ ሊያሳድር የሚችል መሆኑ ይታመናል፡፡
4. የግላዊያን ሞዴል (Individualist model) :- በዚህ ሞዴል ንድፈ ሐሳብ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎች ግላዊ ልምድ ክምችት ጋር ይያያዛል፡፡ በሌላ አነጋገር ተግባር ንድፈ ሐሳብን ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

ከፍ ሲል ለመመልከት እንደተሞከረው በማስተማር ልምምድ ንድፈ ሐሳብን ከተግባር የተቆራኘ ለማድረግ ያስችላሉ የተባሉ ሞዴሎች መኖራቸውን ነው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ሞዴሎች ንድፈ ሀሳብን ከተግባር ለማዛመድ ያስችላሉ ተብለው ቢታሰቡም ንድፈ ሀሳብና ትግበራ ተነጣጥለው ሊታዩ የማይችሉ መሆናቸው ከግንዛቤ ውስጥ መግባት ይኖርበታል፡፡

ይህም ሆኖ በመምህራን ስልጠና ሂደት መነሳታቸው የማይቀሩ ሦስት ጥያቄዎች መኖራቸውን Fish (1989:15) ሳይጠቁሙ አላለፉም፡፡ እነሱም:–

1. የመምህርነትን ሙያ በማሻሻል ሂደት የልምምድ ተግባር ምንድነው? ብቃትን ለማሻሻል ያለው ድርሻ ምን ያህል ነው?

2. የተማሪ አስተማሪዎች በልምምድ ለመማር የሚያደርጉትን ጥረት ሊያግዛቸው የሚችለው ምንድነው? እንዴትስ ይረዳቸዋል?

3. የተማሪ አስተማሪዎች በልምምድ ሙያቸውን ለማሻሻል የሚያደርጉትን ጥረት የሚረዷቸው እነማናቸው? እንዴትስ ይረዷቸዋል የሚሉት ናቸው።

በመምህራን አሰለጣጠን ሂደት ሌላው የሚነሳው ጥያቄ ከንድፈ ሐሳብ እና ከልምምድ መማር የትኛው የተሻለ ነው? የሚለው ነው። እስካሁን ድረስ ይህ ጥያቄ ሁሉን ሊያስማማ በሚችል መልኩ አልተመለሰም። ይሁን እንጂ መሠረታዊ የሆነ ስልጠና ለማግኘት ከታሰበ በልምምድ መማሩ ጠቃሚ እንደሆነ ከ Fish (1989) ሞዴሎች ለመረዳት እንችላለን።

በሀገራችን ያለውን የመምህራን አሰለጣጠን ሂደት ስንቃኝ በበርካታ ችግሮች ተጠፍሮ እንደተያዘ እንረዳለን። መምህራንን በማሰልጠን ሂደት የሚታየውን ችግር በተመለከተ እነ Abraham (1999:249) ትምህርት ሚኒስቴር (1998)ን በመጥቀስ እንደሚከተለው አስፍረውታል።

> ከመምህራን ስልጠና አንዱና ዋነኛው አካል የሆነው የማስተማር ልምምድ ነው። በሁሉም ተቋማት በተመሳሳይ ሁኔታ ይካሄዳል። ይኸውም ዕጩ መምህራኑ በሚገኙበት ከተማ ባሉ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ተደልድለው ለአንድ ወር (ለአራት ሳምንታት) ልምምድ ያካሄዳሉ። በአብዛኛው ልምምዱ የሚካሄደው በግንቦት ወር ነው። ከተሰጠው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ አንድ ሳምንት ለምልከታ የተቀሩት ሳምንታት ለማስተማር ልምምድ የተመደቡ ናቸው። . . . ከገጠሙት ችግሮች መካከል የዕጩ መምህራን ብዛትና የመለማመጃ ት/ቤቶች ክፍል ባለመመጣጠናቸው የልምምድ ክፍለ ጊዜ እጥረት፣ ዕጩ መምህራን በሰለጠኑበት ቋንቋ ልምምድ ለማካሄድ አለመቻል ናቸው።

ከፍ ሲል እንደተገለፀው የማስተማር ልምምድ በሁሉም ተቋማት ከፍተኛ የሆነ ችግር እየገጠመው ያለ መሆኑን ነው። እነ Abraham (1999:248) የBedru and Fekadu (1996)ን የጥናት ውጤት በመጥቀስ በተጨማሪ እንደገለፁት የማስተማር ልምምድ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ችግሮች አሉበት። እነሱም:-

- የንዑስ ማስተማር (Micro-Teaching) ጠቀሜታ አለመታወቅና አለመተግበር
- የማስተማር ልምምድ ዓላማን ለይቶ አለማወቅ
- ለአራት ሳምንታት የሚቆይ የማስተማር ልምምድ በቂ አለመሆን
- የአንድ ጊዜ አጭር ልምምድ መምህራንን ለማሰልጠን በቂ አለመሆን
- የተማሪ አስተማሪዎች በሱፐርቫይዘሮች የሚገመገሙት የአንድ ትምህርት ይዘትን መሠረት አድርጎ መሆን
- ሱፐርቫይዘሮች የክፍል ውስጥ ምልከታ የሚያደርጉት ለሁለት ጊዜ ብቻ መሆን ወዘተ. ናቸው።

እነዚህን የጥናት ውጤቶች መሠረት በማድረግ ይመስላል ትምህርት ሚኒስቴር አዲስ የመምህራን ስልጠና ፖሊሲ የነደፈው:: በአዲሱ የመምህራን ስልጠና ፖሊሲም የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት የማስተማር ልምምድ ፕሮግራም በሚቀርጹበት ጊዜ ቀጥሎ የተመለከቱትን ነጥቦች ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት እንዳለባቸው ተገልፆ ይገኛል::

1. ከእያንዳንዱ የስልጠና ዓመት መጀመሪያ አንስቶ የማስተማር ልምምድ ፕሮግራሙ የሚካሄድበትን መንገድ ማመቻቸት፣
2. የንዑስ ማስተማር ስልቶችን በመቀየስ መጠቀም፣
3. የሱፐርቪዥንና የመገምገሚያ መስፈርቶችን በማዘጋጀት በንዑስ ማስተማርና በማስተማር ልምምድ ወቅት የተማሪ አስተማሪዎችን እንቅስቃሴ መገምገም፣
4. በማስተማር ልምምድ ፕሮግራም ወቅት የሱፐርቪዥን አተገባበርና የምግበ መረጃ አሰጣጥን በሚመለከት ወጥ የሆነ መመሪያና ደንብ በማውጣት መገልገል ይጠበቅባቸዋል (Abraham and et al. 1999:249-250)::

### 2.4.3 የማስተማር ልምምድ አስፈላጊነት

ስለ ማስተማር ልምምድ አስፈላጊነት የተለያዩ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል:: የማስተማር ልምምድ የተማሪ አስተማሪዎች በእውናዊው የመማሪያ ክፍል አውድ ከሚከናወነው የመማር ማስተማር ሂደት ጋር እራሳቸውን በማስተዋወቅ የቀሰሙትን ስነ ልቦናዊ፣ ስነ ትምህርታዊ፣ ስነ ዘዴያዊ ዕውቀት እንዲሁም ክሂል ወደ ተግባር ለመለወጥ ያስችላቸዋል (KCTE 1992:163-164)::

እንደ Wragg (1974:44) አገላለጽ ከሆነ የማስተማር ልምምድ በመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር የተማሪ አስተማሪዎችን ማንነት፣ አመለካከት፣ ተነሳሽነት፣ ስብዕናና በአጠቃላይ በክፍል ውስጥ ማሳየት የሚገባቸውን ባህሪ ለማሳደግ ያስችላል:: Stones and Morris (1972:23) በበኩላቸው የማስተማር ልምምድን አስፈላጊነት ሲገልፁ የተማሪ አስተማሪዎች ንድፈ ሐሳብን መነሻ አድርገው፣ ነባር መምህራን ሲያስተምሩ በቅርብ ተከታትለው፣ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ያለውን እንቅስቃሴ ተገንዝበውና የራሳቸውን ዝግጅት አድርገው የማስተማር አጋጣሚ ይፈጥርላቸዋል:: ይህ ደግሞ ከመምህራን ማህበራዊና አስተዳደራዊ ኃላፊነት ጋር ያስተዋወቃቸዋል ይላሉ:: አንድን የትምህርት ዓይነት በምን ዓይነት መንገድ እንደሚያስተምሩ፣ ተማሪዎችን እንዴት እንደሚቆጣጠሩ፣ የመማር ማስተማር እንቅስቃሴው በአግባቡ እንዲከናወን ለማድረግ ከሚወሰዱ እርምጃዎች ጋር እንዲተዋወቁ ያደርጋቸዋል በማለት Everston (1985:51) ያስረዳሉ::

Stones and Morris (1972:14-25) የማስተማር ልምምድ የሚከተሉትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ሲባል የሚከናወን መሆኑን ይገልፃሉ::

- የተማሪ አስተማሪዎች ተገቢውን የመምህር ተማሪ ግንኙነት ለመፍጠር የሚችሉበትን አጋጣሚ ለማመቻቸት
- የተማሪ አስተማሪዎች ንድፈ ሐሳብን ወደ ተግባር የሚለወጡበትን አጋጣሚ ለመፍጠር፣

- የተማሪ አስተማሪዎችን በመገምገም ለመምህርነት ሙያ ብቃት ያላቸው መሆናቸውን ለማረጋገጥ፣
- የማስተማር ልምምድ እንዲያደርጉ፣
- ጥሩ ጥሩ የት/ቤት ልምዶችን ለመቅሰም እንዲችሉ
- የማስተማር ችሎታቸውን ለማዳበር፣
- ለመምህርነት ሙያ ያላቸውን አመለካከት ለማሻሻል፣
- የመምህርነት ባህሪያትን ለመረዳት፣
- የሚያስተምሯቸውን ተማሪዎች ዕድገትና ለውጥ ለመገምገም አጋጣሚውን ለመፍጠር ሲባል ይከናወናል፡፡ በአጠቃላይ መምህራን የማስልጠኑ ሂደት የተሳካ እንዲሆን ካስፈለገ ስልጠናው በማስተማር ልምምድ መታገዝ ይኖርበታል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ከታሰበ ደግሞ በማስተማር ልምምድ ወቅት ሊተገበሩ የሚገባቸውን ተግባራት በየደረጃው መፈፀም ያስፈልጋል፡፡ Farrant (1980) በየደረጃው ሊከናወኑ የሚገባቸውን የማስተማር ልምምድ ተግባራት እንደሚከተለው በሦስት ደረጃ ከፍለው ያስቀምጧቸዋል፡፡

## ሠንጠረዥ ሁለት

## ባለ ሦስት ደረጃ የማስተማር ልምምድ

| ደረጃ /Phase | ዓላማ | የሚከናወነው ተግባር | ቆይታ |
|---|---|---|---|
| ደረጃ 1 የት/ቤት ምልከታ | • የተማሪ አስተማሪዎችን ከት/ቤት አካባቢ ጋር ማላማድ<br>• በሰልጣኞች አእምሮ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ምስልን መፍጠር<br>• የምርምር ርዕሶችን እንዲለዩ መርዳት | • እያንዳንዱ የተማሪ አስተማሪ ራሱን ለት/ቤት ማህበረሰብ ያስተዋውቃል፡፡<br>• የት/ቤቱን ግቢ ንጽህና፣ አስፈላጊ መረጃዎችን፣ መጻሕፍትንና ቁሳቁሶችን ይመለከታሉ<br>• የት/ቤቱን አደረጃጀትና አስተዳደር፣ ኃላፊዎችን፣ መምህራንን፣ ትምህርት ማዕከልን ወዘተ. ይጎበኛሉ፡፡ | በአጠቃላይ ለሁለት ሳምንት (ጥቅምት) |
| ደረጃ 2 ዝግጅትና ምርምር | • በት/ቤት ችግሮች ዙሪያ ተግባራዊ ምርምሮችን ለማድረግ የሚያስችሉ መረጃዎችን መሰብሰብ | • ስለተማሪዎች ግላዊና ትምህርታዊ ሁኔታ የሚገልፁ መረጃዎችን ይሰበስባሉ፡፡<br>• በት/ቤት ያሉና የሌሉ | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | • በአንድ ህፃን ላይ የተመሠረተ ውስን ጥናት ማድረግ<br>• ከንድፈ ሐሳብ በዘለለ ስልጠናው ያለው ተግባራዊነት ማሳየት<br>• አስፈላጊ የትምህርት ይዘቶችን ለማዘጋጀት የሚያስችሉ የትምህርት መሣሪያዎችን መሰብሰብ<br>• በሰልጣኞችና በመምህራን መካከል በት/ቤቱና በግል ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት እንዲያደርጉ ማበረታታት<br>• በጋራ ጉዳዮች ላይ ከመምህራን ጋር ውይይት ማድረግ | ቁሳቁሶችን ዝርዝር ያሰባስባሉ።<br>• በየክፍል ደረጃው ያለውን የመምህራን ተማሪ ጥምርታ ያጠናሉ።<br>• አስፈላጊ የሆኑ የመማሪያ መፃሕፍን፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ይሰበስባሉ። | |
| ደረጃ 3 ትግበራ | • ማስተማር<br>• መርጃ መሳሪያዎችን መርጦ ማዘጋጀት<br>• ሕፃናትን ማጥናት<br>• ልምምዱ ሲጠናቀቅ ያዘጋጁትን ሪፖርት ማቅረብ | • የትምህርት ዕድቅ ያዘጋጃሉ<br>• ትምህርቱን በተማሪ ተኮር አቀራረብ ያቀርባሉ።<br>• ተማሪዎችን ይመራሉ ያለማምዳሉ<br>• በመረጡት ርዕስ ዙሪያ መረጃ ያሳስባሉ።<br>• የጥናታቸውን ውጤት በሚመለከት አጭር ንግግር ያደርጋሉ። | |

### 2.4.4 የሱፐርቪዥን ምንነትና አቀራረብ

#### 2.4.4.1 የሱፐርቪዥን ምንነት፣ ተግባርና ዓላማ

የማስተማር ልምምድ ንድፈ ሐሳብን ወደ ተግባር የመለወጫ ዓይነተኛ መንገድ እንደሆነ ለማየት ሞክረናል:: አሁን ደግሞ ስለሱፐርቪዥን ምንነት፣አቀራረብ ከማስተማር ልምምድ ጋር ስላለው ግንኙነት፣ ተግባርና ዓላማው ለማየት እንሞክራለን::

ሱፐርቪዥን በጎ አላማ በነበራቸው የአውሮፓና የሰሜን አሜሪካን ማህበራዊ ተቋማት በ19ኛው ክ/ዘመን እንደተከሰተ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: ሱፐርቪዥኑም ቅጥርን፣ ድርጅትንና የበላይ አካላት ምልከታ ብዛት ያላቸው በጎ ፈቃደኛ በነበሩ ሰዎችና በኋላም በቅጥር ሰራተኞች ይከናወን ነበር:: በጎ ፈቃደኞች በዘልማድ ጎብኝዎች የሚባሉት ሰዎች ናቸው:: ተግባራቸውም ጥቂት ቁጥር ያላቸውን ቤተሰቦች በመምከርና በመርዳት ራሳቸውን ለማስቻልና መልካም ባህሪን ለማዳበር እንዲችሉ ማገዝ ነበር::

አሁን አሁን ሱፐርቪዥን የሚለውን ቃል በተለያየ መንገድ የመጠቀም አዝማሚያ ይታያል:: የትምህርት ባለሙያዎች፣ መምህራን፣ የስርዓተ ትምህርት ኤክስፐርቶችና አማካሪዎች ወዘተ. በሱፐርቪዥን ስራ ላይ በመስማራታቸው ሱፐርቫይዘር በመባል ይጠራሉ (Wallace 1991:107)::

በጥንታዊ ቻይና፣ አፍሪካና አውሮፓ ሥርዓተ ማህበር ሱፐርቪዥን ይንፀባረቅባቸው የነበሩ ሁኔታዎች አሉ:: በዚያ ዘመን የእጅ ባለሙያ የነበሩ ሰዎች ሱፐርቪዥን ያስፈልጋቸው የነበሩና በጌቶቻቸው ስር የሚተዳደሩ ነበሩ:: ይህ በተወሰኑ ሰዎች ወይም ኤክስፐርቶች ቁጥጥር ስር ሆኖ በመስራት መማር (Learning through doing) የሱፐርቪዥን መገለጫ መንገድ ነበር::

ስለትምህርት በተፃፉ በርካታ ጽሁፎች ግን ሱፐርቫይዘር ሊባሉ የሚችሉት የኮሌጅ መምህራን በተለይም ንድፈ ሐሳብና ስነ ዘዴን በማስተማር ትምህርቱ በልምምድ ወደ ተግባር የሚለወጥበትን ሁኔታ በማመቻቸት ክትትል የሚያደርጉ ባለሙያ ናቸው (Woodward 1991:203):: በመምህራን ስልጠና ወቅት የሚደረግ ሱፐርቪዥን ስልጣኞች በማስተማር ልምምድ ላይ እያሉ በክፍል ውስጥ በመገኘት መከታተልን፣ ማዳመጥን፣ ማስታወሻ መያዝን ያጠቃልላል:: ከክፍል ውጭ በምልከታ ውጤትና ምግበ መረጃ ዙሪያ የሚደረግ ውይይትም ከሱፐርቪዥን ይመደባል (Woodward 1991:203)::

ሱፐርቪዥንን የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መንገድ ሲበይኑት ይታያሉ:: ጥቂቶቹ በጣም አጥብበው ሱፐርቪዥን በመምህራን ስልጠና የማስተማር ልምምድ ወቅት ስህተትን (ድክመትን) የመፈለግ ሂደት እንደሆነ ይገልፃሉ:: Gebhard (1990) ሱፐርቪዥን ድክመትን የመፈለግ ሂደት ብቻ ሳይሆን መምህራንን መምራትን ፣ጥሩ የማስተማር ዘዴ መጠቀምን፣ ሌሎች የማስተማሪያ ሞዴሎች ማሳየትን፣ መምህራንን ማማከርና በሚያስተምሩበት ጊዜ መገምገምን ሊያጠቃልል እንደሚችል ይገልፃሉ:: Fanselow (1990) በበኩላቸው ሱፐርቪዥን ጥሩ ልምድና ዕውቀት ያለው ሰው ልምድ የሌለውን ሰው ለመገምገም የሚያስችል መሳሪያ ነው በማለት ይገልፁታል::

በ1910ዎቹና በ1920ዎቹ አካባቢ ሱፐርቪዥን ሰዎች ምን መስራት እንዳለባቸው መንገርና በተነገራቸው መሠረት መስራት መቻል አለመቻላቸውን የማረጋገጥ ሂደት ተደርጎ ይቆጠር ነበር (Lovell 1983:2):: ከዚህ እንደምንረዳው ሱፐርቪዥን በጣም ቀላል ተግባር ተደርጎ ይቆጠር እንደነበር ነው:: ነገር ግን እንዲህ የማዘዝና የመከታተል ሂደት ብቻ ሳይሆን በውስጡ በጣም በርካታ ውስብስብ ነገሮችን ይዞ ይገኛል:: ምንም እንኳን ቀደም ባለው ጊዜ የሱፐርቪዥን ዓላማ ፍንትው ብሎ ባለመቀመጡ ስለተግባሩ አፍን ሞልቶ መናገር ባይቻልም ቀስ በቀስ እየተጠናከረ መጥቶ የመማር ማስተማር ሂደትን ለማጠናከር የሚያስችል ዓይነተኛ ዘዴ ለመሆን እንደበቃ እንገነዘባለን:: በማስተማር ሂደት አንድን ጠንካራ ጎን ይበልጥ እንዲጎለብት ለማድረግና ድክመትን ለማሻሻል የሚያደርገው አስተዋጽኦም ቀላል አይደለም:: በተለይ በማስተማር ልምምድ ውስጥ የሚካሄድ ሱፐርቪዥን በትክክል ከተተገበረ የተማሪ አስተማሪዎች ጥሩ ዕውቀትና ክሂልን ሊያዳብሩበት እንደሚችሉ በእርግጠኛነት መናገር ይቻላል::

### 2.4.4.2 የሱፐርቪዥን አቀራረቦች

ሱፐርቪዥን በተለያየ መንገድ ሊከናወን እንደሚችል መረዳት ይቻላል:: የተለያዩ የመስኩ ምሁራን የሱፐርቪዥን አከናወን ስልትን መነሻ በማድረግ አቀራረቡን እንደየራሳቸው አመለካከትና ተሞክሮ ሲመደቡት ይታያሉ:: ቀጥለን በመምህራን አሰለጣጠን ሂደት ተዘውትረው የሚታዩት የአራት ምሁራን ሱፐርቫይዘራዊ አቀራረቦችን ለመመለከት እንሞክራለን::

የሱፐርቪዥን ሂደት ከሚያሳየው ባህሪ በመነሳት የሱፐርቪዥን አቀራረብን በሦስት መድበው ለመመልከት ሙከራ ያደረጉት Freeman (1982) ናቸው:: እነዚህ ሶስት አይነት ሱፐርቫይዘራዊ አቀራረቦች ሱፐርቫይዘሪ (ትእዛዛዊ) አቀራረብ (Supervisory approach) አማራጫዊ አቀራረብና (Alternative approach) ኢትእዛዛዊ አቀራረብ (non-directive approach) በመባል ይታወቃሉ::

እንደ Freeman (1982) አገላለፅ ከሆነ ሱፐርቫይዘሪ (ትዕዛዛዊ) አቀራረብ በሱፐርቫይዘሩና በተማሪ አስተማሪዎች መካከል ያለው ግንኙነት የመሪና የተመሪ ዓይነት ነው:: የተማሪ አስተማሪዎች ሱፐርቫይዘሩ የሚለውን ሁሉ መቀበል ይጠበቅባቸዋል:: በአማራጫዊ የሱፐርቪዥን አቀራረብ ስልት ግን ሱፐርቫይዘሩ የተለያዩ አማራጮችን በማቅረብ የተማሪ አስተማሪዎች በማስተማር ልምምድ ወቅት ያከናወኗቸው ተግባራት ምን ይመስሉ እንደነበሩ ለመቃኘት ጥረት እንዲያደርጉ ያደርጋል እንጂ ያልኩዋችሁን ሁሉ ልትቀበሉኝ ይገባል አይልም:: በዚህ አቀራረብ ሱፐርቫይዘሩ የተለያዩ አማራጭ የማረሚያ ሐሳቦችን በማቅረብ የተማሪ አስተማሪዎችን ለነፃ ውይይት የሚጋብዝ በመሆኑ የሱ ተጽእኖ ጎልቶ አይታይም:: በኢትእዛዛዊ አቀራረብ ሱፐርቫይዘሩና ተማሪዎች ነፃ የሆነ ውይይት ያደርጋሉ እንጂ ሱፐርቫይዘሩ ምንም አይነት ትዕዛዝ አይሰጥም፣ ምክር አይለግስም:: ይህ አቀራረብ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ

የተማሪ አስተማሪዎች የሱፐርቫይዘራቸውን ሐሳብና አመለካከት ሊቀበሉት ወይም ላይቀበሉት ይችላሉ (ዓለም 1988፣ 20 Wallace 1991:115 Curran 1978)::

Kauffman (1992) Zahorik (1988)ን በመጥቀስ በበኩላቸው የሱፐርቪዥን አቀራረብን ትዕዛዛዊ ባህሪ ሱፐርቪዥን (Behavior Prescriptor)፣ ሀሳብ ገላጭ ሱፐርቪዥን (Idea interpreter) እና ድጋፍ ሰጭ ሱፐርቪዥን (Person supporter) በማለት በሦስት ይከፍሉታል:: ዓለም (1988) ይህን አከፋፈል መነሻ አድርጎ እያንዳንዱን ሱፐርቫይዘራዊ አቀራረብ ሲገልጽ ትዕዛዛዊ ባህሪ ሱፐርቪዥን ስሙ እንደሚያመለክተው ሱፐርቫይዘሮች ለተማሪ አስተማሪዎች መመሪያና ትዕዛዝ በመስጠት የሰጡት መመሪያና ትዕዛዝ ተግባራዊ እንዲሆን ይሻሉ:: ራሳቸውን እንደሞዴል፣ እንደበላይ ኃላፊና ጠባቂ አድርገው ይመለከታሉ ይላል:: ሀሳብ ሰጭ የተሰኘው የሱፐርቪዥን ሂደት ከ (Freeman 1982) አማራጫዊ አቀራረብ ጋር የሚመሳሰል ሲሆን ሱፐርቫይዘሮች የተለያዩ አማራጭ መንገዶችን በመፈለግ ለማመልከት የሚጥሩበት አቀራረብ ነው:: ይሁን እንጂ በተማሪ አስተማሪዎች ላይ ለውጥ ማየትን አጥብቀው ስለሚፈልጉ አልፎ አልፎ ትዕዛዝ በመስጠት የተማሪ አስተማሪዎቹ እንዲከተሏቸው ለማድረግ ሲጥሩ ይታያሉ:: ድጋፍ ሰጭ አቀራረብ እንደስሙ ሁሉ ለተማሪዎች አስፈላጊውን እርዳታ በማድረግ ላይ የተመሠረተ አቀራረብ ነው:: የተማሪ አስተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚኖራቸውን ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት በአግባቡና በተሻለ መንገድ እንዲያከናውኑ ሁኔታዎችን የሚያመቻች ሱፐርቫይዘራዊ አቀራረብ ነው:: ይህን ዓይነት አቀራረብ የሚጠቀሙ ሱፐርቫይዘሮች ከክፍል ምልከታ በኋላ በሚያደርጉት ውይይት ወቅት የተማሪውን ሐሳብ በትዕግስት ያዳምጣሉ:: የክፍል ምልከታ ከማድረጋቸውም በፊት ቢሆን የተማሪ አስተማሪዎች በማስተማር ልምምድ ወቅት ምን ምን ማከናወን እንዳለባቸው በሚገባ ይገልፁላቸዋል:: የተማሪ አስተማሪዎች በማስተማር ልምምድ ወቅት የሚያስተምሩትን የትምህርት ይዘትና ዕቅድ ሲያዘጋጁ ያግዛሉ፣ ይደግፋሉ:: ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ምን ላይ ቢያተኩሩ የተሻለ ሊሆን እንደሚችል በክፍል ውስጥ ያዩትን እንቅስቃሴ መነሻ በማድረግ ይገልፃሉ:: ከተማሪ አስተማሪዎች ጋር ለመስራት ያላቸውን ዝግጁነት ሁልጊዜ ያሳያሉ (ዓለም 1988፣ 21 Proctor 1994:138-139)::

ሌላው ሱፐርቫይዘራዊ አቀራረብን በስድስት ሞዴሎች ከፍለው ለማየት የሞከሩት Gebhard (1990:156-166) ናቸው:: የሳቸው አቀራረብ ከላይ ካየናቸው የሱፐርቪዥን አቀራረብ ዓይነቶች ጋር ብዙ የሚጋሯቸው ነጥቦች ቢኖሩም ሁለቱ የመስኩ ባለሙያዎች ሱፐርቫይዘራዊ አቀራረብን በሦስት መደበው ለመመልከት ሲሞክሩ እሳቸው ግን ሌሎች ሦስት ተጨማሪ የአቀራረብ ስልቶችን ጨምረው ወደ ስድስት ከፍ አድርገዋቸዋል:: ስድስቱንም አቀራረቦች በቅደም ተከተል ለማየት እንሞክራለን::

1. **መራሄ ሱፐርቪዥን (Directive Supervision):–** በዚህ የሱፐርቪዥን አቀራረብ ሱፐርቫይዘሮች የተማሪ አስተማሪዎችን ይመራሉ:: መረጃና መመሪያ በመስጠት የተሰጣቸውን መመሪያና መረጃ መሰረት በማድረግ ስራቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን

ይገመግማሉ:: ይህ አቀራረብ በአንዳንድ የመስኩ ባለሙያዎች የተለያዩ ትችቶች ተሰንዝረውበታል:: የእነዚህ ምሁራን ትችት የሚያነጣጥረው በአንድ ወገን የሚቀርብን መረጃ መነሻ በማድረግ ጥሩ የማስተማር ዘዴ ምን እንደሚመስል መተንበይ ያስቸግራል የሚል ነው:: ሌላው የዚህ አቀራረብ ሞዴል ችግር ሱፐርቫይዘር መር በመሆኑ በተማሪ አስተማሪዎች ላይ የዝቅተኝነት መንፈስ መፍጠሩና ድፍረት ማጣትን የሚያስከትል መሆኑ ነው::

2. ባለአማራጭ ሱፐርቪዥን (**Alternative Supervision**):- ከላይ ከተጠቀሰው የሱፐርቪዥን አቀራረብ በተለየ መልኩ ይህ አቀራረብ ሚናው የተማሪ አስተማሪው በክፍል ውስጥ የተለያዩ አማራጮችን እንዲጠቀም ማበረታታት ነው::

3. ቅንጅታዊ ሱፐርቪዥን (**Collaborative S upervison**):- ይህ የሱፐርቫይዘራዊ አቀራረብ ሞዴል ስሙ እንደሚያመለክተው ሱፐርቫይዘሮች ከተማሪ አስተማሪዎች ጋር በመመካከር የሚሰሩበት ነው:: ምክክርና ቅንጅቱ ከዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ዝግጅት ጀምሮ እስከ ማስተማር ልምምዱ ሂደት ይዘልቃል:: ሱፐርቫይዘሮችና የተማሪ አስተማሪዎች ቅንጅት በመፍጠር ምርምር በማድረግ ወደ መላ ምት (Hypothesis) ይደርሳሉ:: Gebhard (1990:159) Cogan (1973)ን በመጥቀስ እንደሚገልፁት የማስተማር ስራ በአመዛኙ ችግር ፈቺ ሂደት ሆኖ በሱፐርቫይዘሮችና በተማሪ አስተማሪዎች መካከል ሐሳብ መጋራትን የሚጠይቅ ሂደት ነው::

4. ኢአማራጫዊ ሱፐርቪዥን (**Non-alternative supervision**):- በዚህ ሱፐርቫይዘራዊ አቀራረብ ሞዴል የሱፐርቫይዘሮች ሚና የተማሪ አስተማሪዎች ስለሚያስተምሩት ትምህርት በቂ ዕውቀት ኖሯቸው የበለጠ እንዲሰሩ ማበረታታት ነው:: ይሁን እንጂ ከዚህ የሱፐርቪዥን አቀራረብ ሁለት ውጤቶችን መጠበቅ ይቻላል:: በተወሰኑ የተማሪ አስተማሪዎች ላይ ጭንቀትን ሲፈጥር በሌሎች ላይ ደግሞ መገለልን ያስከትላል::

5. ፈጠራዊ ሱፐርቩዥን (**Creative Supervision**) :- የዚህ ሞዴል ሐሳብ አመንጭ De Bono (1970:63) ማንኛውም ሰው የተለያዩ ነገሮችን መረዳት የሚችለው ነገሮቹን በተለያየ መንገድ መመልከት ሲችል ነው ይላሉ:: G ebhard (1990) ይህን ሞዴል አስመልክተው ሲገልጹ እስካሁን ካየናቸው ሞዴሎች የበለጠና የተሻለ የሚሆነው ለተማሪ አስተማሪዎች በስልጠናው ላይ ሙሉ ነፃነት ስለሚሰጥ ነው በማለት ያስረዳሉ:: ይሁን እንጂ እሳቸው የሚመርጡት ሞዴሎችን በቅንጅትና በአንድነት መጠቀምን፣ የሱፐርቪዥኑን ስራ ከሱፐርቫይዘሩ ወደ ሌላ ማዞርን፣ ከሌሎች የሙያ መስኮች ልምድ ለመቅሰም መሞከርን ነው::

6. ራስ አገዝ ሱፐርቪዥን (**Self help-explorative supervison**):- ይህ የሱፐርቪዥን አቀራረብ ቀጣይነትና ቅንጅት ባለው መልኩ መከናወን ያለበት ሞዴል ነው:: የተማሪ አስተማሪዎች እንዴት ባለ ሁኔታ የማስተማር ስነ ዘዴያቸውን ሊያስተካክሉ እንደሚችሉ

ሊያመላክት የሚችል የአቀራረብ ዓይነት ነው፡፡ የዚህን ሞዴል የጥናት ትኩረት በአራት ነጥቦች አጠቃሎ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

እነሱም፡-1. ለምዘና ያገለገሉ ቅጾች

2. ምዘና ለማድረግ የተያዙ መረጃዎች

3. በምዘና ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

4. ለተማሪ አስተማሪዎች ምግበ መረጃ የሚሰጥባቸው መንገዶች ናቸው፡፡

ከላይ ለማየት ከሞከርናቸው የሦስት ምሁራን ሱፐርቫይዘራዊ አቀራረብ ሞዴሎች በተለየ መንገድ ጠበብ አድርገው የሱፐርቪዥን አቀራረብን በሁለት ዋና ዋና ምድቦች ለማስቀመጥ የሞከሩት Wallace (1991:110)ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለት የሱፐርቪዥን አቀራረቦች ትዕዛዛዊ እና ትብብራዊ አቀራረብ በመባል የሚታወቁ ሲሆኑ ዓለም (1988፣21) Wallace (1991:110)ን ጠቅሶ ልዩነታቸውን በቀላሉ ለመረዳት በሚያስችል መልኩ እንደሚከተለው አስቀምጧቸው እናገኛለን፡፡

## ሠንጠረዥ ሦስት

## ሱፐርቫይዘራዊ አቀራረቦች

| ትእዛዛዊ አቀራረብ (Classic Prescriptive approach) | ትብብራዊ አቀራረብ (Classic Collaborative approach) |
|---|---|
| 1. ሱፐርቫይዘር ፈላጭ ቆራጭና ወሳኝ ነው፡፡ | 1. ሱፐርቫይዘር እንደጓደኛና የሥራ ባልደረባ ነው፡፡ |
| 2. ሱፐርቫይዘር የዕውቀት ብቸኛ ምንጭ ነው፡፡ | 2. ሱፐርቫይዘር የተማሪ አስተማሪዎች ዕውቀትና ልምድ ተለዋዋጮች ናቸው፡፡ |
| 3. ሱፐርቫይዘር ፈራጅ ነው፡፡ | 3. ሱፐርቫይዘር ረዳት/አጋዥ ነው፡፡ |
| 4. ሱፐርቫይዘሩ የተማሪ አስተማሪዎች አንድ ወጥ በሆነ መንገድ ትምህርቱን ማቅረብ እንዳለባቸው ያሳያል | 4. ሱፐርቫይዘሩ የተማሪ አስተማሪዎች አንድ ወጥ በሆነ መንገድ ትምህርቱን እንዲያቀርቡ አያደርግም፡፡ የተማሪ አስተማሪዎች ያቀረቡበትን ዘዴ ይቀበላል፡፡ |
| 5. ሱፐርቫይዘሩ ተናጋሪ የተማሪ አስተማሪዎች አድማጮች ናቸው፡፡ | 5. ሱፐርቫይዘሩ ማዳመጥ የመናገርን ያህል አስፈላጊና ጠቃሚ እንደሆነ ይገነዘባል፡፡ |
| 6. ሱፐርቫይዘሩ የበላይነቱንና ሞዴልነቱን ጠብቆ ማቆየት ይፈልጋል፡፡ | 6. ሱፐርቫይዘሩ የተማሪ አስተማሪዎች ራሳቸውን በራሳቸው እንዲገማገሙና ያለፈ እንቅስቃሴያቸውን መለስ ብለው እንዲያጤኑ በማድረግ በራስ የመተማመን መንፈሳቸውን እንዲያጎለብቱ ያደርጋል፡፡ |

ከላይ ከቀረበው የWallace (1991:110) የሱፐርቪዥን አቀራረብ ለመገንዘብ እንደሚቻለው ትዕዛዛዊ አቀራረብ የሱፐርቫይዘሩን ፈላጭ ቆራጭነት የሚያጎላ፣ የእሱን ፍርድ ሰጭነት የሚያደፋፍር ሲሆን የተማሪ አስተማሪዎችን ስሜት በእጅጉ የሚጫን ነው። በትብብራዊ ሱፐርቫይዘራዊ አቀራረብ ግን የተማሪ አስተማሪዎች ከሱፐርቫይዘሩ ተጽእኖ ውጭ የሚንቀሳቀሱበት መንገድ ይመቻችላቸዋል። እንደ አማራጫዊና ኢትዕዛዛዊ አቀራረብ ሁሉ የሱፐርቫይዘሩ ተግባር የተማሪ አስተማሪዎችን መደገፍ፣ ማገዝ፣ ማበረታታትና መርዳት ነው። ሙሉ ኃላፊነቱን የሚወስዱት የተማሪ አስተማሪዎቹ ናቸው። ዓለም (1988፣22) እነ Gebhard (1990)፣ Zahorik (1988)፣ Wallace (1991)፣ Hoover (1988)፣ Kennedy (1993)ን በመጥቀስ እንደገለፀው የሱፐርቪዥን ሂደት ከትዕዛዛዊ አቀራረብ ተላቆ ወደ ትብብራዊ አቀራረብ መሸጋገር የወቅቱ የመምህራን አሰለጣጠን ንድፈ ሐሳብ የሚጠይቀው ነው።

በአጠቃላይ ሱፐርቪዥን በመምህራን አሰለጣጠን የሚኖረው ፋይዳ የጎላ በመሆኑ ከሱፐርቫይዘር ፈላጭ ቆራጭነት ተላቆ አማራጫዊ፣ ቅንጅታዊ፣ ትብብራዊና ፈጠራዊ አቀራረቦችን መሠረት አድርጎ መከናወን ይኖርበታል።

## 2.4.5 ምልከታ

### 2.4.5.1 ምልከታ ምንድነው?

ምልከታ ድርጊቶችን በመከታተል የማጤን ሂደት ነው። ምልከታ እያንዳንዱን እንቅስቃሴ ልቅም አድርጎ ማየትን ይጠይቃል። ከዚህ ባለፈ ቪዲዮ መመልከትን፣ ቴፕ ማዳመጥን፣ ትምህርታዊ ጽሁፎች ማንበብን ፣ አንድን ትምህርታዊ ገለፃ ማዳመጥን፣ ከተማሪዎች ወይም ከመምህራን ጋር መነጋገርን፣ የተማሪዎችን ማስታወሻ ማንበብን፣ በሬዲዮና በቴሌቪዥን የሚተላለፉ ዝግጅቶች መከታተልን ወዘተ. ሁሉ ምልከታ ልንላቸው እንችላለን። ምልከታውን ሊያከናውኑ የሚችሉት የድርጊቱ ተሳታፊዎች ወይም ገለልተኛ ወገኖች ሊሆኑ ይችላሉ። ከዚህ እንደምንረዳው ምልከታ ለብዙ ሰዎች የሚጠቅም፣ ብዙ መልክ ካለው አውድ ጋር የሚያስተዋውቅና የተለያየ ዕውቀትን የሚያስጨብጥ ሂደት እንደሆነ ነው (Woodward 1991: 203-204 Wajnryb 1992:1)።

አጠቃላይ ስለምልከታ ምንነት ይህን ያህል ካልን አሁን ደግሞ የመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር አንዱ ወደሆነው የክፍል ምልከታ እንሸጋገራለን።

### 2.4.5.2 የክፍል ምልከታ ለምን?

የክፍል ምልከታ ዕጩ መምህራን የቀሰሙትን መሠረታዊና ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀት ወደ ተግባር መለወጥ ይችላሉን? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ሱፐርቫይዘሮች የተማሪ አስተማሪዎች የማስተማር ልምምድ ወደሚያደርጉበት ክፍል በመዝለቅ የሚያደርጉት ክትትል ነው። የተሻለው

የማስተማር ዘዴ የትኛው ነው? የሚለው ጥያቄም መልስ የሚያገኘው የተማሪ አስተማሪዎቹ በማስተማር ልምምዳቸው ወቅት ትክክል መስራት አለመስራታቸው እየተገመገሙ ወደ ትክክለኛው የማስተማር ዘዴ እንዲመጡ የሚደረገው ልምምድ የሚያደርጉበት ክፍል በመገኘት በተከታተሏቸው ሱፐርቫይዘሮች አማካይነት ነው (William 1989:85) ::

የክፍል ምልከታ ሁልጊዜ በሱፐርቫይዘሮች ብቻ የሚከናወን እንዳልሆነ መገንዘብ ተገቢ ይሆናል:: ምክንያቱም ለፕራክቲከም ወይም ለማስተማር ልምምድ የሚመደቡ የተማሪ አስተማሪዎች በተመደቡበት ት/ቤትና በመማሪያ ክፍል ውስጥ ያለውን ትዕይንት ይመለከታሉ:: ምልከታቸውም በአካላዊና ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች፣ በተማሪና መምህር መካከል ባለው ግንኙነት፣ የተለየ ባህሪና አመለካከት በሚታይባቸው ተማሪዎች ላይ ያነጣጠረ ሊሆን ይችላል (Azeb 1971, Wragg 1974)::

የክፍል ምልከታ በተወሰኑ መሪ ነጥቦች ላይ ይመሠረታል:: በክፍል ምልከታ የመማሪያ ክፍሎችን፣ መምህራንን፣ ተማሪዎችን እና የትምህርት ይዘቶችን ለመቃኘትም ጥረት ይደረጋል:: በእያንዳንዱ መሪ ነጥብ ስር በርካታ ንዑሳን ክፍሎችን መንብኘትም ይቻላል:: ለምሳሌ የትምህርት ዕቅድ፣ የክፍል ቁጥጥር፣ የጥያቄና መልስ ስልት፣ የተማሪዎች እርስ በርሳዊ ግንኙነት ፣ በምልከታ ወቅት ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ንዑሳን ነጥቦች ናቸው (Calvert and Fletcher 1994)::

የክፍል ምልከታ ሁለት መልክ እንዳለው ከላይ ለማየት ሞክረናል:: በዕጩ መምህራን የሚደረግ የክፍል ምልከታና በአሰልጣኝ መምህራን ወይም በሱፐርቫይዘሮች የሚከናወን የክፍል ምልከታ ተብሎም ይለያል:: የክፍል ምልከታ በተለምዶ በት/ቤት አስተዳደሮችና ልምድ ባላቸው መምህራን አማካይነት በስራ ላይ ያሉ መምህራንን ለመገምገም ሲባል ይከናወን እንደነበር ይታወቃል:: ይሁን እንጂ የክፍል ምልከታ የሚደረግባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ:: የመጀመሪያ የክፍል ምልከታ ዓላማ የማስተማር ሙያን ለማሻሻል ወይም ለማሳደግ ማስቻል ነው:: ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሲታሰብ ምልከታው በስራ ላይ ባሉ ባለስልጣናት፣ ገና ወደ መምህርነት ሙያ ለመግባት በመሰልጠን ላይ ባሉ የተማሪ አስተማሪዎች እንዲሁም ሙያቸውን ለማሻሻል በሚፈልጉ መምህራን ሊከናወን ይችላል:: የተማሪ አስተማሪዎች በስልጠናቸው ሂደት ልምድ ያካበቱ መምህራንን፣ እንደሞዴል የሚመለከቱዋቸው አሰልጣኞችን፣ ለፕራክቲከም ወይም ለማስተማር ልምምድ የተመደቡባቸው ተባባሪ ት/ቤቶችን አስተዳደራዊና ትምህርታዊ እንቅስቃሴን፣ የክፍል ጓደኞቻቸውን ሲያስተምሩ ምልከታ በማድረግ በቂ ግንዛቤ ያገኛሉ:: በማሰልጠኛ ተቋማት አማካይነት የሚመደቡ ሱፐርቫይዘሮችም የተማሪ አስተማሪዎችን ለመርዳት ሲሉ ወደሚያስተምሩበት ክፍል ጎራ በማለት የማስተማር ልምምድ ሂደቱን ይመለከታሉ::

### 2.4.5.3 የክፍል ምልከታ እንዴት?

የሱፐርቫይዘሮች የክፍል ውስጥ ምልከታ ትኩረት በተማሪ አስተማሪዎች የክፍል ውስጥ ትምህርት የማቅረብ ችሎታ፣ ጥያቄ የመጠየቅና የመመለስ ችሎታ፣ የሚያስተምሩትን ትምህርት ጠንቅቀው የማወቅ ችሎታ፣ የክፍል ውስጥ መስተጋብርን የመቆጣጠር ችሎታ ወዘተ ላይ ሊያነጣጥር ቢችልም የግዴታ በአንድ ጊዜ ሁሉንም ላይመለከቱ ይችላሉ። አንዱን ወይም ሁለቱን ብቻ በመምረጥ ምልከታ ማድረግ ይችላሉና። ምልከታቸው በዘፈቀደ የሚካሄድ ሳይሆን ስርዓታዊ የምልከታ መሳሪያዎችን አዘጋጅተው ቢሆን ተመራጭነት አለው። የምልከታ መከታተያ መሳሪያዎችን በማዘጋጀት የሚደረግ ምልከታ ከምልከታ በኋላ ለሚደረገው ምግበ መረጃ ውይይት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ምክንያቱም ምግበ መረጃ ውይይቱ ከግምገማ ይልቅ በገለፃ፣ ከአጠቃላይ ይልቅ በዝርዝር፣ ስብዕናን ከመንካት ይልቅ ቀለል ባሉ ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩር ይረዳል። እንዲሁም ኃላፊነቱ የሁለቱም መሆኑን ለመቀበልም ያስችላቸዋል። ሱፐርቫይዘሮች የተለያየ አይነት የክፍል ምልከታ መከታተያ ቅጽ አዘጋጅተው መጠቀም የሚችሉ መሆኑ ቢታወቅም የምልከታ መከታተያ ቅጹን ከማዘጋጀታቸው በፊት የምልከታቸውን መጠነ ርዕይ መወሰንና መረጃውን ሊያሰባስቡ የሚችሉበትን መሳሪያ መምረጥ ይጠበቅባቸዋል (Wajnryb 1992:8)።

በመቀጠልም ብዙ የምልከታ መከታተያ ቅጾች ሊጋሩዋቸው የሚችሏቸውን አላባውያን መነሻ በማድረግ የየራሳቸውን የምልከታ መከታተያ ቅጽ ማዘጋጀት ይችላሉ። ብዙዎቹ የምልከታ ቅጾች የሚጋሩዋቸው አላባውያን የሚባሉት፡-

- የምልከታው ዓላማ ግልጽ ሆኖ መቀመጡ፣
- ተጠየቃዊ መዋቅርን የተከተለ መሆኑ፣
- የመማር/ማስተማር ስልቶችን ያገናዘበ መሆኑ፣
- ግላዊ የመግባባት ችሎታና በራስ የመተማመን ብቃትን የሚቃኝ መሆኑ፣
- በክፍል ውስጥ የትምህርት ይዘት አቀራረቡን የሚመለከት መሆኑና
- የተማሪ አስተማሪዎችና የተማሪዎችን ግንኙነት ለመፈተሽ የሚያስችሉ ናቸው።

የክፍል ውስጥ ምልከታ መከታተያ ቅጾች ከላይ የተመለከቱትን ነጥቦች ይጋሩ እንጂ የራሳቸው የሆነ ቅርጽ አላቸው። የሁሉንም የክፍል መከታተያ ቅጾች ናሙና እዚህ አምጥቶ ማሳየቱ ተገቢ ባለመሆኑ በተለይ በመምህራን ስልጠና የማስተማር ልምምድና ሱፐርቪዥን ወቅት አገልግሎት ላይ ሊውል የሚችል አንድ ናሙናዊ ቅጽ መመልከቱ አስፈላጊ ይሆናል። በአባሪነት የተያያዘው የክፍል ምልከታ መከታተያ ቅጽ ከድህረ ገጽ የተወሰደ ሲሆን ቋንቋን በማስተማር ልምምድ ወቅት ተግባራዊ የሚሆን ነው።

ይህን የክፍል ምልከታ በናሙናነት ለማሳየት ተሞከረ እንጂ በሱፐርቪዥን ወቅት ይህ ናሙና ብቻ አገልግሎት ላይ ሊውል ይገባዋል ማለት አይደለም::

ቀደም ሲል ሱፐርቫይዘሮች የክፍል ምልከታ የሚያደርጉት አስፈሪና አስደንጋጭ በሆነ መንገድ ነበር:: የተማሪ አስተማሪዎች በሚያስተምሩበት ክፍል የመጨረሻ ወንበር ተቀምጠው የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋሙ ባዘጋጀው የመገምገሚያ ቅጽ ላይ የትኛው ጥሩ የትኛው መጥፎ የማስተማር ስነ ዘዴ እንደሆነ የሚወስኑበት ሂደት ነበር:: የተማሪ አስተማሪዎች ዕድል በሱፐርቫይዘሩ የተያዘውን ሪፖርት ማንበብ እንጂ በግንባር ተገናኝተው በመወያየት ድክመትና ጥንካሬያቸውን መገንዘብ አይችሉም:: ይህ ደግሞ በሚቀጥለው ልምምድ ስህተታቸውን አርመው እንዳይገኙ ያደርጋቸዋል:: በተለይም ምልከታው የሚከናወነው በሙያው ባልሰለጠኑ ሰዎች የመሆኑ ጉዳይ አሉታዊ ተጽዕኖውን ያጎላዋል (ዓለም 1988:24):: እነዚህ ሰዎች በምዘናው ላይ የተማሪ አስተማሪዎች ምንም ዓይነት ኃላፊነት እንዲወስዱ እድሉን ካለመስጠታቸውም በላይ የራሳቸው የሆነ የምልከታ መሳሪያና መስፈርት ስለሌላቸው በስሜታዊነት ለመከታተል ይገደዳሉ:: በተቋሙ የመገምገሚያ ቅጽ አንድ ጉዳይ ላይ ብቻ ማነጣጠራቸውም ምልከታው ስለመበላሸቱ ጠቋሚ ነው (William 1989:85)::

እንደ Sheal (1989:92-103) አገላለጽ ጥንታዊው የክፍል ምልከታ በሰለጠኑ መምህራን መደረግ ሲገባው በት/ቤት አስተዳዳሪዎች ይደረግ ነበር:: በጥንታዊው የክፍል ምልከታ የብጤ ምልከታ ብሎ ነገር ካለመታወቁም በላይ ይደረግ የነበረው የክፍል ምልከታ ስርዓትን ያልተከተለና ስሜታዊነትም ጎልቶ ይታይበት ነበር:: አብዛኛውን ጊዜ ምልከታው ለመፍትሔ ፍለጋ የሚደረግ ሳይሆን የተማሪ አስተማሪዎችን ለመገምገም ሲባል የሚካሄድ ስለነበር የክፍል ውስጥ ጭንቀትን ሲፈጥር ነበር::

በአጠቃላይ ከምልከታ አስፈላጊው ጠቀሜታ እንዳይገኝ የሚያስተጓጉሉ ጉዳዮችን ዓለም (1988፣24) Sheall (1989)ን በመጥቀስ በአራት ከፍሎ ለመመልከት ሞክሯል::

እነሱም:– 1. የክፍል ምልከታው ለሙያው ባይተዋር በሆኑ ሰዎች መካሄዱ፣
2. የክፍል ምልከታው የሚካሄደው ግምገማን ዓላማ አድርጎ መሆኑ፣
3. የክፍል ምልከታው በዘፈቀደ የሚካሄድ መሆኑንና
4. ከምልከታው በኋላ የሚካሄደው ውይይት ይዘትና ባህሪ በተማሪ አስተማሪዎች ስብዕና ላይ ያተኮረ መሆኑ ናቸው::

Gaise and Bowers (1990:168) በግልጽ እንዳስቀመጡት በማስተማር ልምምድ ሱፐርቪዥን በሚከናወንበት ጊዜ ተግባር ላይ መዋል ያለበት የክፍል ምልከታ የራሱ የሆነ ደረጃ ያለው ሆኖ ከላይ የተጠቀሱትን እንቅፋቶች ሊያስወግድ የሚችል መሆን አለበት:: እንደነ Gaise (1990) አከፋፈል የክፍል ምልከታ ሶስት ደረጃዎችን ማለፍ ይጠበቅበታል:: እነሱም ቅድመ ምልከታ ውይይት (Pre-observation Consultation) ፣ ጊዜ ምልከታና (Observation) ድህረ ምልከታ

ውይይት (Post-observation) በመባል ይታወቃሉ። በቅድመ ምልከታ የተማሪ አስተማሪዎችና ሱፐርቫይዘራቸው ለፕራክቲከም ወይም ለማስተማር ልምምድ ወደ ተመደቡበት ተባባሪ ት/ቤት ከመሄዳቸው በፊት በሚማሩበት ተቋም ቅጥር ግቢ ተገናኝተው የምልከታቸውን አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማ በመነጋገር ግልጽ ያደርጋሉ። በዚህ ውይይት የተማሪ አስተማሪዎች በምን መስፈርት ሊገመገሙ እንደሚችሉ፣ መስፈርቶቹ ምን ምን እንደሆኑ ይገነዘባሉ። በጊዜ ምልከታ ወቅትም ሱፐርቫይዘሮች የተማሪ አስተማሪዎች የማስተማር ልምምድ በሚያደርጉበት ክፍል ውስጥ በመገኘት ምልከታ ያደርጋሉ። በመጨረሻም የድህረ ምልከታ ውይይት ይደረጋል። በድህረ ምልከታ ውይይት ሱፐርቫይዘሮችና የተማሪ አስተማሪዎች ፊት ለፊት ተገናኝተው ስለነበረው የማስተማር ልምምድ እንቅስቃሴ ሱፐርቫይዘሮች በመረጡት የምልከታ መከታተያ ቅጽ የያዙትን መረጃ መሠረት በማድረግ የምግበ መረጃ ልውውጥ ያደርጋሉ።

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ቀደም ባለው ጊዜ የነበረው የክፍል ምልከታ ትኩረት መፍትሔ ለመፈለግ የሚደረግ እንዳልነበረ እንረዳለን። የምግበ መረጃ ውይይቱም ቢሆን የዕጩ መምህራን ክሂልን ለማሳደግ በሚረዱ ነጥቦች ላይ ከመነጋገር ይልቅ በባህሪያቸው ላይ ያነጣጠረ ነበር።

አዲሱና ዘመናዊው የክፍል ምልከታ ግን ከዚህ በእጅጉ ይለያል። ምክንያቱም ምልከታው የተማሪ አስተማሪዎች በክፍል ውስጥ ምን ሲያከናውኑ እንደነበር ማስታወሻ ተይዞ እንዲያነቡት የሚደረግበት ሳይሆን ራሳቸው ሰልጣኞቹ ውሳኔ እንዲሰጡበት የሚያበረታታ ነው።። በአንድ መገምገሚያ ነጥብ ላይ ያላተኮረና በተማሪ አስተማሪዎች ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ነው። ከሱፐርቫይዘሮች ይልቅ የተማሪ አስተማሪዎች ኃላፊነትን የሚወስዱበትና ለውይይት ራሳቸውን የሚያዘጋጁበት መንገድ ሆኗል። የክፍል ውስጥ የማስተማር ልምምድ ትኩረታቸው ኮርሱን ሲወስዱ ከተነሱ ነጥቦች ጋር የተገናዘበ እንዲሆን ይረዳቸዋል። እራሳቸውን በራሳቸው ለማሻሻል እንዲችሉ ዕድል ይሰጣቸዋል። ስለዚህ ምልከታው ጠቃሚና የሚያበረታታ፣ ስሜታቸውን የማይጎዳ፣ አዎንታዊ በሆኑ እንቅስቃሴዎች ላይ ብቻ ተመስርቶ ይበልጥ የሚሻሻሉበትን መንገድ ማመላከት የሚችልበት ደረጃ ላይ መድረስ ይጠበቅበታል።

በክፍል ውስጥ የሚደረገውን የመማር ማስተማር ሂደት መመልከት ለተማሪ አስተማሪዎች ሙያ መሻሻል እንደ ጥሩ ዕቃ ሊቆጠር ስለሚችል ምልከታው የተሳካ ይሆን ዘንድ አሰልጣኝ መምህራንም ሆኑ ሱፐርቫይዘሮች ልብ ሊሏቸው የሚገቡ የምልከታ ቁልፍ ነገሮች አሉ (Wajnryb 1992:21)። እነሱም:-

1. የተማሪ አስተማሪዎች ራሳቸውን ከክፍሉ ጋር የሚያስማሙበት ጊዜ መፈለጋቸውን መረዳት፣
2. ስልጠና የህይወት መጨረሻ ሳይሆን ጥሩ መምህራንን ለመፍጠር የሚያስችል መንገድ መሆኑን በመረዳት የተማሪ አስተማሪዎችን ማበረታታት፣

3. ከክፍል ምልከታ በኋላ አሰልጣኞች ፣ ሱፐርቫይዘሮችና ነባር መምህራን ለተማሪ አስተማሪዎች ልምዳቸውን ማካፈል፣
4. የክፍል ምልከታው ከሌሎች መማሪያ መንገዶች ጋር እንዲዛመድ ማድረግ ወዘተ. ናቸው፡፡

ምልከታ ለመፈተን ሳይሆን ችግርን በጋራ የመፍታት ልምድን ለማግኘት የሚያገለግል መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ የመጀመሪያው የተማሪ አስተማሪዎች የክፍል ምልከታ ኮርሱ መስጠት በጀመረበት ወቅት ቢካሄድ መልካም ነው፡፡ ምክንያቱም የመጀመሪያው ጉብኝት በተከታዩ ምልከታ ምን ሊሆን ወይም ምን ሊከናወን እንደሚችል ሊያመላክት ከመቻሉም በላይ ቀጥሎ የተመለቱት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል (William 1989)፡፡

1. የምልከታውን አዎንታዊ ጎንና ጠቀሜታ ያስገነዝባል፡፡
2. ወደፊት በክፍል ውስጥ ምን ሊከናወን እንደሚገባ ይጠቁማል፡፡
3. የተማሪ አስተማሪዎች በመጠኑም ቢሆን ብዙ ነገሮችን እንዲሞክሩ ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡
4. ለተማሪ አስተማሪዎች በክፍል ውስጥ ምን እየተከናወነ እንደሆነ በመመልከት ከተማሪዎች ጋር እንዴት ባለ መንገድ መግባባት እንደሚችሉ፣ ተማሪዎች ምን መስራት እንዳለባቸው፣ የክፍል ውስጥ የቋንቋ አጠቃቀም ስልት ምን እንደሚመስል ያስገነዝባል፡፡
5. በክፍል ውስጥ የቀሰሙትን ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀት በእውናዊው የማስተማሪያ ክፍል ውስጥ ወደ ተግባር የመለወጥ ሙከራ እንዲያደርጉ ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡

በክፍል ምልከታ ወቅት የተማሪ አስተማሪዎች ሊያከናውኑ የሚገባቸው ተግባር እንዳለ ሁሉ ሱፐርቫይዘሮች/አሰልጣኝ መምህራንም ቀጥሎ የተመለከቱትን ተግባራት ማከናወን እንዳለባቸው (William 1989) ይገልፃሉ፡፡

- ከተማሪ አስተማሪዎች ጋር በመመካከር ኮርሱን ሲወስዱ የነበራቸውን ጥንካሬ፣ ድክመት፣ ፍላጎትና የመማር ስልት በማስታወስ እውን ሊያደርጉዋቸው የሚችሉ ተግባራትን እንዲመርጡ ማድረግ፣
- የተማሪ አስተማሪዎቹ ቅድመ ምልከታ ላይ ያላቸው ቁርጠኝነትና ተነሳሽነት ለማስተማር ልምምዳቸው መሳካት ወሳኝ መሆኑን መግለጽ፣
- ወደ ማስተማር ልምምዱ ሲገቡና ሲወጡ እንዳይሳቀቁ ማረጋጋት፣ ምክንያቱም የሱፐርቫይዘሩ በክፍል ውስጥ መገኘት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ልንገመገም ነው የሚል ስሜት ስለሚያድርባቸው ጫና ሊፈጥርባቸው ይችላል፡፡
- ድህረ የማስተማር ልምምድ በሚደረግ ውይይት የማጠናከሪያ ሐሳብና ስለ ክፍል ውስጥ ውሳኔ አሰጣጥ በቂ መረጃ መስጠት የመሳሰሉትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡

### 2.4.5.4 ድህረ ምልከታ የምግበ መረጃ አቀራረብ

በክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ በራሱ ምንም አይፈይድም:: ድህረ ምልከታ በሚደረግ ውይይት ላይ ትኩረት ተሰጥቶበት የተማሪ አስተማሪዎቹ ከመረጃዎቹ ተጠቃሚ ለመሆን እንዲችሉ መደረግ ይኖርበታል:: ከማስተማር ልምምድ በኋላ የሚካሄደው ውይይት የመምህራን ስልጠና ዝግጅት አንዱ ክፍል ነው:: ይህ ድህረ ማስተማር የሚካሄድ ውይይት በሴሚናር፣ በሱፐርቫይዘራዊ ጉባኤ ወይም በተማሪ አስተማሪዎችና አሰልጣኞች ወይም ሱፐርቫይዘሮች መካከል በሚደረገው የማስታወሻ ልውውጥ አማካይነት ሊካሄድ ይችላል (ዓለም 1988:26):: የምግበ መረጃ ልውውጡ በአግባቡ ካልተካሄደና የማስተማር ልምምዱን ማገዝ ካልቻለ በመምህራን አሰለጣጠኑ ሂደት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ማድረጉ አይቀርም:: ስለዚህ ምግበ መረጃ ልውውጡ በምን በምን ነጥቦች ላይ ሊያተኩር እንደሚገባውና በምን ዓይነት መንገድ መቅረብ እንዳለበት በመገንዘብ ሊደርስ የሚችለውን አሉታዊ ተጽእኖ ማቃለል ይቻላል::

ዓለም (1988:27-31) የምግበ መረጃ አቀራረብ ስልትንና የትኩረት አቅጣጫ የተለያዩ የመስኩ ምሁራንን በመጥቀስ እንደሚከተለው ለማሳየት ሞክሯል::

1. የምግበ መረጃ ልውውጥ በባህሪ ላይ እንጂ በስብዕና ላይ ማተኮር የለበትም:: በስብዕና ላይ የሚያተኩር ከሆነ የምግበ መረጃ ተቀባዩን ሊያስቆጣና ሊያበሳጭ ይችላል::
2. ምግበ መረጃ በምልከታ ወቅት በተመለከትነውና በማስታወሻ በያዝነው ነገር ላይ እንጂ በእኛ ስሜት በተገነዘብነው ነገር ላይ መመስረት አይኖርበትም::
3. ምግበ መረጃ ተጨባጭ ሁኔታን በማብራራትና በመተንተን ላይ ያተኩራል እንጂ በግላዊ ፍርድ ወይም ዳኝነት ላይ መመስረት የለበትም::
4. ምግበ መረጃ በሐሳብ ወይም በመረጃ ልውውጥ ላይ ሊያተኩር ይገባል እንጂ በምክር ልገሳና በማሳመን ላይ ሊመሰረት አይገባውም:: ይልቅስ ብዙ አማራጮችን በማቅረብ ምግበ መረጃ ተቀባዩ የሚመስለውንና የሚያምንበትን መንገድ መርጦ እንዲከተል ቢደረግ ተመራጭነት ይኖረዋል::
5. በምግበ መረጃ ወቅት በሚካሄደው ውይይት የሚታየው የቋንቋ አጠቃቀም ፀፀትንና ቁጭትን ከሚገልፁ ቃላትና ሐረጋት የፀዳ መሆን ይኖርበታል:: ለምን ይህን ሳታደርግ ቀረህ፣ እኔ አንተን ብሆን ኖሮ . . . ፣ ልታደርግ ይገባህ ነበር፣ ወዘተ. ከሱፐርቫይዘሮች የሚደመጡና ማድረግ ይገባኝ ነበር፣ ማድረግ አልነበረብኝም ወዘተ. ከተማሪ አስተማሪዎች በኩል የሚሰነዘሩ ሐሳቦች ከባድ የሆነ ስሜታዊ ተጽእኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ የቋንቋ አጠቃቀሞች ናቸው:: ይህ ደግሞ በተማሪ አስተማሪዎች ላይ ግራ መጋባትንና ያለመረጋጋት ስሜትን የመፍጠር አቅም ስላለው በማስተማር ልምምድ ሙያቸውን ለማሻሻል ከመጣር ይልቅ ሲሸማቀቁ ይታያሉ::

6. የምግበ መረጃ ልውውጥ አጠቃላይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ባያተኩር ይመረጣል:: ምክንያቱም አጠቃላይነት ባለው ምግበ መረጃ ተፈላጊውን መልዕክት ወደሚፈለገው ወገን ማስተላለፍ አይቻልም::

7. የሚቀርበው መረጃ ትክክለኛነት በምግበ መረጃ አቅራቢውም ሆነ በተቀባዩ ሊረጋገጥ የሚችል መሆን ይጠበቅበታል:: አንዱ ትክክለኛ ነው ሌላው ደግሞ አይደለም ቢል እንኳን በጋራ ትክክለኛነቱን የሚያረጋግጡበትን መንገድ ሊፈልጉ ይገባል::

8. በምግበ መረጃ ልውውጥ ሱፐርቫይዘሮች የተማሪ አስተማሪዎችን እንዳይጫኑ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል::

ከላይ በዝርዝር የተመለከቱትን ነጥቦች መሠረት አድርጎ የሚከናወን የምግበ መረጃ ልውውጥ ውጤቱ አመርቂ ሊሆን እንደሚችል ጥርጥር የለውም::

## 2.5 በመምህራን ስልጠና የማሰልጠኛ ተቋማት፣ የሱፐርቫይዘሮች፣ የተባባሪ ት/ቤቶች፣ የነባር መምህራንና የተማሪ አስተማሪዎች ተግባርና ኃላፊነት

### 2.5.1 የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

በመምህራን አሰለጣጠን ሂደት ማሰልጠኛ ተቋማት ከፍተኛውን ድርሻ እንደሚይዙ ይታወቃል:: በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ጎጂ ልማዶችን በማስወገድና አዳዲስ ሐሳቦችን በማስፋፋት ጉልህ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ መምህራንን ለማፍራት የመምህራን ስልጠና መርሀ ግብርን ቀርጸው ስልጠናው በአግባቡ እንዲካሄድ የሚያደርጉት እነዚሁ ማሰልጠኛ ተቋማት ናቸው:: መምህራንን በማሰልጠኑ ሂደት ተቋማቱ ንድፈ ሐሳብንና ተግባርን በማጣመር ሊተገብሩ የሚችሉ መምህራንን ለማፍራት ደግሞ ከተባባሪ ት/ቤቶች ጋር መተባበር እንዳለባቸው ይታመናል::

እንደ Forlung (1996) ገለፃ ከሆነ የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት፣ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ለመምህራን ስልጠና ልዩ ትኩረት በመስጠት ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀትን ከማስጨበጥ አንስተው እስከ ማስተማር ልምምዱ ፍፃሜ ድረስ ብርቱ ክትትል ሊያደርጉ ይገባቸዋል::

MOE (2003:46) የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማትን ተግባርና ኃላፊነት እንደሚከተለው አስፍሮት እናገኘዋለን::

- የተማሪ አስተማሪዎች ለስልጠናው የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ያሟላሉ
- የተባባሪ ት/ቤቶች መምህራንና ሰራተኞች የመምህራን ስልጠናው ቀጥተኛ ተሳታፊ የሚሆኑበትን መንገድ ያመቻቻሉ::
- የተማሪ አስተማሪዎችና ተባባሪ ት/ቤት ሰራተኞች የፕራክቲከሙን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያዳብሩ ያደርጋሉ::

- ፕራክቲከሙ ከመጀመሩ በፊት ከተባባሪ ት/ቤቶች ጋር ተገናኝተው በመወያየት ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፡፡
- ተባባሪ ት/ቤቶችንና ለማስተማር ልምምድ የሚያገለግሉ ክፍሎችን መስፈርት አወጥተው ይመርጣሉ፡፡
- ለተማሪ አስተማሪዎች የተመደቡባቸውን ት/ቤቶች በማስተዋወቅ እንዲጎበኙ ያደርጋሉ፡፡
- የክፍል ምልከታ መመዝገቢያ ቅጽና የመጨረሻ ምዘና መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ይቀርፃሉ፣ ያዘጋጃሉ፡፡
- የተባባሪ ት/ቤት ሰራተኞችን ማስልጠን ቢያስፈልግ በቂ ልምድ የሚቀስሙበት ክፍለ ጊዜ ይመድባሉ፡፡
- የተማሪ አስተማሪዎች ወደ ተባባሪ ት/ቤቶች የሚመላለሱበትን መጓጓዣ ያዘጋጃሉ፡፡
- የተማሪ አስተማሪዎቹ የሚገመገሙበትንና የሚመዘኑበትን መስፈርት ያዘጋጃሉ፡፡
- ተባባሪ ት/ቤቶች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ይቆጣጠራሉ፡፡
- እያንዳንዱን የተማሪ አስተማሪ የሚረዳና የሚመራ የትምህርት ባለሙያ ወይም ሱፐርቫይዘር ይመድባሉ፡፡
- ለፕራክቲከሙ/ለማስተማር ልምምዱ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ያሟላሉ፡፡
- በማንኛውም ቦታ ስልጠናውን በተመለከተ ከተባባሪ ት/ቤቶች ጋር ተገናኝተው ለመወያየት ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፡፡

ይህ የሚያመለክተው በመምህራን ስልጠና ፕራክቲከምንና የማስተማር ልምምድን በተመለከተ በአግባቡ የመከታተል ኃላፊነት ለማስልጠኛ ተቋማት መስጠቱን ነው፡፡

### 2.5.2 የሱፐርቫይዘሮች ተግባርና ኃላፊነት

ሱፐርቫዘሮች በመምህራን ማስልጠኛ ተቋማት አማካይነት ፕራክቲከምን ወይም የማስተማር ልምምድን ሱፐርቫይዝ እንዲያደርጉ የሚመደቡ የትምህርት ባለሙያዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ባለሙያዎች ከተባባሪ ት/ቤቶች ጋር የጠበቀ ግንኙነት ሊኖራቸው ግድ ነው፡፡ ምክንያቱም በተቋማቱና በተባባሪ ት/ቤቶች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያጠናክሩት እነሱ ናቸው ፡፡

### 2.5.3 የተባባሪ ት/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት

ቀደም ሲል በየትኛውም ሀገር ጀማሪ መምህራንን የማስልጠኑ ኃላፊነት ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ለመምህራን ማስልጠኛዎች ብቻ ተትቶ እንደነበር ይታወሳል፡፡ የኋላ ኋላ ግን ት/ቤቶችም የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ እንዳለባቸው እየታመነበት መጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ መምህራንን በማስልጠኑ ሂደት በተባባሪ ት/ቤቶች ዙሪያ የሚከተሉት ጥያቄዎች መነሳታቸው አልቀረም (McIntyre and te al 1994:13-14)፡፡ ከጥያቄዎቹ መካከል:-

- ተባባሪ ት/ቤቶች አዳዲስ መምህራንን ለማሰልጠን የሚደረገውን እንቅስቃሴ ከግብ ለማድረስ ሙሉ ፈቃደኛና ምቹ ናቸውን?
- ተባባሪ ት/ቤቶች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችል አቅም አላቸውን?
- በማሰልጠኛ ተቋማት የሚመደበው ክፍል ጊዜ፣ የክፍል ደረጃ፣ የትምህርት ዓይነት የተማሪ አስተማሪዎቹ በቂ ዕውቀትና ልምድ ለመቅሰም ያስችላቸዋልን?
- ተባባሪ ት/ቤቶች እያንዳንዱን የተማሪ አስተማሪ ለመርዳት አቅም አላቸውን? የሚሉት ይገኙባቸዋል።

ተባባሪ ት/ቤቶች የመምህራን ስልጠና የተሳካ እንዲሆን ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚችሉት ደግሞ ብቻቸውን በመንቀሳቀስ ሳይሆን ከማሰልጠኛ ተቋማት ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር በቅንጅት ሲሰሩ ብቻ ነው። ተቋማቱ የተባባሪ ት/ቤቶችን አቅም በማገናዘብ የተማሪ አስተማሪዎችን ቁጥር መጥነው፣ስንት ያህል ጊዜ በት/ቤቶቹ ሊቆዩ እንደሚችሉ ወስነው፣ የፕራክቲከምና የማስተማር ልምምድ ፕሮግራም አውጥተው ለት/ቤቶቹ ይልካሉ። ት/ቤቶቹም የተላኩላቸውን የተማሪ አስተማሪዎች ተቀብለው ከመምህራን ማረፊያ ክፍል በመጀመር ከት/ቤቶች አስተዳደራዊ መዋቅር፣ ከትምህርት ክፍል ስብሰባዎች፣ የመማር ማስተማሩ ከሚታገዝበት መንገድ፣ ከአጠቃላይ የመምህራን ስብሰባዎች፣ ከተለያዩ የሥራ ክፍሎች ከተጓዳኝ ክበባት እንቅስቃሴና ከመምህራን ጋር እንዲተዋወቁ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ይኖርባቸዋል (McIntyre and et al 1994:14)።

## 2.5.4 የነባር መምህራን ተግባርና ኃላፊነት

በመምህራን ስልጠና ሂደት ሰልጣኞች ትምህርት የሚቀስሙት ከአሰልጣኝ መምህራን፣ ከሱፐርቫይዘሮችና ከክፍል ጓደኞቻቸው ብቻ ሳይሆን ከተባባሪ ት/ቤት ነባር መምህራንም ነው። ነባር መምህራን በተለይም ለፕራክቲከም መሳካት ቁልፍ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። የተማሪ አስተማሪዎች ለፕራክቲከምና ለማስተማር ልምምድ ወደ ት/ቤታቸው ተመድበው የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በማገዝ ላቅ ያለ ሚና አላቸው። በተለይም የተማሪ አስተማሪዎቹ በራስ የመተማመን ብቃታቸውን ለማዳበር የሚያደርጉትን ጥረት በእጅጉ ያግዛሉ።

Pelletier (2000) የነባር መምህራንን ኃላፊነትና ተግባር እንደሚከተለው በአስር ነጥብ ጠቅለል አድርገው ያስቀምጡታል። ነባር መምህራን፡-

1. ለተማሪ አስተማሪዎች ት/ቤታቸውን ያስተዋውቃሉ።
2. የተማሪ አስተማሪዎች ዕቅድ በሚያዘጋጁበት ጊዜ ይረዷቸዋል።
3. ከጥሩ የማስተማር ዘዴ ሞዴሎች ጋር ያስተዋውቋቸዋል።
4. አዳዲስ የማስተማር ዘዴዎችን ተጠቅመው እንዲያስተምሩ ያበረታቱዋቸዋል።
5. ገንቢ የሆነ መረጃ ይሰጡዋቸዋል።

6. አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ያደርጉላቸዋል፡፡
7. ሱፐርቫይዘሮች በተገኙበት ውይይት እንዲካሄድ ያደርጋሉ፡፡
8. ስለ ተማሪ አስተማሪዎች አጠቃላይ ሁኔታ ለሱፐርቫይዘሮች ሪፖርት ያደርጋሉ፡፡
9. በተማሪ አስተማሪዎች የግምገማ ውጤት ዙሪያ ከሱፐርቫይዘሮች ጋር ይወያያሉ፡፡
10. በተማሪዎች የመገምገሚያ ቅጽ ላይ ይፈርማሉ፡፡

Richards (1987:221-222) በበኩላቸው የተማሪ አስተማሪዎች በፕራክቲከምና የማስተማር ልምምድ ወቅት በማሰልጠኛ ተቋማት፣ በተባባሪ ት/ቤቶችና በነባር መምህራን መረዳትና መገምገም እንዳለባቸው በመግለጽ የነባር መምህራንን ተግባርና ኃላፊነትን እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ፡፡

1. ሰዓታቸውን በአግባቡ በመጠቀም ምልከታ እንዲያደርጉ ይመክራሉ፡፡
2. የተማሪ አስተማሪዎችን ይቆጣጠራሉ፣ ይገመግማሉ፣ ተግባራዊ እርዳታ ያደርጋሉ፣
3. የተማሪዎችን የፕራክቲከም አፈፃፀም ይገመግማሉ፡፡
4. በክፍል ውስጥ የሚደረገውን የማስተማር ልምምድ በቀና መንፈስ ያግዛሉ፡፡
5. የክፍሉን ሁኔታ በማረጋጋት የተማሪ አስተማሪዎች የክፍሉን ስርዓት የማስከበር አቅማቸውን እንዲያጎለብቱና ችግሮችን በራሳቸው ለመፍታት እንዲችሉ ያበረታታሉ፡፡
6. ከፕራክቲከሙና ከማስተማር ልምምዱ በቂ ልምድ እንዲቀስሙ ለመርዳት ሱፐርቫይዝ ያደርጋሉ፡፡
7. በየዕለቱ የሚመለከቱትን ደካማና ጠንካራ ጎን በቃል ወይም በጽሁፍ ለተማሪ አስተማሪዎቹ ይገልፃሉ፡፡
8. የተማሪ አስተማሪዎች የመረጡትን የትምህርት ይዘት ጥሩ አድርገው ማቅረብ እንዲችሉ ያበረታቱዋቸዋል፣ የትምህርት ዕቅድ በማዘጋጀት ይረዱዋቸዋል፡፡ በቡድን እንዲሰሩ ያበረታቱዋቸዋል፡፡

MOE (2003:21-22) በበኩሉ ነባር መምህራን ለፕራክቲከም መሳካት ዋነኛና ቁልፍ ሰዎች ናቸው በማለት ይገልፃቸዋል፡፡ ምክንያቱም የተማሪ አስተማሪዎችን ቀን በቀን መርዳት በሚያመቻቸው ቦታ ላይ ያሉ በመሆናቸው እንዴት መዘጋጀት እንዳለባቸውና የክፍል ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባቸው ማማከር ይችላሉ፡፡ በየቀኑም ምግበ መረጃ ለመስጠት አይቸገሩም፡፡ በክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን ዕውቀትና የመረዳት አቅም በሚገባ ስለሚያውቁ የተማሪ አስተማሪዎች ተገቢውን ዝግጅት አድርገው በመምጣት የሕፃናቱን የመማር ስልት በመመልከት መገምገም የሚችሉበትን መንገድ ያመቻቻሉ፡፡ በአጠቃላይ ነባር መምህራን የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች አሏቸው፡፡

- የተማሪ አስተማሪዎች በት/ቤት ቅጥር ግቢና በክፍል ውስጥ ምልከታ የሚያደርጉበትንና የሚገመግሙበትን አጋጣሚ ያመቻቻሉ፣ ይረዳሉ፣ በማስተማር ሙያ ዙሪያ ያወያያሉ፡፡

- ለተማሪ አስተማሪዎች ተገቢውን ምክርና እርዳታ ያደርጋሉ፣ ከተመደበው ሱፐርቫይዘር ጋር በመመካከር ፕራክቲከሙን በመቆጣጠር፣ የፕራክቲከም ፋይሎችን በመመርመር ልምምዱ የሚሻሻልበትን መንገድ ሊጠቁም የሚችል የምልከታ ሪፖርት በመፃፍ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።
- ከሱፐርቫይዘሩ ጋር በመሆን የተማሪ አስተማሪዎችን የመጨረሻ የመገምገሚያ ቅጽ ይሞላሉ።
- መምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ፕሪክቲከምን በተመለከተ በሚያዘጋጁዋቸው ስብሰባዎች ላይ እንዲገኙ ሲጋበዙ ይገኛሉ (MOE 2003:22)።

በአጠቃላይ ለፕራክቲከምና ለማስተማር ልምምድ መሳካት ነባር መምህራን የሚጫወቱት ሚና ላቅ ያለ መሆኑን በመረዳት የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት ይችሉ ዘንድ ኮሌጆች አስፈላጊውን ግንዛቤ ሊያስጨብጧቸው ይገባል።

### 2.5.5 የተማሪ አስተማሪዎች ተግባርና ኃላፊነት

በመምህራን ስልጠና የተማሪ አስተማሪዎች የራሳቸው የሆነ ተግባርና ኃላፊነት እንዳላቸው McIntyre and et al (1994:31) ይገልፃሉ። በተለይም ከተባባሪ ት/ቤት ማህበረሰብ (ነባር መምህራንና ተማሪዎች፣ የት/ቤት ኃላፊዎች)፣ ከወላጆች፣ ከሱፐርቫይዘሮችና ሌሎች መንግስታዊ አካላት ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር ብዙ ዕውቀትና ልምድ መቅሰም ይኖርባቸዋል። ይህ ደግሞ ኃላፊነታቸውን በሚገባ ለመወጣት እንዲችሉ ትልቅ እገዛ ያደርጋል።

የማስተማር ልምምድን ከግብ ለማድረስ በሚደረግ ጥረት ንዑስ ማስተማር የሚጫወተው ሚና ላቅ ያለ ነው (Stones and Morris 1972:79)። በንዑስ ማስተማር የተማሪ አስተማሪዎች አንድን አጭር የትምህርት ይዘት ለጥቂት ተማሪዎች እንዲያስተምሩ ይደረጋል። ከዚያም ያስተማሩዋቸውን ተማሪዎች ከክፍል በማስወጣት ከሱፐርቫይዘራቸው ጋር የማስተማር እንቅስቃሴያቸው ምን ይመስል እንደነበር ይወያያሉ። ከጥቂት እረፍት በኋላ የተሰጣቸውን ምግበ መረጃ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ያንኑ ይዘት ለሌሎች ተማሪዎች ያስተምራሉ። በዚህን ጊዜ ከመምህርነት ሞያ ጋር ይተዋወቃሉ። በቀጣይነት በመደበኛው ክፍል ገብተው ለማስተማር የሚችሉ መሆናቸውንም ይረዳሉ።

በአጠቃላይ የተማሪ አስተማሪዎች በመምህራን ስልጠና ሂደት ከንዑስ ማስተማር ልምምዱ በተጨማሪ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናሉ (MOE 2003:47)።

1. ለማስተማር ልምምድ አስፈላጊውን የትምህርት ይዘት ያዘጋጃሉ፣ በቡድን ይሰራሉ።
1. ገንቢ አስተያየቶችንና ምጋቤ ምላሾችን በመውሰድ ቀጣይ የማስተማር ልምምዳቸውን ለማሻሻል ይጥራሉ።
2. በተባባሪ ት/ቤቶች የሚከናወነውን የመማር ማስተማር እንቅስቃሴ በሚገባ ይከታተላሉ።

3. ሙሉ በሙሉ በተባባሪ ት/ቤቶች እንቅስቃሴ ውስጥ ይሳተፋሉ።
4. ከት/ቤቶቹ የቀሰሙትን ልምድ ለሱፐርቫይዘራቸው እና ለክፍል ኃደኛቸው ያንፀባርቃሉ።
6. በተመደቡበት ት/ቤት በመገኘት ንቁ ምልከታ በማድረግ የመማር ማስተማሩን እንቅስቃሴ፣ የት/ቤቱን አጠቃላይ ሁኔታ፣ አደረጃጀት፣ የክፍል አወድ፣ የመሳሪያዎች መሟላት አለመሟላት፣ ችግርን የመፍታት ብልሃት ወዘተ. የሚመለከት የጽሁፍ ሪፖርት ያቀርባሉ።

## 2.6 በማስተማር ልምምድና በሱፐርቪዥን ላይ የተካሄዱ ቀደምት ሀገራዊ ጥናቶች ቅኝት

በመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት የሚካሄድ የማስተማር ልምምድና ሱፐርቪዥን አተገባበርን በሚመለከት እስከአሁን የተካሄዱ ጥናቶች ጥቂት የሚባሉ አይደሉም። ይሁን እንጂ በመምህራን አሰለጣጠን ሂደት ከፍተኛ ድርሻ አላቸው በሚባሉት የማስተማር ልምምድና ሱፐርቪዥን ላይ ካተኮሩ በርካታ ጥናታዊ ፅሁፎች መካከል የተቃኙት ጥቆቶቹ ናቸው። ጥናቶቹ የተከናወኑት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሰልጣኝ መምህራን ላይ ነው። ከዚህ ቀጥሎ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተሰሩትን ጥናቶች በማስቀደም በአጭር በአጭሩ ለመዳሰስ እንሞክራለን።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማስተማር ልምምድ ላይ ተመስርተው ከተከናወኑ ጥናቶች መካከል የGebremedhin (2001) "Aspects of teacher development for English language teaching" በሚል ርዕስ የሰራው ሥራ አንዱ ነው። Gebremedhin በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል የሚካሄደውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህር አሰለጣጠን ሂደትና አተገባበርን ለመቃኘት ሞክሯል።

Gebremedhin የመምህራን ስልጠናውንና የማስተማር ልምምዱን ለመፈተሽ አስራ አምስት የሚሆኑ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ድህረ ምረቃ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚያቀርቡትን ገለፃና የተለያዩ ተዛማጅ ፅሁፎችን የተጠቀመ መሆኑን ገልጿል። የተማሪ አስተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ የሚያደርጉትን የማስተማር ልምምድ ለአንድ ወር በመከታተል መረጃ ማሰባሰቡን ጠቁሟል። በጥናቱ ማጠቃለያም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚካሄደው የመምህራን አሰለጣጠን ጥቂት ጠንካራ ጎኖች ቢኖሩትም በርካታ ችግሮች ያሉበት እንደሆነ ለማረጋገጥ በቅቷል። ብዙዎቹ የተማሪ አስተማሪዎች ለንዑስ ማስተማርም ሆነ ለማስተማር ልምምድ ያላቸው ተነሳሽነት በጣም ዝቅተኛ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ ስለማስተማር ምንም ዓይነት ግንዛቤ እንደሌላቸውና የማስተማር ልምምድ እንደመመረቂያ መስፈርት አድርገው እንደሚቆጥሩት ለማወቅ ችሏል። Gebremedhin ከዚሁ ጋር በማያያዝ ሰልጣኞች ከሁለቱ ልምምዶች ንዑስ ማስተማርና የማስተማር ልምምድ ጋር ይበልጥ እንዲተዋወቁ ማድረግ የሚቻልበት ሁኔታ እንደገና ተፈትሾ ለልምምድ የተመደበው ክፍለ ጊዜ ተራዝሞ ተገቢውን ክትትል ማድረግ ቢቻል

የሚል የመፍትሄ ሐሳብ አቅርቧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም መምህራንን በማሰልጠን ሂደት ነባ የሆኑ ተባባሪ ት/ቤቶች የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ቢደረግ ጥሩ እንደሆነ በመግለፅ ጥናቱን አጠናቋል፡፡

ሌላው የመምህራንን አሰለጣጠን በሚመለከት የተሰራው ጥናት የAlemayehu (1998) ነው፡፡ "Teacher Education trends in some countries: Implications for the Ethiopian context" በሚል ርዕስ በሌሎች ሀገሮች ያለውን የመምህራን ስልጠና ሁኔታ ከአገራችን ጋር በማነፃፀር ለማሳየት ሞክሯል፡፡ በመምህራን ሥልጠና የማስተማር ልምምድ በሦስት መንገድ ሊከናወን እንደሚችል አመልክቷል፡፡ የመጀመሪያው ምልከታና የማስተማር ልምምድን ከኮርሱ ጋር ለወራት ወይም ለአንድ አመት ማከናወን የሚቻልበት መንገድ ነው፡፡ ሁለተኛው በማስተማር ልምምዱ ላይ ብቻ የማተኮር ስልት ነው፡፡ የማስተማር ልምምዱም ከሁለት እስከ አምስት ሳምንታት ሊዘልቅ ይችላል፡፡ ሦስተኛው ደግሞ የማስተማር ልምምዱ ዓመቱን ሙሉ የሚዘልቅ ይሆናል፡፡

Alemayehu ለማመልከት እንደሞከረው በሀገራችን ለማስተማር ልምምድ የተመደበው ጊዜ ከሌሎች ሀገሮች ጋር ሲነፃፀር በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ስለዚህ የማስተማር ልምምድ ዕጩ መምህራን በራስ የመተማመን መንፈሳቸውን በማጎልበት የቀሰሙትን እውቀት ለተማሪዎች ማስተላለፍ መቻል አለመቻላቸውን የሚያረጋግጡበት በመሆኑ እንደ ሌሎች ሀገሮች ሁሉ ተጨማሪ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል በማለት ጥናቱን አጠናቋል፡፡

በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ያለውን የማስተማር ልምምድና የክፍል ምልከታን በተመለከተ ካጠኑት መካከል Lemma & Taffese ( 1997) ይጠቀሳሉ፡፡ እነ Lemma በኮሌጁ በመከናወን ላይ ያለውን የማስተማር ልምምድ ለማጥናት በዋነኛነት በ1996/97 የትምህርት ዘመን ለማስተማር ልምምድ የወጡ የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የዲፕሎማና የዲግሪ ዕጩ መምህራንን የፅሁፍ መጠይቅ በማስሞላት በመረጃነት ተጠቅመውበታል፡፡

በጥናታቸው የማስተማር ልምምድ አጠቃላይ የመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር አንድ ክፍል ሆኖ ሳለ ችላ እንደተባለ ጠቁመዋል፡፡ ኮሌጁም የተማሪ አስተማሪዎችን፣ የተባባሪ ት/ቤቶችና ነባር መምህራንን፣ የሱፐርቫይዘሮችን ተግባርና ኃላፊነት የሚገልፅ መመሪያ እንዳላዘጋጀ ገልፀዋል፡፡ አብዛኞቹ የተማሪ አስተማሪዎች በጉብኝታቸው የነባር መምህራንን የትምህርት እቅድ ብቻ ይመለከታሉ እንጂ የራሳቸውን እቅድ ለማዘጋጀት እንደማይጥሩና ስለአዘገጃጀቱም ከነባር መምህራን ወይም ከሱፐርቫይዘራቸው ጋር እንደማይወያዩ አስፍረዋል፡፡

እነ Lemma የተማሪ አስተማሪዎች በማስተማር ልምምድ ምልከታ አጠቃላይ ከት/ቤቱ አውድ ጋር ለመተዋወቅ የሚችሉ መሆናቸውን ያመኑበት አይመስሉም፡፡ ምክንያቱም በጥናታቸው የብዙ የተማሪ አስተማሪዎች ትኩረት የት/ቤቱ ሕግና ደንብ፣ የገቢ ምንጭ፣ የትምህርት ክፍሎች ላይ መሆኑን አልወደዱትም፡፡ በመጨረሻም የማስተማር ልምምድ ምልከታ አስተማሪ ሊሆን የሚችልባቸውን ነጥቦች እንደሚከተለው በማስቀመጥ ጥናታቸውን ፈፅመዋል፡፡

1. የተማሪ አስተማሪዎች በምልከታ ሳምንት በደንብ ሊመራቸው የሚችል መመሪያ ሊዘጋጅላቸው ይገባል::
2. የተባባሪ ት/ቤት ነባር መምህራንና የት/ቤቱ አመራሮች ለተማሪ አስተማሪዎቹ ገለፃ በመስጠትና በመምራት የድርሻቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል::
3. የተማሪ አስተማሪዎች ለማስተማር ልምምድ ወደ ተባባሪ ት/ቤት የሚመጡ መሆናቸውን ገና ሲመዘገቡ ሊገለፅባቸው ይገባል::

ሌላው "Standardizing Supervisions' Evaluations" በሚል ርዕስ በማስተማር ልምምድና ሱፐርቪዥን አተገባበር ላይ ተመርኩዞ ጥናቱን ያከናወነው Zeleke (1997) ነው:: Zeleke በጥናቱ ለመቃኘት የሞከረው በመምህራን አሰለጣጠን ሂደት የሱፐርቫይዘሮች ግምገማ መደበኛነትን ነው:: ሱፐርቫይዘሮች ሊገለገሉባቸው የሚችሉ የተለያዩ የመገምገሚያና የመመዘኛ መንገዶች ቢኖሩም ሁሉም የትምህርት ክፍሎች የተውጣጡ የመገምገሚያ መስፈርቶችን በማዘጋጀት ቢጠቀሙ ተመራጭ እንደሆነ ጠቁሟል::

Belay & Gebre (1993) በበኩላቸው "Critics on practice teaching program of KCTE" በሚል ርዕስ ባቀረቡት የሴሚናር ወረቀት በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ለማስተማር ልምምድ በቂ የሆነ ዝግጅት አለመኖሩንና ቅድመ ማስተማር ልምምድ የሱፐርቫይዘሮች ገለፃ ከትምህርታዊ ጉዳዮች ይልቅ በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮረና የሚካሄደው የማስተማር ልምምድ ግልፅ የሆነ ዓላማ የሌለው መሆኑን አመልክተዋል:: ለማስተማር ልምምዱ የተመደበው ጊዜ በጣም አጭር መሆኑንም ጠቁመዋል:: እነ Belay ቅድመ ማስተማር ልምምድ የሚደረገው አስተዳደራዊ ገለፃ፣ የተባባሪ ት/ቤት ኃላፊዎች፣ ነባር መምህራን፣ ሱፐርቫይዘሮችና የተማሪ አስተማሪዎች በተገኙበት ትምህርታዊ ጉዳዮችም ላይ ያነጣጠረ መሆን እንዳለበት ጠቁመዋል::

Fesiha (1993) "An assessement of the training program of KCTE" በሚል ርዕስ የኮሌጁን የማስተማር ልምምድ አተገባበር በተመለከተ አጥንቶ የደረሰበትን ውጤት ለመሰንዘር በቅቷል:: Fesiha የማስተማር ልምምድ አደረጃጀትና አተገባበር የተሳሰሩ ጉዳዮች መሆናቸውን በማስታወስ ወደ ማስተማር ልምምድ ለመሸጋገር በብጤ ማስተማርና በንዑስ ማስተማር ልምምድ ማድረግ ተገቢ መሆኑን አስገንዝቦአል:: የተማሪ አስተማሪዎች ከሱፐርቫይዘራቸው የሚያገኙት ምክር፣ ምግበ መረጃና ድጋፍ ለማስተማር ልምምዱ መሳካት ትልቅ እገዛ ስለሚያደርግ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባም አሳስቦአል::

ሌላው በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል የሚካሄደውን የማስተማር ልምምድ ለመቃኘት ሙከራ ያደረገው ደግሞ ወንድወሰን (1995) እንደሆነ ዓለም (1988፣35-36) ገልጸ ወንድወሰን በጥናቱ የማስተማር ልምምዱ:-

- በቂ ክትትልና ድጋፍ የማይደረግለት መሆኑን፣
- ለፕሮግራሙ የተዘጋጀው ስርዓተ ትምህርት ወቅታዊ አለመሆኑን፣

- ሱፐርቪዥኑ የተባባሪ ት/ቤት ነባር መምህራንን የማያካትት መሆኑን፣
- የሱፐርቫይዘሮችና የተማሪ አስተማሪዎች ሚና በግልፅ አለመታየቱን . . . ወዘተ. በመግለጽ እነዚህ ጉድለቶች ሊስተካከሉ እንደሚገባቸው ጠቁሟል ይላል።

ከዚሁ ጋር አያይዞ ከተማሪ አስተማሪዎች ጋር ቅድመ ማስተማር ልምምድ ውይይት በማድረግ የሚገመገሙበትን መስፈርት መግለፅ ያስፈልጋል። በአጠቃላይ የመምህራን ስልጠና ወደ ሙያዊ እድገት መሸጋገር እንዳለበት በማሳሰብ ጥናቱን አጠናቅአል በማለት ዓለም ይገልፃል።

ሌላው በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ትምህርት ክፍል የተማሪ አስተማሪዎችን በተመለከተ ጥናት ያደረገው ሳህሉ (1986) ነበር። ሳህሉ በጥናቱ እንዳመለከተው በተማሪ አስተማሪዎች ዘንድ ተገቢውን የማስተማር ዘዴ መርጦ የመጠቀም ችግር ይታያል። ለዚህ ችግር መከሰት የትምህርት ክፍሉ የኮርስ አሰጣጥ በመሆኑ ስርዓተ ትምህርቱ ተገምግሞ ሊለወጥ ይገባዋል በማለት ይገልፃል።

በዚህ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ትምህርት ክፍል አብይ የአማርኛ ኮርሶች ኮሌጁ መምህራንን ለማስልጠን ከነደፈው ዓላማ ጋር መጣጣሙን ለመመዘንና ለመተንተን ሞክሮ የነበረው ደረጀ (1986) ነው። በጥናቱም ኮርሶቹ ጥሩ የቋንቋ ችሎታ ያለውን መምህር የመፍጠር አቅም እንደሌላቸው ገልጿል።

ከላይ ከተመለከትናቸው ጥናቶች ይልቅ የማስተማር ልምምድን በሚመለከት ጠለቀ ያለ ፍተሻ ያደረገው ዓለም (1988) ነው። ዓለም በጥናቱ እንደነ Belay & Gebre (1993) እና Fesiha (1993) ሁሉ በማስተማር ልምምድ ሂደት የታዩ የሱፐርቪዥንና ምግበ መረጃ አቀራረቦች ከችግር የፀዱ አለመሆናቸውን አረጋግጧል። የተማሪ አስተማሪዎችን ማስታወሻ፣ የካሴት ቅጂ፣ የፅሁፍ መጠይቅና ኮሌጁ ያዘጋጀውን የመገምገሚያ ቅፅ በመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያነት የተገለገለው ዓለም በማስተማር ልምምድና በሱፐርቪዥን አተገባበር ላይ የታዩትን ችግሮች እንደሚከተለው በ4 ጠቅለል አድርጎ አስቀምጧቸዋል። እነሱም፡-

1. ሱፐርቫይዘሮች ስለማስተማር ልምምድና ስለሱፐርቪዥን አተገባበር በቂ ስልጠና የሌላቸው መሆኑ፣
2. ኮሌጁ ለማስተማር ልምምዱ የሚሰጠው ትኩረት የቀዘቀዘ መሆኑ፣
3. በሱፐርቫይዘሮችና በተማሪ አስተማሪዎች ዘንድ መሠረታዊ የማስተማር ልምምድ ዓላማ ግንዛቤ አለመኖር፣
4. የማስተማር ልምምዱ በበቂ ቅድመ ዝግጅት ላይ ያልተመሰረተ መሆኑ ናቸው።

# ምዕራፍ ሦስት

## የጥናቱ ዘዴና የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች

### 3.1 የጥናቱ ተተኳሪዎች

ይህ ጥናት በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የ (10+1) ሰርተፍኬት መርሃ ግብር ሰልጣኝ መምህራን ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ ጥናቱ በ1997 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ሁለተኛው መንፈቀ ዓመት የፕራክቲከም፣ የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥን አተገባበርን ይቃኛል፡፡ በኮሌጁ በመደበኛና ተከታታይ ትምህርት መርሃ ግብር የዲፕሎማና የሰርተፍኬት ሰልጣኞች ቢኖሩም የዚህ ጥናት ተተኳሪዎች መደበኛ የሰርተፍኬት (10+1) ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከሬጅስትራር በተገኘው መረጃ መሠረት የ1997 ዓ.ም ሰርተፍኬት መርሃ ግብር ተማሪዎች ቁጥርና ሴክሽን የሚከተለውን ይመስላል፡፡

**ሠንጠረዥ አራት**

**የተተኳሪዎች ሴክሽንና ቁጥር**

| ሴክሽን | የተማሪዎች ብዛት | | ድምር | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | | |
| A | 13 | 28 | 41 | |
| B | 10 | 30 | 40 | |
| C | 18 | 23 | 41 | |
| D | 10 | 30 | 40 | |
| E | 11 | 31 | 42 | |
| F | 13 | 28 | 41 | |
| G | 11 | 28 | 39 | |
| H | 8 | 32 | 40 | |
| I | 4 | 36 | 40 | |
| K | 12 | 28 | 40 | |
| L | 10 | 30 | 40 | |
| M | 14 | 25 | 39 | |
| ድምር | 145 | 378 | 523 | |

ከዚህ መረጃ በመነሳት የጥናቱ ተተኳሪዎች በታቀደ የናሙና አመራረጥ ስልት ተመርጠዋል፡፡ ናሙናውን ለመምረጥ በመነሻነት ያገለገለው በኮሌጁ የፕራክቲከምና ፕሮግራም

ቢሮ የወጣው የፕራክቲከም የጊዜ ሰሌዳ ምቹነት ነው፡፡ እነዚህ በ13 ሴክሽኖች የሚማሩ 523 ተማሪዎች ለፕራክቲከምና ለማስተማር ልምምድ በተለያዩ የመንግስትና የሕዝብ ት/ቤቶች ተደልድለዋል፡፡ ከየካቲት 21 ቀን 1997 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 28 ቀን 1997 ዓ.ም በሚቆየው ፕራክቲከም በሁሉም ት/ቤቶች የተመደቡ የተማሪ አስተማሪዎችን በሙሉ የዚህ ጥናት ተተኳሪዎች ለማድረግ የማይቻል በመሆኑ በአመቺ ናሙና አመራረጥ (Purposive sampling) ዘዴ መምረጡ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ምክንያቱም በተመሳሳይ ቀንና ሰዓት የሚካሄደውን የፕራክቲከምና የማስተማር ልምምድ እንዲሁም ድህረ ማስተማር ውይይት ለመከታተል አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ስለዚህ የዚህ ጥናት አቅራቢ በተለይም የተማሪ አስተማሪዎች የሚይዙለትን ዕለታዊ ማስታወሻ ለማሰባሰብ ያመቸው ዘንድ የሚከተለውን ናሙና ወስዷል፡፡ በናሙናነት የተመረጡት ሴክሽኖች፣ የተማሪዎች ብዛት፣ ፈረቃ፣ ት/ቤቶችና የጊዜ ሰሌዳ የሚከተለውን ይመስላሉ፡፡

## ሠንጠረዥ አምስት

## የተመረጡ ተተኳሪዎች የፕራክቲከምና የማስተማር ልምምድ ፕሮግራም

| ተ.ቁ | ሴክሽን | የተመደቡባቸው ት/ቤቶች | የተማሪ ብዛትና ፈረቃ | | 1ኛ ዙር | 2ኛ ዙር | 3ኛ ዙር | 4ኛ ዙር | 5ኛ ዙር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጠዋት | ከሰዓት | | | | | |
| 1 | B | እንጦጦ አምባ | - | 16 | 21/6/97 | 6/7/97 | 21/7/97 | 29/7/97 | 3/8/97-28/8/97 |
| 2 | C | እየሩሳሌም | 12 | - | 21/6/97 | 6/7/97 | 21/7/97 | 29/7/97 | 3/8/97-28/8/97 |
| 3 | E | ኮከበ ጽባህ | - | 22 | 22/6/97 | 7/7/97 | 22/7/97 | 30/7/97 | 3/8/97-28/8/97 |
| 4 | G | ቀ/ሚኒልክ | 4 | - | 22/6/97 | 7/7/97 | 22/7/97 | 30/7/97 | 3/8/97-28/8/97 |
| 5 | M | ፀሐይ ጮራ | - | 8 | 24/6/97 | 9/7/97 | 19/7/97 | 27/7/97 | 3/8/97-28/8/97 |
| 6 | L | ፀሐይ ጮራ | 3 | - | 24/6/97 | 9/7/97 | 19/7/97 | 27/7/97 | 3/8/97-28/8/97 |
| 7 | K | ብሔራዊ ቤተመንግስት | 8 | - | 25/6/97 | 5/7/97 | 20/7/97 | 28/7/97 | 3/8/97-28/8/97 |
| 8 | J | ምስራቅ በር ቁ.1 | - | 13 | 25/6/97 | 5/7/97 | 20/7/97 | 28/7/97 | 3/8/97-28/8/97 |
| | | ድምር | 27 | 59 | | | | | |

በሠንጠረዥ ሦስት ስር የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው በስምንት ት/ቤቶች የተመደቡ 86 ተማሪዎችን ከየካቲት 21 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሚያዝያ 28 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ በመከታተል መረጃ ለማሰባሰብ ተችሏል፡፡ በ1997 ዓ.ም የሰርተፍኬት (10+1) ዕጩ መምህራንን በማሰልጠኑ ሂደት የተሳተፉ ሱፐርቫይዘሮችም የዚህ ጥናት ተተኳሪዎች እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ በአጠቃላይ በኮሌጁ በተለያየ ትምህርት ክፍል ከሚያስተምሩ መምህራን መካከል ሃያ ዘጠኝ የሚሆኑት በፕራክቲከምና በማስተማር ልምምድ ወቅት በሱፐርቫይዘርነት ተመድበዋል፡፡

እነዚህ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የመንግስትና የሕዝብ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ተመድበው የተማሪ አስተማሪዎችን እንዲከታተሉ የተደረጉ ሱፐርቫይዘሮች በሙሉ የዚህ ጥናት ተተኳሪዎች ሆነዋል፡፡ ይሁን እንጂ በፕራክቲከም መርሃ ግብሩ የፕሮግራም መደራረብ ምክንያት ከተማሪዎቻቸው ጋር ያደርጉትን ውይይት ለመከታተል የተቻለው የስምንቱን ብቻ ነው፡፡

## 3.2 የጥናቱ መረጃ አሰባሰብ ዘዴ

ጥናቱ በዋናነት የተገለገለባቸው የመረጃ ማግኛ መንገዶች የተማሪ አስተማሪዎች ማስታወሻ፣ ተከታታይ ምልከታ፣ የጽሁፍ መጠይቅ፣ ቃለ መጠይቅና ኮሌጁ ያዘጋጀው መገምገሚያ ቅጽ ናቸው፡፡ መረጃውን የማሰባሰቡ ሂደት እንዴት እንደተከናወነ ቀጥሎ ለማየት እንሞክራለን፡፡

### 3.2.1 የተማሪ አስተማሪዎች ማስታወሻ

የዚህ ጥናት ተተኳሪ ከሆኑት 523 የተማሪ አስተማሪዎች መካከል በታቀደ ናሙና አመራረጥ 86 የሚሆኑትን በመምረጥ በየተመደቡበት ትምህርት ቤት በመሄድ በፕራክቲከም፣ በማስተማር ልምምድና በሱፐርቪዥን ወቅት ሂደታዊ ማስታወሻ በመያዝ ትብብር እንዲያደርጉ በመጠየቅ ማስታወሻውን እንዴት ሊይዙ እንደሚችሉ የሃያ ደቂቃ ገለፃ ተደርጎላቸዋል፡፡ ግልጽ ባልሆኑ ጉዳዮች ላይ ውይይት ከተካሄደ በኋላ የተማሪ አስተማሪዎቹ ማስታወሻቸውን በሚይዙበት ጊዜ ሊያተኩሩ የሚገባቸውን ነጥቦች ሊያመላክት የሚችል "በፕራክቲከምና በማስተማር ልምምድ ወቅት ማስታወሻ እንዴት ይያዛል?" የሚል አጭር የማስታወሻ አያያዝ መመሪያ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ይህ መመሪያ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን በመጀመሪያው ክፍል አጠቃላይ መግለጫ ማለትም ማስታወሻው መቼ መቼ ሊያዝ እንደሚገባው የተጠቀመበት ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል በተለይም በፕራክቲከምና በማስተማር ልምምድ ወቅት ማስታወሻ ሲይዙ ሊያተኩሩባቸው የሚገቡ ነጥቦች የቀረበበት ነው፡፡ በዚህ መሠረት ከሰማንያ ስድስቱ የተማሪ አስተማሪዎች በየዙሩ ፕራክቲክሙን በተመለከተ የፃፉትን ማስታወሻ ይዘው እንዲመጡ በማድረግ በመጀመሪያው ዙር 61፣ በሁለተኛው ዙር 57፣ በሦስተኛው ዙር 48፣ በአራተኛው ዙር ፕራክቲከም ደግሞ 48 በአጠቃላይ 214 ማስታወሻወችን ለማሰባሰብ ተችሏል፡፡ በአራቱ ሳምንታት የማስተማር ልምምድ ወቅት 59 የተማሪ አስተማሪዎች ማስታወሻዎችን ማሰባሰብ የተቻለ ሲሆን በፕራክቲከሙና በማስተማር ልምምዱ ወቅት በድምሩ 273 ማስታወሻዎች ተሰብስበዋል፡፡ ይሁን እንጂ ሊሰበሰብ የታቀደው 430 ማስታወሻዎችን ነበር፡፡ ነገር ግን የተማሪ አስተማሪዎች በተለይም በማስተማር ልምምዱ ወቅት ለማስተማር የሚያደርጉትን ዝግጅት የሚሻማቸው መስሎ ስለተሰማቸው ማስታወሻ ለመያዝ ያልቻሉ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም ሆኖ ሊሰበሰብ ከታቀደው ከግማሽ በላይ በመሰብሰቡ በጥናቱ ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ የጎላ ባለመሆኑ የተሰበሰቡትን ማስታወሻዎች በአግባቡ ለመጠቀም ተሞክሯል፡፡ ይህ

ደግሞ የፕራክቲከሙን፣ የማስተማር ልምምዱንና የሱፐርቪዥኑን አተገባበሩን በሦስተኛ ወገን ምልከታ ላይ ብቻ ተመርኩዞ ከመግለጽ ይልቅ ከጉዳዩ ባለቤቶች ከሚገኝ መረጃ ጋር በማዛመድ ማቅረቡ ጥናቱን የተሟላ ያደርገዋል፡፡

### 3.2.2 ተከታታይ ምልከታ

የጥናቱ ተተኳሪዎች ከተመረጡ በኋላ በየተመደቡበት ት/ቤት በመዘዋወር የፕራክቲከም፣ የማስተማር ልምምድና የምግበ መረጃ ልውውጥ አሰጣጥ ሂደቱን በመመልከት መረጃ ለማሰባሰብ ተችሏል፡፡ ከፕራክቲከም ምልከታ በኋላ የተማሪ አስተማሪዎች የሰሩትን የጽሁፍ ሪፖርት በመመልከት ውጤት ከመስጠት ባለፈ የተማሪ አስተማሪዎችና ሱፐርቫይዘሮች ፊት ለፊት ተገናኝተው ያደረጉት ውይይት የጎላ ባይሆንም ድህረ ማስተማር ልምምድ ያደረጉትን ውይይት በመከታተል ስለሱፐርቪዥኑ አተገባበር በቂ የሆነ መረጃ ለመወሰድ ተችሏል፡፡ የውይይቱ ናሙናዊ ጥንቅርም በአባሪነት እንዲያያዝ ተደርጓል፡፡

### 3.2.3 የጽሁፍ መጠይቅ

የዚህ ጥናት ሦስተኛው የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ የጽሁፍ መጠይቅ ነው፡፡ የጽሁፍ መጠይቅ ከምልከታና ከተማሪ አስተማሪዎች ማስታወሻ ለማግኘት ያልተቻሉ መረጃዎችን ለማሰባሰብ እንደሚያስችል ይታመናል፡፡ በዚሁ መሠረት በፕራክቲከሙና በማስተማር ልምምዱ ሂደት ተሳታፊ ከነበሩ 523 የተማሪ አስተማሪዎች መካከል ሰላሳ በመቶው የሚሆኑትን ከሁሉም ሴክሽኖች በመውሰድ የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ምንም እንኳን በነሲብ ወይም በብድግ ብድግ ናሙና አወሳሰድ ዘዴ (Random Sampling) ከየሴክሽኑ አስራ ሁለት $12 \times 13 = 156$ የተማሪ አስተማሪዎች ተመርጠው መጠይቁን እንዲሞሉ ቢሰጣቸውም ሞልተው የመለሱት 110 ያህሉ ብቻ ናቸው፡፡ ይህም በመቶኛ ሲሰላ 70 በመቶ ይሆናል፡፡ ለተማሪ አስተማሪዎቹ የቀረበው መጠይቅ በሦስት ደረጃ ተከፍሎ ፕራክቲከም፣ የማስተማር ልምምድና ሱፐርቪዥን ላይ እንዲያተኩር ተደርጓል፡፡ በዚህ የጽሁፍ መጠይቅ የሚገኘው መረጃ በተማሪ አስተማሪዎች ማስታወሻ፣ በምልከታና በቃለ መጠይቅ ለተገኘው መረጃ ከፍተኛ የሆነ እገዛ ያደርጋል፡፡

በዚህ ጥናት በመረጃ ማሰባሰቢያነት የተዘጋጀው የጽሁፍ መጠይቅ ለተማሪ አስተማሪዎች ብቻ አይደለም፡፡ ፕራክቲከሙንና የማስተማር ልምምዱን ከሚከታተሉት ሱፐርቫይዘሮችም መረጃ ለማሰባሰብ የሚያስችል መጠይቅ በማዘጋጀት ሃያ ዘጠኙም ሱፐርቫይዘሮች እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ መጠይቁን ሞልተው የመለሱት ሱፐርቫይዘሮች ሃያ ብቻ ናቸው፡፡ ቀርቦላቸው የነበረው የጽሁፍ መጠይቅ ዝግ (Closed) እና ክፍት(Open) ጥያቄዎችን የያዘ ነበር፡፡

ከተማሪ አስተማሪዎችና ከሱፐርቫይዘሮች አጋዥ መረጃዎችን ለማግኘት አገልግሎት ላይ የዋለው መጠይቅ እንደአስፈላጊነቱ በመረጃ ትንተና ውስጥ በሠንጠረዥ መልክ ተቀምጧል፡፡ በሠንጠረዡ ውስጥ የሚታዩት ቁጥሮች የየራሳቸው ውክልና አላቸው፡፡ በዚሁ መሠረት፡-

5 = በጣም እስማማለሁ

4 = እስማማለሁ

3 = ለመወሰን እቸገራለሁ

2 = አልስማማም

1 = ፈጽሞ አልስማማም የሚለውን ሐሳብ ያመለክታሉ፡፡

በመረጃ ትንታኔው ሁለቱን አዎንታዊ መልሶች ማለትም አምስትና አራት አንድ ላይ ተሰልተው ሲቀመጡ፣ ሁለቱ አሉታዊ መልሶች ሁለትና አንድ ደግሞ አንድ ላይ ተሰልተው እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡ ሦስተኛው መልስ ግን ከማንኛውም ወገን የሚመደብ ባለመሆኑ ብቻውን ተሰልቶ ተቀምጧል፡፡ በሦስት የተመደበው የመላሾች ድምር ወደመቶኛ ተለውጧል፡፡

### 3.2.4 የመገምገሚያ ቅጽ

ይህ ቅጽ በኮሌጁ የፕራክቲከምና ፕሮግራም ቢሮ የተዘጋጀ ነው፡፡ ቅጹ የኮሌጁ ሱፐርቫይዘሮች ፕራክቲከሙንና የማስተማር ልምምዱን በመከታተል በቀላሉ ለመገምገም ያስችላቸዋል ተብሎ ተዘጋጅቷል፡፡ ይህ ቅጽ ሁለት ክፍሎች ሲኖሩት የመጀመሪያው የተማሪ አስተማሪዎችን ስብእና በሚመለከት አስራ አንድ መንቀሻ ነጥቦችን የያዘ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የተለማማጆቹን ዝግጅትና የትምህርት አቀራረብ ለመመዘን ያስችላሉ የተባሉ 9 ነጥቦችን ይዟል፡፡

ይህ የተለያዩ መንቀሻ ነጥቦችን የያዘው የመገምገማያ ቅጽ የዕጩ መምህሩ ስም፣ የተመደበበት ት/ቤት፣ ክፍልና ሴክሽን፣ የሚያስተምረው የትምህርት ዓይነትና ክፍለ ጊዜ የሚፃፍበት ክፍት ቦታ አለው፡፡

ይኸው ቅጽ በመጀመሪያው፣ ሁለተኛውና ሦስተኛው ሳምንት ለሚደረግ የማስተማር ልምምድ ግምገማ እንደሚያገለግል ከመገለጹም በላይ የግምገማው አካሄድ በማሳሳቢያ መልክ ተቀምጧል፡፡ በመጨረሻም ሱፐርቫይዘሩ አስተያየቱን በነፃነት በማስፈር ስሙን ከፃፈ በኋላ ፊርማውን እንዲያኖር የተተው ክፍት ቦታዎች አሉ፡፡ እነዚህ ክፍት ቦታዎች የገምጋሚው ትችት የሚቀመጥባቸው ሲሆኑ

ሀ. ጠንካራ ጎኖች

ለ. ደካማ ጎኖች

ሐ. የተሰጡ ምክሮች ተብለው የተለዩ ናቸው፡፡

የጥናቱ አቅራቢ ፕራክቲከሙና የማስተማር ልምምዱ ሲጠናቀቅ በቅጹ ላይ የተሰነዘሩትን አስተያየቶችና የእርምት ምክሮች በመውሰድ በሌላ መንገድ ከተገኙ መረጃዎች ጋር በትንታኔው ውስጥ በመጠቀም ጥናቱን የተሟላና ሶስት ጎንዮሻዊ ለማድረግ ሞክሯል፡፡

በአጠቃላይ የመረጃ አተናተን ዘዴው በአራቱም መንገድ የተሰበሰቡትን መረጃዎች እንደየአስፈላጊነታቸው በቅንጅት ወይም በተናጠል በመምዘዝ ይሆናል። ይሁን እንጂ ከላይ በተዘረዘሩት የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች በሙሉ በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል ማለት አይደለም።

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና የተገኘው ውጤት

## 4.1 የሱፐርቫይዘሮች የትምህርት ደረጃና የአገልግሎት ዘመን

በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በሰርተፍኬት ፕሮግራም በሱፐርቫይዘርነት የተሳተፉ መምህራን ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ በሰጡት መልስ መሠረት የትምህርት ደረጃቸውና የአገልግሎት ዘመናቸው የሚከተለውን ይመስላል::

### ሠንጠረዥ ስድስት

### የተተኳሪ ሱፐርቫይዘሮች የትምህርት ደረጃና የአገልግሎት ዘመን

| ሱፐርቫይዘር | ያለው የትምህርት ደረጃ | የአገልግሎት ዘመን |
|---|---|---|
| 1 | ሁለተኛ ዲግሪ | 33 ዓመት |
| 2 | » » | 25 » |
| 3 | » » | 23 » |
| 4 | » » | 19 » |
| 5 | » » | 18 » |
| 6 | » » | 2 » |
| 7 | » » | 18 » |
| 8 | » » | 25 » |
| 9 | » » | 24 » |
| 10 | የመጀመሪያ ዲግሪ | 1 » |
| 11 | » » | 1 » |
| 12 | » » | 1 » |
| 13 | » » | 1 » |
| 14 | » » | 7 ወር |
| 15 | » » | 4 ዓመት |
| 16 | » » | 1 ዓመት |
| 17 | ዲፕሎማ | 30 ዓመት |
| 18 | » | 32 » |
| 19 | » | 24 » |
| 20 | » | 25 » |

ከላይ በቀረበው ሠንጠረዥ እንደሚታየው ሱፐርቫይዘሮቹ ከዲፕሎማ እስከ ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው ናቸው:: ይሁን እንጂ የአብዛኞቹ ሱፐርቫይዘሮች የስልጠና መስክ ከሱፐርቪዥን ጋር የሚቀራረብ አይደለም:: ይህ ደግሞ ፕራክቲከሙንና የማስተማር ልምምዱን በአግባቡ ለመከታተል እንዳይችሉ ሊያደርጋቸው እንደሚችል ይታመናል:: ከዚሁ ጋር በማያያዝ ሱፐርቫይዘሮቹ ፕራክቲከምና ሱፐርቪዥንን በተመለከተ ስልጠና፣ ሴሚናር ወይም ወርክ ሾፕ ወስደው እንደሆነ ለማረጋገጥ የሚያስችል ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር:: ይሁን እንጂ ስልጠና፣ ሴሚናር ወይም ወርክሾፕ እንደወሰዱ የገለፁት አስሩ ብቻ ናቸው:: ቀሪዎቹ አስሩ ምንም ዓይነት ስልጠናም ሆነ ሴሚናር እንዳልወሰዱ ገልፀዋል:: ስልጠና የወሰዱትም ቢሆኑ ስልጠናው የተካሄደው እርስ በእርስ እንደሆነ በማስታወስ በቂ ግንዛቤ ያስጨበጠ እንዳልሆነ ገልፀዋል::

እንደ Woodward (1991:203) አገላለጽ ሱፐርቫይዘር ሊባሉ የሚችሉት የኮሌጅ መምህራን በተለይም ንድፈ ሐሳብና ስነ ዘዴን በማስተማር ትምህርቱ በልምምድ ወደ ተግባር የሚለወጥበትን ሁኔታ በማመቻቸት ክትትል ማድረግ የሚችሉ ባለሙያዎች ናቸው:: ይህን ለማድረግ ደግሞ የሰለጠኑበት ሙያ ከመምህራን ስልጠና ጋር ተቀራራቢነት ቢኖረው ተመራጭነት ይኖረዋል:: ከላይ በተመለከተው ሠንጠረዥ ግን ፕራክቲከሙንና የማስተማር ልምምዱን እንዲከታተሉ የተመደቡት ሱፐርቫይዘሮች በተለያየ የሙያ መስክ የሰለጠኑ ሆነው እናገኛቸዋለን::

## 4.2 የጥናቱ ተተኳሪ የተማሪ አስተማሪዎች ዕድሜ፣ የ10ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ውጤትና ወደ ኮሌጅ አገባባቸው

በሀገራችን ዘመናዊ ትምህርት ታሪክ መምህራንን ማሰልጠን ሲጀመር በመምህርነት ሙያ ይሰለጥኑ የነበሩት በትምህርታቸው ላቅ ያለ ውጤት የነበራቸው ተማሪዎች እንደነበሩ ይታወሳል:: በአዲሱ የመምህራን ስልጠና ፖሊሲ መሰረት ወደ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም ገብተው መሰልጠን የሚገባቸው የ10ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ተማሪዎች መሆን እንዳለባቸው ተገልጿል:: በዚሁ መሠረት በ1997 ዓ.ም ለመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል /1-4/ መምህርነት በመሰልጠን ያሉ የተማሪ አስተማሪዎች በቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ ላይ ባሰፈሩት መረጃ መሠረት ዕድሜያቸው፣ የ10ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ውጤታቸውና የኮሌጅ አገባባቸው የሚከተለውን ይመስላል::

## ሠንጠረዥ ሰባት

### የተተኳሪ ተማሪ አስተማሪዎች ዕድሜ፣ የ10ኛ ክፍል ውጤትና ወደ ተቋም አገባብ

| ዕድሜ | | | | | | የ10ኛ ክፍል ብ/ፈተና ውጤት | | | ወደ ተቋም አገባብ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | >20 | ከ1.8 በታች | ከ1.8 -1.99 | ከ2.00 በላይ | ተወዳ ድሬ | አማራጭ አጥቼ | መር ጨ | ተመድቤ /በኮታ/ |
| 3 | 8 | 42 | 37 | 11 | 9 | 4<br>3.6% | 72<br>65.5% | 34<br>30.9% | 90<br>82% | 17<br>15% | 1<br>0.9<br>% | 2<br>1.8% |

ከላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያስረዳው የአብዛኞቹ ሰልጣኞች ዕድሜ ከ18 ዓመት በታች ነው፡፡ በሀገራችን ሕገ መንግስት የሥራ መቀጠሪያ ዕድሜ 18 ዓመት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ አሁን በተገኘው መረጃ መሠረት እነዚህ የተማሪ አስተማሪዎች ሲመረቁ 18 ዓመት ስለሚሞላቸው መቀጠር የሚችሉበት ዕድሜ ላይ ይደረሳሉ ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አስራ አንድ የሚሆኑት ሰልጣኞች ከሥራ መቀጠሪያ ዕድሜ በታች እንዳሉ የሚመረቁ መሆኖቸውን ከመረጃው መገንዘብ ይቻላል፡፡

የ10ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ውጤታቸውን በምንመለከትበት ጊዜ 69.1 ከመቶ የሚሆኑት ከሁለት ነጥብ በታች ያመጡ ናቸው፡፡ የትምህርት ጥራትን ከማስጠበቅ አኳያ እነዚህን ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ዕጩ መምህራንን ማሰልጠኑ ምን ያህል ስኬታማ ሊሆን እንደሚችል ያጠራጥራል፡፡ ምንም እንኳን ዘጠና በመቶው የሚሆኑት የተማሪ አስተማሪዎች ወደ ተቋሙ የገቡት ተወዳድረው እንደሆነ የገለፁ ቢሆንም 15 ከመቶ የሚሆኑት አማራጭ በማጣታቸው ወደ መምህርነት ሙያ ለመግባት መገደዳቸውን ገልፀዋል፡፡ ተወዳድረው የገቡትም ቢሆኑ ይህን ዝቅተኛ ውጤት ይዘው ሌላ ቦታ ሊገቡ ባለመቻላቸው ወደዚህ ሙያ ሊገቡ እንደቻሉ ለመገመት አያዳግትም፡፡

## 4.3. የፕራክቲከም፣ የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥን አተገባበር በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ

### 4.3.1 የኘራክቲከም ሂደትና አተገባበር

በማስተማር ሥራ ዋነኛና መሠረታዊ አላባ በመባል የሚታወቀው ፕራክቲከም የአንድን እውናዊ ት/ቤት አጠቃላይ ገጽታ ለማወቅ ያስችላል፡፡ Richards and Naunan (1990:101) እንደገለፁት ፕራክቲከም በት/ቤት ውስጥ እየተከናወነ ያለውን የመማር ማስተማር እንቅስቃሴ፣ የተማሪዎችን ባህሪና እውነተኛው የመምህርነት ሙያ ምን እንደሚመስል በመመልከት ዕውቀትና ክሂልን ለማሳደግ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡ በእርግጥ የተፈለገው ውጤት ላይ

ለመድረስ የሚቻለው የፕራክቲከሙ ሂደትና አተገባበር የተሳካ ሲሆን ብቻ ነው። ይህንኑ ንድፈ ሐሳብ መነሻ በማድረግ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የፕራክቲከም ሂደትና አተገባበር ምን እንደሚመስል እንቃኛለን።

#### 4.3.1.1 የፕራክቲከም ሂደት

የፕራክቲከም ሂደት ተጠየቃዊ አካሄድን የተከተለና የራሱን ቅደም ተከተል ጠብቆ እያደገ መሄድ ይጠበቅበታል። የፕራክቲከሙ መሠረት ደግሞ በክፍል ውስጥ የሚሰጠው ንድፈ ሐሳባዊ ትምህርት መሆኑ ግልጽ ነው። ይህንን በሚመለከት በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሚሰለጥኑ ዕጩ መምህራን በክፍል ውስጥ የቀሰሙት ንድፈ ሐሳብ በፕራክቲከም ወቅት ከተመለከቱት ነገር ጋር መጣጣም አለመጣጣሙን በጽሁፍ መጠይቅ ተጠይቀው ነበር። የሰጡት ምላሽ የሚከተለውን ይመስላል።

### ሠንጠረዥ ስምንት

### የንድፈ ሐሳብ ትምህርትና ፕራክቲከም መጣጣም

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | በክፍል ውስጥ የቀሰምኩት ንድፈ ሐሳብና በፕራክቲከም ወቅት የተመለከትኩት ነገር ፈጽሞ የሚጣጣም አይደለም። | 40<br>36.4% | | 22<br>19.9% | 45<br>40.9% | | 3<br>2.7% |

ከላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ ለመረዳት እንደሚቻለው 40.9 ከመቶው የንድፈ ሐሳብ ትምህርቱና ፕራክቲከሙ የሚጣጣም መሆኑን ገልፀዋል። 36.4 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ አዎን አይጣጣምም በማለት መልስ ሰጥተዋል። 19.9 ከመቶ ያህሉ ግን ለመወሰን የተቸገሩ ናቸው።

በፕራክቲከም ወቅት የተማሪ አስተማሪዎች የያዙትን ማስታወሻ በምናይበት ጊዜ ከላይ የቀረበውን ሐሳብ የሚያጠናክር ሆኖ እናገኘዋለን።

> አንድን ዕውቀት ለመተግበር መንደርደሪያው ንድፈ ሐሳብ መሆኑ ግልጽ ነው። በንድፈ ሐሳብ ደረጃ የቀሰምነውና በተግባር የተመለከትነው ነገርም ይጣጣማል።
>
> ለፕራክቲከም በወጣሁበት ወቅት የገጠመኝ ነገር በክፍል ከቀሰምኩት ዕውቀት ጋር ይጣጣማል። ምክንያቱም በክፍል ውስጥ ስማር ስለተማሪዎቹ ባህሪና እንዴት ማስተማር እንዳለብኝ ግንዛቤ አግኝቻለሁ። ለፕራክቲከም ስወጣም የገጠመኝ ቀድሜ የተማርኩት ነገር ነው።
>
> በክፍል ውስጥ የቀሰምኩት ዕውቀት በተግባር በፕራክቲከም ምልከታዬ ወቅት ካየሁት ነገር ጋር ይጣጣማል። ለምሳሌ በPS III ኮርስ የተማርነው ስለህፃናት ባህሪ ነው። በፕራክቲከም ተግባር

አንድ ላይም እንድናጠና የተደረገው ስለአንድ ተማሪ ባህሪያት ነው፡፡ ስለዚህ ሕፃኑን ለማጥናት በክፍል ውስጥ የቀሰምኩት ትምህርት አግዞኛል ማለት ነው፡፡

ከላይ በተመለከተው አኳኋን ንድፈ ሐሳብና ፕራክቲከም የማይነጣጠሉና ተደጋጋፊዎች እንደሆኑ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በሌላ መንገድ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

## ሠንጠረዥ ዘጠኝ

## የንድፈ ሐሳብ ትምህርትና ፕራክቲከም ተደጋጋፊነት

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 15 | በክፍል ውስጥ ከሚሰጥ የንድፈ ሐሳብ ትምህርት ይልቅ ፕራክቲከም በቂ ግንዛቤ ያስጨብጣል፡፡ | 81<br>73.6% | | 13<br>11.8% | 16<br>14.5% | | - |

በተራ ቁጥር 15 ለቀረበው አዎንታዊ ጥያቄ 73.6 ከመቶ የሚሆኑ መላሾች በክፍል ውስጥ ከሚሰጥ ትምህርት ይልቅ ለፕራክቲከም ወደ ተባባሪ ት/ቤቶች ሄደው ከሚያደርጉት ምልከታ ስለመምህርነት ሙያ የተሻለ ግንዛቤ ሊያገኙ የሚችሉ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ከያዙት ማስታወሻም መመልከት እንደሚቻለው ከላይ የቀረበውን ሐሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን ማስታወሻዎች እንመልከት፡፡

> በክፍል ውስጥ ያገኘነው እውቀት ከፕራክቲከሙ ጋር አይጣጣምም፡፡ በክፍል ውስጥ የምናገኘው ዕውቀት በማስመሰል የሚቀርብ ነው፡፡ ሕፃን አጠገባችን ሳይኖር እኛ እንደህፃን እየሆንን የምናስተምርበት ዘዴ ነው፡፡ ለፕራክቲከም በወጣንበት ት/ቤት የነበሩ ሕፃናት በጣም አስቸጋሪዎች በመሆናቸው ራሳችንን አስተካክለን ለመገኘት ያስችለናል፡፡
>
> በክፍል ውስጥ ብዙ ነገሮችን የተማርኩ ቢሆንም ደካማ ተማሪዎችን እንዴት መርዳት እንዳለብኝ ግን አልተማርኩም፡፡ በፕራክቲከም ወቅት ግን ደካማ ተማሪዎችን እንዴት ልረዳ እንደምችል ተገንዝቤያለሁ፡፡

የንድፈ ሐሳብ ትምህርትና ፕራክቲከም ሊኖራቸው ስለሚችለው ተደጋጋፊነት ሁለት የተለያዩ ሐሳቦች ይቅረቡ እንጂ ምንም ዓይነት ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀት የሌለው ልምምድ ወይም

ተግባር ውጤታማ ይሆናል ብሎ ለማሰብ ያስቸግራል:: ስለዚህ በመምህራን ስልጠና ፕራክቲከም የተጠበቀውን ውጤት ሊያስገኝ የሚችለው ከንድፈ ሐሳብ ትምህርት ተፋቶ ሳይሆን ንድፈ ሐሳብን መሠረት አድርጎ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል::

የፕራክቲከም ሂደት ሦስት ደረጃዎች እንዳሉት ይታወቃል:: እነሱም ቅድም ፕራክቲከም፣ ሙሉ ፕራክቲከም እና ክሊኒካል ልምምድ በመባል ይታወቃሉ:: የተማሪ አስተማሪዎች ለፕራክቲከም ወደ ተባባሪ ት/ቤት ከመላካቸው በፊት ከሱፐርቫይዘራቸው ጋር የቅድመ ፕራክቲከም ውይይት ማካሄድ አለባቸው:: በዚህ ውይይት በፕራክቲከም ወቅት ሊያተኩሩባቸው የሚገቡ ነጥቦች ሊገለፅላቸው ይገባል:: ከፕራክቲከሙ በኋላ ከእነሱ ምን እንደሚጠበቅ የሚነገራቸውም በዚሁ ውይይት ነው::

በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በሚማሩ የሰርተፍኬት ተማሪዎችና በሱፐርቫይዘሮች መካከል ቅድመ ፕራክቲከም ውይይት መኖሩን ለማረጋገጥ የጽሁፍ መጠይቅ ለሁለቱም ወገኖች ቀርቦላቸው ነበር:: በመጀመሪያ የተማሪ አስተማሪዎችን ምላሽ እንመልከት::

## ሠንጠረዥ አስር

### ቅድመ ፕራክቲከም ውይይትን በተመለከተ የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ለፕራክቲከም ወደ ትምህርት ቤቶች ከመሄዳችን በፊት ስለፕራክቲከም ምንነት በቂ ገለፃ ተደርጎልናል:: | 33<br>29.9% | | 31<br>28.2% | 45<br>40.9% | | 1<br>0.9% |

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው 40.9 ከመቶው የሚሆኑት መላሾች ለፕራክቲከም ወደየተመደቡባቸው ት/ቤቶች ከመሄዳቸው በፊት ገለፃ ያልተደረገላቸው መሆናቸውን ነው:: አጥኚው የፕራክቲከሙን ሂደት ለመከታተልና የተማሪ አስተማሪዎችን ማስታወሻ ለማሰባሰብ በተንቀሳቀሰባቸው ት/ቤቶች ያገኛቸው የተማሪ አስተማሪዎች እንደገለፁለት በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ፕራክቲከምና ፕሮግራም ቢሮ የተዘጋጀውን የተግባር መመሪያ ከመቀበላቸው ውጭ ማድረግ ስለሚገባቸው ነገር አልተብራራላቸውም:: በዚህ ምክንያት ሊያተኩሩባቸው የሚገቡ ጥያቄዎች ግልፅነት የጎደላቸው ከመሆናቸውም በላይ ተደጋጋሚነት ስለሚታይባቸው ግርታን ፈጥረውባቸው እንደነበር ለመረዳት ተችሏል::

ለሱፐርቫይዘሮችም ተመሳሳይ ጥያቄ ቀርቦላቸው የሰጡ ምላሽ የሚከተለውን ይመስላል::

የተማሪ አስተማሪዎቹ ማስታወሻ እንደሚያመለክተው እንኳንስ መመሪያ ሊሰጧቸው ቀርቶ ከሱፐርቫይዘራቸው ጋር ተገናኝተው የማያውቁ መኖራቸውን ነው:: ለአብነት ያህል ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን የተማሪ አስተማሪ ማስታወሻዎች ለማየት እንሞክር::

> ሱፐርቫይዘራችን የምናዘጋጀው የፕራክቲከም ሪፖርት ሊያተኩርበት የሚገባው በምን በምን ላይ እንደሆነ የሚጠቁመውን ወረቀት አስረክቦን ተመለሰ እንጂ ት/ቤት ሄዳችሁ ይህን ታደረጋችሁ በኋላ ሪፖርቱን በእንዲህ ያለ መንገድ አዘጋጁ አላለንም::
>
> . . . የፕራክቲከም ጥያቄውን እንኳን መጥቶ አልሰጠንም:: በተወካያችን አማካይነት ነው የላከልን::
>
> ሱፐርቫይዘሬ እራሱ የትኛው እንደሆነ ለኔ ግልጽ አይደለም:: በሄድንበት ት/ቤት ያለው ነው? ወይስ ፕራክቲከም የሚቀበለን ነው? ማንም መጥቶ ስለ የትኛውም ሁኔታ የነገረን ነገር የለም::
>
> እንኳንስ ገለፃና መመሪያ ሊሰጠን ይቅርና ጥያቄውንም በእጃችን አላስረከበንም:: እኔም ያወቅኩት የተግባር አንድን ሪፖርት ላስረከበው ቢሮው ስሄድ ነው::

እነዚህ ማስታወሻዎች አብዛኞቹ ሱፐርቫይዘሮች ከተመደቡላቸው የተማሪ አስተማሪዎች ጋር የማይተዋወቁና ብዙም ተቀራርበው የሚሰሩ አለመሆናቸውን ያመላክታሉ:: ባለመቀራረባቸውም ምክንያት የተማሪ አስተማሪዎች በፕራክቲከሙ ወቅት የሚገጥሟቸውን ችግሮች በማቃለል ሂደት የሱፐርቫይዘሮች እገዛ አናሳ እንዲሆን ሳያደርገው አልቀረም:: ይህን ለማረጋገጥ ለተማሪ አስተማሪዎች ከዚህ በታች የተመለከተው ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር:: የሰጡት መልስም የሚከተለውን ይመስላል::

## ሠንጠረዥ አስራ ሦስት

## የሱፐርቫይዘሮች እገዛ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 26 | በፕራክቲከም ሂደት የገጠሙኝን ችግሮች በመፍታት ሂደት ሱፐርቫይዘሬ ምንም እገዛ አላደረገልኝም:: | 38<br>34.5% | | 18<br>16.4% | 49<br>44.5% | | 5<br>4.5% |

በሠንጠረዡ እንደሚታየው በፐርሰንት 44.5 ከመቶ የሚሆኑት የተማሪ አስተማሪዎች የገጠማቸውን ችግር በመፍታት ሂደት ከጎናቸው እንደቆሙ ይገልፃሉ:: ይሁን እንጂ 34.5 ከመቶ የሚሆኑት የተማሪ አስተማሪዎች እገዛ አልተደረገላቸውም:: 16.4 ከመቶ ያህሉ ደግሞ ቁርጠኛ ምላሽ ለመስጠት የተቸገሩ ናቸው:: ቀሪዎቹ 4.5 ከመቶ የሚሆኑት የተማሪ አስተማሪዎች ግን ለጥያቄው መልስ ከመስጠት የተቆጠቡ ናቸው:: የተማሪ አስተማሪዎች በየደረጃው

የሚገጥሟቸውን ችግሮች በመፍታት ሂደት እገዛ ካልተደረገላቸው ተገቢውን የመምህርነት ሙያ ተላብሰው ይወጣሉ ለማለት ያዳግታል፡፡ ስለዚህ በተለይ በዚህ ኘሮግራም የሚሰለጥኑት መምህራን አሃዳዊ የትምህርት አሰለጣጠንን ተግባራዊ የሚደርጉ በመሆናቸው የችግር ፈችነት አቅማቸውን ማጐልበት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በስተቀር ሁሉንም የትምህርት ዓይነቶች የሚያስተምሩት በአማርኛ ቋንቋ በመሆኑ የአማርኛ ቋንቋ አጠቃቀማቸውን በማጐልበት ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች አፋጣኝ መፍትሄ መሻት ይኖርባቸዋል፡፡

### 4.3.1.2 የኘራክቲከም አተገባበር

በመምህራን ስልጠና ፕራክቲከም የተጠበቀውን ውጤት ሊያስገኝ የሚችለው በአግባቡ የተተገበረ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ የተማሪ አስተማሪዎች ከቅድመ ፕራክቲከም ውይይት በኋላ የሚሸጋገሩት ዋናውን የፕራክቲከም ተግባር ወደማከናወን ነው፡፡ በዋነኛ የፕራክቲከም ምልከታቸው አጠቃላይ ከተመደቡበት ት/ቤት አውድ ጋር ማለትም ከት/ቤቱና ከተማሪዎች ባህሪያት፣ የመማር ማስተማር ሂደትና ደረጃ፣ የተማሪዎች ትምህርት የመቀበል አቅም፣ ነባር መምህራን እየተገለገሉበት ካለው የማስተማር ዘዴ ጋር ይተዋወቃሉ (Moore 1994:39-40) ፡፡

በዚህ ሁሉ መሃል የሱፐርቫይዘሮች ሚና በቀላሉ የሚገመት አይሆንም፡፡ ምክንያቱም የተማሪ አስተማሪዎቹ በጽሁፍም ይሁን በቃል የተሰጣቸውን መመሪያ መነሻ በማድረግ አዘጋጅተው የሚያቀርቡትን ዝግበ ጥናት (Portfolio) በማረም አስተያየት መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ ባለፈም በየዙሩ መጨረሻ ስለነበረው የፕራክቲከም ሂደት የተማሪ አስተማሪዎችን ማወያየት ይኖርባቸዋል፡፡ በውይይቱ መካከል ስለነበራቸው ጠንካራና ደካማ ጎን ስሜትን በማይጎዳ መንገድ በማቅረብ በሚቀጥለው ዙር እንዲያሻሽሉ መጠቆም ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይህን በሚመለከት ለተማሪ አስተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጎ የተገኘው ውጤት ቀጥሎ የተመለከተው ነው፡፡

## ሠንጠረዥ አስራ አራት

### በኘራክቲከም ሪፖርት ላይ የተደረገ ውይይት ስለመኖሩ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | ከሱፐርቫይዘሬ ጋር በየዙሩ በመገናኘት ባቀረብኩት ሪፖርት ላይ ውይይት አድርገናል፡፡ | 27<br>24.5% | | 18<br>16.4% | 61<br>55.5% | | 4<br>3.6% |

ከላይ በሠንጠረዡ ለቀረበው ጥያቄ የተገኘውን ምላሽ ስንመለከት የሚከተለውን ሐሳብ ይሰጠናል፡፡ ጥያቄው አዎንታዊ ነው፡፡ ለጥያቄው የተሰጠው አዎንታዊ ምላሽ 24.5 ከመቶ ነው፡፡ ይህም ከ100 ተጠያቂ የተማሪ አስተማሪዎች ሃያ አራት የሚሆኑ በአራቱም ዙር ፕራክቲከም

በሰሩት የጽሁፍ ሪፖርት ላይ ከሱፐርቫይዘራቸው ጋር የተወያዩ መሆናቸውን ገልፀዋል ማለት ነው፡፡ ቀሪዎቹ 55.5 ከመቶ የሚሆኑት ግን በየዙሩ ከሱፐርቫይዘሮቻቸው ጋር ፈጸሞ አልተወያየንም ሲሉ ቀሪዎቹ 16.4 ከመቶ ደግሞ ለመወሰን የተቸገሩ ናቸው፡፡

በዚሁ ጉዳይ ላይ በተመሳሳይ መንገድ ለሱፐርቫይዘሮች ጥያቄው ቀርቦላቸው ቀጥሎ በሠንጠረዡ ላይ በሰፈረው መልክ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

## ሠንጠረዥ አስራ አምስት

### በፕራክቲከም ሪፖርት ላይ ውይይት ስለመደረጉ

<table>
<tr><th>ተ.ቁ</th><th>ጥያቄ</th><th>5</th><th>4</th><th>3</th><th>2</th><th>1</th><th>ያልመለሱ</th></tr>
<tr><td>4</td><td>በአራቱም ዙር ፕራክቲከም መጨረሻ ላይ ከተማሪ አስተማሪዎች ጋር ውይይት አላደረኩም፡፡</td><td colspan="2">9</td><td>2</td><td colspan="2">9</td><td>-</td></tr>
</table>

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው በአሉታዊ ለቀረበው ጥያቄ ሱፐርቫይዘሮች የሰጡት ምላሽ እኩል አዎንታዊም አሉታዊም ነው፡፡ ዘጠኙ ውይይት ያላደረጉ መሆናቸውን ሲገልጹ ሌሎች ዘጠኝ ደግሞ መወያየታቸውን ገልፀዋል፡፡ ውይይቱን አካሂጃለሁ ወይም አላካሄድኩም በማለት ቁርጥ ያለ መልስ ለመስጠት ያልደፈሩ ሁለት ሱፐርቫይዘሮችም ነበሩ፡፡ ከምላሾቹ ለመገንዘብ እንደሚቻለው በየዙሩ ስለ ፕራክቲከሙ መወያየት የሚከብድ መሆኑን ነው፡፡ ሱፐርቫይዘሮች ፕራክቲከሙን በሚመለከት በጽሁፍ እንዲመልሱ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት መልስም ይህንኑ ያጠናክራል፡፡

> እያንዳንዱ ሱፐርቫይዘር ከተሰጠው አስራ ሁለት ክሬዲት ሐወር የማስተማር ስራ ጋር አራቱንም ዙር ፕራክቲከም እንደተፈለገው ለመከታተል ፍፁም አስቸጋሪ ነው፡፡
>
> በአዲሱ የTESO ፕሮግራም የፕራክቲከም አፈፃፀም መመሪያ አኳያ በርካታ ዕጩ መምህራንን መገምገምና አስፈላጊውን /የሚጠበቀውን ምክር መስጠት አዳጋች ነው፡፡ . . . በተለይ በየደረጃው በፕራክቲከም የሚሰሯቸው ተግባራት ት/ቤትን ከማየት፣መምህራንን በክፍል ሲያስተምሩ ከመመልከት፣ ተማሪዎችን ከማጥናት ፣ አኳያ የሚጽፏቸውን ወረቀቶች አንብቦ አስተያየት ለመስጠት አስቸጋሪ ነው፡፡
>
> ከተመደቡልኝ ተማሪዎችና ካለብኝ ተደራራቢ ኃላፊነት አንፃር አስር ተማሪዎችን አራት ወይም ሦስት ጊዜ ማወያየት ጊዜ የሚወስድና አድካሚ ስለሆነ አቅም በፈቀደ መጠን ቢያንስ ሁለት ጊዜ ማወያየት ይበቃ ይመስለኛል፡፡

ከላይ በሠንጠረዥ አስራ ስድስት ከቀረበው ጥያቄ በተጨማሪ የተማሪ አስተማሪዎች በመጀመሪያው በሁለተኛው፣ በሦስተኛውና በአራተኛው ዙር ፕራክቲከም መገባደጃ ላይ ከሱፐርቫይዘሮቻቸው ጋር መወያየት አለመወያየታቸውን ለማወቅ አዎንታዊና አሉታዊ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው ነበር:: የተገኘው መልስ እንደሚከተለው ቀርቧል::

## ሠንጠረዥ አስራ ስድስት

### በፕራክቲከም አራት ተግባራት መገባደጃ ላይ የተካሄደ ውይይት ስለመኖሩ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 4 | 3 | 2 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|
| 12 | ከመጀመሪያው ዙር ፕራክቲከም ምልከታዬ በኋላ ከሱፐርቫይዘሬ ጋር ውይይት አድርጌያለሁ:: | 34<br>30.9% | 17<br>15.5% | 58<br>52.7% | 1<br>0.9% |
| 3 | ሁለተኛው ዙር የፕራክቲከም ምልከታዬን በሚመለከት ከሱፐርቫይዘሬ ጋር አልተወያየሁም:: | 47<br>42.7% | 21<br>19% | 41<br>37.3% | 1<br>0.9% |
| 5 | ከሦስተኛው ዙር የፕራክቲከም ምልከታዬ በኋላ ከሱፐርቫይዘሬ ጋር ተወያይቻለሁ:: | 38<br>34.5% | 17<br>15.5% | 50<br>45.5% | 5<br>4.5% |
| 8 | የአራተኛውን ዙር ፕራክቲከም በተመለከተ ከሱፐርቫይዘሬ ጋር አልተወያየሁም | 51<br>46.4% | 12<br>10.9% | 46<br>41.8% | 1<br>0.9% |

ከላይ ለተማሪ አስተማሪዎች በዝግ የጥያቄ ዓይነት የቀረቡት ጥያቄዎች በሠንጠረዡ የተመለከተው ድህረ ፕራክቲከም ተግባራት ውይይት መደረግ አለመደረጉን ይጠቁማሉ::

ለጥያቄ ቁጥር አስራ ሁለት የተሰጠውን ምላሽ ስንመለከት ከመጀመሪያው ዙር/ተግባር/ የፕራክቲከም ምልከታቸው በኋላ ከሱፐርቫይዘራቸው ጋር ተገናኝተው ውይይት ያደረጉት 30.9 ከመቶው ብቻ ናቸው:: 52.7 ከመቶ የሚሆኑት ግን ውይይት አላደረጉም:: ቀሪዎቹ በፐርሰንት 15.5 ከመቶ ደግሞ ለመወሰን የተቸገሩ ናቸው::

በተራ ቁጥር ሦስት ለቀረበው አሉታዊ ጥያቄ የተሰጠው ምላሽም እንዲሁ 42.7 ከመቶው አዎንታዊ ሆኖ እናገኘዋለን:: ይህም በአብዛኛው ከሁለተኛው ዙር ፕራክቲከም ምልከታ በኋላ ውይይት ያልነበረ መሆኑን ያመለክታል::

ለጥያቄ ቁጥር አምስት የሰጡትን መልስ ስናይ ከሦስተኛው ዙር ፕራክቲከም ምልከታ በኋላ 45.5 ከመቶ የሚሆኑ የተማሪ አስተማሪዎች ከሱፐርቫይዘራቸው ጋር አልተወያዩም::

የአራተኛው ዙር ፕራክቲከም ለማስተማር ልምምድ ዝግጅት የሚደረግበት በመሆኑ ከየትኛውም ዙር በተለየ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል:: ስለዚህ ባዘጋጁት የትምህርት ዕቅድ ላይ በመወያየት እርምት መስጠት በቀጣይነት ለሚያደርጉት የማስተማር ልምምድ በእጅጉ ይረዳቸዋል:: ይሁን እንጂ ከሠንጠረዡ እንደሚታየው 46.4 ከመቶ የሚሆኑት የተማሪ አስተማሪዎች የአራተኛውን ዙር ፕራክቲከም በተመለከተ ከሱፐርቫይዘሮቻቸው ጋር ያልተወያዩ

ናቸው:: 41.8 ከመቶ የሚሆኑት ግን እንደተወያዩ ይገልፃሉ:: ቀሪዎቹ 10.9 ከመቶ ያህል መላሾች ግን መወያየት አለመወያየታቸውን ለይተው ለመግለጽ ተቸግረዋል::

### 4.3.1.2.1 ነባር መምህራን በፕራክቲከም ትግበራ

ለፕራክቲከም ወደ ተባባሪ ት/ቤቶች የሚወጡ የተማሪ አስተማሪዎች በተቻለ መጠን የት/ቤቶቹ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ተሳታፊዎች መሆን ይጠበቅባቸዋል:: ተሳትፎአቸው የተሳካ ይሆን ዘንድ ነባር መምህራን የሚያደርጉላቸው እገዛ ወሳኝነት ይኖረዋል:: በዚህ መሰረት ነባር መምህራን በፕራክቲከሙ ወቅት የነበራቸው አስተዋጽኦ ምን ይመስል እንደነበር የተማሪ አስተማሪዎቹ ከያዙት ማስታወሻ ለናሙናነት እንይ::

> ለፕራክቲከም ተግባር በወጣን ቁጥር የምናገኛቸው ተማሪዎችንና ነባር መምህራንን መሆኑ ይታወቃል:: ይህም የተለያዩ እርዳታዎችን ከመምህሩ ለመጠየቅ ምቹ ሁኔታ ፈጥሮልን እንጠይቃለን፤ እነሱም ይተባበሩናል::
>
> ነባር መምህሯ በጣም ነው የረዳችኝ:: ገለፃ በማድረግም ሆነ የሚያስፈልጉኝን ማቴሪያሎች በማሳየት በጣም ረድታኛለች::
>
> እኔ የገባሁበት ክፍል መምህርት ራሷ ምን ልረዳሽ በማለት የእረፍት ሰዓቷን ሳይቀር መስዋዕት በማድረግ ረድታኛለች:: ለኔ ሊጠቅመኝ የሚችለውን ነገር ሁሉ በሚገባ ገልፃልኛለች::
>
> የክፍል መምህሯ ለወደፊት ምን ማድረግ እንዳለብኝ መክራኛለች:: በማስተማር ልምምድ ጊዜ እንዳልቸገርና እንዳልፈራ በፕራክቲከም ወቅት አንድ ክፍለ ጊዜ እንዳስተምር አድርጋኛለች::

ከተማሪዎቹ ማስታወሻ መረዳት እንደሚቻለው ብዙዎቹ ነባር መምህራን በአራቱም ዙር ፕራክቲከም በሚገባ እንደረዷቸው ነው:: ይሁን እንጂ አንዳንድ ነባር መምህራን ምንም ዓይነት እርዳታ ሳያደርጉላቸው እንደቀሩ ገልፀዋል:: ለምሳሌ

> ወደ ክፍል መጀመሪያ ስገባ ጥሩ አቀባበል አድርገውልኛል:: ገብቼ ከተቀመጥኩ በኋላ ግን ምንም ዓይነት እገዛ አላደረጉልኝም::
>
> የክፍል መምህሯ እንኳንስ እኔን ልትረዳኝ ይቅርና የሆነ ነገር ላደርግ የመጣሁ ስለመሰላቸው በጣም የመንቀጥቀጥና ግራ የመጋባት መንፈስ ይታይባቸው ነበር::
>
> የክፍል መምህሩ እኔ ከመጠየቁ በፊት ምን እንደሚያስፈልገኝ በመረዳት ሊያግዙኝ ሲገባ ሊረዱኝ ፈቃደኛ አልነበሩም::

መደበኛ ወይም ነባር መምህራን የተማሪ አስተማሪዎችን ለመርዳት የነበራቸውን ፍላጎት ለማወቅ ለተማሪ አስተማሪዎች ጥያቄ ቀርቦላቸው የሰጡት መልስ የሚከተለውን ይመስላል::

## ሠንጠረዥ አስራ ሰባት

### የመደበኛ /ነባር/ መምህራን ፈቃደኛነት

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 16 | የት/ቤቱ መደበኛ መምህራን እኔን ለመርዳት ፈቃደኛ አልነበሩም:: | 35<br>29.1% | | 15<br>13.6% | 63<br>57.3% | | |

ከላይ ከሠንጠረዡ እንደሚታየው ምንም እንኳን ለአሉታዊ ጥያቄው የተሰጠው ምላሽ 29.1 ከመቶ ሆኖ ከላይ የቀረበውን ሐሳብ የሚያጠናክር ቢሆንም 57.3 ከመቶ የሚሆኑት የተማሪ አስተማሪዎች ነባር መምህራን በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ እገዛ አድርገውላቸዋል::

የዚህ ጥናት አቅራቢ የተወሰኑ ነባር መምህራንን ባነጋገረበት ወቅት እንደተረዳው 29.1 ከመቶ የሚሆኑት የተማሪ አስተማሪዎችን ለመርዳት ያልቻሉት ከግንዛቤ እጥረት መሆኑን ነው:: ፕሮግራሙ አዲስ በመሆኑና ምንም ዓይነት ስልጠናም ሆነ ገለፃ ስላልተደረገላቸው በተፈለገው መንገድ ሊደግፏቸው አለመቻላቸውን ሲገልጹ ተደምጠዋል::

### 4.3.1.2.2. የኘራክቲከምና የማስተማር ልምምድ ተደጋጋፊነት

በአሁኑ ወቅት መምህራንን በማሰልጠን ሂደት ፕራክቲከም፣ የማስተማር ልምምድና ሱፐርቪዥን ሊነጣጠሉ የማይገባቸው መሆናቸው ግልፅ ነው:: እርግጥ ነው መምህራንን ለማሰልጠን ሲታሰብ ንድፈ ሐሳባዊ መሠረትን መነሻ ማድረግ የግድ ይሆናል:: ይሁን እንጂ ንድፈ ሐሳብ ብቻውን አንድ ጥሩ መምህርን ሊፈጥር አይችልም:: በሀገራችንም ንድፈ ሐሳብን፣ ፕራክቲከምን የማስተማር ልምምድንና ሱፐርቭዥንን አሰናስሎ የሰመረ ግንኙነት እንዲኖራቸው በማድረግ መምህራንን የማሰልጠኑ እንቅስቃሴ ከተጀመረ ሁለተኛ ዓመቱን ይዟል:: በተለይም የፕራክቲከሙንና የማስተማር ልምምዱን ዝምድና ለመቃኘት ተሞክሯል:: በዚሁ መሠረት ለተማሪ አስተማሪዎቹ የሚከተለው ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር:: የሰጡት ምላሽ የሚከተለውን ይመስላል::

## ሠንጠረዥ አስራ ስምንት

### የፕራክቲከምና የማስተማር ልምምድ ተደጋጋፊነት

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 30 | ኘራክቲከሙና የማስተማር ልምምድ ደተጋጋፊዎች በመሆናቸው ጠቀሜታቸው የጎላ ነው:: | | 100<br>90.9% | 6<br>5.5% | 4<br>3.6% | | - |

በሠንጠረዡ ላይ እንደሚታየው የፕራክቲከም ምልከታና የማስተማር ልምምድ በጣም ተደጋጋፊዎች ናቸው፡፡ ቀደም ሲል በነበረው የመምህራን አሰለጣጠን ሂደት የማስተማር ልምምዱ ይካሄድ የነበረው ስልጠናው መጠናቀቂያ ላይ እንደነበር ይታወሳል፡፡ በአጠቃላይ በስልጠናው ለንድፈ ሐሳብ ትምህርት እንጂ ለማስተማር ልምምዱ ብዙም ትኩረት አይሰጠውም ነበር፡፡ በአዲሱ የመምህራን አሰለጣጠን የነበረውን ችግር ይቃለላል በሚል ሀሳብ ስልጠናው ሙሉ በሙሉ በፕራክቲከም (የት/ቤት ልምድ) ላይ እንዲመሰረት ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሠረት እየተከናወነ ያለውን የሰርተፍኬት (10+1) መምህራን ስልጠና ለመፈተሽ በተደረገው ጥረት የተማሪ አስተማሪዎቹ ከያዙት ማስታወሻ ከፕራክቲከሙ በቂ ግንዛቤ እንዳገኙ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለናሙናነት የተወሰኑትን ማስታወሻዎች እንመልከት፡፡

> . . . አንድ መምህር ተመርቆ ወደ ሥራ ዓለም ከመግባቱ በፊት ማስተማር ምን ይመስላል የሚለውን ጥያቄ በዚህ ፕሮግራም ያየዋል፡፡ ወደ ሥራ ሲገባ አዲስ ስለማይሆንበት ፕራክቲከም ጥሩ ፕሮግራም ነው፡፡
>
> ፕራክቲከሙ ብዙ ነገሮችን እንድናጠናና እንድንተዋወቅ አድርጎናል፡፡ ፕራክቲከም በወጣንበት ጊዜ ሁሉ ነባር መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት በማየታችን ለማስተማር ልምምድ ስንወጣ በሚገባ እንድናስተምርና ከተማሪዎቻችን ጋር በስርዓት እንድንግባባ አድርጎናል፡፡
>
> ፕራክቲከሙ ለማስተማር ልምምድ ከመውጣታችን በፊት የሚከናወን ተግባር ስለሆነ ብዙ ነገር ያስተምራል፡፡ ስለማስተማር ሥራ ምንነት በሚገባ ለማወቅም ይረዳል፡፡
>
> ፕራክቲከሙ በጣም ጥሩና ለማስተማር ልምምዱ በር መክፈቻ ወይም መለማመጃ ነው፡፡ የተማሪዎችን ባህሪ፣ የት/ቤትን አደረጃጀት፣ የክፍል ቁጥጥርን፣የመርጃ መሣሪያ አጠቃቀምንና የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችን ሁሉ ለማወቅ ያስችላል፡፡

ከተማሪ አስተማሪዎቹ ዕለታዊ ማስታወሻ እንደምንረዳው በመምህራን ስልጠና ፕራክቲከም ላቅ ያለ አስተዋጽኦ እንዳለው ነው፡፡ በመጀመሪያ በክፍል ውስጥ የቀሰሙትን ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀት መነሻ በማድረግ የሚያከናውኑት የፕራክቲከም ምልከታ ከሚጠብቁት በላይ ከመምህርነት ሙያ ጋር አስተዋውቋቸዋል፡፡ ይህንንም በማስታወሻቸው እንደሚከተለው አስፍረውታል፡፡

> በፕራክቲከም ምልከታዬ ወቅት ተማሪዎችን እንዴት መቆጣጠርና ማነቃቃት እንደሚቻል ተገንዝቤያለሁ፡፡
>
> ሕፃናትን ለማስተማር ምን ዓይነት ዘዴ መጠቀም እንዳለብኝና ተማሪዎችን በምን ዓይነት ማቅረብ እንዳለብኝ ተገንዝቤያለሁ፡፡
>
> በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚሰቃቀሉ የተለያዩ መርጃ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት እንደሚቻል አይቻለሁ፡፡

ዕጩ መምህራን እንደመሆናችን መጠን ወደፊት ሊገጥሙን የሚችሉ ነገሮችን ሁሉ እንድናውቅ ረድቶናል፡፡

የመምህርነት ሥራ በጣም ትዕግስትንና መስዋዕትን የሚጠይቅ እንደሆነ ተረድቻለሁ፡፡

ስለዚህ ከፕራክቲከም ይህን ያህል ዕውቀት ማግኘት የሚቻል ከሆነና የማስተማር ልምምዱን በጥሩ ሁኔታ ለማከናወን መሠረት ከሆነ ያሉበትን ችግሮች በመንቀስ በአግባቡ ማከናወን ተገቢ ይሆናል፡፡

#### 4.3.1.2.3. የተማሪ አስተማሪዎችና ሱፐርቫይዘሮች ስለፕራክቲከም ያላቸው አስተያየት

ፕራክቲም የተማሪ አስተማሪዎች በመምህርነት ሙያ ስልጥነው በመመረቅ ወደ ክፍል በመግባት በማስተማር ሥራ ላይ ከመሠማራታቸው በፊት የአንድን ት/ቤት አደረጃጀት፣ የመማር ማስተማር ሂደት፣ የመምህራንና ተማሪዎች ግንኙነት፣ የመደበኛ ተማሪዎች ባህሪያት፣ የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት ምን እንደሚመስል ምልከታ የሚያደርጉበት ፕሮግራም ነው፡፡

በምልከታው ወቅት የቀሰሙትን ንድፈ ሐሳብ መነሻ በማድረግ ሕፃናት በክፍል ውስጥ እንዴት እየተማሩ እንደሆነ ያጠናሉ፣ ሕፃናትን በማስተማር ረገድ የት/ቤቶችንና የወላጆችን ሚና ሁሉ ይመለከታሉ፡፡ የተጓደኝ ክበባትን እንቅስቃሴም ይቃኛሉ፡፡ በመጨረሻም የተመደቡበትን ት/ቤት ስርዓተ ትምህርት መነሻ በማድረግ በተገቢው ርዕስ የትምህርት ዕቅድ ያዘጋጃሉ፡፡ የሁሉንም ሕፃናት የመማር ልምድ ወይም ስልት ለመመርመር ይሞክራሉ፡፡ ይህን ሁሉ እንቅስቃሴ የማከናወናቸው ፋይዳ በአንድ ትምህርት ቤት የመማሪያ ክፍል መቼት ውስጥ ትክክለኛውን የመማር ማስተማር መርህ ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ አጋጣሚውን ለመፍጠር ነው፡፡

ከላይ በቀረበው ሐሳብ መነሻነት የተማሪ አስተማሪዎች እውን ከፕራክቲከሙ ኃላፊነታቸውን፣ ያላቸውን ችሎታና ልምድ ለማሻሻል መቻላቸውንና በአጠቃላይ ፕራክቲከሙን በተመለከተ መግለጽ የሚፈልጉት ነገር እንዳለ በማለት በክፍት ቀርቦላቸው ለነበረው ጥያቄ ተከታዩን ምላሽ በጽሁፍ አስፍረዋል፡፡

> ከፕራክቲከሙ ብዙ ልምድ የቀሰምኩ ስለሆነ በጣም አስደስቶኛል፡፡
>
> ስለፕራክቲከም ያለኝ አስተያየት ጥሩ ነው፡፡ ምክንያቱም ከፕራክቲከም በክፍል ውስጥ ከምንቀስመው ዕውቀት የበለጠ እናገኛለን፡፡ ለምሳሌ ነገሮችን በቅርብ ሆነን በስፋትና በጥልቀት እንድንገነዘብ ፣ ያየነውን በቃላት አቀነባብረን በጽሁፍ እንዲፅፍ

የፃፍነው በሱፐርቫይዘራችን ፊት እንድናቀርብ ወዘተ. ስለሚያደርገን ጥሩ ነው እላለሁ፡፡

ፕራክቲከሙ በጣም ጥሩ ዕውቀትን የገበየሁበት በክፍል ከሚነገረኝ ይልቅ በተግባር ያየሁበት ልምምድ ነው፡፡ የተማሪዎችን ፀባይ በአግባቡ ለማወቅም ረድቶኛል፡፡

ፕራክቲከም የተመለከትነውን ነገር በጽሁፍ መግለጽ እንድንችል አድርጎናል፡፡

ፕራክቲከም ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አለው፡፡ ምክንያቱም የተማሪዎችን ባህሪ እንድናውቅ ረድቶናል፡፡

ከላይ በተማሪ አስተማሪዎች የተሰጡትን መልሶች ስንመረምር ፕራክቲከም እጅግ ጠቃሚ ፕሮግራም መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይሁን እንጂ በአተገባበር ላይ ችግር የሚታይበት ነው፡፡ ይህንንም ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ቀጣዩን ይመለከታል፡፡

እኔ ለመግለጽ የምፈልገው ስለ ድህረ ፕራክቲከም ውይይት ማድረጊያ ጊዜ ነው፡፡ የመጀመሪያውን ዙር ፕራክቲከም ምልከታ ሪፖርት ጽፈን እንዳቀረብን ሳንወያይ የቀጣዩን ዙር ተግባር ሰርተን እናስረክባለን፡፡ ከዚህ በኋላ የበፊቱን ሪፖርት በሚመለከት ለሱፐርቫይዘራችን በቃል እንድናስረዳ እንጠይቃለን፡፡ በዚህን ጊዜ የበፊቱን ለማስታወስ እንቸገራለን፡፡ ይህ ደግሞ በውጤታችን ላይ ችግር ማስከተሉ አይቀሬ ይሆናል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ስለፕራክቲከም በቂ የሆነ ገለፃ ቢደረግልን መልካም ይመስለኛል፡፡

ለምንመደብባቸው ት/ቤቶች ማህበረሰብ በሙሉ ስለፕራክቲከሙ በቂ የሆነ ግንዛቤ እንዲያገኙ ቢደረግ መልካም ነው፡፡

ኮሌጁ ባዘጋጀው የፕራክቲከም መመሪያ ውስጥ አንዳንድ ከርዕሱ ጋር የማይሄዱና የተማሪ አስተማሪዎችን ግራ የሚያጋቡ ጥያቄዎች ነበሩ፡፡ እነዚህን ጥያቄዎች የተመደቡልን ሱፐርቫይዘሮች በአካል እየተገኙ ቢያስረዱን መልካም ይሆናል፡፡

ኮሌጁና ተባባሪ ት/ቤቶች ስለ እኛ ጉዳይ ቢነጋገሩ ጥሩ ነው፡፡ ምክንያቱም እዚያ ሄደን ከየት መጣችሁ? እነማናችሁ? እየተባልን ከምንሰቃይ ኮሌጁ ስለኛ ወደ ት/ቤታቸው መመደብ ቢያሳውቅ ጥሩ ነው፡፡

በተማሪ አስተማሪዎች የተሰጡት እነዚህ መልሶች እንደሚጠቁሙት ምንም እንኳን የፕራክቲከም ጥቅም ላቅ ያለ ቢሆንም የተፈለገው ውጤት ላይ እንዳይደርስ ሲያስተጓጉላቸው የነበሩ ችግሮች መኖራቸውን ነው፡፡

ፕራክቲከሙን በሚመለከት አስተያየታቸውን በጽሁፍ እንዲገልፁ የተደረጉት የተማሪ አስተማሪዎች ብቻ አይደሉም። ፕራክቲከሙን ሲከታተሉ ለነበሩ ሱፐርቫየዘሮችም ዕድሉ ተሰጥቷቸው ሐሳባቸውን እንደሚከተለው አስፍረዋል።

> ስለ ፕራክቲከም አፈፃፀም ለሱፐርቫይዘሮች ገለፃ ቢደረግላቸው ለአንድ ሱፐርቫይዘር በርካታ የተማሪ አስተማሪዎች ባይመደቡ ፕራክቲከሙን በጥልቀት ለመገምገም ይቻላል።
>
> በፕራክቲከሙ የሚካተቱ ጥያቄዎች በየዓመቱ አንድ አይነት ባይሆኑ ተመራጭነት ይኖረዋል።
>
> የፕራክቲከም ሥራ ግምገማ መቶ በመቶ ለተባባሪ ት/ቤቶች መደበኛ መምህራን ቢሰጥ ጥሩ ነበር።

ሱፐርቫይዘሮቹ ከሰጡት አስተያየትም ለመገንዘብ እንደሚቻለው የተማሪ አስተማሪዎች በፕራክቲከም ወቅት የሚያጋጥሟቸው ችግሮች በአብዛኛው አስተዳደራዊ ሆነው እናገኛቸዋለን። ምክንያቱም ኮሌጁ የፕራክቲከሙን አፈፃፀም በሚመለከት ለሱፐርቫይዘሮች ካለመግለጽ ጀምሮ የሥራ ጫናን ባለማገናዘብ ለአንድ ሱፐርቫይዘር እስከ 20 የሚደርሱ የተማሪ አስተማሪዎችን ይመድባል። ይህ ደግሞ የእያንዳንዱን የተማሪ አስተማሪ እንቅስቃሴ ለመከታተልና የሁሉንም የጽሁፍ ሪፖርት አንብቦ አስተያየት ለመስጠት አስቸጋሪ እንዲሆን ሊያደርገው እንደቻለ መገመት ይቻላል።

በአጠቃላይ የፕራክቲከም አተገባበሩን ስንቃኝ ተገቢ የሆነ ክትትል የማይደረግለት መስሎ ይሰማናል። ስለዚህ ፕራክቲከም የመምህራን ስልጠና መሠረታዊ አላባ ነው ከተባለ በአተገባበሩ ሂደት ታዩ ለተባሉ ችግሮች መፍትሔ መሻት ያስፈልጋል።

### 4.3.2 የማስተማር ልምምድ ሂደትና አተገባበር

ዓለም (1988፣14) እንደገለፀው የማስተማር ልምምድ በመምህራን አሰለጣጠን ሂደት አብይ ተተኳሪ ጉዳይ በመሆኑ የተማሪ አስተማሪዎች ለልምምድ ከተመደቡበት ት/ቤት መምህራን፣ ከአሰልጣኞች፣ ከሱፐርቫይዘሮችና ከክፍል ጓደኞቻቸው ድጋፍና እርዳታ ማግኘት ይኖርባቸዋል። ይህ በአንድ የመማሪያ ክፍል አውድ ውስጥ በሱፐርቫይዘሮች እየተጎበኙ ወይም እየተገመገሙ የሚያከናውኑት ተግባር የተማሪ አስተማሪዎች ሁለንተናዊ ስብዕናቸውንና ብቃታቸውን በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ አለው (Tann 1994:94)። ስለዚህ ሂደቱና አተገባበሩ የተቀጣለት ሊሆን ግድ ነው። በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ያለውን የማስተማር ልምምድ ሂደትና አተገባበር እንደሚከተለው ለመፈተሽ ጥረት ተደርጓል።

ምንም እንኳን በአሁኑ ወቅት የማስተማር ልምምድ አንዱ የፕራክቲከም ክፍል እንደሆነ ተደርጎ ቢቆጠርም ሂደቱን ለመመልከት ይቻል ዘንድ ለብቻው ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

የማስተማር ልምምዱ የተሳካ እንዲሆን ካስፈለገ ሂደቱ የተቀዋጣለት መሆን ይጠበቅበታል። በዚሁ መሠረት በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሰርተፍኬት መምህራን አሰለጣጠን ሂደት በምን ዓይነት መንገድ እየተከናወነ እንደሆነ ለመፈተሽ ሙከራ ተደርጓል።

የማስተማር ልምምዱ ንድፈ ሃሳባዊ መሠረት ሊኖረው እንደሚገባ ግልጽ ነው። ለዚህም ሲባል ከተማሪ አስተማሪዎች መረጃ ለማግኘት የሚከተለው ጥያቄ ቀርቦ የተገኘው ምላሽ ይህንን ይመስላል።

## ሠንጠረዥ አስራ ዘጠኝ

### በኮሌጁ የቀሰሙት የንድፈ ሐሳብ ትምህርት ለማስተማር ልምምዱ የነበረው ፋይዳ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 34 | በክፍል ውስጥ የቀሰምኩት ንድፈ ሐሳብ የማስተማር ልምምዱን ለማከናወን ረድቶኛል። | 90<br>81.8% | | 11<br>9.9% | 8<br>7.3% | | 1<br>0.9% |

ከሠንጠረዡ እንደሚታየው 81.8 ከመቶ የሚሆኑት የተማሪ አስተማሪዎች የማስተማር ልምምዱን በአግባቡ ለማከናወን የረዳቸው በኮሌጁ የቀሰሙት ንድፈ ሐሳባዊ እውቀት ነው። ቀደም ብለን በተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ንድፈ ሐሳብ፣ ፕራክቲከም፣ የማስተማር ልምምድና ስትርቪዥን የጠበቀ ዝምድና እንዳላቸው ያነሳነውን ሐሳብ ሙሉ በሙሉ ያጠናክረዋል። ምክንያቱም በማስተማር ልምምድ የሚደረገው እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ንድፈ ሐሳብን ከተግባር የማዛመድ ጥረት ነው። በእርግጥ Fish (1989) እንደሚገልጹት ንድፈ ሐሳብን ከተግባር የማዛመጃ የተለያዩ ሞዴሎች ቢኖሩን እንደ አስፈላጊነቱ አመቺ የሆነውን መርጦ መጠቀም ይቻላል። ከሞዴሎቹ ውስጥ ንድፈ ሐሳብና ተግባር ሊነጣጠሉ የማይችሉ መሆናቸውን የሚያሳየው አዛማጅ ሞዴል (The relationist model) ነው። ስለዚህ ያለ በቂ ንድፈ ሐሳብ ዕውቀት የማስተማር ልምምድ ውጤታማ ሊሆን አይችልም ማለት ነው።

ሌላው ለማስተማር ልምምዱ ውጤታማነት ትልቅ ድርሻ አለው ተብሎ የሚገመተው የፕራክቲከም ምልከታ የነበረውን አስተዋጽኦ ለማወቅ ለተማሪ አስተማሪዎች የቀረበላቸው ጥያቄ የሚከተለው ነበር።

## ሠንጠረዥ ሃያ

### ለማስተማር ልምምድ መሳካት የፕራክቲከም ምልከታ ያለው ፋይዳ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 31 | በፕራክቲከም ወቅት ያደረኩት ምልከታ የማስተማር ልምምድ በማደርግበት ጊዜ ምንም እገዛ አላደረገልኝም:: | 24<br>21.8% | | 13<br>11.8% | 73<br>66.4% | | - |

ከሠንጠረዡ መገንዘብ እንደሚቻለው የጥያቄው አቀራረብ አሉታዊ ቢሆንም 66.4 ከመቶው መላሾች በአሉታ መልስ ሰጥተዋል:: ይህም ማለት የፕራክቲከም ምልከታቸው የማስተማር ልምምዱን ሳይቸገሩ ለማከናወን ረድቷቸዋል ማለት ነው:: የማስተማር ልምምዱን በቀላሉ ለማካሄድ እገዛ አላደረገልንም በማለት የመለሱ 21.8 ከመቶ ሲሆን ቀሪዎቹ 11.8 ከመቶ ያህሉ ደግሞ ለመወሰን የተቸገሩ ናቸው::

### 4.3.2.1 ቅድመ ማስተማር ልምምድ ውይይት

ቅድመ ማስተማር ልምምድ ውይይት የተማሪ አስተማሪዎች ለማስተማር ልምምድ ወደ ተባባሪ ት/ቤቶች ከመሄዳቸው በፊት በሚሰለጥኑበት ተቋም ከተመደበላቸው ሱፐርቫይዘር ጋር ተገናኝተው የሚያደርጉት ውይይት ነው:: በዚህ ውይይት የተማሪ አስተማሪዎች ወደተመደቡበት ት/ቤት ሄደው ምን ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ይገልጽላቸዋል:: የመገምገሚያ መስፈርቶቹንም እንዲገነዘቡ ያደርጋል:: በዚህ መሠረት በቅድመ ማስተማር ልምምድ የግዴታ ተገናኝተው መወያየት ይጠበቅባቸዋል:: ይህን ሐሳብ መነሻ በማድረግ ለተማሪ አስተማሪዎቹ በማስተማር ልምምድ ሂደት ሊያከናውኑ በሚገባቸው ነጥቦች ዙሪያ ከሱፐርቫይዘሮቻቸው ጋር ተወያይተው እንደሆነ በማለት ከዚህ የሚከተለው ጥያቄ ቀርቦላቸው በሠንጠረዡ ላይ የተመለከተውን ምላሽ ሰጥተዋል::

## ሠንጠረዥ ሃያ አንድ

### ቅድመ ማስተማር ልምምድ ውይይት

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 29 | ለማስተማር ልምምድ ወደ የተመደብንበት ት/ቤት ከመሄዳችን በፊት ከሱፐርቫይዘሮቻችን ጋር ተገናኝተን አልተወያየንም:: | 105<br>95.5% | | 1<br>0.9% | 3<br>2.7% | | 1<br>0.9% |

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው ቅድመ ማስተማር ውይይት ከሱፐርቫይዘሮቻቸው ጋር አለማድረጋቸውን የሚገልፁት 95.5 ከመቶ የሚሆኑት የተማሪ አስተማሪዎች ናቸው:: 2.7

ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ ውይይቱን ያደረጉ መሆናቸውን ይገልፃሉ፡፡በተመሳሳይ ሁኔታ ሱፐርቫይዘሮቹም ተጠይቀው የሰጡት መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

## ሠንጠረዥ ሃያ ሁለት
## ቅድመ ማስተማር ልምምድ ገለጻ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | የተማሪ አስተማሪዎች ለፕራክቲከምና ለማስተማር ልምምድ ከመውጣታቸው በፊት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ገለፃ አድርጌላቸዋለሁ፡፡ | 16 | | 1 | 3 | | - |

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው ለተማሪ አስተማሪዎቻቸው ቅድመ ማስተማር ገለጻ አላደረግንም ያሉት 3 ሱፐርቫይዘሮች ሲሆኑ 16 የሚሆኑት ግን ለተማሪ አስተማሪዎቹ ቅድመ ማስተማር ልምምድ ገለጻ ማካሄዳቸውን ገልጸዋል፡፡

እዚህ ላይ ሱፐርቫይዘሮቹ በእርግጥም ቅድመ ማስተማር ልምምድ ከተማሪ አስተማሪዎቹ ጋር ውይይት አድርገው ቢሆን ኖሮ ይህን ያህል የተለያየ መልስ ባልታየ ነበር፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢ ከተማሪ አስተማሪዎቹ ጋር ጉዳዩን ለማጣራት ባደረገው ቃለ ምልልስ ለመረዳት እንደቻለው ምንም ዓይነት ቅድመ ማስተማር ልምምድ ውይይት ያልተከናወነ መሆኑን ነው፡፡

ይህ የቅድመ ማስተማር ልምምድ ውይይት አለመካሄድ ደግሞ የክፍል ምልከታው ሊያተኩር የሚችልባቸውን ነጥቦች ባለመገንዘብ የተማሪ አስተማሪዎች አላስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩሩ በር ይከፍታል፡፡ ሱፐርቫይዘሮችም ቢሆኑ የሱፐርቪዥኑን ግልጽ የሆነ ዓላማ ቸል በማለት የተማሪ አስተማሪዎችን ከመደገፍና ከማበረታታት ይልቅ መገምገምና መመዘን ይቀናቸዋል፡፡ ግምገማና ምዘናቸውንም ቢሆን በእቅድና በፕሮግራም ለማከናወን ይቸገራሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በማያያዝ ሱፐርቫይዘሮች በቅድመ ማስተማር ውይይት ወደ ተባባሪ ት/ቤቶች በመሔድ የሚገናኙበትን ጊዜ ለተማሪ አስተማሪዎች ያሳውቁ እንደነበር ለማወቅ ቀርቦላቸው ለነበረው ዝግ የጽሁፍ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

## ሠንጠረዥ ሃያ ሦስት

### ሱፐርቫይዘሮች የሚጎበኙበትን ጊዜ ስለማሳወቃቸው

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | የማስተማር ልምምዱን ለመጎብኘት እመጣበት የነበረውን ጊዜ ለተማሪ አስተማሪዎች በቅድሚያ አላሳውቅም:: | 14 | | 1 | 5 | | - |

ከላይ ለቀረበው አሉታዊ ጥያቄ 14 የሚሆኑት ሱፐርቫይዘሮች የሰጡት መልስ አዎንታዊ ነው:: ይህም ሱፐርቫይዘሮች ያለ ዕቅድና ፕሮግራም ድንገተኛ የሆነ ጉብኝት ያደርጋሉ ማለት ነው:: አምስቱ ግን ለጉብኝት ሊመጡ የሚችሉበትን ቀንና ሰዓት ለተማሪ አስተማሪዎቹ በማሳወቅ የሚገመግሙ መሆናቸውን ገልፀዋል:: በድንገት የሚደረግ ጉብኝት በተማሪ አስተማሪዎቹ ላይ ሊፈጥር የሚችለው ጫና ቀላል አይደለም:: ሱፐርቪዥኑን በሚመለከት የተማሪ አስተማሪዎች የያዙት ማስታወሻም ይህንኑ ነው የሚያረጋግጠው::

> በማስተማር ላይ ሳለሁ ድንገት ሱፐርቫይዘሬ በመምጣታቸው ከመደንገጤ የተነሳ ማስተማር አቅቶኝ ነበር:: በተለይ የዕለቱን የትምህርት ዕቅድ መግለጫ ይዤ ባለመግባቴ ሄጄ እንዳመጣ ብጠይቃቸው ዝም ብለሽ አስተምሪ ሲሉኝ በጣም ደነገጥኩ::
>
> ሱፐርቫይዘሬ በፕሮግራም እና በእቅድ መቼ እንደሚመጡ ቢገልጹልኝ ኖሮ የአማርኛ ቋንቋን እያስተማርኩ ወደ ክፍል ሲገቡ የድንጋጤ ስሜት አይሰማኝም ነበር::
>
> በፕራክቲከምም ሆነ በማስተማር ልምምድ ወቅት ልንገመገም የምንችልበት መስፈርትና የምንጎበኝበትን ጊዜ በቅድሚያ ቢገለጽልን ጥሩ ነበር:: ምክንያቱም ራሳችንን አዘጋጅተን ለመገኘት ይጠቅመናልና::

ይህ ሁሉ መረጃ የሚያመለክተው የሱፐርቫይዘሮችን ድንገተኛ ግምገማና ሱፐርቪዥኑ አንድ ወጥ የሆነ የአተገባበር ስልት እንደሌለው ነው:: ምክንያቱም ሱፐርቫይዘሮች የሱፐርቪዥኑን ዓላማ ወደጎን በመተው የተማሪ አስተማሪዎችን ከመደገፍና ከማበረታታት ይልቅ መገምገምና መመዘን የሚቀናቸው ከዚሁ ኢስርዓታዊ የሱፐርቪዥን አተገባበር በመነጨ ነው::

ለተማሪ አስተማሪዎች ቀርቦ ከነበረው ምላሽም የምንረዳው ይህንኑ ነው% ሱፐርቫይዘሮች እንደ አመቻቸው ድንገት ጎራ እያሉ የማስተማር ልምምዱን ይከታተሉ እንደነበር:: የሰጡት መልስ የሚከተለውን ይመስላል::

## ሠንጠረዥ ሃያ አራት

### ሱፐርቫይዘሮች የጉብኝት ጊዜን ስለማሳወቃቸው

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 38 | ሱፐርቫይዘሬ ሊጎበኘኝ እንደሚመጣ በቅድሚያ ያሳውቀኛል:: | 50<br>45.5% | | 7<br>6.4% | 51<br>46.4% | | 2<br>1.8% |

በሠንጠረዡ ላይ እንደሚታየው 45.5 ከመቶ የሚሆኑ መላሾች ሱፐርቫይዘሮቻቸው መቼ ሊጎበኟቸው እንደሚመጡ ይገለጹልናል ሲሉ 46.4 ከመቶ የሚትን ደግሞ በድንገት እየመጡ እንደሚገመግሟቸው ገልፀዋል:: 6.4 ከመቶው ቁርጠኛ ምላሽ ለመስጠት የተቸገሩ ሲሆን 1.8 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ ለጥያቄው መልስ ከመስጠት ይልቅ ማለፍን መርጠዋል:: የተገኘውን መረጃ ስንመረምር ልንደርስ የምንችለው አብዛኞቹ ሱፐርቫይዘሮች እንዳመቻቸው ድንገተኛ ግምገማ የሚያደርጉ መሆናቸውን ነው::

የዚህ ጥናት አቅራቢ ሱፐርቫይዘሮች ለምን ይህን ዓይነት የመከታተያ መንገድ እንደመረጡ ለማጣራት ከተወሰኑ ሱፐርቫይዘሮች ጋር ባደረገው ቃለመጠይቅ ያገኘው መረጃ በዚህ ቀንና ሰዓት መጥተን እንገመግማችኋለን የማይሏቸው ሁልጊዜ ሲመጡ ይችላሉ በሚል ስጋት ተዘጋጅተው ሊያስተምሩ ይችላሉ ከሚል ሐሳብ በመነጨ እንደሆነ ይጠቁማል::

ከዚሁ ጋር በማያያዝ ሱፐርቫይዘሮች የሚጎነኙበትን ጊዜ አሳውቀውም ሆነ ሳያሳውቁ ወደ ተባባሪ ት/ቤት በመሔድ ያደርጉት የነበረውን ድጋፍ ለማወቅ ለተማሪ አስተማሪዎቹ ቀጣዩ ጥያቄ ቀርቦላቸው የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል::

## ሠንጠረዥ ሃያ አምስት

### የሱፐርቫይዘሮች ድጋፍ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 40 | ሱፐርቫይዘሬ የማስተማር ልምምድ ወደማደርግበት ት/ቤት የሚመጣው እኔን ለመደገፍና ለማረታታት ሳይሆን ለመገምገምና ለመመዘን ነበር:: | 61<br>55.5% | | 19<br>17.3% | 29<br>26.4% | | 1<br>0.9% |

ከሠንጠረዡ ላይ እንደሚታየው በፐርሰንት 26.4 ከመቶ የሚሆኑት መላሾች ሱፐርቫይዘሮቻቸው እንደሚደግፏቸውና እንደሚያበረታቷቸው ሲገልፁ 17.3 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ ቁርጠኛ መልስ ለመስጠት የተቸገሩ ናቸው:: ከመላሾቹ 55.5 ከመቶ የሚሆኑት ግን ሱፐርቫይዘሮቻቸው ለማስተማር ልምምድ ወደተመደቡበት ት/ቤቶች የሚመጡት ገምግመው ውጤታቸውን ለሬጂስትራር ቢሮ ለማስተላለፍ ብቻ እንደሆነ ነው የገለጹት:: ይህንንም ለማድረግ

ቢሆን ወደ ተባባሪ ት/ቤቶች የሚሄዱት በኘሮግራምና በእቅድ እንዳልነበረ ለሱፐርቫይዘሮች ቀርቦ ለነበረው ዝግ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ያስረዳል፡፡

### 4.3.2.2 በማስተማር ልምምድ ሂደት የሱፐርቫይዘሮች ክትትል

ከኘራክቲከሙ ያገኙትን ዕውቀት መነሻ በማድረግ የማስተማር ልምምድ በሚያደርጉበት ጊዜ ከኮሌጁ የተመደቡ ሱፐርቫይዘሮችና መደበኛ መምህራን ከጎናቸው በመሆን መርዳት እንዳለባቸው MOE (2003) ይገልፃል፡፡

ይህንን ሐሳብ መነሻ በማድረግ ሱፐርቫይዘሮች በማስተማር ልምምዱ ወቅት ለተማሪ አስተማሪዎች ያደርጉት የነበረውን እርዳታ ለማወቅ ለተማሪ አስተማሪዎች ዝግ የጽሁፍ ጥያቄ ቀርቦላቸው የሰጡት ምላሽ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

## ሠንጠረዥ ሃያ ስድስት

## በማስተማር ልምምድ የሱፐርቫይዘሮች ክትትል

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 32 | በማስተማር ልምምድ ወቅት ሱፐርቫይዘሬ በዕቅድና በኘሮግራም እየተመራ ለ3 ጊዜ ጎብኝቶኛል፡፡ | 90<br>34.5% | | 11<br>11.8% | 8<br>52.7% | | 1<br>0.9% |

ከሠንጠረዡ እንደምንረዳው 34.5 ከመቶ የሚሆኑ መላሾች በሱፐርቫይዘሮቻቸው በእቅድና በፕሮግራም መጎብኘታቸውን ሲገልጹ 52.7 ከመቶ የሚሆኑት መላሾች ሱፐርቫይዘሮቻቸው በዕቅድና በፕሮግራም እንዳልተከታተሏቸው ገልፀዋል፡፡ከዚሁ ጋር በማያያዝ ለሱፐርቫይዘሮቹ ተከታዩ ጥያቄ ቀርቦላቸው የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል፡፡

## ሠንጠረዥ ሃያ ሰባት

## ሱፐርቫይዘሮች የማስተማር ልምምዱን በእቅድና በፕሮግራም ስለመከታተላቸው

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | በዕቅድና በኘሮግራም እየተመራሁ የእያንዳንዱን ተማሪ የማስተማር ልምምድ ለ3 ጊዜ ጎብኝቻለሁ፡፡ | 12 | | 2 | 5 | | |

በጥያቄ ተራ ቁጥር 5 ለቀረበው ጥያቄ 12 የሚሆኑ ሱፐርቫይዘሮች በስራቸው የተመደቡላቸውን የተማሪ አስተማሪዎች በዕቅድና በፕሮግራም እያንዳንዳቸውን ለሶስት ጊዜ

ያህል መትብኘታቸውን ገልፀዋል:: ሁለቱ ሱፐርቫይዘሮች ለመወሰን የተቸገሩ ሲሆን አምስቱ ግን የተማሪ አስተማሪዎቹን መልስ ይጋራሉ:: ምናልባት በሁለቱ ወገኖች የተሰጠው መልስ ሊለያይ የቻለው ሱፐርቫይዘሮች ተማሪዎቻቸው ወደተመደቡበት ት/ቤት ለሦስት ጊዜ ከመምጣታቸው ጋር አያይዘው ምላሽ በመስጠታቸው ሳይሆን አይቀርም:: ምክንያቱም የዚህ ጥናት አቅራቢ የማስተማር ልምምዱን ለመከታተል በተዘዋወረባቸው ት/ቤቶች ብዙዎቹ የተማሪ አስተማሪዎች በሱፐርቫይዘሮቻቸው ያልተጎበኙ መሆናቸውን አረጋግጧል:: የተማሪ አስተማሪዎቹ ማስታወሻም ይህንኑ ሐሳብ ይደግፋል::

> እኛ ያጋጠመን ሱፐርቫይዘር አይከታተለንም:: መጥቶም የጎበኘን አንድ ጊዜ ብቻ ነው:: አንድ ጊዜ ብቻ በክፍል ውስጥ ተገኝቶ ሲገመግመን ግርም ነው ያለን:: ለዚያውም ለ15 ደቂቃ ብቻ:: ሌላ ት/ቤት የተመደቡ ጓደኞቻችን ቢያንስ ሁለት ጊዜ ነው የተገመገሙት::
>
> እኔን በጣም ግርም ያለኝ ሱፐርቫይዘሬ አንድ ጊዜም መጥቶ ሳይገመግመኝ መቅረቱ ነው:: በኘራክቲከም ወቅት ብቅ ብሎ አላየኝም ነበር:: አሁንም የማስተማር ልምምድ ላይ ሳለሁ አላየኝም:: ታዲያ እንዴት ውጤት ይሰጠኝ ይሆን ብዬ በመጠበቅ ላይ ነኝ::
>
> የእኛ ሱፐርቫይዘር የመጡት በመጨረሻው የማስተማር ልምምድ ሳምንት በመሆኑ ስህተታችንን ቶሎ አውቀን ለማረም ሳያስችለን ቀርቷል::

የማስተማር ልምምዱን ሂደት ለመከታተል ወደ ተባባሪ ት/ቤቶች የሚወጡ ሱፐርቫይዘሮች በሳምንት አንድ ጊዜ ቢሆን ተመራጭነት እንዳለው ይታመናል:: ምክንያቱም የተማሪ አስተማሪዎች በቀጣዩ ሳምንት የነበረባቸውን ድክመት አርመውና አሻሽለው መምጣታቸውን ለማረጋገጥ የሚችሉት ቀደም ባለው ሳምንት የሰጧቸውን ምግበ መረጃ መነሻ አድርገው መሆን ይኖርበታል:: ይህን መሠረት በማድረግ ሱፐርቫይዘሮች በየሳምንቱ በተያዘው ዕቅድ የተማሪ አስተማሪዎችን ለመጎብኘት ሳይችሉ የቀሩበትን ምክንያት ለማወቅ የሚከተለው መጠይቅ ቀርቦላቸው ነበር::

## ሠንጠረዥ ሃያ ስምንት

## የሱፐርቫይዘሮች ተጨማሪ የስራ ጫና

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ያለብኝ የሥራ ጫና የኘራክቲከሙንና የማስተማር ልምምድ አተገባበሩን በአግባቡ ለመከታተል እንዳልችል አድርጎኛል:: | 15 | | 3 | 2 | | - |

በሠንጠረዡ ላይ መመልከት እንደሚቻለው አብዛኞቹ ሱፐርቫይዘሮች ያለባቸው ተጨማሪ የማስተማርና የቢሮ ሥራ የፕራክቲከሙንም ሆነ የማስተማር ልምምድ አተገባበሩን በአግባቡ ለመከታተል እንዳይችሉ እንቅፋት ፈጥሮባቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሱፐርቫይዘሮቹ የማስተማር ልምምዱን በተመለከተ ሌላ መግለጽ የሚፈልጉት ነገር ካለ በጽሁፍ እንዲያስረዱ ተጠይቀው የሰጡትን መልስ ስንቃኝ የሚከተለውን እናገኛለን፡፡

> የመምህራን የስራ ጫና ግምት ውስጥ ሳይገባ እስከ ሃያ የሚደርሱ የተማሪ አስተማሪዎችን ሰጥቶ በተለያየ ት/ቤት እየተዘዋወርክ ፕራክቲከሙንም ሆነ የማስተማር ልምምዱን ተከታተል ማለት ይከብዳል፡፡
>
> ካለብን ተጨማሪ የማስተማርና የቢሮ ሥራ አንፃር ፕራክቲከሙንም ሆነ የማስተማር ልምምዱን ለመከታተል አስቸጋሪ ብቻ ሳይሆን አይቻልም፡፡
>
> የሚመደብልን የተማሪ ቁጥር ከፍተኛ ነው፡፡ ስለዚህ ያለውን የሥራ ጫና ያላገናዘበ ስለሆነ ቢያንስ የተጨማሪ ሰዓት ክፍያ ሊኖረው ይገባል፡፡
>
> ፕራክቲከምም ሆነ የማስተማር ልምምድ አስፈላጊና ጠቃሚ መሆኑን አምንበታለሁ፡፡ ሆኖም የተማሪ አስተማሪዎች ብዛት ስለሚኖር በአሠራርና በአፈፃፀም ላይ አድካሚ ሥራ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡
>
> ለእያንዳንዱ ሱፐርቫይዘር የሚሰጠው የሥራ ጫና ቢቀንስና በሚያመቸው አካባቢ በሚገኙ ት/ቤቶች ቢመደብ አመቺ ይሆናል፡፡

ከሱፐርቫይዘሮቹ መልስ መረዳት እንደሚቻለው ከተጨማሪ ሥራው ሌላ የማስተማር ልምምድ አተገባበሩን እንዳይከታተሉ ችግር የፈጠሩባቸው ምክንያቶች የሚከታተሏቸው የተማሪ አስተማሪዎች ቁጥር መብዛትና የተባባሪ ት/ቤቶች ርቀት ናቸው፡፡

### 4.3.2.3. በማስተማር ልምምድ የመደበኛ መምህራን ክትትል

MOE (2003) ባዘጋጀው የTESO ፕሮግራም በመምህራን ስልጠና በኮሌጆች ከሚመደቡ ሱፐርቫይዘሮች ባልተናነሰ ሁኔታ የተባባሪ ት/ቤት መደበኛ መምህራን ጉልህ ድርሻ እንዳላቸው ይገልፃል፡፡ ስለዚህም እነዚህ የኮሌጅ ሱፐርቫይዘሮችና ነባር መምህራን ተባብረው ፕራክቲከሙንም ሆነ የማስተማር ልምምዱን በመከታተል አስፈላጊውን ምግበ መረጃ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ የተማሪ አስተማሪው ከሁለት አቅጣጫ ምግበ መረጃ እንዲያገኝ ያስችለዋል፡፡ ይህን ሐሳብ መነሻ በማድረግ በማስተማር ልምምዱ ወቅት የነባር መምህራን እገዛ ምን ይመስል እንደነበር ለማረጋገጥ ለተማሪ አስተማሪዎቹ ቀጣዩ ጥያቄ ቀርባላቸው ነበር፡፡

## ሠንጠረዥ ሃያ ዘጠኝ

### የተባባሪ ት/ቤት መደበኛ መምህራን እገዛ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 33 | በማስተማር ልምምድ ወቅት የተባባሪ ት/ቤት መምህራን እገዛ የጎላ ነበር:: | 79<br>71.8% | | 9<br>8.2% | 22<br>19.9% | | - |

በሠንጠረዡ ላይ እንደሚታየው 71.8 ከመቶ የሚሆኑት የተማሪ አስተማሪዎች ከተባባሪ ት/ቤት መደበኛ መምህራን ተገቢው እገዛ ተደርጎላቸዋል:: 19.9 ከመቶ የሚሆኑት ምንም ዓይነት እርዳታ እንዳልተደረገላቸው ገልፀዋል:: ቀሪዎቹ 8.2 ከመቶ ያህሉ ደግሞ የተባባሪ ት/ቤቱ ነባር መምህራን ያደረጉላቸውን እገዛ ቁርጥ አድርገው መግለጽ የተቸገሩ ናቸው:: ከላይ የቀረበውን መረጃ ስንመለከት በሁሉም ተባባሪ ት/ቤቶች የሚገኙ ነባር መምህራን ሁሉ ባይሆኑም አብዛኞቹ ለተማሪ አስተማሪዎቹ የተቻላቸውን ያህል ለመርዳት ጥረት እንዳደረጉ ነው::

ዓለም (1988፣52) እንደገለፀው በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ መምህራን አሰለጣጠን ሂደት የማስተማር ልምምዱን ይከታተሉት የነበሩት በኮሌጁ የሚመደቡ ሱፐርቫይዘሮች ብቻ በመሆናቸው የተባባሪው ት/ቤት መደበኛ መምህራን በማስተማር ልምምዱ አይሳተፉም ነበር:: ከዚህ አንፃር አሁን ጉልህ አስተዋጽኦ ማድረግ ጀምረዋል ለማለት ያስደፍራል:: እዚህ ላይ አንድ የተማሪ አስተማሪ ከያዘው ማስታወሻ የተገኘውን መረጃ ስንመለከት ደግሞ የነበረውን የመደበኛ መምህራን አስተዋጽኦ አጉልቶ የሚያሳይ ሆኖ እናገኘዋለን::

> ከኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሱፐርቫይዘሮች ይልቅ ለእኛ ጥሩ እገዛ ሊያደርጉልን የሚችሉት የየት/ቤቶቹ መደበኛ መምህራን ስለሆኑ እነሱ አብረው ቢሰሩ እና ማስተካከል ያለብንን ነገር እየተከታተሉ እንዲገለፁልን ቢደርግ መልካም ነው::

Pelletier (2000) እንደሚገልፁት ዕጩ መምህራንን በማሰልጠኑ ሂደት ተሳታፊ የሚሆኑት አሰልጣኝ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ብቻ ሳይሆኑ የተባባሪ ት/ቤት መደበኛ መምህራንም ጭምር ናቸው:: ምክንያቱም መደበኛ መምህራን ለተማሪ አስተማሪዎች ትምህርት ቤታቸውን ከማስተዋወቅ ጀምሮ የተማሪ አስተማሪዎች ዕቅድ በሚያዘጋጁበት ጊዜ ይረዷቸዋል:: ጥሩ ጥሩ የማስተማር ዘዴዎችን ያስተዋውቋቸዋል:: አስፈላጊና ገንቢ የሆኑ አስተያየቶችን ይሰጧቸዋል:: ከዚህ ባለፈም ስለተማሪ አስተማሪዎች አጠቃላይ ሁኔታ ለሱፐርቫይዘሮች ሪፖርት ያደርጋሉ:: በግምገማ ውጤታቸው ዙሪያ ከሱፐርቫይዘሮች ጋር በመወያየት በተማሪ አስተማሪዎች የመገምገሚያ ቅጹ ላይ ይፈርማሉ::

ስለዚህ እነዚህ የተማሪ አስተማሪዎችን ቀን በቀን በማግኘት ሊረዱ የሚችሉት መደበኛ መምህራን የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ መሆኑን በመረዳት የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት ይችሉ ዘንድ ኮሌጁ የመገምገሚያ ቅጾችን ከመላክ ባለፈ በፕራክቲከምም ሆነ በማስተማር ልምምድ ሂደት ሊኖራቸው የሚገባውን ኃላፊነትና ተግባር በግልጽ ሊያሳውቃቸው ይገባል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ MOE (2003:40) የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማትን ተግባርና ኃላፊነት በዝርዝር ያስቀመጠ ቢሆንም የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የተባባሪ ት/ቤቶች መደበኛ መምህራን የፕራክቲከሙና የማስተማር ልምምዱ ቀጥተኛ ተሳታፊ የሚሆኑበትን መንገድ አላመቻቸም፡፡ ፕራክቲከሙም ሆነ የማስተማር ልምምዱ ከመጀመሩ በፊት ከተባባሪ ት/ቤቶች ጋር ተገናኝቶ ሁኔታዎችን አላመቻቸም፡፡ ተባባሪ ት/ቤቶችንና ለማስተማር ልምምድ የሚያገለግሉ ክፍሎችን መምረጫ መስፈርት አውጥቶና የክፍል ምልከታ መመዝገቢያ ቅጽ እንዲሁም የመጨረሻ ምዘና መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ቀርጾ የማስተማር ልምምዱን መከታተል ሲገባው ይህን እንዳላደረገ ከተባባሪ ት/ቤት መደበኛ መምህራን ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል፡፡

> . . . ኮሌጁ ያዘጋጀውን የፕራክቲከምና የማስተማር ልምምድ መገምገሚያ ቅጽ በመላክ ሞልተን እንድንልክ ከማድረግ ውጭ እንዴት ልንከታተላቸውና ልንገመግማቸው እንደምንችል የአጭር ጊዜ ስልጠና እንድናገኝ አላደረገም፡፡ በጽሁፍ የተዘጋጀ መመሪያም እንዲደርሰን ለማድረግ አልሞከረም፡፡ ስለዚህ ያለን አማራጭ የመጨረሻውን የመገምገሚያ ቅጽ ሞልተን መላክ ብቻ ነው፡፡

የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ከተባባሪ ት/ቤቶች ጋር የጠበቀ ግንኙነት የሌለው መሆኑን አመላካች መረጃዎችም የዚህ ጥናት አቅራቢ ምልከታ ባደረገበት ወቅት ተገኝተዋል፡፡ ለምሳሌ ኮሌጁ የፕራክቲከምና የማስተማር ልምምድ ፕሮግራሙን ሲያዘጋጅ ተባባሪ ት/ቤቶችን ባለማማከሩ የተነሳ የፈረቃ ሁኔታንና ወርሃዊ የፈተና መስጫ ፕሮግራምን ከግንዛቤ ውስጥ እንዲገባ አላደረገም፡፡ በዚህ ምክንያት የተማሪ አስተማሪዎች ወደተመደቡባቸው ት/ቤቶች ከሄዱ በኋላ ፈረቃው ትክክል ባለመሆኑ ወይም የፈተና ጊዜ በመሆኑ ወደቤታቸው የሚመለሱበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ይህንን በተመለከተ የተማሪ አስተማሪዎቹ ከፃፉት ማስታወሻ መሐከል የሚከተለውን ለናሙና ያህል እንመልከት፡፡

> ተማሪዎቹ ወርሃዊ ፈተና ላይ ስለነበሩ በመጀመሪያው ሳምንት የማስተማር ልምምድ ለሁለት ቀን ያህል አላስተማርኩም፡፡

ኮሌጁና ተባባሪ ት/ቤቶች የጠበቀ ግንኙነት ቢኖራቸው ኖሮ ግን ይህን ዓይነት ችግር ሊከሰት እንደማይችል መገመት ይቻላል፡፡

ከዚሁ ጋር በማያያዝ ምናልባትም መደበኛ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች በቅርብ እየተገናኙ . ፕራክቲከሙንና የማስተማር ልምምድ አተገባበሩን ይከታተሉ እንደሆነ በማለት ለተማሪ አስተማሪዎች ከዚህ በታች የተመለከተው ጥያቄ ቀርቦላቸው የሰጡት መልስ የሚከተለውን ይመስላል::

## ሠንጠረዥ ሰላሳ

## ሱፐርቫይዘሮችና መደበኛ መምህራን በጋራ ስለመስራታቸው

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሰ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 23 | ሱፐርቫይዘሪና የት/ቤቱ መደበኛ መምህራን በአንድ ላይ ሆነው በነበረኝ የፕራክቲከምና የማስተማር ልምምድ ቆይታ ዙሪያ አወያይተውኛል:: | 18<br>16.4% | | 13<br>11.8% | 78<br>70.9% | | 1<br>0.9% |

በሠንጠረዡ በጥያቄ ተራ ቁጥር 23 ላይ ከተቀመጠው ምላሽ እንደምንገነዘበው ሱፐርቫይዘሮቻቸውና መደበኛ መምህራን በአንድ ላይ ሆነው ያወያዩዋቸው የተማሪ አስተማሪዎች 16.4 ከመቶው ብቻ ናቸው:: 11.8 ከመቶ የሚሆኑት ቁርጥ ያለ መልስ ለመስጠት አልደፈሩም:: ቀሪዎቹ 70.9 ከመቶ የሚሆኑት ግን ሁለቱን አንድ ላይ አይተናቸውም አናውቅም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል:: በተመሳሳይ ሁኔታ ሱፐርቫይዘሮችም ተጠይቀው የሰጡት መልስ ተከታዩን ይመስላል::

## ሠንጠረዥ ሰላሳ አንድ

## ሱፐርቫይዘሮችና መደበኛ መምህራን በጋራ መስራት

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሰ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 13 | ለፕራክቲከምና ማስተማር ልምምድ መሳካት ከት/ቤቱ መደበኛ መምህራን ጋር በመተባበር ሠርቻለሁ:: | 12 | | 4 | 4 | | - |

በጥያቄ ተራ ቁጥር 13 ለሱፐርቫይዘሮች ቀርቦ ለነበረው ጥያቄ የተሰጠውን ምላሽ ስንቃኝ ደግሞ አራት ሱፐርቫይዘሮች ከመደበኛ መምህራን ጋር እየተመካከሩ አለመስራታቸውን ይስማሙበታል:: ቀሪዎቹ አራት ሱፐርቫይዘሮች ለጥያቄው ቁርጠኛ መልስ ለመስጠት ተቸግረዋል:: አስራ ሁለቱ ግን ለፕራክቲከሙም ሆነ ለማስተማር ልምምዱ ውጤታማነት ከመደበኛ መምህራን ጋር በመተባበርና በመመካከር የሰሩ መሆናቸውን ገልፀዋል:: የሁለቱ ወገኖች መልስ ሊለያይ የቻለው ምናልባትም ሱፐርቫይዘሮቹ ከመደበኛ መምህራን ጋር ሰርተናል

ለማለት የደፈሩት የመገምገሚያ ቅጹን በመስጠትና በመቀበል የነበረውን ግንኙነታቸውን መነሻ አድርገው ሳይሆን አይቀርም።

ይህ ሁሉ ኃላፊነትና ተግባር ያላቸው መደበኛ መምህራን በቀናነት የተማሪ አስተማሪዎችን ከመርዳታቸውና የግምገማ ቅጽ ሞልተው ከመመለሳቸው ውጪ ኃላፊነታቸውን በሚገባ ተገንዝበው የሚጠበቅባቸወን ሁሉ ተወጥተዋል ለማለት አያስደፍርም።

### 4.3.2.4 የተማሪ አስተማሪዎችና ሱፐርቫይዘሮች ለማስተማር ልምምዱ ያላቸው አስተያየት

ማስተማርን የመማሩ ጉዳይ ሙሉ በሙሉም ባይሆን ቢያንስ በከፊል በማስተማር ልምምድ ሊገኝ ይችላል (ዓለም 1988፣13)። ከማስተማር ልምምድ የሚገኘው ዕውቀትና ችሎታ ከፊል ነው የተሰኘው ልምምድ በብዙ ችግሮች ውስጥ የሚካሄድ በመሆኑ ብቻ ነው። የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ግን ለማስተማር ልምምዱ በቂ ጊዜ መድበው ሰፋ ያለ ቅደመ ዝግጅት አድርገው፣ የልምምዱን ሂደት በቅርበት ተከታተለው ውጤቱ የሰመረ ማድረግ ይችላሉ። ይህን ንድፈ ሐሳባዊ መሠረት መነሻ በማድረግ በ1997 ዓ.ም በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ስለነበረው የማስተማር ልምምድ የተማሪ አስተማሪዎችን አስተያየት ለማወቅ ሙከራ ተደርጎ ነበር። ለማስተማር ልምምዱ የተመደበው ጊዜ በቂ ስለመሆኑ ከተገኘው ውጤት በመጀመር አስተያየታቸውን እንመልከት።

**ሠንጠረዥ ሰላሳ ሁለት**

**ለማስተማር ልምምዱ ስለተመደበው ጊዜ**

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 28 | ለማስተማር ልምምድ የተመደበው 4 ሳምንት በቂ አይደለም። | 57<br>51.8% | | 10<br>9.1% | 43<br>39.1% | | -<br>- |

ከላይ በሠንጠረዡ እንደሚታየው በአሉታ ለቀረበው ጥያቄ 51.8 ከመቶ የሚሆኑት መላሾች አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል። ይህም ለማስተማር ልምምዱ የተመደበው 4 ሳምንት የታሰበውንና ንድፈ ሐሳብን ከተግባር የማዛመድ ዓላማ ለማሳካት አያስችልም ማለት ነው የአራት ሳምንታት ልምምድ በቂ ነው በማለት መልስ የሰጡት መላሾች 39.1 ከመቶ የሚሆኑት ናቸው። የቀሪዎቹ መልስ ግን ከዚህ ይለያል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የተማሪ አስተማሪዎች የማስተማር ልምምዱን በተመለከተ የሚሉት ነገር ካለ በማለት ክፍት ጥያቄ ቀርቦላቸው የሰጡት መልስ የሚከተለውን ይመስላል።

የማስተማር ልምምድ በክፍል ውስጥ የቀሰምነውን ንድፈ ሐሳብና በፕራክቲከም ወቅት በምልከታ ያገኘነውን ዕውቀት መነሻ በማድረግ በአንድ የመማሪያ ክፍል አውድ ወደ ተግባር የምንለውጥበት ጊዜ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እኔ ይህን ተግባር በአራት ሳምንታት ውስጥ አጠናቆ ጥሩ መምህር ለመሆን ያስችላል የሚል ግምት የለኝም፡፡

βእኔ አመለ∝ከት የማስተማር ልምምዱ ጥሩ ቢሆንም የተሰጠው የአራት ሳምንታት ጊዜ በቂ አይመስለኝም፡፡ ስለዚህ ልምምዱ ቢያንስ ለሁለት ወራት የሚቆይበትን መንገድ ኮሌጁ ማመቻቸት አለበት፡፡

ለማስተማር ልምምዱ የተመደበው ጊዜ በጣም አጭር በመሆኑ የቆይታ ጊዜው ቢጨመር በጣም ጥሩ ይመስለኛል፡፡

ይህን የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ ስንመለከት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሚከናወን የማስተማር ልምምድ በመምህራን ስልጠና የተፈለገውን ውጤት ሊያስገኝ አለመቻሉን ነው፡፡ በተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት እንደተጠቀመው በአዲሱ የመምህራን ስልጠና ፖሊሲ ማስልጠኛ ተቋማት የማስተማር ልምምድ ፕሮግራም ሲቀርፁ ከእያንዳንዱ የመምህራን ስልጠና ዓመት መጀመሪያ አንስቶ የማስተማር ልምምድ የሚካሄድበት መንገድ ማመቻቸት ይኖርባቸዋል፡፡ Farant (1980) በበኩላቸው በማስተማር ልምምድ ወቅት በየደረጃው ሊከናወኑ የሚገባቸው ተግባራት እንዳሉ በመጠቆም ልምምዱ ቢያንስ ለሦስት ወራት መካሄድ ይኖርበታል በማለት ይገልፃሉ፡፡

### 4.3.3 የሱፐርቪዥን አቀራረብና አተገባበር

#### 4.3.3.1 ሱፐርቪዥኑ እንዴት እየተተገበረ ነው?

Gebhard (1990) ሱርቪዥን ድክመትን የመፈለግ ሂደት ብቻ ሳይሆን የተማሪ አስተማሪዎችን የመምራት፣ ከጥሩ የማስተማር ዘዴ ጋር የማስተዋወቅ፣ ሌሎች የማስተማሪያ ሞዴሎችን የማሳየት፣ የማስተማር ልምምድ በሚያደርጉበት ጊዜ የማማከርና የመገምገም ሂደትን ሁሉ ሊያጠቃልል እንደሚችል ይገልፃሉ፡፡ የመምራቱም፣ የማስተዋወቁም፣ የማሳየቱም ሆነ የማማከርና የመገምገሙ ሂደት የሚከናወነው የተማሪ አስተማሪዎቹ በተቋሙ የቀሰሙትን መሠረታዊና ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀት በአንድ ክፍል አወድ ወደ ተግባር በሚለውጡበት ጊዜ ምልከታ ከተደረገ በኋላ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ስለዚህ የሱፐርቪዥኑ ሂደትና ትግበራ የሚጀምረው በክፍል ውስጥ ተገኝቶ ከሚደረግ ምልከታ ነው፡፡ የክፍል ምልከታ ደግሞ በተወሰኑ መሪ ነጥቦች ላይ ይመሠረታል፡፡ በእያንዳንዱ መሪ ነጥብ ስር በርካታ ንዑሳን ክፍሎችን ለመመልከት ይቻላል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት ሱፐርቫይዘሮች የተማሪ አስተማሪዎችን በክፍል ውስጥ የትምህርት አቀራረባቸውን፣ ጥያቄ የመጠየቅና የመመለስ ችሎታቸውን፣ የክፍል ቁጥጥራቸውን ወዘተ. በመገምገም የሚሰጥ ምግበ መረጃ ላይ ያነጣጠረ በመሆኑ ይህንኑ

ለመቃኘት ይሞክራል። በመጀመሪያ ሱፐርቫይዘሮች የሱፐርቪዥኑን ሂደት እንዴት ሲከታተሉት እንደነበር እንመለከታለን።

ሱፐርቫይዘሮች የተለያየ ዓይነት የክፍል ምልከታ መከታተያ ቅጽ በማዘጋጀት ሊጠቀሙ ይችላሉ። ይሁን እንጂ የምልከታ መከታተያ ቅጹን ከማዘጋጀታቸው በፊት የምልከታቸውን መጠነ ርዕይ መወሰንና መረጃውን ሊያሰባስቡ የሚችሉበትን መሣሪያ መምረጥ ይጠበቅባቸዋል ። ይህን ሐሳብ መነሻ በማድረግ የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሱፐርቫይዘሮች አዘጋጅተው የሚገለገሉበት የክፍል ምልከታ መከታተያ ቅጽ እንዳለ ለማረጋገጥ በሱፐርቪዥን ሂደት ምን ዓይነት የመገምገሚያና የመከታተያ መንገድ ይከተሉ ነበር≅ የሚል ጥያቄ በጽሁፍ እንዲመልሱ ቀርቦላቸው የሰጡት ምላሽ የሚከተለውን ይመስላል።

> እኔ የክፍል ምልከታ የማደርገው ኮሌጁ ያዘጋጀውን የመገምገሚያ ቅጽ ብቻ በመጠቀም ነው።
>
> ለመከታተልና ለመገምገም ያስችላል ተብሎ የተዘጋጀውን ቅጽና የክፍል ምልከታ መርህን መነሻ በማድረግ እከታተላለሁ።
>
> ኮሌጁ ያዘጋጀውን ፎርማት በመከተልና አጠቃላይ የመማር ማስተማር መርሆዎችን በመከተል የተማሪ አስተማሪዎችን ተግባራት፣ የፈጠራ ችሎታ፣ በቂ ዝግጅት፣ ዕቅድን ከተጨባጭ ሁኔታ ከማገናዘብና ከመተግበር ችሎታ አኳያ እከታተላለሁ።
>
> ኮሌጁ ካዘጋጀው ቅጽ በተጨማሪ የራሴን ኖት እየያዝኩ ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን በጥሩ አገላለጽ እገልጽላቸዋለሁ።
>
> የተሰጠኝን የመገምገሚያ ቅጽ ተጠቅሜ አላውቅም በአብዛኛው በትምህርት ይዘት፣አቀራረብ፣ የቋንቋ አጠቃቀም፣የክፍል ቁጥር ላይ በማተኮር ነው የምከታተላቸው።
>
> የኮሌጁን የመገምገሚያ ቅጽ ከእኔ የሥራ ዓለም ግንዛቤ በመውሰድ ዕለታዊ የትምህርት ዝግጅት ከአመታዊው ዕቅድ ጋር ተገናዝቦ መሠራቱን እከታተል ነበር። ከዚህ በተረፈ የተማሪ አስተማሪው ሳይፈራና ሳይሸማቀቅ መስራቱን አያለሁ።

ከላይ በሱፐርቫይዘሮች የተሰጡ የጽሁፍ ምላሾችን ስንመለከት የሱፐርቪዥኑን ሂደት የሚከታተሉት እንደየራሳቸው አመለካከትና የዕውቀት ደረጃ ነው። ምንም እንኳን እያንዳንዱ ሱፐርቫይዘር የየራሱን የሱፐርቪዥን መከታተያ ቅጽ በማዘጋጀት መጠቀም የሚችል ንድፈ ሓሰባዊ መሠረት ቢኖረውም ብዙዎቹ የምልከታ መከታተያ ቅጾች የሚጋሩዋቸው መሠረታዊ ነጥቦች ስላሉ ወጥ የሆነ የአገማገም ስልት ይኖር ዘንድ እነዚህን መሠረታዊ ነጥቦች መነሻ አድርገው በማዘጋጀት ቢጠቀሙ ተመራጭነት ይኖረዋል። ይህም ሱፐርቫይዘሮች የተማሪ አስተማሪዎችን የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ ወጥና ስርዓታዊ በሆነ መንገድ በመመዝገብ

ተገቢውን ምግበ መረጃ ለመስጠት ያስችላቸዋል:: ያለበለዚያ ሁሉም ሱፐርቫይዘር እንደመሰለው የተመለከተውንና የተገነዘበውን ነገር ማስታወሻ ይያዝ ከተባለ የሱፐርቪዥኑ አተገባበር ወጥነት ያጣል:: ወጥነቱን ሲያጣ ደግሞ ምግበ መረጃውም ሆነ የግምገማ ውጤቱን ኢተአማኒ ያደርገዋል::

### 4.3.3.2 የምግበ መረጃ አቀራረብ

ሱፐርቫይዘሮች የማስተማር ልምምዱን በአግባቡ ከተከታተሉ በኋላ ቀጣይ ተግባራቸው ከተማሪ አስተማሪዎች ጋር በመገናኘት የምግበ መረጃ ልውውጥ ማድረግ ነው:: ለምግበ መረጃ ልውውጡ መሳካት የተማሪ አስተማሪዎች በተመደቡበት ት/ቤት መደበኛ የመማሪያ ክፍል የሚያከናውኑትን ተግባር በቅርብ ተገኝቶ መከታተልን ይጠይቃል:: ክትትሉ በዘፈቀደ የሚካሄድ ሳይሆን ስርዓታዊ የምልከታ መሳሪያዎችን በመጠቀም ቢሆን ይመረጣል:: ምክንያቱም የምልከታ መከታተያ መሣሪያዎችን መገልገል ከማስተማር ልምምድ በኋላ ለሚደረግ የምግበ መረጃ ውይይት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል:: ውይይቱም ከግምገማ ይልቅ በገለፃ፣ ከአጠቃላይ ይልቅ በዝርዝር፣ ስብዕናን ከመንካት ይልቅ ቀለል ባሉ ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩር ያደርገዋል (Wajnryb 1992:8)::

በምልከታ መከታተያ ቅጽ የተመዘገቡ ማስታወሻዎችን መነሻ በማድረግ የሚደረግ የምግበ መረጃ ውይይት የተማሪ አስተማሪዎች ጠንካራ ጎናቸውን ይበልጥ ለማጎልበትና ድክመታቸውን ደግሞ ለማሻሻል የሚያደርገው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው:: ይህም የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት በማያዘጋጁት የመገምገሚያ ቅጽ አንድ ጉዳይ ላይ ብቻ በመመርኮዝ ምልከታ ከማድረግ ያድናል (William 1989:85) :: የምልከታ መከታተያ ቅጽ በአንድ የመገምገሚያ ነጥብ ላይ ካላተኮረና በተማሪ አስተማሪዎች ፍላጎት ላይ ከተመሰረተ ከሱፐርቫይዘሮች ይልቅ የተማሪ አስተማሪዎች ኃላፊነት እንዲወስዱና ራሳቸውን ለውይይት እንዲያዘጋጁ ያደርጋቸዋል::

ይሁን እንጂ የማስተማር ልምምድን በመከታተል የተገኘ መረጃ በራሱ ምንም ፋይዳ የለውም:: ምክንያቱም ድህረ ማስተማር ልምምድ በሚደረግ ውይይት የተማሪ አስተማሪዎች ከተገኘው መረጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረግ ይኖርበታል:: ይህም የሚሆነው የተለያዩ የሱፐርቪዥን አቀራረቦችን በመጠቀም ነው::

በንድፈ ሐሳብ ደረጃ የተለያዩ የሱፐርቪዥን አቀራረቦች ቢኖሩም መምህራንን በማሰልጠን ሂደት ይበልጥ ተመራጭነት ኖሯቸው አገልግሎት ላይ ይውላሉ የሚባሉት የሱፐርቪዥን አቀራረብ ሞዴሎች የ Freeman (1988) አማራጫዊ አቀራረብ (Alternative approach) ፣ የ zahorik (1988) ድጋፍ ሰጭ አቀራረብ (Person Supporter)፣ የ Gebhard (1990) ቅንጅታዊ ሱፐርቪዥን (Collaborative Supervision) እና የ Wallace (1991) ትብብራዊ አቀራረብ (Classic collaborative approach) ፣ ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ይህን ሐሳብ መሠረት በማድረግ የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሱፐርቫይዘሮች የሚከተሉትን የሱፐርቪዥን አቀራረብ ለማወቅ ለተማሪ አስተማሪዎች ቀጣዩ ጥያቄ ቀርቦላቸው የሰጡት መልስ የሚከተለውን ይመስላል::

## ሠንጠረዥ ሰላሳ ሦስት

## የሱፐርቫይዘሮች ምግበ መረጃ አቀራረብ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 42 | በድህረ ማስተማር ልምምድ ውይይት ወቅት ሱፐርቫይዘሬ ተናጋሪ እኔ አድማጭ ነበርኩ:: | 26<br>23.6% | | 21<br>19.1% | 59<br>53.6% | | 4<br>3.6% |

ከሠንጠረዡ ለመረዳት እንደሚቻለው በፐርሰንት 53.6 ከመቶ የሚሆኑ መላሾች በምግበ መረጃ ልውውጡ ወቅት ሙሉ ተሳታፊዎች እንደነበሩና ሐሳባቸውን ለመግለጽ እንደቻሉ ገልፀዋል:: 23.6 ከመቶ የሚሆኑት መላሾች ደግሞ በድህረ ማስተማር ልምምድ ውይይት ሱፐርቫይዘሮቻቸው የሚሰጧቸውን መመሪያና ምክር ተቀባዮች መሆናቸውን ያስረዳሉ:: 19.1 ከመቶ ያህሉ ግን ለጥያቄው ቁርጥ ያለ መልስ ለመስጠት ሲቸገሩ ቀሪዎቹ ለጥያቄው መልስ ለመስጠት ያልፈለጉ ናቸው:: መረጃው እንደሚጠቁመው የተወሰኑ ሱፐርቫይዘሮች የተማሪ አስተማሪዎችን ለመምራት ሲሞክሩ ይታያሉ:: ይህ ደግሞ በተማሪ አስተማሪዎች ዘንድ የአላዋቂነትና የዝቅተኝነት መንፈስን መፍጠሩና ድፍረትን ማሳጣቱ አይቀሬ ነው:: ስለዚህ በመምህራን አሰለጣጠን ሂደት ትብብራዊ የሱፐርቪዥን አቀራረብን በመጠቀም በተማሪ አስተማሪዎች ላይ ሊፈጠር የሚችለውን አሉታዊ ስሜት ማስወገድ ይገባል::

ከዚሁ ጋር በማያያዝ የተማሪ አስተማሪዎች በድህረ ማስተማር ልምምድ ውይይት ወቅት ተሰምቷቸው የነበረውን ስሜት ለማወቅ ተከታዩ ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር::

## ሠንጠረዥ ሰላሳ አራት

## በድህረ ማስተማር ልምምድ ውይይት ወቅት የተማሪ አስተማሪዎች ስሜት

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 13 | ከሱፐርቫይዘሬ ጋር በምወያይበት ጊዜ የፍርሃት ስሜት ተሰምቶኝ ነበር:: | 29<br>26.4% | | 25<br>22.7% | 55<br>49.9% | | 1<br>0.9% |

ከሠንጠረዡ እንደሚታየው 26.4 ከመቶ የሚሆኑ መላሾች የምግበ መረጃ ውይይት ባደረጉበት ጊዜ የፍርሃት ስሜት ተሰምቷቸው እንደነበረ የገለፁ ናቸው:: 22.7 ከመቶ የሚሆኑት መላሾች ለመወሰን ሲቸገሩ 49.9 ከመቶ የሚሆኑት ግን በውይይቱ ወቅት የፍርሃት ስሜት እንዳልተሰማቸው ገልፀዋል::

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሱፐርቫይዘሮች በተማሪ አስተማሪዎች ዘንድ ፍርሃትና ጭንቀት እንዳይነግስ ያደረጉት ሙከራ ካለ በሚል ዝግ የጽሁፍ ጥያቄ ቀርቦላቸው የሰጡትን መልስ እንመልከት፡፡

## ሠንጠረዥ ሰላሳ አምስት

### የውይይቱ መንፈስ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 12 | በድህረ ማስተማር ልምምድ ወቅት በሚደረግ ውይይት የተማሪ አስተማሪዎች ዘና እንዲሉ አደርግ ነበር፡፡ | 15 | | 3 | 2 | | |

ከላይ ከቀረበው መረጃ ለመረዳት እንደሚቻለው 15 የሚሆኑት ሱፐርቫይዘሮች የተማሪ አስተማሪዎችን በማበረታታት፣ በመደገፍና ችግራቸውን ለማቃለል ከመጣራቸውም በላይ ዘና የሚሉበትን ሁኔታ ይፈጥሩ እንደነበር ይገልፃሉ፡፡

ሱፐርቫይዘሮች ሁኔታውን በማመቻቸት የተማሪ አስተማሪዎች ዘና ብለው በምግበ መረጃ ልውውጡ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማስቻል በሚያደርጉት ጥረት የተማሪ አስተማሪዎችን ስብዕና ሊነካ የሚችል አገላለፅን መጠቀም የለባቸውም፡፡ ይሁንን ሐሳብ መነሻ በማድረግ ሱፐርቫይዘሮች ያደርጉት የነበረውን ጥንቃቄ ለመረዳት ራሳቸው ተጠይቀው ቀጣዩን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

## ሠንጠረዥ ሰላሳ ስድስት

### የተማሪ አስተማሪዎችን ስብዕና ላለመንካት የተደረገ ጥንቃቄ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 15 | በድህረ ማስተማር ልምምድ ውይይት ወቅት የተማሪ አስተማሪዎችን ስብዕና ላለመንካት ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርጌያለሁ፡፡ | 17 | | 1 | 2 | | - |

ከላይ ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠውን ምላሽ ስንመለከት 17 የሚሆኑት ሱፐርቫይዘሮች የተማሪ አስተማሪዎችን ስብዕና ላለመንካት ተጠንቅቀው ውይይቱን የሚያካሄዱ ናቸው፡፡ ሁለቱ ደግሞ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ አይደለም ብለው ያምናሉ፡፡ ምክንያታቸውም በምግበ መረጃ ውይይት ስብዕናን ላለመንካት ሲባል የታዩ ደካማ ጎኖች በሙሉ ለተማሪ አስተማሪዎቹ ሳይገለፁ መቅረት የለባቸውም የሚል ነው፡፡ ለዚህም ነው የተወሰኑ ሱፐርቫይዘሮች አስተያየታቸውን በሚከተለው አኳኋን እንደሚሰጡ ከተማሪ አስተማሪዎች ማስታዎሻ ማረጋገጥ የተቻለው፡

- በምታስተምርበት ጊዜ ወደ ተማሪዎቹ አትመለከትም

- ደካማ የሆኑ ተማሪዎችን ለመርዳት ምንም አይነት ሙከራ አላደረክም::
- የመርጃ መሳሪያ አልተጠቀምክም::
- ሂሳብ በምታስተምርበት ጊዜ የቅንፍ አጠቃቀምህ ትክክል አልነበረም::
- የክፍል ቁጥጥርህ በጣም ደካማ ነው::
- የጥቁር ሰሌዳ አጠቃቀምህ ትክክል አይደለም::
- የሰዓት አጠቃቀም ችግር አለብህ ብለውኛል::

ከላይ ከተመለከተቱት የተማሪ አስተማሪዎች ማስታወሻዎች መረዳት እንደሚቻለው የተወሰኑ ሱፐርቫይዘሮች የተለያዩ አማራጭ ሐሳቦችን ከመለገስ ይልቅ ለተማሪ አስተማሪዎች አማራጭ የሌለው አስተያየት በመስጠት የምግበ መረጃ ውይይቱን ሲያካሄዱ መታየታቸውን ነው::

#### 4.3.3.2.1 በምግበ መረጃ ልውውጥ የተማሪ አስተማሪዎችና የሱፐርቫይዘሮች ሚና

በሱፐርቫይዘሮችና በተማሪ አስተማሪዎች መካከል በሚደረግ የምግበ መረጃ ልውውጥ ሱፐርቫይዘሮች ብዙውን ጊዜ በመውሰድ ባይናገሩ ይመረጣል:: ምክንያቱም እነሱ ተናጋሪ የተማሪ አስተማሪዎች አድማጭ ከሆኑ ራሳቸውን በራሳቸው ከመመርመር ይልቅ ሁልጊዜ ስህተታቸውን እንዲጠቆሙ ይሻሉ:: ይሁን እንጂ የድህረ ማስተማር ልምምዱን በመከታተል የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው አብዛኛው የውይይት ጊዜ የሚሸፈነው በሱፐርቫይዘሮች ንግግር ነው:: የተማ አስተማሪዎች አጫጭር መልሶችን ከመስጠት በዘለለ በውይይቱ ያላቸው ድርሻ ዝቅተኛ ነው:: ይህ ደግሞ በሁለቱ ወገኖች መካከል የመቀራረብና የጓደኝነት መንፈስ እንዳይኖር ትልቅ እንቅፋት ይፈጥራል:: ይህንን ጉዳይ በሚመለከት የተማሪ አስተማሪዎች ተጠይቀው የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል::

**ሠንጠረዥ ሰለሳ ሰባት**

**የተማሪ አስተማሪዎች ለሱፐርቫይዘሮቻቸው ያላቸው አመለካከት**

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 44 | ሱፐርቫይዘሬን እንደጓደኛና የስራ ባልደረባዬ አየዋለሁ:: | 53<br>48.2% | | 19<br>17.3% | 36<br>32.7% | | 2<br>1.8% |

ከሠንጠረዡ ላይ ማየት እንደሚቻለው 32.7 ከመቶ የሚሆኑ መላሾች ከሱፐርቫይዘሮቻቸው ጋር ብዙም ቀረቤታ የሌላቸው ናቸው:: 17.3 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ ያላቸውን ቅርበት ወስነው ለመግለጽ ተቸግረዋል:: 48.2 ከመቶ የሚሆኑት ግን ሱፐርቫይዘሮቻቸውን እንደጓደኛና የስራ ባልደረባ አድርገው የሚቆጥሩ መሆናቸውን ይገልፃሉ::

ይሁን እንጂ የጥናቱ አቅራቢ ተከታታይ ምልከታ ባደረገበት ወቅት ለመገንዘብ እንደቻለው ብዙዎቹ የተማሪ አስተማሪዎች ሱፐርቫይዘሮቻቸውን ከሚገባው በላይ ይፈሯቸዋል፡፡ ምክንያታቸውንም ሲገልፁ ብዙ ጊዜ የማይገናኙ በመሆናቸው ባህሪያቸውን ባለመረዳታቸው እንደሆነ ነው፡፡ ለዚህም ነው ስለነበረው የሱፐርቪዥን አተገባበር መግለጽ የሚፈልጉትን ነገር በጽሁፍ እንዲያሰፍሩ ለቀረበላቸው ጥያቄ አንድ የተማሪ አስተማሪ የሚከተለውን መልስ አስፍሮ የምናገኘው፡፡

> በማስተማር ልምምድ ላይ ሳለሁ ሱፐርቫይዘሬ ድንገት ሲመጣ በጣም ፈርቼ ነበር፡፡

#### 4.3.3.2.2 የምግበ መረጃ ውይይቱ የትኩረት አቅጣጫና የሱፐርቫይዘሮች ሀሳብ ተቀባይነት

ዓለም (1988፣29-31) የተለያዩ የመስኩ ምሁራንን ጠቅሶ እንደገለፀው የምግበ መረጃ ውይይት በስብዕና ላይ ሳይሆን በባህሪ፣ በስሜት ሳይሆን በተያዘ ማስታወሻ፣ በግላዊ ፍርድ ወይም ዳኝነት ሳይሆን በተጨባጭ መረጃ፣ በምክር ልገሳና በማሳመን ሳይሆን በመረጃ ልውውጥ ላይ ቢያተኩር ይመረጣል፡፡ ይህን መንገድ የተከተለው የሱፐርቪዥን አተገባበር ደግሞ ትብብራዊ አቀራረብ ነው (Wallace 1991:110)፡፡ የትኩረት አቅጣጫውም የሱፐርቫይዘሮችን ፈላጭ ቆራጭነት ለማጎልበትና ፍርድ እንዲሰጡ ለማደፋፈር ሳይሆን የተማሪ አስተማሪዎችን ለመደገፍ፣ ለማበረታታትና ለመርዳት ይሆናል፡፡

ከዚህ ንድፈ ሀሳባዊ ጭብጥ በመነሳት በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የምግበ መረጃ ውይይት ያተኩርባቸው የነበሩ ነጥቦችን ለመፈተሽ ጥረት ተደርጓል፡፡ በመጀመሪያ ለማረጋገጥ የተሞከረው ሱፐርቫይዘሮች በምግበ መረጃ ውይይቱ ጊዜ ይበልጥ ያተኩሩበት የነበረው ጉዳይ ምን እንደሆነ ነበር፡፡ በዚሁ መሠረት ለተማሪ አስተማሪዎች ቀጣዩ ጥያቄ ቀርቦላቸው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

## ሠንጠረዥ ሰላሳ ስምንት
## የምግበ መረጃ ውይይቱ ትኩረት

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 36 | በድህረ ማስተማር ልምምድ ውይይት ሱፐርቫይዘሬ ከሚገባው በላይ ትኩረት የሰጠው ለጠንካራ ጎኔ ነበር፡፡ | 28<br>25.5% | | 29<br>26.4% | 50<br>45.5% | | 3<br>2.7% |

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው 45.5 ከመቶ የሚሆኑ መላሾች የድህረ ማስተማር ልምምድ ውይይቱ በነበራቸው ጠንካራ ጎን ላይ ከማተኮር ይልቅ በደካማ ጎናቸው ላይ ብቻ ያተኩር እንደነበር ገልጸዋል፡፡ 25.5 ከመቶ የሚሆኑት መላሾች ደግሞ

በውይይቱ ወቅት ሱፐርቫይዘሮቻቸው ስለጠንካራ ጎናቸው ያወያዩዋቸው መሆኑን ሲገልፁ 26.4 ከመቶ የሚሆኑት ግን ውይይቱ በምን ላይ ያተኮረ እንደነበር ለማስታወስ የተቸገሩ ናቸው:: ቀሪዎቹ ለጥያቄው መልስ መስጠት አልፈለጉም:: ምናልባትም ሱፐርቫይዘሮች ደካማ ጎንን ብቻ እየመዘዙ የሚያደርጉት ውይይት በተማሪ አስተማሪዎች ዘንድ ያለው ተቀባይነት ምን ያህል እንደሆነ በሚል ቀጣዩ ጥያቄ ቀርቦ ከተማሪ አስተማሪዎች የተገኘው ምላሽ ተከታዩን ይመስላል::

## ሠንጠረዥ ሰላሳ ዘጠኝ

## የሱፐርቫይዘሮች ሀሳብ ተቀባይነት

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 37 | ሱፐርቫይዘሬ ከፕራክቲከምና ከማስተ ማር ልምምድ በኋላ የሚያቀርብልኝ ሐሳብ ተቀባይነት አልነበረውም:: | 20<br>18.2% | | 28<br>25.5% | 59<br>53.6% | | 3<br>2.7% |

ከሠንጠረዡ ማየት እንደሚቻለው 53.6 ከመቶ የሚሆኑት መላሾች በሱፐርቫይዘሮቻቸው የቀረበላቸው ምግበ መረጃ ተቀባይነት እንደነበረው ቢስማሙም 25.5 ከመቶ ያህሉ ቁርጠኛ መልስ ለመስጠት አልቻሉም:: ቀሪዎቹ 18.2 ከመቶ መላሾች ግን ምግበ መረጃው ተቀባይነት አልነበረውም ብለዋል:: ከተማሪ አስተማሪዎች ዕለታዊ ማስታወሻ የተገኘው መረጃም ይህንኑ ሐሳብ ደጋፊ ነው::

> ሱፐርቫይዘሬ ምንም ዓይነት ጠንካራ ጎን እንደነበረኝ ሳይጠቁመኝ ድክመቴን ብቻ ነው የነገረኝ:: ይህ ደግሞ ተቀባይነት የለውም:: ግምገማን እንደማስተማሪያ ሳይሆን ድክመትን እንደመፈለጊያ መሳሪያ የሚያዩ ሱፐርቫይዘሮች እንዳሉ ግልጽ ነው:: ስለዚህ የሚያቀርቡት ምግበ መረጃ ሁሉ ተቀባይነት ይኖረዋል ለማለት አያስደፍርም::

የተማሪ አስተማሪዎች ስለነበረው የሱፐርቪዥን አተገባበር ሌላ መግለጽ የሚፈልጉት ነገር ካለ በሚል በክፍት ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽም ከዚህ የተለየ አይደለም::

### 4.3.3.2.3 የምግበ መረጃው አጠቃላይ ትኩረት

አጠቃላይ ምግበ መረጃው ያተኮረባቸው ነጥቦች ምን ምን እንደሆኑ ለማወቅ ተሞክሮ በተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይ ያነጣጠረ እንደነበር ለማረጋገጥ ተችሏል:: እነሱም:-

ቀጥሎ

የተማሪ አስተማሪዎች ጊዜ አጠቃቀም፣ የጥቁር ሰሌዳና የክፍለ ጊዜ አጠቃቀም፣ የእጅ ጽሁፍ ሁኔታ፣ የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አቀራረብ፣ የክፍል አመራር ችሎታና አጠቃላይ

ስብዕና እንደነበሩ ከምልከታ፣ ከጽሁፍ መጠይቅ፣ ከተማሪ አስተማሪዎች ማስታወሻና ከመገምገሚያ ቅጽ ከተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል::

በነዚህ መረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎች ከተሰበሱ መረጃዎች መካከል የነበረውን አጠቃላይ የምግበ መረጃ ትኩረት ሊጠቁሙ የሚችሉትን በናሙናነት እንመልከት::

- በመጀመያ የምገልጽልህ ነገር ቢኖር ስታስተምር ድምጽህ አይሰማም ነበር:: ምን ሆነህ ነው፰
- የቋንቋ አጠቃቀምህና አፃፃፍህ ችግር ታይቶበታል፤ ስለዚህ ማስተካከል ይጠበቅብሀል::
- Classroom Management Very poor ነው:: ለምን ? አንተ እኮ ለዚያ ክፍል ማኔጀር ነህ::
- የትምህርት ዕቅድና ኖት ማዘጋጀት ይኖርብሻል::
- ሱፐርቫይዘር መጣም አልመጣም በሚገባ ተዘጋጅተሽ ብትገቢ ኖሮ ክፍለ ጊዜውን በክለሳ አትጨርሽውም ነበር::
- የዕለታዊ የትምህርት ዕቅድሽ በጣም ጥሩ ነው::
- የምታስተምረውን ትምህርት በመርጃ መሳሪያ አስደግፈኸው ቢሆን ጥሩ ነበር::
- በዕለታዊ ትምህርት ዕቅድህ ላይ የዓላማ አነዳደፍህ አጠቃላይነት ባይኖረው መልካም ነው::
- ስትጽፍ ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ እየተጠቀምክ ቢሆን ጥሩ ነው::
- ክፍሉን በደንብ ተቆጣጥረሀዋል:: ይሁን እንጂ የምታስተምረውን ነገር በደንብ ተዘጋጅተህበት የመጣህ አይመስለኝም::
- . . . ድምጽሽን ከፍ አድርገሽ ለማስተማር ሞክሪ ወደፊት በጣም በርካታ ተማሪዎችን በዚህ መልኩ የምታስተምሪ ከሆነ ሊያዳምጡሽ አይችሉም::
- ስታስተምር ድምጽህ Aggressive እንደነበር ትዝ ይለኛል::

ከላይ በናሙናነት የቀረቡትን የተማሪ ማስታወሻዎችና በመገምገሚያ ቅጽ ላይ የሰፈሩም መረጃዎችን ስንመለከት የምግበ መረጃው አጠቃላይ ትኩረት በተማሪ አስተማሪዎች ደካማ ጎን ላይ ያነጣጠሩ ሆነው እናገኛቸዋለን:: ከዚህ በተጨማሪ የምግበ መረጃ ልውውጡ ከሱፐርቫይዘሮች የሚሰጥ መመሪያና አስተያየትን አዳምጠው እንዲቀበሉ የሚያደረግ ሆኖ ይታያል:: እንዲህ አይነቱ አማራጭ የሚያሳጣ አስተያየት ደግሞ የተማሪ አስተማሪዎች በራሳቸው እንዳይተማመኑና አማራጭ ሀሳቦችን እንዳያመነጩ ያደርጋቸዋል:: ስለዚህ ምግበ መረጃ ውይይቱ በደካማ ጎናቸው ላይ ብቻ ከሚያተኩር ይልቅ ጠንካራ ጎናቸውንም በመጠቆም ይበልጥ እንዲያጎለብቱት ማበረታታት ተገቢ ይሆናል::አቀራረቡም ቢሆን አማራጭ የሚያሳጣ መሆን የለበትም:: የተማሪ አስተማሪዎችም የየራሳቸውን አስተያየትና ሀሳብ እንዲያንፀባርቁ እድሉ ሊሰጣቸው ይገባል::

#### 4.3.3.3. የተማሪ አስተማሪዎችና ሱፐርቫይዘሮች ሱፐርቪዥኑን በሚመለከት ያላቸው አስተያየት

በመምህራን ስልጠና የተማሪ አስተማሪዎች የራሳቸው የሆነ ተግባርና ኃላፊነት አላቸው (McIntyre and et al 1994:31)። በተለይም ከተባባሪ ት/ቤት ማህበረሰብ ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር ዕውቀትና ልምድ የሚቀስሙበትን አጋጣሚ ማስፋት ይጠበቅባቸዋል። MOE (2003:47) እንደገለፀው የተማሪ አስተማሪዎች የማስተማር ልምምዱን በአግባቡ ለማከናወን ይችሉ ዘንድ በቂ ዝግጅት ካደረጉ ፣ ገንቢ የሆኑ አስተያየቶችንና ምጋቤ ምላሾችን ከተቀበሉ፣ ሙሉ በሙሉ የተመደቡበት ት/ቤት እንቅስቃሴ ተሳታፊ ከሆኑና ለሱፐርቪዥኑ አተገባበር ቀና አመለካከት ካላቸው የተፈለገውን ውጤት ማስመዝገብ ይችላሉ።

ይህን ሐሳብ መነሻ በማድረግ የተማሪ አስተማሪዎችና ሱፐርቫይዘሮች ስለሱፐርቪዥን አተገባበሩ ያላቸውን አስተያየት ለመዳሰስ ተሞክሯል።

##### 4.3.3.3.1 የተማሪ አስተማሪዎች አስተያየት

ለአንድ ፕሮግራም መሳካት የዚያ ፕሮግራም ተሳታፊዎች ቀና አመለካከት ጉልህ ድርሻ አለው። በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በነበረው የመምህራን አሰለጣጠን ሂደት መሳካት የተማሪ አስተማሪዎች ሊጫወቱ የሚችሉት ሚና በቀላሉ የሚገመት አይለም። ይህንኑ ሐሳብ መነሻ በማድረግ ለፕሮግራሙ በተለይም ለሱፐርቪዥኑ ያላቸው አስተያየት ምን እንደሚመስል ለመቃኘት ተሞክሯል።

በመጀመሪያ በሱፐርቪዥኑ ሂደት ድህረ ማስተማር ልምምድ ከሱፐርቫይዘሮቻቸው ያገኙት የነበረው ምግበ መረጃ የማስተማር ብቃታቸውን ለማሻሻል ስለነበረው ፋይዳ ተጠይቀው የሰጡት መልስ የሚከተለውን ይመስላል።

**ሠንጠረዥ አርባ**

**የምግበ መረጃው ፋይዳ**

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 41 | ከሱፐርቫይዘሬ ያገኘሁት ምግበ መረጃ የማስተማር ብቃቴን እንዳሻሽል ትልቅ እገዛ አድርጎልኛል። | 66<br>59.9% | | 18<br>16.4% | 23<br>20.9% | | 3<br>2.7% |

ምንም እንኳን ቀደም ሲል የምግበ መረጃው ውይይት በደካማ ጎን ላይ ይበልጥ ተመርኩዞ መመሪያና ትዕዛዝ የመስጠት አዝማሚያ የሚታይበት መሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም ከላይ በቀረበው ሠንጠረዥ እንደሚታየው 59.9 ከመቶ የሚሆኑ የተማሪ አስተማሪዎች ከሱፐርቫይዘሮቻቸው የሚያገኙት ምግበ መረጃ የማስተማር ልምዳቸውን ለማሻሻል አስችሏቸዋል፡፡ ይህም ሆኖ በፐርሰንት 20.9 የሚሆኑት መላሾች የምግበ መረጃውን ፋይዳ እናንቀውታል፡፡ ቀሪዎቹ ደግሞ ምግበ መረጃው ስለነበረው ፋይዳ አንድ መልስ መስጠት የተቸገሩና ከነጭራሹ ያልመለሱ ናቸው፡፡

በክፍት ለቀረበው የጽሁፍ ጥያቄ በተማሪ አስተማሪዎች የተሰጠውን ምላሽ ስንቃኝ አንዳንድ ሱፐርቫይዘሮች የማስተማር ልምምዱን ስለማይከታተሉና ከተከታተሉም በኋላ ተገቢውን አስተያየት ስለማይሰጡ የምግበ መረጃውን ፋይዳ ለመረዳት እንዳልቻሉ ነው፡፡

> ሱፐርቫይዘሬ በአግባቡ ገምግሞኝ ነበር ይሁን እንጂ ከግምገማው በኋላ አስተያየት አልሰጠኝም፡፡
>
> ሱፐርቫይዘሬ ወደኔ ክፍል ገብቶ ስለማያውቅ የሱፐርቨዥኑን አተገባበር ማለትም የምግበ መረጃውን ጠቀሜታ በተመለከተ የምለው ነገር የለኝም፡፡
>
> ሱፐርቫይዘሮች ከግምገማ በኋላ ይህ ይህ ጠንካራ ይህ ይህ ደካማ ጎን አለብህ፡፡ ስለዚህ ደካማ ጎንህን ማሻሻል ይጠበቅብሃል በማለት ቢናገሩ ደስ ይለኛል፡፡
>
> ሱፐርቫይዘሮቻችን ከማስተማር ልምምድ በኋላ ሊያወያዩን ይገባ ነበር፡፡
>
> . . . እንዴት እንደታየ አላውቅም . . . እኛ ባደረግነው የማስተማር ልምምድ ላይ እስ፡ሁን የተሰጠን አስተያየት የለም፡፡ ይህ ደግሞ በኮሌጁ ውስጥ የላላ ስርዓት እንዳለ ያመለክታል፡፡
>
> ሱፐርቫይዘሬ ከጎበኘኝ በኋላ ምንም ዓይነት አስተያየት አይሰጠኝም፡፡

እነዚህ ከፍ ሲል የተጠቀሱት አስተያየቶች ሱፐርቫይዘሮች ድህረ ማስተማር ውይይቱን ለማከናወን የሚያስችል ክትትል እንደማያደርጉና ለመከታተል ቢሞክሩም ለተማሪ አስተማሪዎች ጠቃሚ የሆነ ምግበ መረጃ እንደማይሰጡ ጠቋሚዎች ናቸው፡፡

#### 4.3.3.3.2 የሱፐርቫይዘሮች አስተያየት

የሱፐርቪዥኑን ሂደት በሚመለከት በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሰርተፍኬት መርሃ ግብር ሱፐርቫይዘሮች ያላቸውን አስተያየት በጽሁፍ እንዲገልፁ በተጠየቁት መሠረት የሚከተለውን ምላሽ ሰጠተዋል፡፡

አንዳንድ የተማሪ አስተማሪዎች በተመደቡበት ክፍልና ክፍለ ጊዜ አለመገኘታቸው ሱፐርቪዥኑ በታሰበው መልክ ለማካሄድ አልተቻለም።

በኮሌጁ የተዘጋጀው የመገምገሚያ ቅጽ ተማሪ ተኮር በሆነ መልኩ ባለመዘጋጀቱ በሱፐርቪዥኑ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል።

ሱፐርቪዥኑን ለመከታተል የሚያስችል ገለፃ ለሱፐርቫይዘሮች ቢሰጥ ጥሩ ነው።

ስለሱፐርቪዥኑ ዓላማና አተገባበር ከተባባሪ ት/ቤት መደበኛ መምህራን ጋር ውይይት ቢደረግ መልዐም ነው።

ከላይ በሱፐርቫይዘሮች የተሰጡትን አስተያየቶች ስንመለከት የሱፐርቪዥኑን በመከታተል ሂደት እንቅፋት ሊፈጥሩ የቻሉ የተለያዩ ችግሮች መታየታቸውን ገልጸው መፍትሔ ነው ያሉትን ሐሳቡም አያይዘው ጠቁመዋል።

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳብ

### 4.1 ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ መምህራንን በማስልጠኑ ሂደት የፕራክቲከም፣ የማስተማር ልምምድና የሚካሄደውን የሱፐርቪዥን አተገባበር ለመፈተሽ ጥረት ተደርጓል። በዚሁ መሠረት የመምህራን ስልጠና በፕራክቲከምና በማስተማር ልምምድ መታገዙ አስፈላጊ መሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም አተገባበሩን የሚያስተጓጉሉ ችግሮች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል።

በጥናቱ ውስጥ በተተነተኑት መረጃዎች መሠረት ፕራክቲከሙን፣ የማስተማር ልምምዱን እንዲሁም የሚካሄደውን ሱፐርቪዥንና የምግበ መረጃ ልውውጥ ሂደቱን በአግባቡ ለማከናወን እንዳይቻል ያደረጉትን ዋና ዋና ጉዳዮች እንደሚከተለው በቅደም ተከተል ለማስቀመጥ ተሞክሯል።

1. በኮሌጁ የቅድመ ፕራክቲከም ውይይት አለመካሄድ፦ በመምህራን ስልጠና ሂደት ፕራክቲከም ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ይታወቃል። ይሁን እንጂ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ካለፈው አመት ጀምሮ ስልጠናው በፕራክቲከም እንዲታገዝ ቢደረግም የአተገባበር ችግር ታይቶበታል። ከችግሮቹ መካከል ቅድመ ፕራክቲከም መደረግ የነበረበት ውይይት አለመኖር ተጠቃሽ ነው። ቅድመ ፕራክቲከም ውይይት ባለመካሄዱ የተማሪ አስተማሪዎች በፕራክቲከም ምልከታቸው ወቅት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ባለመረዳታቸው ሲቸገሩ የታዩ ከመሆናቸውም በላይ ከምልከታ መልስ የሚያቀርቡትን የጽሁፍ ሪፖርት እንዴት ሊያዘጋጁ እንደሚችሉ ገለፃ ስላልተደረገላቸው ሪፖርቱን ለማዘጋጀት መቸገራቸው ታውቋል። ይህም የተከሰተው የፕራክቲከሙ የሥራ አቅጣጫ ለሱፐርቫይዘሮች ግልጽ ካለመሆኑ የተነሳ፣ ፕሮግራሙ በግድ እየተገፋ በመምጣቱና የደረሰበት ይድረስ ተብሎ የሚንጠረዘዝ የአተገባበር ችግር የሚታይበት በመሆኑ ይመስላል።
2. መደበኛ መምህራን ስለፕራክቲከም ያላቸው ግንዛቤ አናሳ መሆን፦ በፕራክቲከም የተደገፈ የመምህራን ስልጠና ውጤታማ የሚሆነው ሱፐርቫይዘሮችና መደበኛ መምህራን ጥበባዊ ምልከታ በማድረግ የተማሪ አስተማሪዎችን መርዳት ሲችሉ ብቻ መሆኑ ግልጽ ነው። አሁን ባለው ሁኔታ ሱፐርቫይዘሮችም ሆኑ የተባባሪ ት/ቤት መደበኛ መምህራን ፕራክቲከሙን በሚመለከት የወሰዱት ስልጠና ባለመኖሩና ስለ

ፕራክቲከም ያላቸው ግንዛቤ አናሳ በመሆኑ ለፕሮግራሙ መሳካት የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት ሲቸገሩ ታይተዋል:: ይሁን እንጂ አንዳንድ መደበኛ መምህራን ካላቸው ቅን አመለካከት በመነጨ በፕራክቲከሙ ሂደት መጠነኛ አስተዋጽኦ ሲያደርጉ መታየታቸው አይካድም::

3. **በኮሌጁ የማስተማር ልምምድን በአግባቡ አለመከታተል፡-** የማስተማር ልምምድ የተማሪ አስተማሪዎች የቀሰሙትን ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀት፣ የማስተማር ዘዴና መርህ በአንድ የመማሪያ ክፍል አውድ በሱፐርቫይዘሮች እየተጎበኙ የሚያከናውኑት ተግባር ነው (Tann 1994:94):: ብዙዎቹ የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ግን ይህን ጉዳይ ችላ በማለትና የስልጠናው አንዱ ክፍል መሆኑን በመዘንጋት ለይስሙላ በስልጠናው ማጠናቀቂያ ላይ ሲያካሂዱት እንደነበር ይታወሳል:: በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ያለው የማስተማር ልምምድ ከነዚህ ችግሮች የተላቀቀ መስሎ አይታይም:: እንደ ፕራክቲከሙ ሁሉ የማስተማር ልምምዱም በቅድመ ማስተማር ልምምድ ውይይት ሲደገፍና በቂ የሆነ ክትትል ሲደረግለት አልታየም::

4. **ሱፐርቪዥኑ የተማሪ አስተማሪዎችን በመገምገምና በመመዘን ላይ ብቻ ያተኮረ መሆኑ፡-** ሱፐርቪዥን ድክመትን የመፈለግ ሂደት ሳይሆን የተማሪ አስተማሪዎችን የመምራት፣ ከጥሩ የማስተማር ዘዴ ጋር የማስተዋወቅ፣ የተለያዩ የማስተማሪያ ሞዴሎችን የማሳየት፣ የመምከርና የማበረታታት እንቅስቃሴ እንጂ የመገምገምና የመመዘን ሂደት ብቻ እንዳልሆነ ይታወቃል:: በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሚካሄደው ሱፐርቪዥን ግን ከዚህ በተለየ ግምገማ ላይ ያነጣጠረ ነው:: አብዛኞቹ ሱፐርቫይዘሮችም ሂደቱን ሲከታተሉ የነበረው ኮሌጁ ያዘጋጀውን የመገምገሚያ ቅጽ በመጠቀም ሲሆን የተወሰኑት ግን የየራሳቸውን ማስታወሻ በመመዝገብ በድህረ ማስተማር ልምምድ ውይይት ወቅት ለተማሪ አስተማሪዎች የሚገልፁላቸውን መረጃዎች ይይዙ እንደነበር ታውቋል::

5. **የምግበ መረጃ ውይይቱ በአብዛኛው በተማሪ አስተማሪዎች ደካማ ጎን ላይ ያነጣጠረ መሆኑ፡-** በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የምግበ መረጃ ውይይት የትኩረት አቅጣጫ በአብዛኛው የተማሪ አስተማሪዎች ደካማ ጎን ላይ ያነጣጠረ ከመሆኑም በላይ በውይይቱ ወቅት ሱፐርቫይዘሮች ተናጋሪ የተማሪ አስተማሪዎች ደግሞ አድማጭ በመሆናቸው ራሳቸውን በራሳቸው ከመመርመር ይልቅ ሁልጊዜ ተማሪ ሆነው በሱፐርቫይዘሮቻቸው የሚቀርብላቸውን አማራጭ የሌለው ሐሳብ እንዲቀበሉ ያደርጋቸዋል::

6. **በፍላጎት ላይ ያልተመሰረተና ዝቅተኛ ውጤት ያላቸውን ሰልጣኞች በመቀበል ማሰልጠን ፡-** ኮሌጁ የትምህርት ጥራትን ከማስጠበቅ አኳያ ለመምህርነት ሙያ ልዩ ፍቅር ያላቸውንና ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ሰልጣኞችን መቀበል ሲገባው የ2ኛ ደረጃ

መልቀቂያ ፈተና ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑትንና ለሙያው ፍቅር የሌላቸውን ተቀብሎ በማሰልጠን ላይ" መሆኑ የታሰበው ውጤት ላይ እንደይደርስ እንቅፋት ሊፈጥር እንደሚችል ይገመታል።

## 5.2 የመፍትሄ ሐሳብ

ከፍ ሲል በማጠቃለያው ላይ ለማንሳት እንደተሞከረው በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ መምህራንን በማሰልጠኑ ሂደት የፕራክቲከም፣ የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥን አተገባበሩ ችግሮች የሚታዩበት በመሆኑ አፋጣኝ መፍትሄ ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን ይህ ጥናት ይጠቁማል። በዚሁ መሠረት በጥናቱ የተተነተኑትን መረጃዎች መነሻ በማድረግ በአሁኑ ወቅት መምህራንን በማሰልጠኑ ሂደት የሚታዩትን ችግሮች ለመቅረፍ ከዚህ በታች ያሉትን የመፍትሔ ሐሳቦች ለመሰንዘር ተሞክሯል።

1. ኮሌጁ ፕራክቲከሙ የመምህራን ስልጠናው መሠረታዊ ክፍል መሆኑን በመገንዘብ ፕራክቲከሙን እንዲከታተሉ የሚመደባቸው ሱፐርቫይዘሮች ስለ ፕራክቲከም ምንነትና አተገባበር በቂ ዕውቀት የሚያገኙበትን መንገድ መቀየስ ይኖርበታል። ለተባባሪ ት/ቤት መደበኛ መምህራንም እንዲሁ መመሪያዎችን መስጠት ይጠበቅበታል።

2. በሱፐርቫይዘርነት የሚመደቡ የኮሌጁ መምህራን ፕራክቲከሙንና የማስተማር ልምምዱን በአግባቡ ለመከታተል ይችሉ ዘንድ ያለባቸውን የስራ ጫና ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መመደብ ይኖርባቸዋል።

3. ሱፐርቫይዘሮች ከተማሪ አስተማሪዎች ጋር ቅድመ ፕራክቲከምና የማስተማር ልምምድ ውይይት በማድረግ የተማሪ አስተማሪዎች በፕራክቲከም ምልከታና በማስተማር ልምምድ ወቅት ምን ምን ተግባራትን ማከናወን እንዳለባቸው ሊገለጽላቸው ይገባል።

4. በሱፐርቪዥኑና በምግበ መረጃ ውይይቱ ወቅት ሱፐርቫይዘሮች ተናጋሪ የተማሪ አስተማሪዎች ደግሞ አድማጭ ሳይሆኑ ሁለቱም ወገኖች ሐሳብ የሚለዋወጡበትን ሁኔታ በማመቻቸት ሱፐርቪዥን ለመገምገምና ለመመዘን ብቻ የሚያገለግል አለመሆኑ መገንዘብ ይገባል።

5. McIntyre and et al (1994:13-14) እንደገለፁት ቀደም ሲል በየትኛውም ሀገር ጀማሪ መምህራንን የማሰልጠኑ ኃላፊነት ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ለመምህራን ማሰልጠኛዎች ብቻ ተትቶ እንደነበር ይታወሳል። ይሁን እንጂ መምህራንን የማሰልጠኑን ሂደት ከግብ ለማድረስ ተባባሪ ት/ቤቶች ከማሰልጠኛ ተቋማት ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት የሚችሉበትን መንገድ ኮሌጁ ማመቻቸት ይጠበቅበታል። በጥናቱ እንደተረጋገጠው ኮሌጁ ከተባባሪ ት/ቤቶች ጋር ሳይነጋገር የተማሪ አስተማሪዎችን ለፕራክቲከምና ለማስተማር ልምምድ በመመደቡ

የተማሪ አስተማሪዎቹ ከፍተኛ መንገላታት ደርሶባቸዋል፡፡ ስለዚህ ከተባባሪ ት/ቤቶች ጋር በቅርበት በመገናኘት ቅድሚያ በመመካከር ሊከሰት የሚችለውን ችግር ማስቀረት መቻል ይኖርበታል፡፡

6. ሱፐርቫይዘሮች በድህረ ማስተማር ልምምድ ውይይቱ ወቅት በተማሪ አስተማሪዎች ደካማ ጎን ላይ ከማተኮርና አማራጭ የሚያሳጣ ሐሳብ ከማቅረብ በመቆጠብ የተማሪ አስተማሪዎች የራሳቸውን ሐሳብና ስሜት የሚገልፁበትን ሁኔታ መፍጠር ይጠበቅባቸዋል፡፡

7. የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ለመምህርነት ሙያ ፍቅር ያላቸውንና ጥሩ ውጤት ያስመዘገቡ ሰልጣኞችን በመመልመል ማሰልጠን የሚጠበቅበት መሆኑን በመጠቆም ጥናቱ ተጠናቋል፡፡

# ዋቢ ጽሁፎች


ሳህሉ አክሊሉ:: 1986:: "በአማርኛ ቋንቋ ንዑስ የማስተማር ልምምድ ውስጥ የተማሪ አስተማሪዎች ይዘትንና የማስተማር ዘዴዎችን ማዛመድ ያቅታቸዋል::" ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ለሴሚናር የቀረበ::

ዓለም እሸቱ:: 1988:: "በኮ.መ.ት.ኮ. በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል ድህረ የማስተማር ልምምድ ውይይት የሱፐርቫይዘሮች ምግበ መረጃ ትንተና::" አ.አ.ዩ፣ (ያልታተመ)::

ደረጀ ገብሬ:: 1986:: "በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በዲፕሎማ መርሃ ግብር የሚሰጡ ዓቢይ የአማርኛ ኮርሶች ትንተናና ግምገማ::" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ /ያልታተመ/::

Abraham hagos and et al. 1999. Teacher Education Handbook. Addis Ababa: ICDR.

Alemayehu Debebe. 1998. "Teacher Education Trends in some countries: Implications for the Ethiopian contex. In Proceedings of the National Conference Held in Awassa College of Teacher Education (12-18 July).

Azeb Desta, 1971. "A Handbook for Elementary School Student-Teaching" A.A. Faculty of Education H.S.I.U (Unpublished).

Bartlett, L. 1990. "Teacher development through reflective teaching." In Richards, J.C and Nunan, D. (eds.) Second Language Teacher Education. Cambridge: CUP.

Belay T. and Gebre B. 1993. Critics on the Practice Teaching Programme of KCTE. A Paper Presented at the Multi-displinary Seminar at KCTE.

Brandt, R. 1987. On Cooperation in schools: A conversation with David and Roger Johnson. Educational Leadership, Vol. 45(3), PP. 14-19.

Breen, M. 1989. "The Evolution of Teacher Training Programme". In Johnson, R. The Second Language Curriculum. Cambridge: CUP.

Britten, D. 1988. "Three stages in Teacher Training". ELT Journal, Vol. 42 No. 1 PP.3-8.

Brown, R.W. 1990. "The place of Beliefs and Concept Formation in Language Teacher Training Theory" System, 18/2:85-96.

Calvert. M. and S. Fletcher. 1994. Working with your Student: Teachers. Cheltenham: Mary Glasgow Publications.

Cogan, M. 1973. Clinical Supervision. Boston: Houghton-Mifflin.

Curran, C. 1978. Understanding: A Necessary Ingredient in Human Belonging. Apple River, III.: Apple River Press.

De Bono, E. 1979. Lateral Thinking: Creativity Step by Step. New York: Harper and Row.

Dobbyn, M. and L.A. Hill. 1979. A Teacher Training Course for Teachers of EFL. London: Cassel.

Ellis, R. 1986. "Activities and Procedures for Teacher Training" ELT Journal, Vol. 40, No. 2 PP. 91.

Evertson, C. 1985. "Training Teachers in Classroom Management: An Experimental Study in Secondary Classrooms". The Journal of Educational Research, Vol. 79, No. 1.

Fanselow, J. F. 1990. " Let's see': Contrasting Conversations about teaching''.In Richards, J. C and Nunan, D. (eds.). Second Language Teacher Education. Cambridge: CUP.

Farrant, J.S. 1980. Principles and Practice of Education. Singapore: Longman.

Fidler, B. 1994. Improving Intial Teacher Training? New roles for Teachers, Schools and HE. Longman: BEMAS.

Fiseha M. 1993. An Assessment of the Training Pragramme Multi-displinary seminar at KCTE.

Fish, D. 1989. Learning Through Practice in Initial Teacher Training: A challenge for the Partners. London: Kogan Page.

Freeman, D. 1982. Observing Teachers: three Approaches to in Service Training and Development. TESOL Quarterly Vol.16, pp. 21-28.

Freeman, D. 1990. "Intervening in Practice Teaching". In Richards, J.C and Nunan, D. (eds.). Second Language Teacher Education. Cambridge: CUP.

Furlong, V. and et al. 1988. Initial Teacher Training and the Role of the School. Manchester: Open University Press.

Gaies, S. and Roger Bowers. 1990. "Clinical Supervision of Language Teaching: The supervision as trainer and educator. In Richards, J.C and David N. (eds) Second Language Teacher Education. Cambridge: CUP.

Gebhard, J. G. 1990. "Models of Supervision Choices. " In Richards, J.C and Nunan, D. (eds.) Second Language Teacher Education. Cambridge: CUP.

Gebremedhin simon. 2001. "Aspects of Teacher Development for English Language

Teaching:Implications for Quality of Education in Primary Schools.In Proceedings of the National Conference Held in Adama Ras Hotel,(November 9-11).

Gowers, R. and et al. 1995. Teaching Practice Handbook. London: Heinemann.

Hailom Bantyerga. 1997. "Context Generated Supervision in Teaching Practice: Skills in Observation and the management of feed back" In Proceedings of the first workshop on Teaching Practice. Addis Ababa: KCTE.

Haroldfs 2001. Language Classroom Observation Form. http://ccat.Sas.Upenn.edu/-haroldfs)pedagogy/evaluation/evaluate. html.

Jarvis, J. 1987. "Integrating Methods and Materials: Developing Trainees reading Skills" ELT Journal: Vol.41, No 3 , PP 181.

Kauffman, D. 1992. Supervision of Student Teachers. http://www. Ericdigests.org/1992-4/ student. htm.

KCTE 1992. Kotebe College of Teacher Education in (Catalogues) A.A.

Lemma Setegn and Taffesse Asfaw.1997. "Pre-Teaching practice Classroom Observation in the Coopating Schools: Principles, Practice and results." In Proceedings of the first workshop on Teaching Practice.Addis Ababa: KCTE.

Lovell, J. and Kimballwiles 1983. Supervision for Better Schools. Prentice-Hall, USA, Englewood Cliffs.

McIntryre, D. and et al. 1994. The management of Student Teachers' Learning: A Guide for Professional Tutors in Secondary Schools. London: KoGan Page.

MOE, 2003. Teacher Education System Overhaul (TESO) Handbook. Addis Ababa.

Moore, R. 1994. "Professionalism, Expertise and Control in Teacher Trainig. In Wilkin, M. and Sandkey, S. (eds). Collaboration and Transition in Initial Teacher Training. London: Kogan Page.

Nettle, T. 1988. " A Teaching and Learning Approach to Supervision within a Teacher Education Program" Journal of Education for Teaching. Vol. 14, No. 25.

Omotoso, S.O.1986. Hints on Teaching Practice. London: Macmillan Education LTD.

Pelletier, C.M 2000. Strategies for Successful teaching:A comprehensive Guide.Boston,MA:Allyn and Bacon.

Proctor, A. 1994. "Supervision Strategies and their Application in the School Context. In Wilkin, M. and Sankey, D. (eds.) Collaboration and Transition in Initial Teacher

Training. London: Kogan Page Lmited.

Richards, J. C. 1987. "The dilemma of Teacher Education. TESOL Quarterly Vol. 21/2 PP. 209-225.

Richards, J. C. and Nunan, D. 1990. Second Language Teacher Education. Cambridge: CUP.

Schon, D.A. 1983. The Reflective Practitioner: How in Professionals think in Action. London: Englewood Cliffs.

Sheal, P. 1989. "Classroom Observation: Training the Observers" ELT Journal ,Vol. 43/2 PP. 22-103.

Stones, E. and Morris, S. 1972. Teaching Practice Problems and Perspectives. London: Methuen and Co. Ltd.

Tann, S 1994. "Supporting the Student Teacher in the Classroom" In Wilkin, M.and Sankey,D. (eds). Collaboration and Transition in Initial Teacher Training. London: KOgan Page Limited.

Transitional Government of Ethiopia.1994.Educationa and Training Policy. Addis Ababa.

Ur, P. 1996. A course in Language Teaching Practice and Theory. Cambridge: CUP.

Wajnryb, R. 1992. classroom Observation Tasks. A resource book for Language teachers and Trainers. Cambridge: CUP

Wallace, M. J. 1991. Training Foreign Language Teachers: A reflective Approach. Cambridge: CUP.

Williams, M. 1989. "A developmental View of Classroom Observations." ELT Journal, Vol. 43/2, PP. 85-91.

Woodward, T. 1991. Models and Metaphors in Language Teacher Training. Cambridge: CUP.

Wragg, E.C. 1974. Teaching Teaching. London: David and Charles.

Zeichner, K. 1992. " Rethinking the Practicum in Professional Development School Partnership "Journal of Teacher Education. Vol. 39, No. 2, PP. 9-15.

Zeleke Demilew.1997. " Standardizing Supervisions' Evaluations". In Proceedings of the first workshop on Teaching Practice.Addis Ababa: KCTE.

# አባሪ ፩

# በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

# የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የዚህ ጥናት ዓላማ የፕራክቲክም ፣ የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥን አተገባበር በኮ.መ.ት.ኮ (10+1) ሰርተፍኬት መርሃ ግብር ምን እንደሚመስል በመቃኘት ድክመትና ጥንካሬውን መጠቆም ነው፡፡ ለጥናቱ መሳካት እናንተ እጩ መምህራን የምትይዙት ማስታወሻ ትልቅ እገዛ ያደርጋል፡፡

ስለዚህ ከዚህ በታች በቀረበላችሁ የማስታወሻ አያያዝ መመሪያ መሰረት ማስታወሻችሁን በመያዝ እንድትተባበሩኝ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

*I. አጠቃላይ መግለጫ*

- ማስታወሻው የሚያዘው በፕራክቲከምና በማስተማር ልምምድ ወቅት ነው፡፡
- በአራት ዙር ፕራክቲከም አራት ማስታወሻዎች ይያዛሉ፡፡
- በአራት ሳምንታት የማስተማር ልምምድ በየሳምንቱ አንድ አንድ ማስታወሻ ይያዛል፡፡
- ማስታወሻችሁ በፕራክቲከም ምልከታ እና ከምልከታ በኋላ ከሱፐርቫይዘራችሁ ጋር ባደረጋችሁት ውይይት ላይ ማተኮር ይኖርበታል፡፡
- የፕራክቲከም ማስታወሻችሁን በየዙሩ መጨረሻ፣ የማስተማር ልምምድ ማስታወሻችሁን በየሳምንቱ መጨረሻ ከእናንተ ለሚወከለው ተማሪ ታስረክቡልኛላችሁ፡፡
- ማስታዎሻዎቻችሁ ስርዝ ድልዝ ባይኖራቸው መልካም ነው፡፡

## II. *በፕሪክቲከምና በማስተማር ልምምድ ወቅት ማስታወሻ እንዴት ይያዛል?*

*ሀ. በፕራክቲከም ወቅት ማስታወሻ ስትይዙ ልታተኩሩባቸው የሚገባቸው ነጥቦች*

- በክፍል ውስጥ የቀሰማችሁትን ዕውቀትና በፕራክቲከም ወቅት የገጠማችሁ ነገር መጣጣም አስመጣጣሙን
- ለፕራክቱከም በተመደባችሁ ት/ቤት
  - የርዕሰ መምህራን ዕርዳታ
  - የክፍል መምህራን እገዛ
  - የጓደኞቻችሁ እገዛ ምን ይመስል እንደነበር
- የክፍል ውስጥ ምልከታ ስታደርጉ የተገነዘባችሁትን ነገር

- ሱፐርቫይዘራችሁ ለፕራክቲከም ከመውጣታችሁ በፊት ስለተመደባችሁበት ት/ቤት፣ በፕራክቲከሙ ወቅት መፈፀም ስላለባችሁ ተግባር ያደረጉላችሁ ገለፃ መኖር አለመኖሩን
- ሱፐርቫይዘራችሁ ወደተመደባችሁበት ት/ቤት መጥቶ የጐበኛችሁ ስለመሆኑ
- ከመጀመሪያው፣ ሁለተኛው፣ ሦስተኛውና አራተኛው የፕራክቲከም ምልከታችሁ በኋላ ከሱፐርቫይዘራችሁ ጋር ያደረጋችሁትን ውይይት በተመለከተ
- ውይይቱ በጠንካራ ወይም በደካማ ጐናችሁ ላይ ብቻ ያተከረ ውይይቱ በጠንካራና ደካማ ጐናችሁ ላይ ያተከረ ስለመሆኑ
- በውይይቱ ወቅት የሱፐርቫይዘራችሁና የእናንተ ሚና ምን ይመስል እንደነበር
- ከሱፐርቫይዘራችሁ ጋር ስትወያዩ የተሰማችሁን ስሜት (ለምሣሌ ጥሩ ወይም መጥፎ ስሜት ከተሰማችሁ)
- የፕራክቲከም ውጤታችሁን ስታውቁ የተሰማችሁን ስሜት
- አጠቃላይ ከፕራክቲከሙ ያገኛችሁትን እውቀት
- በንድፈ ሀሣብ ደረጃ የቀሰማችሁት እውቀትና በተግባር የተመለከታችሁት ነገር መጣጣም አለመጣጣሙን
- አጠቃላይ ለፕራክቲከሙ ያላችሁን አመለካከት ወዘተ. ጠቅሳችሁ ማስታወሻ ብትይዙልኝ መልካም ይሆናል።

*ለ .በማስተማር ልምምድ ወቅት ማስታወሻ ስትይዙ ልታተኩሩባቸው የሚገባቸው ነጥቦች*

- በየተመደባችሁበት ክፍል ዕለት በዕለት የሚያጋጥማችሁን ነገር ሁሉ
- ሱፐርቫይዘራችሁ የሚያደርግላችሁን እገዛ
- የነባር መምህራን ክትትልና እገዛ ምን ይመስል እንደነበር
- በአጠቃላይ የተመደረባችሁበት ት/ቤት ማህበረሰብ ለእናንተ ያለውን አመለካከት
- ሱፐረቫይዘራችሁ በምታስተምሩበት ክፍል ሲገኝና ሳይገኝ የሚሰማችሁን ስሜት
- ለማስተማር የምታደርጉትን ዝግጅት
- በፕራክቲከም ወቅት በምልከታ ያገኛችሁት እውቀት ለማስተማር ልምምዱ ያደረገላችሁን አስተዋጽኦ ወዘተ. መሰረት በማድረግ ማስታዎሻችሁን ብትይዙልኝ ተመራጭ ነው።

*ስለ ትብብራችሁ ከልብ አመሰግናለሁ*

# አባሪ ፪

## የተማሪ አስተማሪዎች ማስታወሻ ናሙናዊ ጥንቅር

### 1.1 በተቋሙ የቀሰሙት ንድፈ ሐሳብ ለፕራክቲከም ምልከታ ያለውን አስተዋጽኦ በሚመለከት

- በክፍል ውስጥ የቀሰምኩት ትምህርት በተባባሪ ት/ቤት ውስጥ ካለው የፕራክቲከም ተግባር ጋር ያለው ልዩነት እንደየትምህርት ዓይነቱ የተለያየ ነው፡፡ ለምሳሌ ሒሳብ በክፍል ውስጥ ስንማር በጣም ከባድ ነው፡፡ ነገር ግን የክፍል መምህሩ ሲያስተምር ቀላል ይመስላል፡-
- በክፍል ውስጥ ብዙ ዓይነት ትምህርቶችን ተምረናል፡፡ በፕራክቲከሙ ወቅት የገጠመኝ ነገርም እንዳሰብኩት ነው፡፡ ትንሽ ፍርሃት ግን ነበረብኝ፡፡
- በክፍል ውስጥ ብዙ ነገሮችን የተማርኩ ቢሆንም ደካማ ተማሪዎችን እንዴት መርዳት እንዳለብኝ ግን አልተማርኩም፡፡ በፕራክቲከም ወቅት ግን እንዴት ደካማ ተማሪዎችን ልረዳ እንደምችል ተገንዝቤያለሁ፡፡
- በክፍል ውስጥ ያገኘነው እውቀት ከፕራክቲከሙ ጋር አይጣጣምም በክፍል ውስጥ የምናገኘው ዕውቀት በማስመሰል የሚቀርበው ነው፡፡ ሕፃን አጠገባችን ሳይኖር እኛ እንደህፃን እየሆን የምናስተምርበት ዘዴ ነው፡፡ ለፕራክቲከም በወጣንበት ት/ቤት የነበሩ ሕፃናት በጣም አስቸጋሪዎች በመሆናቸው ወደፊት ራሳችንን አስተካክለን ለመገኘት ያስችለናል፡፡
- መምህራኑ ክፍል በመገኘት የሚያስተምሩን አልፎ አልፎ በመሆኑ ብዙም ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀት አልቀሰምንም፡፡ በፕራክቲከም ግን ለየት ያለ ዕውቀት ነው ያገኘ ነው፡፡ ምክንያቱም በመደበኛው የመማሪያ ክፍል ተገኝተን የመማር ማስተማሩን ሂደት በአይናችን በማየት ለመገንዘብ ችለናል፡፡
- በተቋሙ ለሁሉም ተማሪ እኩል አመለካከት ሊኖረኝ እንደሚገባ ተምሬያለሁ፡፡ የማስተምረው ትምህርት እጥር ምጥን ያለ ሆኖ የተማሪዎቹን ዕድሜና ችሎታ ያገናዘበ መሆን እንዳለበት ተገንዝቤያለሁ፡፡ በፕራክቲከም ይህ ሁሉ እንዴት ሊተገበር እንደሚችል በአይኔ ለማየት በቅቻለሁ፡፡
- አንድን ዕውቀት ለመተግበር መንደርደሪያው ንድፈ ሐሳብ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በንድፈ ሐሳብ ደረጃ የቀሰምነውና በተግባር የተመለከትነው ነገርም ይጣጣማል፡፡

- ለፕራክቲከም በወጣሁበት ወቅት የገጠመኝ ነገር በክፍል ከቀሰምኩት ዕውቀት ጋር ይጣጣማል:: ምክንያቱም በክፍል ውስጥ ስማር ስለተማሪዎቹ ባህሪ፣ እንዴት ማስተማር እንደለብኝ ወዘተ ግንዛቤ አግኝቻለሁ:: ስለሆነም ለፕራክቲከም ስወጣ የገጠመኝ ቀድሜ የተማርኩን ነው::
- በንድፈ ሐሳብ ደረጃ የቀሰምነው ዕውቀት በክፍል ውስጥ ሲተገበር ከምናየው ጋር መጣጣም አለመጣጣሙን መመልከታችን ለእኛ በጣም ጥሩ ነው:: ምክንያቱም እንድናስተምር ስንመደብ ተማሪዎቹን ስለምናውቃቸው ችግር አይፈጠርም:: የየራሳችንን በቂ ዝግጅት እንድናደርግ ይረዳናልና::
- በክፍል ውስጥ ስንማር ሕፃናት ምንም እንደማያውቁ በተለይም ቁጥር እንደማይችሉ ተደርጎ ነው የተገለፀልን:: ስናስተምርም ቁጥሮችን መደጋገም እንዳለብን ተነግሮን ነበር:: ለፕክቲከም ወጥተን የተገነዘብነው ግን አብዛኞቹ ተማሪዎች ቁጥሮችን መፃፍም ሆነ ማንበብ በሚገባ የሚችሉ መሆኑን ነው::
- በክፍል ውስጥ የቀሰምኩት ዕውቀት በተግባር በፕራክቲከም ምልከታ ወቅት ካየሁት ጋር ይጣጣማል:: ለምሳሌ በ PS III ኮርስ የተማርነው ስለህፃናት ባህሪ ነው:: በፕራክቲከም ተግባር አንድ ላይም ያጠናሁት ስለተማሪዎች ባህርያት ነው:: ስለዚህ ለዚህ ጥናት በክፍል ውስጥ የቀሰምኩት ትምህርት አግዞኛል::

## 1.2 ከፕራክቲከም ምልከታ ያገኙትን ዕውቀት በሚመለከት

- በክፍል ምልከታ ወቅት ተማሪዎችን እንዴት መቆጣጠርና ማነቃቃት እንደሚቻል ተገንዝቤያለሁ::
- ሕፃናትን ሳስተምር ምን ዓይነት የማስተማር ዘዴን መጠቀም እንዳለብኝና ተማሪዎችን በምን ዓይነት መልኩ እንደምቀርባቸው ተምሬያለሁ::
- በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚሰቃቀሉ የተለያዩ መርጃ መሣሪያዎች መኖራቸውን አይቻለሁ::
- የነባር መምህራንን የማስተማር ስልትና የክፍል ቁጥጥር በመመልከት ጥሩ ዕውቀት አግኝቻለሁ::
- ዕጩ መምህራን እንደመሆናችን መጠን ወደፊት ሊገጥሙን የሚችሉ ነገሮችን ሁሉ እንድናውቅ ረድቶኛል::
- የመምህርነት ሥራ በጣም ትዕግስትንና መስዋዕትነትን የሚጠይቅ እንደሆነ ተረድቻለሁ::

- ከፕራክቲከም ምልከታዬ የተገነዘብኩትና በጣም ያስደሰተኝ ነገር ቢኖር የመማሪያ ክፍሉ ግድግዳ ዙሪያውን በየተማሪዎቹ ስም/ለእያንዳንዳቸው አንድ አንድ ጥቁር ሰሌዳ ያላቸው መሆኑ ነው:: በክፍል በመምህሩ ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ ተነስተው ስማቸው ወደ አለበት ጥቁር ሰሌዳ በመሄድ የተጠየቁትን ጥያቄ ይሰራሉ::
- በአጠቃላይ ከፕራክቲከም ያገኘሁት እውቀት በጣም ብዙ ነው:: ለምሳሌ ከብዙ መምህራን ጋር ተዋውቄያለሁ:: የማስተማር ስልታቸውንም አይቻለሁ:: ልምድ ቀስሜያለሁ:: በራስ የመተማመን መንፈስ እንዲኖረኝም ትልቅ እገዛ አድርጎልኛል::
- በፕራክቲከም ምልከታዬ ወቅት የተገነዘብኩት ነገር ቢኖር የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎችን በክፍል ውስጥ መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን፣መሣሪያዎቹን በግድግዳው ላይ መለጠፍ ተማሪዎች ቀና ባሉ ቁጥር ሊማሩባቸው መቻላቸውን ነው::
- ከፕራክቲከም ምልከታዬ የተረዳሁት ተማሪዎች በክፍልና ከክፍል ውጭ ያላቸው ባህሪ ምን እንደሚመስል ነው::

### 1.3. ሱፐርቫይዘራቸው ለፕራክቲከም ከመውጣታቸው በፊት ገለፃ ያደረገላቸው መሆኑን በሚመለከት

- ለፕራክቲከም ከመውጣታችን በፊት ምንም ዓይነት ገለፃ አልተደረገልንም፣ እንኳንስ ገለፃ ሊያደርግልን ይቅርና እስካሁንም ተያይተን አናውቅም::
- ሱፐርቫይዘራችን ምንም አይነት ገለፃ አላደረገልንም:: የሰራነውን የፕራክቲከም ሪፖርት በተወካያችን በኩል መላክ ነው እንጂ ሱፐርቫይዘሩን ከስሙ በስተቀር መልኩን አናውቀውም::
- እንኳንስ ገለፃ ሊያደርጉልን ቀርቶ እኛ የእነሱን ማንነት አናውቅም፣ እነሱም የእኛን ማንነት አያውቁም::
- ሱፐርቫይዘራችን የምናዘጋጀው ሪፖርት ሊያተኩርበት የሚገባው በምን በምን ላይ እንደሆነ የሚጠቁመውን ወረቀት አስረክቦን ተመለሰ እንጂ ት/ቤት ሄዳችሁ ይህን ካደረጋችሁ በኋላ በእንዲህ ያለ መንገድ አዘጋጁ አላለንም::
- ሱፐርቫይዘራችን ለፕራክቲከም ከመውጣታችን በፊት ስለተመደብንበት ት/ቤትም ሆነ በፕራክቲክሙ ወቅት መፈፀም ስላለብን ተግባር ምንም ዓይነት ገለፃ አላደረጉልንም:: የተመደብንበትን ት/ቤት በማስታወቂያ፣ ምን መስራት እንዳለብን ደግሞ በወረቀት ተጽፎ ነው የተሰጠን::

- የፕራክቲከም ጥያቄውን እንኳን መጥቶ አልሰጠንም፡፡ በተወካያችን አማካይነት ላከልን እንጂ፡፡
- ሱፐርቫይዘሬ እራሱ የትኛው እንደሆነ ለኔ ግልጽ አይደለም፡፡ በሄድንበት ት/ቤት ያለው ነው? ወይስ ፕራክቲከም የሚቀበለን ነው? ማንም መጥቶ ስለየትኛውም ሁኔታ የነገረን ነገር የለም፡፡
- ሱፐርቫይዘራችን ለፕራክቲከም ከመውጣታችን በፊት ስለት/ቤቱ፣ በፕራክቲከም ወቅት መፈፀም ስላለባቸው ነገሮች ያደረገልን ገለፃ በጭራሽ የለም፡፡
- እንኳንስ ገለፃ ሊያደርግልን ይቅርና ጥያቄውንም በእጃችን አላስረከበንም፡፡ ያወቅኩት ተግባር አንድን ሳስረክብ ነው፡፡

## 1.4 የርዕሰ መምህራንና የነባር መምህራን እገዛን በሚመለከት

- ለፕራክቲከም ተግባር በወጣን ቁጥር የምናገኛቸው ተማሪዎችንና ነባር መምህራንን መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህም የተለያዩ እርዳታዎችን ከመምህሩ ለመጠየቅ ምቹ ሁኔታ ፈጥሮልን እንጠይቃለን፤ እነሱም ይተባበሩናል፡፡
- ነባር መምህሯ ለእኔ በጣም ነው የረዳችኝ፡፡ ገለፃ በማድረግም ሆነ የሚያስፈልጉኝን ማቴሪያሎች በማሳየት በጣም እረድታኛለች፡፡
- ነባር መምህሩ ወደ ክፍል በምገባበት ጊዜ ተማሪዎችን ፀጥ በማስባል ይተባበሩኛል፡፡ ለእኔ ያላቸው አመለካከትም ቀና ነው፡፡
- ወደ ክፍል መጀመሪያ ስገባ ጥሩ አቀባበል አድርገውልኛል፡፡ ነገር ግን ገብቼ ከተቀመጥኩ በኋላ ምንም ዓይነት እገዛ አላደረጉልኝም፡፡
- በምን መልኩ ሕፃናትን ማስተማር እንዳለብኝና ምን ዓይነት ፀባይ ለተማሪዎች ማሳየት እንዳለብኝ አስረድተውኛል፡፡
- በፕራክቲከም ዙሪያ ከሆነ ምንም ዓይነት እገዛ አላደረጉልኝም፡፡
- እኔ የገባሁበት ክፍል መምህርት እኔ ጠይቄያት ሳይሆን ራሷ ምን ልርዳሽ በማለት የእረፍት ሰዓቷን ሳይቀር መስዋዕት በማድረግ ረድታኛለች፡፡ ለእኔ ሊጠቅመኝ የሚችለውን ነገር ሁሉ በሚገባ ገልፃልኛች፡፡
- የፈለግነውን መረጃ በመስጠት ጠንክረን እንድንማርና እንድንበረታ ጥሩ ምክር ለግሰውናል፡፡
- እኔ የተመደብኩበት ክፍል መምህር ምንም ዓይነት እገዛ አላደረጉልኝም፡፡ ተማሪዎቹም እንደ መምህር አልተመለከቱኝም፡፡
- የክፍል መምህሯ እንኳንስ እኔን ልትረዳኝ ይቅርና የሆነ ነገር ላደርግ የመጣሁ ስለመሰላቸው በጣም የመንቀጥቀጥና ግራ የመጋባት መንፈስ ይታይባቸው ነበር፡፡ የማደርገውን ነገር ብነግራቸውም ግራ መጋባቱ አለቀቃቸውም፡፡

- የክፍል መምህሩ ወደ ውስጥ ይዞኝ ከገባ በኋላ ምንም ሳያነጋግረኝ ቀጥታ ማስተማሩን ነው የቀጠለው::
- የርዕስ መምህሩ እርዳታ በጣም አነስተኛ ነበር:: እንኳንስ ሊረዳን ይቅርና በስነ ስርዓት የምንገባበትን ክፍል አላሳየንም::
- ለፕራክቲከም የተመደብንበት ት/ቤት ርዕሰ መምህር እርዳታ አድርገውልናል:: ምክንያቱም ከኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የስም ዝርዝራችን ባይደርሳቸውም ወደ ክፍል ገብተን ምልከታ እንድናደርግ ፈቅደውልናል::
- የስም ዝርዝራችን ያልደረሳቸው በመሆኑ ርዕሰ መምህሩ ወደቤታችን እንድንመለስ አድርገውናል::
- የክፍል መምህሩ እኔ ከመጠየቄ በፊት ምን እንደሚያስፈልገኝ በመረዳት ሊያግዙኝ ይገባ ነበር:: ይህን አላደረጉም::
- ለኘራክቲከም የተመደብንበት ት/ቤት ርዕሰ መምህር ዕርዳታ ጥሩ ነው:: ገና ወደ ግቢ እንደገባን በትህትና በመቀበል የምንፈልገው ክፍል ድረስ ወስደው ከየክፍል መምህራን ጋር አስተዋውቀውናል::
- የክፍል መምህሯ ለወደፊቱ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ትመክረኛለች በማስተማር ልምምድ ጊዜ እንዳልቸገርና እንዳልፈራ በኘራክቲከም ወቅት አንድ ክፍል ጊዜ እንዳስተምር አድርጋኛ ለች::
- ለኘራክቲከም የተመደብንበት ት/ቤት ርዕሰ መምህር በወቅቱ አልነበሩም ም/ር/መምህሩ ግን ምንም ዓይነት እገዛ አላደረጉልንም:: ት/ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ለብዙ ሰዓት ተንገላተን ስናናግራቸው የራሳችሁ ጉዳይ እኔ አያገባኝም ነበር ያሉን::

## 1.5 ሱፐርቫይዘራቸው ለኘራክቲከም ወደተመደቡበት ተባባሪ ት/ቤት መጥቶ የጎበኛቸው ስለመሆኑ

- ሱፐርቫይዘሬ ኘራክቲከም ወደተመደብኩበት ት/ቤት መጥቶ አያውቅም::
- እንኳንስ መጥቶ ሊጎበኘን ይቅርና እዚያው ኮሌጁ ቅጥር ግቢ ስለፕራክቲከሙ አነጋግሮን አያውቅም::
- አይደለም ሊጎበኘን ሊመጣ ይቅርና የት እንደተመደብን እንኳን የሚያውቅ አይመስለኝም::
- ከመጀመሪያው እስከ አራተኛው ዙር ፕራክቲከም የተመደብንበት ት/ቤት ድረስ መጥቶ ሊረዳን ይቅርና የፃፍነውን ሪፖርት ለመስጠት ስንሄድ አንድ ቀን እንኳን በእጁ አልተቀበለንም::
- እስከ አሁን አራት ጊዜ ለፕራክቲከም ወጥተናል:: ነገር ግን ሱፐርቫይዘራችን መጥቶ አልጎበኘንም::

- ሱፐርቫይዘራችን በአሁኑም ሆነ ባለፈው ፕራክቲከም ጎብኝቶን አያውቅም::
- በመጀመሪያ ደረጃ ሱፐርቫይዘራችን አንድም ቀን መጥቶ ጎብኝቶን አያውቅም፤ ግንኙነታችን የሰራነውን የፕራክቲከም ወረቀት የመስጠትና የመቀበል ብቻ ነው::

## 1.6 ከመጀመሪያው፣ ከሁለተኛው፣ ከሦስተኛውና ከአራተኛው ዙር ፕራክቲከም በኋላ ከሱፐርቫይዘራቸው ጋር ውይይት ስለማድረጋቸው

- በአራቱም ዙር ምንም ዓይነት ውይይት አላደረግንም::
- ከሱፐርቫይዘራችን ጋር ውይይት ያደረግነው በመጀመሪያው ሴሚስተር ለአንድ ጊዜ ለዚያውም ለ25 ደቂቃ ብቻ ነበር:: ውይይቱም ስለ ኮሌጁ ደካማና ጠንካራ ጎንና ሔደንበት ስለነበረው ት/ቤት ችግር እንጂ እኛን በሚመለከት ምንም ዓይነት ውይይት አድርገን አናውቅም:: ስለጠንካራና ደካማ ጎናችን የምናውቀው ነገር የለም::
- አራቱንም ዙር ፕራክቲከም ወጥተን የፃፍነውን ሪፖርት ስናስረክብ አንዴ እንኳን እንወያይ ብሎን አያውቅም::
- እንዲያውም ሱፐርቫይዘሮቻችንን የምናውቃቸው በአካል ሳይሆን በስም ብቻ ነው:: ፈልገናቸው ወደ ቢሮአቸው ጎራ ባልን ቁጥር እነሱን ሳይሆን የተዘጋ ቢሮአቸውን ነው የምናገኘው:: የሚገኙበትን ሰዓት በቢሮአቸው በር ላይ ባለመለጠፋቸው ተቸግረናል::
- በሁሉም ዙር ፕራክቲከም አላወያየንም:: የሰራነው ሪፖርት እንኳን የሚሰበስበው በተወካያችን አማካይነት ነው::
- በሦስተኛው ዙር ፕራክቲከም ላይ ውይይት አድርገን ነበር:: የውይይቱ ትኩረት ግን በፕራክቲከሙ ጥያቄዎች ላይ ያተኮረ ነበር እንጂ አጋጥመውን በነበሩ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው ላይ አልነበረም::

## 1.7 በአጠቃላይ ከፕራክቲከም ያገኙትን ዕውቀት በሚመለከት

- ከፕራክቲከሙ ብዙ ትምህርት አግኝቻለሁ:: ለማስተማር ልምምድ ስወጣ ምንም ችግር የሚገጥመኝ አይመስለኝም:: ምክንያቱም በፕራክቲከም ተግባሮች ሁሉንም ነገር ተመልክቻለሁ::
- ለፕራክቲከም ወደተመደብንበት ት/ቤት በመሄድ ያቀረብነው የጽሁፍ ሪፖርት ተነቦ ጠንካራና ደካማ ጎናችን ስላልተገለፀልንና ምን ማድረግ እንዳለብን የተነገረን ነገር ባለመኖሩ ተገቢውን ዕውቀት አላገኘንም ባይ ነኝ::
- ከፕራክቲከሙ የመምህር ሙያ ትዕግስትን፣ ትህትናን፣ ግልጽነትን፣ ታማኝነትን፣ የሚጠይቅ መሆኑን ተገንዝቤያለሁ::

- ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ሕፃናት ስለሆኑ መረበሻቸው አይቀርም:: ስለዚህ በዱላ ከማስፈራራት ይልቅ በእርጋታ መምከር እንዳለብኝ ተረድቻለሁ::
- ልጆችን እንዴት እንደምናስተምር፣ መርጃ መሣሪያ እንዴት እንደምንጠቀም፣ ምን ዓይነት የማስተማር ዘዴ መጠቀም እንዳለብን ወዘተ. ተምሬያለሁ::
- ከትንሽ ጊዜ በኋላ መምህራን መሆናችን ስለማይቀር ሊገጥመን ከሚችለው ችግር ጋር አስተዋውቆናል::
- ከምንም ነገር በማስቀደም የተማሪዎችን ባህሪ አውቆ መቆጣጠር ማስፈለጉን አስገንዝቦኛል::
- ለልጆች እናታዊ/አባታዊ ፍቅርን ማሳየት እንዳለብኝ ተረድቻለሁ::
- ከፕራክቲከም የክፍል ምልከታዬ የተለያዩ ነገሮችን ተገንዝቤያለሁ:: እነሱም:-
  - የተማሪዎቹን ባህሪ
  - እንዴት ማስተማር እንዳለብኝ
  - ተማሪዎቹ ሊስተካከሉ የሚችሉት በምክር ወይስ በዱ ለሚለው ጥያቄ መልስ አግኝቻለሁ
- ከተለያየ የማስተማር ስልት ጋር ተዋውቄያለሁ:: ተማሪን እንዴት መቆጣጠር እንዳለብኝም ተረድቻለሁ::
- ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴን በመጠቀም ማስተማር እንዳለብኝ ተገንዝቤያለሁ መምህሩ ብቻ የሚነግራቸው ከሆነ እንቅልፍ ሊወስዳቸው ይችላል:: ስለዚህ አንድ ርዕስ በመስጠት እርስ በርሳቸው እንዲማማሩ ማድረግ ይገባል::
- ሕፃናትን እንዴት አድርጌ በማስተማር ለጥሩ ውጤት ማብቃት እንዳለብኝ ተገንዝቤያለሁ::
- ተማሪዎችን እንዴት ማነቃቃት፣ በምን ዓይነት መልኩ ማሳተፍና መቆጣጠር እንዳለብኝ በፕራክቲከም ወቅት አውቄያለሁ::
- በኘራክቲከም ምልከታዬ የተገነዘብኩት ትምህርቱን በተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴ ለማቅረብ የሚያስቸግር መሆኑን ነው:: ምክንያቱም:-
  - የወንበሮቹ አለመመቸት
  - የሚመሰረተው ቡድን መብዛት
  - የክፍል ጥበት ይህንን ዘዴ ለመተግበር አያስችሉም::

## 1.8 ለኘራክቲክም ያላቸውን አመለካከት በሚመለከት

- ፕራክቲከም በጣም ሊበረታታ የሚገባው ሲሆን ዕጩ መምህራን ስለማስተማር ሙያ በቂ ዕውቀት የሚያገኙበት የመጀመሪያ መንገድ በመሆኑ ሊቀጥል ይገባዋል::

- በየት/ቤቶች በመዘዋወር ልምድ እንድንቀስም፣ ከነባር መምህራን እንድንማር፣ ስለተማሪዎች ፀባይ እንድናውቅ ትልቅ እገዛ የሚያደርግ ፕሮግራም ስለሆነ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት::
- በአጠቃላይ ለፕራክቲከም ያለኝ አመለካከት በጣም ጥሩ ነው:: ብዙ የማላውቃቸውን ነገሮች አውቄበታለሁ:: ለምሳሌ አንድ ረባሽ ተማሪ ቢያጋጥመኝ ከመምታት ይልቅ መምከር እንዳለብኝ ተረድቻለሁ:: በመጀመሪያ ግን ቶሎ ስለምናደድ ልመታው እችል ነበር:: በፕራክቲከሙ ወቅት መምህሩ በምን ዓይነት መልኩ ረባሽ ተማሪዎችን እንደሚቆጣጠራቸው ተመልክቻለሁ::
- ፕራክቲከም ጥሩ ነው:: ከመምህርነት ሙያ ጋር በሚገባ ያስተዋውቃል ይሁን እንጂ ከተቋሙ ወደተመደብንበት ት/ቤት ስንሄድ የሆነ ፍንጭ ሲሰጠን ሲገባ አልተሰጠንም:: ት/ቤቶችም ከተቋሙ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ስለሌላቸው በአፈፃፀሙ ላይ ጉልህ ተጽእኖ አሳድሯል:: ለምሳሌ ለት/ቤቶች መላክ የነበረበት የፕራክቲከም መገምገሚያ ቅጽ ሳይላክ በመቅረቱ በት/ቤቱ መምህራን ሳንገመገም በመቅረታችን በውጤታችን ላይ ችግር ተፈጥሯል::
- ለፕራክቲከም በወጣንበት ት/ቤት ያገኘናቸው መምህራን ብዙ ዓመት የሥራ ልምድ ያላቸው ስለሆነ ለእኛ ብዙ ትምህርት አስተላልፈውልናል:: ስለዚህ ፕራክቲከም በመምህራን ስልጠና ትልቅ ቦታ ሊሰጠው ይገባል እላለሁ::
- ለፕራክቲከም ስንወጣ ተዘጋጅቶ የሚሰጠን ጥያቄ ተደጋጋሚ፣ አሰልቺና ግልጽነት የጎደለው ስለሆነ ይህ ችግር ተቀርፎ ፕራክቲከም ቢካሄድ ጥሩ ይሆናል የሚል አመለካከት አለኝ::
- ኘራክቲከም በጣም ጥሩ ነው:: ስለምንሄድበት ት/ቤትና አጠቃላይ ማድረግ ስላለብን ነገር አስቀድሞ ገለፃ ቢደረግልንና ከተባባሪ ት/ቤቶችም ጋር የጠበቀ ግንኙነት ቢኖር፣ ፕራክቲከሙ የታሰበውን ያህል ውጤት ሲያስገኝ ይችላልና ቢታሰብበት::
- ለኘራክቲከም ያለኝ አመለካከት ጥሩ ነው:: ምክንያቱም በክፍል ውስጥ ከምንቀስመው ዕውቀት ይልቅ ከፕራክቲከም የበለጠ እናገኛለን:: ለምሳሌ ነገሮችን በቅርብ ሆነን በስፋትና በጥልቀት እንድንገነዘብ፣ ያየነውን በቃላት አቀነባብረን ሀሳባችን በጽሁፍ እንድንገልጽ፣ የጻፍነውን በሱፐርቫይዘራችን ፊት እንድናቀርብ ወዘተ. ስለሚያደርገን ጥሩ ነው እላለሁ::
- ፕራክቲከም ጥሩ ነው እላለሁ:: ምክንያቱም የተማሪዎችን ባህሪ እንድናውቅ ረድቶናል::

## 2. የማስተማር ልምምዱን በተመለከተ

- በፕራክቲከም ሦስት ተግባር አራት ወቅት በክፍል ውስጥ ተገኝቼ የዕለቱን ትምህርት አቀራረብ ተመልክቼ ስለነበር የማስተማር ልምምዱን ስጀምር እንዳልቸገር አድርጎኛል:: ምክንያቱም መምህሩ ትምህርቱን እንዴት እንደሚያስተዋውቅና ክፍሉን እንዴት እንደሚቆጣጠር አይቼው ነበር::

- ተማሪዎቹ ወርሃዊ ፈተና ላይ ስለነበሩ በመጀመሪያው የማስተማር ልምምድ ሳምንት ለሁለት ቀን ያህል አላስተማርኩም::
- በማስተማር ላይ እንዳለሁ ድንገት ሱፐርቫይዘሬ በመምጣታቸው ከመደንገጤ የተነሳ ለማስተማር አቅቶኝ ነበር:: በተለይ የዕለቱን ዕቅድ ይገኙ ባለመግባቱ ሄጄ እንዳመጣ ብጠይቃቸው ዝም ብለሽ አስተምሪ ሲሉኝ በጣም ተደናገጥኩ::
- ሱፐርቫይዘሬ ከዕቅዴ ውጭ እንዳስተምር ስለጠየቁኝ የጀመርኩትን የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት አቋርጬ ሒሳብ ለማስተማር ተገድጃለሁ::
- አንድ ጊዜ ብቻ በክፍል ውስጥ ተገኝቶ ሲገመግመኝ ግርም ነው ያለኝ% ለዚያውም ለ15 ደቂቃ ብቻ:: ሌላ ት/ቤት የተመደቡ ጓደኞቼ ቢያንስ ሁለት ጊዜ ነው የተገመገሙት::
- ሱፐርቫይዘሬ ለ20 ደቂቃ ሳስተምር ከተመለከቱኝ በኋላ ከክፍል ወጥተን አስተያየት ሰጥተውኛል:: የክፍል ቁጥጥሬ የላላ እንደነበርም ነግረውኛል:: እኔም ድክመቴን ለማሻሻል እንደምሞክር ለራሴ ቃል ገብቻለሁ::
- በምገመገምበት ወቅት አስተምር የነበረው ትምህርት ሒሳብ ነው:: በዚያን ወቅት መጠነኛ ስህተት መፈፀሜን አላወቅኩም ነበር:: ነገር ግን አንዲት ተማሪ እጅዋን አውጥታ መሳሳቴን ስትነግረኝ በጣም ነው የደነገጥኩት::
- በማስተምርበት ጊዜ የክፍል መምህሯ ክፍል ውስጥ በመቀመጧ በነፃነት እንዳላስተምር እንቅፋት ፈጥሮብኛል::
- ለማስተማር ልምምዱ በቂ የሆነ ዝግጅት በማድረጌ ሱፐርቫይዘሬ በመጣ ጊዜ ምንም አልተረበሽኩም::
- ሱፐርቫይዘሬ በክፍል ውስጥ ሳይገኝ ጥሩ የማስተምር ይመስለኛል:: ሲገኝ ግን ትንሽ የመረበሽ መንፈስ ይሰማኛል::
- እኔን በጣም ግርም ያለኝ ሱፐርቫይዘሬ አንድ ጊዜም መጥቶ ሳይገመግመኝ መቅረቱ ነው:: በፕራክቲከም ወቅት ብቅ ብሎ አላየኝም ነበር:: አሁንም የማስተማር ልምምድ ላይ ሳለሁ አላየኝም:: ታዲያ እንዴት ውጤት ይሰጠኝ ይሆን ብዬ በመጠበቅ ላይ ነኝ::
- ነባር መምህሩ የገመገመኝ መሆኑን ባውቅም የሰጠኝን ውጤት አላሳየኝም:: ድክመትና ጥንካሬ የንም አልነገረኝም::
- እኛ የተመደብንበት ት/ቤት ከሌሎቹ በተለየ መንገድ የራሱን የመገምገሚያ ቅጽ አዘጋጅቶ በነባር መምህራን ካስገመገመን በኋላ ነው ማስተማር እንድንጀምር ያደረገው::
- የተመደብንበት ት/ቤት የሕዝብ ነው:: ከሌሎቹ ት/ቤት በተለየ ሁኔታ በማስተማር ልምምድ ወቅት እንግሊዝኛ እንድናስተምር አልፈቀደልንም:: ይህም በእኛ እንደማይተማመኑ ያመለክታል::

- እንግሊዝኛ እንዳናስተምር መደረጉ የት/ቤቱ ማህበረሰብ ለእኛ ያለው ግምት ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጎታል::
- በክፍል ውስጥ የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎች በየግድግዳው ተለጥፈው ስለሚገኙ በቀላሉ ልጠቀምባቸው ችያለሁ::
- በፕራክቲከም ወቅት የነባር መምህሩን ትምህርት አሰጣጥ ስለገመገምንና የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀቱን፣ የክፍል አመራሩን፣ የመርጃ መሳሪያ አጠቃቀሙን ከተማሪዎች ጋር ያለውን ግንኙነት ወዘተ. መነሻ አድርገን ለማስተማር ቀላል ሆኖልናል ብዬ እገምታለሁ::
- በፕራክቲከም ሁለት ተግባር አራት ላይ ስለትምህርት ዕቅድ ዝግጅት ማየቴ በማስተማር ልምምድ ወቅት ዕለታዊ ዕቅድ በማዘጋጅበት ጊዜ እንዳልቸገር ረድቶኛል::

## 3. ድህረ ማስተማር ልምምድ የነበረውን ውይይት በተመለከተ

### 3.1 የነበረው የውይይቱ ትኩረት

- ሂሳብ በምታስተምርበት ጊዜ የብራኬት አፃፃፍህ ትክክል አልነበረም ተብያለሁ::
- በፍጥነት መፃፍህ የእጅ ጽሁፍህ እንዲበላሽ አስተዋጽኦ አድርጓልና በጣም ሳትፈጥን በጣምም ሳትንቀረፈፍ መፃፍ ይኖርብሃል ተብያለሁ::
- ምናልባት ከምታስተምረው ይዘት ጋር አልሄድ ብሎህ ይሆናል የመርጃ መሳሪያ አልተጠቀምክም::
- Inactive የሆኑ ልጆችን ለመርዳት ምንም ዓይነት ሙከራ ኣላደረክም::
- አንተ ገምጋሚ ብትሆን ራስህን እንዴት ትገመግመው ነበር በማለት ጠይቆኛል::
- በዕለታዊ ትምህርት ዕቅዴ ላይ የዓላማ አነዳደፌ ሊመዝን የማይችል መሆኑን ገልፆልኛል::
- የክፍል ቁጥጥሬ በጣም Poor እንደሆነ ተገልፆልኛል::
- ጥያቄ የምጠይቀው የተወሰኑ ተማሪዎችን ብቻ እንደነበር በመጠቆም በውይይት ለማስተማር መሞከር እንዳለብኝ ተጠቁሚያለሁ::
- የጥቁር ሰሌዳ አጠቃቀሜ ትክክል እንዳልነበረገልፃልኛል::
- ሱፐርቫይዘሬ እኔ ክፍል የገባው ክፍለ ጊዜው ሊጠናቀቅ 10 ደቂቃ ሲቀረው ከመሆኑም በላይ ቀጣዩ የምሳ ሰዓት በመሆኑ ሰርቪስ እንዳያመልጠኝ ቸኩዬ ስለነበር የሰጠኝን አጭር አስተያየት ማስታወስ አልችልም::
- ከሱፐርቫይዘሬ ጋር ያደረግነው ውይይት ሳይሆን እሳቸው ተናጋሪ እኔ አድማጭ ነበርኩ
- ሱፐርቫይዘሬ አስተያየት የሚሰጡኝ በፍጥነት ስለነበር የሚነግሩኝን በአግባቡ ለመገንዘብ ተቸግሬያለሁ::
- በክፍል ውስጥ ሳስተምር በ5 ደቂቃ ካዩኝ በኋላ የሰጡኝ አስተያየት ምን ያህል እኔን ሊጠቅመኝ እንደሚችል አላውቅም::

- ቀድሞ ደካማ ጎኔን ከዘረዘሩልኝ በኋላ ጠንካራ ጎኔን ቢገልፁልኝም ጥሩ ስሜት አልተሰማኝም::
- ውይይታችን አተኩሮ የነበረው በዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ዓላማ አነዳደፌ ላይ ነበር::
- በምታስተምርበት ጊዜ ወደ ተማሪዎቹ አልተመለከትክም ተብያለሁ::
- ውይይቱ በደካማ ጎኔ ላይ ቢያነጣጥርም ጠንካራ ጎኔንም የዳሰሰ ነበር::
- የሰዓት አጠቃቀም ችግር እንዳለብኝ ተነግሮኛል::
- ሳስተምር ድምፄ Aggressive እንደነበር ጠቁሞኛል:: የተቆጣሁ እንደምመስልም ነግሮኛል::
- ያዘጋጀሁትን የትምህርት ዕቅድ ሳልይዝ በመገኘቴ ቅር መሰኘቱን ገልፆልኛል::
- ጠመኔ በጋዋን ኪስ መያዝ እንደሌለብኝ ተገልፆልኛል::
- የኔ ሱፐርቫይዘር ስህተቴን አጉልቶ ለማሳየት አይፈልግም ነበር እንዲያውም እኔ ራሴ እዚህ እዚህ ላይ ድክመት የነበረብኝ ይመስለኛል ስለው ምንም አይደል በጣም ቀላልና ልታሻሽለው የምትችለው ነገር ነው ነበር ያለኝ::
- በውይይቱ ሱፐርቫይዘሬ እኔ ምንም ዓይነት ሐሳብ እንድሰጥ አይፈልግም ነበር::
- ሱፐርቫይዘሬ ምንም ዓይነት ጠንካራ ጎን እንደነበረኝ ሳይጠቁመኝ ድክመቴን ብቻ ነው የነገረኝ::

## 3.2 ሱፐርቪዥኑን በተመለከተ የተማሪ አስተማሪዎች አስተያየት

- ሱፐርቫይዘሬ የገመገመኝ አንድ ቀን ብቻ ነው:: ለዚያውም ለ10 ደቂቃ በዚያች 10 ደቂቃ ምልከታው የመርጃ መሳሪያ አልተጠቀምክም ብሎኛል:: ይህ ደግሞ አግባብ አይደለም:: እኔ የማስተምረው የትምህርት ዕቅዴን ተከትየ በመሆኑ እሱ በመጣበት ክ/ጊዜ መርጃ መሳሪያ መጠቀም አያስፈልገኝም ነበር:: ስለዚህ አንድን የተማሪ አስተማሪ በአንድ ጊዜ ምልከታ ብቻ መገምገሙ በጣም አስቸጋሪ ስለሚሆን ሊታሰብበት ይገባል::
- በፕራክቲከምም ሆነ በማስተማር ልምምድ ወቅት ልንገመገም የምንችልበትን መስፈርት በቅድሚያ ቢገለጽልን በጣም ጥሩ ነበር:: ምክንያቱም እራሳችንን አዘጋጅተን ለመገኘት ይጠቅመናልና::
- ግምገማን እንደማስተማሪያ ሳይሆን ድክመትን እንደመፈለጊያ መሳሪያ የሚያዩ ሱፐርቫይዘሮች ስላሉ ይህ ሁኔታ ቢታረም ጥሩ ነው ባይ ነኝ::
- በፕራክቲከምም ሆነ በማስተማር ልምምድ ወቅት የተመደቡልን ሱፐርቫይዘሮች ሥራ ይበዛብናል በማለት ምንም አይነት እገዛ ሳያደርጉልን የሚቀሩበት አጋጣሚ በጣም በርካታ ስለሆነ ቢታሰብበት::

- ከሱፐርቫይዘሬ ጋር ጀምረነው የነበረውን ውይይት ሳንጨርሰው ነው የተለያየነው። በቂ የመወያያ ጊዜ ስላልነበረና ሰርቪስ ጥሎኝ እንዳይሄድ በመስጋት ሌላ ጊዜ እንደምንገናኝ በመነጋገር ተለያየን ደግመን ሳንገናኝ ቀረን።
- ሱፐርቫይዘሮች የተማሪ አስተማሪዎችን በሚያወያዩበት ጊዜ እነሱ ብቻ ተናጋሪ ከሚሆኑ ይልቅ የተማሪ አስተማሪዎቹንም ሐሳብ በጥሞና ቢያዳምጡ መልካም ነው።
- ሱፐርቫይዘሮች በአንድ ክፍል ውስጥ በመገኘት ሦስቱንም የመገምገሚያ ቅጾች ባይሞሉ። ምክንያቱም ለሦስት ጊዜ የምንገመገመው በመጀመሪያው የነበሩንን ደካማ ጎኖች በሁለተኛ ው፣ በሁለተኛው የታዩብንን ደካማ ጎኖች ደግሞ በሦስተኛ ዙር የማስተማር ልምምድ እንድናሻሽል ለማድረግ ታስቦ ነው።
- የማስተማር ልምምድ የምናደርገው ለአራት ሳምንታት መሆኑ ግልጽ ነው። ስለዚህ ሱፐርቫይዘሮች በየሳምንቱ መጥተው ሊጎበኙን ይገባል። ይሁን እንጂ በየሳምንቱ ከመምጣት ይልቅ በአንዱ ሳምንት ብቻ ገምግመው ነው የሚጨርሱት። ይህ ባይሆን ጥሩ ነው።
- አብዛኞቻችን በአራቱም ዙር ፕራክቲከም ምልከታችን ሰርተን ባቀረብነው ሪፖርት ላይ ከሱፐርቫይዘራችን ጋር ምንም አይነት ውይይት አላደረግንም። እንዲያውም ሱፐርቫይዘራችንን በአካል ለማግኘት እየተቸገርን በበር ስር ነበር ወረቀታችንን ቢሮው ውስጥ የምናስገባው። ስለዚህ ይህ ሁኔታ የሚሻሻልበት መንገድ ቢፈጠር።

# አባሪ ፫

## የሱፐርቫይዘሮችና የተማሪ አስተማሪዎች ውይይት ምልከታ ናሙናዊ ጥንቅር

## ሱፐርቫይዘር «4»

## ውይይት 1

| | |
|---|---|
| ሱፐርቫይዘር | እንደምን ዋልክ≘ |
| የተማሪ አስተማሪ | እግዚአብሔር ይመስገን |
| ሱፐርቫይዘር | በምታስተምርበት ጊዜ እንደተመለከትኩት ብዙ ጠንካራ ጎኖች አሉህ:: ይሁን እንጂ ሊሻሻሉ የሚገባቸው ደካማ ጎኖችም አሉህ:: ስለዚህ ቀጥሎ የምጠቁምህን ነጥቦች አዳምጠህ ለማሻሻል መሞከር ይኖርብሃል:: |
| የተማሪ አስተማሪ | እሺ |
| ሱፐርቫይዘር | በመጀመሪያ የምገልፅልህ ነገር ቢኖር ስታስተምር ድምጽህ አይሰማም ነበር:: ምን ሆነህ ነው? |
| የተማሪ አስተማሪ | ምንም አልሆንኩ |
| ሱፐርቫይዘር | ምንም ካልሆንክ ታዲያ የምታስተምረውን ነገር ተማሪዎችህ በሚገባ ሊያዳምጡህ በሚችሉበት ሁኔታ ልታስተምራቸው የሚገባ አይመስልህም? |
| የተማሪ አስተማሪ | ይገባል:: |
| ሱፐርቫይዘር | ሌላው ደግሞ የጥቁር ሰሌዳ አጠቃቀምህ በጣም ጥሩ ነው:: ነገር ግን በፍጥነት ለመፃፍ በምትሞክርበት ጊዜ የእጅ ጽሁፍህን ለማንበብ የማይቻልበት ሁኔታ ላይ ሲደርስ አይቻለሁ:: ሕፃናት ደግሞ የመምህራቸውን የእጅ ጽህፈት አስመስለው ለመፃፍ ስለሚሞክሩ አጉል ሞዴል እንዳትሆናቸው መጠንቀቅ ይገባሃል:: |
| የተማሪ አስተማሪ | በፍጥነት የሞጽፈው ለምን እንደሆነ ያውቃሉ≘ |
| ሱፐርቫይዘር | ለምንድነው? |
| የተማሪ አስተተማሪ | ክፍለ ጊዜውን በአግባቡ ለመጠቀም ነው:: |
| ሱፐርቫይዘር | ቢሆንም ሰዓት ለመሻማት ብለህ አጉል ነገር ማስጨበጥ አይኖርብህም:: የትምህርት ዕቅድህን በጥሩ ሁኔታ ካዘጋጀህና በእያንዳንዷ ደቂቃ ምን መስራት እንዳቀብህ ከወሰንክ የሰዓት ችግርህን በቀላሉ መፍታት ትችላለህ:: |
| የተማሪ አስተማሪ | እሺ |

ሱፐርቫይዘር ጥቁር ሰሌዳ ላይ በምትጽፍበት ጊዜ ተማሪዎች አይታየንም ይሉህ ነበር:: ለምን ይመስልሃል ይህን ጥያቄ የሚጠይቁህ?

የተማሪ አስተማሪ እነሱ ሁልጊዜ ነው ይህን ጥያቄ የሚጠይቁኝ:: ጥያቄያቸውን ብትቀበላቸው ኖሮ ጥሩ ነበር:: ምናልባትም መስኮቱ ክፍት ስለነበር እያንፀባረቃቸው ሊሆን ይችላል:: ያ ከሆነ ደግሞ መፍትሔ ተገኘለት ማለት ነው የተማሪዎቹ ጥያቄ::

የተማሪ አስተማሪ ባልጠይቃቸውም መስኮቱን ለመዝጋት ግን ሞክሬ ነበር::

ሱፐርቫይዘር ባለፈው ሳምንት ምልከታየ ጥቁር ሰሌዳው ላይ ቀን አትጽፍም ነበር:: ዛሬ ግን ጽፈሐል ጥሩ ነው:: ሌላው ያየሁት ቦርድ ላይ ስትፅፍ በምትሳሳትበት ጊዜ በእጅህ ስታጠፋ ነው:: በእጅህ ማጥፋት አይኖርብህም:: ምክንያቱም ዳስተርህን በአግባቡ ልትጠቀምበት ይገባል::

የተማሪ አስተማሪ ለነገሩ በፕራክቲከም ወቅት እንዳየሁት ነባር መምህሩም በእጅ ያጠፋ ነበር::

ሱፐርቫይዘር መደበኛ መምህሩ በእጅ ስላጠፋ አንተም ማጥፋት አይኖርብህም:: ሌላው ከዚሁ ጋር በማያያዝ የምጠቁምህ ነገር ስታስተምር በጣም ትፈጥናለህ:: መፍጠን የለብህም ይህን ስልህ በጣም ተንቀርፈፍ ማለቴ አይደለም:: በጣም አትፍጠን በጣምም አትንቀርፈፍ::

የተማሪ አስተማሪ ቀድሞ እንደገለጽኩት ፍጥነቴ ሰዓቱን ከመሻማት የመጣ ነው::

ሱፐርቫይዘር የምታስተምራቸውን ልጆች ማነቃቃት ይኖርብሃል እንዲሳተፉም ማድረግ ይጠበቅብሃል:: በተወሰኑት ላይ ብቻ ማተኮርም የለብህም:: ለምሳሌ እናንተ ስትማሩ ሁላችሁም እጃችሁን ታወጡ ነበር? አታወጡም:: ነገር ግን እጃችሁን ያላወጣችሁትም እንድትሳተፉ ይደረግ ነበር:: ስለዚህ ዕድሉን እጅ ለሚያወጡ ብቻ ከመስጠት ይልቅ ያላወጡትንም እንዲሞክሩ በማድረግ ማሳተፍ ያሻል:: ለማሳተፍ ብለህ "አንተ" "አንቺ" ማለትም የለብህም::

የተማሪ አስተማሪ ማንን እንደጠራሁ ስለሚያውቁ ችግር የለውም ብዬ ነው::

ሱፐርቫይዘር ሌላው ሂሳብ በምታስተምርበት ጊዜ ያየሁት ነገር ምንድነው የብራኬት አፃፃፍህ ትክክለኛውን ቅርጽ የጠበቀ አይደለም:: አምስት ቁጥርን ስትጽፍም ኤስ/S/ ነው የምታስመስለው:: ተማሪዎች መምህር ያደረገውና የፃፈው ሁሉ ትክክል ነው ብለው ይወስዱታል:: ስለዚህ ለሁሉም ነገር መጠንቀቅ ጥሩ ይሆናል:: መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በምትጽፍበት ጊዜ 2ሀ ከማለት ይልቅ በቁጥሩና በፊደሉ መካከል ነጥብ በማስገባት 2.ሀ ብትጽፈው የተሻለ ይሆን ነበር::

| | |
|---|---|
| የተማሪ አስተማሪ | መሀል ላይ ስላሰመርኩ ነው |
| ሱፐርቫይዘር | መቼ አሰመርክ አላሰመርክም አንተው የፃፍከውን ነው ማስታወ የያዝኩት:: |
| የተማሪ አስተማሪ | ይሆናል:: |
| ሱፐርቫይዘር | አዎ ቅድም እየደጋገምክ መቅደስ ገብቶሻል? ትል ነበር:: ለምን ነበር ይህ ያደረከው? |
| የተማሪ አስተማሪ | እሷ ተሳታፊ በመሆኗ ልጠይቃት ፈልጌ ነበር:: |
| ሱፐርቫይዘር | አዎ ትልሃለች እንጂ አታዳምጥህም ነበር:: በመላ ነው የምትመልስል ሌላው ለተማሪዎቻችን የምንነግራቸው ነገር ግልጽ መሆን አለበት: ትዕዛዞችንም ቢሆን ግራ የሚያጋባ መሆን አይኖርበትም:: ለምሳሌ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፋችሁንና ደብተራችሁን አውጡ ብለህ ብታገ መልካም ነው:: |
| የተማሪ አስተማሪ | እየተያየን ስለምነግራቸው ግራ ይገባቸዋል ብዬ ስለማስብ ነው:: |
| ሱፐርቫይዘር | ቀደም ብለህ መልሱን አንተ ከነገርካቸው በኋላ ማን ማን እንዳላሳረመ መጠየቅህ ለምን አስፈለገ? |
| የተማሪ አስተማሪ | የማይሰሩ ተማሪዎችን ሰርተው እንዲያሳርሙ ለማበረታታት:: |
| ሱፐርቫይዘር | ለዛሬ ያሉኝ አስተያየቶች እነዚሁ ናቸው:: በዚሁ ቀጥል ጨርሻለሁ:: |
| የተማሪ አስተማሪ | አመሰግናለሁ:: |

## ውይይት 2

| | |
|---|---|
| ሱፐርቫይዘር | እራስህን ስትገመግመው ምን ይመስልሃል? ጥሩ ሰርቻለሁ ወይም ድክመት ያሳየሁበት ሁኔታ አለ ብለህ ትገምታለህ |
| የተማሪ አስተማሪ | ስገመግም ይህ የመጀመሪያዬ ስለሆነ የተደናገጥኩ ይመስለኛል:: |
| ሱፐርቫይዘር | የለም አልተደናገጥክም:: ለምን ትደናገጣለህ በደንብ ተዘጋጅተህ ለማስተማር አልገባህም እንዴ? |
| የተማሪ አስተማሪ | ኧረ ተዘጋጅቻለሁ:: ሌሰንፕላንም አዘጋጅቻለሁ:: |
| ሱፐርቫይዘር | Inactive የሆኑ ተማሪዎችን ለማነቃቃት ወይም ለመርዳት ምን አደረክ? |
| የተማሪ አስተማሪ | እንዲህ ያሉ ተማሪዎች ከጉበዝ ተማሪዎች ጋር እንዲቀመጡ አድርጌያለሁ:: |
| ሱፐርቫይዘር | ሌላ የሚታይህ ድክመት ምንድን ነው? |

| | |
|---|---|
| የተማሪ አስተማሪ | እኔማ መቼ ድክመቴ ይታየኛል ከእናንተ ድክመቴን ልስማው እንጂ /የዚህን ጥናት አቅራቢ ከሱፐርቫይዘሩ ጋር ስለተመለከተው ነው ከእናንተ ልስማው ማለቱ/ |
| ሱፐርቫይዘር | ልጅቱ ያነበበችው ግጥም የማን ነበር? |
| የተማሪ አስተማሪ | የራሷ |
| ሱፐርቫይዘር | ስትጨርስ ስለግጥሙ ወይም ስለአነባበቧ ምንም ሳትል ለምን ወደሌላ ርዕስ ተሸጋገርክ? |
| የተማሪ አስተማሪ | አስጨብጭቤለታለሁ እኮ |
| ሱፐርቫይዘር | Class room Management very poor ነው ለምን? |
| የተማሪ አስተማሪ | ደካማ ተማሪዎች እየዞርኩ አያለሁ፡፡ ክፍሉንም ለመቆጣጠር ሞክሬያለሁ፡፡ |
| ሱፐርቫይዘር | የአካባቢ ሳይንስ በምታስተምርበት ጊዜስ ለህዝብ ምንነት ገለፅክላቸው ወዲያውኑ ሕዝብ ምንድነው የሚል ጥያቄ አቀረብክላቸው ለምን? |
| የተማሪ አስተማሪ | እንዲሳተፉ |
| ሱፐርቫይዘር | አንተ ለዚያ ክፍል ማኔጀር ሆነህ ሳለ በሚገባ ክፍሉን አትቆጣጠርም፡፡ የተኛ ልጅ ሁሉ ነበር፡፡ |
| የተማሪ አስተማሪ | እየተቆጣጠርኩ ነበር፡፡ |
| ሱፐርቫይዘር | ሌላው ተማሪዎቹ ሲዘምሩ አንተ ግን ዝም ብለህ ነበር፡፡ ነገር ግን አንተ አብረህ ባትዘምር እንኳን በእጅህ እንቅስቃሴ ልታበረታታቸው ትችል ነበር በተረፈ እያስተማርክ ብዙ ጊዜ ጥያቄ ጥያቄ ትላለህ ለምን፧ |
| የተማሪ አስተማሪ | ሰዓት ስለሌለኝ እንጂ እየወጡ እንኳን እንዲሰሩ ማድረግ እችል ነበር፡፡ ጥያቄ አላችሁ ወይ የምቸው እንዲሳተፉ በማሰብ ነው፡፡ |
| ሱፐርቫይዘር | ሁልጊዜ ስታስተምር Concentrate ማድረግ አለብህ በክፍል ውስጥ ያለውን እያንዳንዱን እንቅስቃሴ መቃኘትም ይኖርብሃል፡፡ |
| የተማሪ አስተማሪ | ዛሬ ተማሪዎች ሲረብሹ አይተዋልን ? |
| ሱፐርቫይዘር | አዎን ሲደባደቡ ሁሉ ነበር፡፡ በመጨረሻ ላይ ሁሉም ተማሪዎች ተነስተው ሳለ አንተ ግን እያስተማርክ ነበር ሰዓትህን ተቆጣጥረህ ማስተማርህን መቀጠል አለብህ፡፡ በአጠቃላይ ሁሉም የሚሻሻል ነገር ነው በርታ፡፡ ይኸው ነው ጨርሻለሁ፡፡ |

## ሱፐርቫይዘር "8"

## ውይይት 1

| | |
|---|---|
| ሱፐርቫይዘር | አንተ ገምጋሚ ብትሆን ራስህን እንዴት ትገመግመው ነበር፧ |

**የተማሪ አስተማሪ** እየፈጠንኩ ነበር የማስተምረው

**ሱፐርቫይዘር** ታዲያ ምን ማድረግ ነበረብህ≡

**የተማሪ አስተማሪ** ባለፈው እንደነገርኩዎት የሰዓት አጠቃቀም ችግር አለብኝ::

**ሱፐርቫይዘር** ሌላስ≡

**የተማሪ አስተማሪ** ሌሰንፕሌን እንዳሰብኩት አላዘጋጅሁትም::

**ሱፐርቫይዘር** ሙሉ በሙሉ ክፍሉን ተረክበህ በማስተማር ላይ ስለሆንክ ሁልጊዜ ሌሰንፕላንህን አስበህ መስራት ይኖርብሃል:: በክፍል ውስጥ ስለ መቻቻልና መረዳዳት ስታስተምር ተማሪዎች የየራሳቸውን ልምድ እንዲናገሩ ማድረግህ በጣም ጥሩ ነው:: ልምዳቸውን መጠየቁ ትምህርቱን እውናዊ ያደርገዋል:: ሆኖም ግን ስለልማት ምንባቡን ከማስነበብህ በፊት በአንባቢያቸውና በት/ቤታቸው እየተከናወኑ ያሉ ልማቶችን እንዲገልፁ ማድረግ ትችል ነበር::

**የተማሪ አስተማሪ** ይህንን በሚገባ ያደረኩ ይመስለኛል::

**ሱፐርቫይዘር** እንደሚመስለኝ ትንሽ የመደናገጥ ነገር ነበር:: መደናገጥ የለብህም:: አንተ እኮ ለማስተማር ተዘጋጅተህ ነው የገባኸው:: እኔ ግን ምንም አልተዘጋጀሁም::

**የተማሪ አስተማሪ** ብዙም የተደናገጥኩ አልመሰለኝም ነበር::

**ሱፐርቫይዘር** ጥሩ አዎ ሌላው ጥያቄ ስትጠይቅ የተወሰኑ ተማሪዎች ላይ ብቻ ታተኩራለህ:: ይህ ደግሞ የተማሪዎቹን ሞራል ሊነካ ይችላል:: ስለዚህ በውይይት ለማስተማር ብትሞክር ጥሩ ነው:: የምታስተምረው የመማሪያ መጽሐፉን ይዘህ ነው:: ኖት ማዘጋጀትም ነበረብህ::

**የተማሪ አስተማሪ** ኖት ያላዘጋጀሁት ነባሩ መምህር ኖት አትስጣቸው ስላለኝ ነው::

**ሱፐርቫይዘር** በራስህ ተማመን፣ ልጆችን በሚገባቸው መንገድ ለማስተማር ጥረት አድርግ:: ለምሳሌ ማቴሪያል የሚል ቃል ስታስተምራቸው ነበር:: ሌላው ገብቶሃል ገብቶሻል ስትል የሰማሁ መሰለኝ:: ይህ አባባል ተማሪዎች እኔ ለካ ከጓደኞቼ በታች የሆንኩ ደደብ ነኝ እንዲሉ ሊያደርጋቸው ይችላል::

**የተማሪ አስተማሪ** እሺ አሻሽላለሁ::

## ውይይት 2

**ሱፐርቫይዘር** How you assess your teaching practice? እንዴት ታየዋለህ?

**የተማሪ አስተማሪ** ጥሩ ነው::

**ሱፐርቫይዘር** ማስተካከል አለብኝ የምትለው ነገር አለህ?

**የተማሪ አስተማሪ** አዎ ለምሳሌ የሰዓት አጠቃቀም ችግር አለብኝ::

| | |
|---|---|
| ሱፐርቫይዘር | እኔም እንደ ሱፐርቫይዘርነቴ ስታስተምር ያየሁትን ጠንካራና ደካማ ጎ ልግለጽ:: ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቃለ ምልልስ እንዲያነቡ ስታደርግ ነበር:: አንተ የእንግሊዝኛ ቋንቋን እያስተማርክ እንደመሆንህ መጠን ተማሪዎች ሲያነቡ በሚሳሳቱበት ጊዜ እየተከታተልክ ልታርማቸው ይገባል:: ለምሳሌ Verb agreement (One boys, one girils) እያሉ ሲያነቡ ምንም Correction አትሰጥም ነበር:: ሌላው ምንም ማንበብ ላልቻሉ ተማሪዎች ሁሉ እንዲያጨበጭቡላቸው ታደርጋለህ:: ጭብጨባ ዋ ላለው ስራ ቢሆን ይመረጣል:: መድረክ ላይ ስለመውጣታቸው ምናልባት ማበረታታት ከፈለግክ ሌሎች መንገዶችን መጠቀም ትችል ነበር:: |
| የተማሪ አስተማሪ | ብዙዎቹ ተማሪዎች ግን ሲጨበጨብላቸው ይደሰታሉ:: ተሳትፏቸውም ይጨምራል:: |
| ሱፐርቫይዘር | በጣም ግርም ያለኝ የክፍል አለቃዋ ጉዳይ ነው:: ልክ እንደፖሊስ ሆነች እኮ:: እየተዘዋወረች ተማሪዎቹን ስትኮረኩም ነበር:: ይህ አካላዊ ቅጣት አይበረታታም:: እናንተም ብትሆኑ ከዲሞክራሲ የተገኛችሁ ወይም የመጣችሁ መሆናችሁን አትዘንጉ:: |
| የተማሪ አስተማሪ | እሺ |
| ሱፐርቫይዘር | ለመሆኑ የበላኸው ቁርስ ምንድነው? በጣም የሚገርመው ስታስተምር ድምጽህ በጣም በጣም ከፍተኛ ነበር:: ስለዚህ ለስለስ ባለ ጽምጽ ለማስተማር ብትሞክር መልካም ይሆናል:: ሌላው በምልልስ የራስ ስም እንደማይጠራ መረዳት ያስፈልጋል:: ለምሳሌ እኔና አንተ አሁን ስንነጋገር ራሳችንን እየጠራን ነው እንዴ? |
| የተማሪ አስተማሪ | ምልልሱን ያስተጓጉለዋል ማለት ነው? |
| ሱፐርቫይዘር | በትክክል:: በኃይሌና በእናቱ መካከል የተደረገውን ምልልስ ተማሪዎቹ እየተቀባበሉ ሲያነቡት እንዳዳመጥከው የኃይሌን ድርሻ የሚያነበው ኃይሌ እያለ ነበር:: |
| የተማሪ አስተማሪ | ይህ ችግር የሚፈጠር መሆኑ አልገባኝም ነበር:: |
| ሱፐርቫይዘር | የቋንቋ አጠቃቀምህና አፃፃፍህ ችግር ታይቶበታል:: ተማሪዎች መምህር ይሳሳታል ብለው አይገምቱም:: ለዚህም ነው ጥሩ ዝግጅት ማድረግ የሚያስፈልገው:: ለመሆኑ ጠመኔ በጋዋን ኪስህ ለምን ያዝክ? |
| የተማሪ አስተማሪ | መያዣ የለም:: |
| ሱፐርቫይዘር | መያዣ እኮ በጣም ቀላል ነገር ነው ራስህም ልታዘጋጀው ትችላለህ:: በመጨረሻም እስካሁን በተነጋገርነው ጉዳይ የምትስማማበትና የማትስማማበት ነገር አለህንቻ ከሌለህ እኔ ጨርሻለሁ:: |

## ሱፐርቫይዘር "12"
## ውይይት 1

| | |
|---|---|
| ሱፐርቫይዘር | አንቺ ሁልጊዜ ሱፐርቫይዘር መጣም አልመጣም በጥሩ ሁኔታ ለማስተማር ተዘጋጅተሽ መግባት አልነበረብሽምጭ |
| የተማሪ አስተማሪ | ነበረብኝ፡፡ |
| ሱፐርቫይዘር | ይህን ብታደርጊ ኖሮ ክፍለ ጊዜውን በክለሳ አትጨርሽውም ነበር፡፡ |
| የተማሪ ስተማሪ | አይደለም፡፡ እያስተማርኩ ነው ኮ፡፡ |
| ሱፐርቫይዘር | እኔ ያልኩሽ ያለፈውን ክፍለ ጊዜ ይዘት በማንሳት አትክልሽ አይደለም ለክለሳ የሰጠሽው ጊዜ በጣም በዛ ነው፡፡ በአራትና አምስት ደቂቃ ውስጥ በመከለስ ወደ ዕለቱ ትምህርት መሸጋገር አልነበረብሽም፡፡ |
| የተማሪ አስተማሪ | ኖት ብቻ ነው የቀረኝ እንጂ አስተምሬያለሁ፡፡ |
| ሱፐርቫይዘር | ስለምን ነበር የምታስተምሪው? |
| የተማሪ አስተማሪ | ስለዝናብ ስርጭት |
| ሱፐርቫይዘር | ክለሳ ስታደርጊ የነበረው ስለ አራቱ ወቅቶች ነበር ከዚያ በኋላ የዕለቱ ትምህርት ርዕስ የዝናብ ስርጭት ከሆነ ወደ አዲስ ርዕስ ስትገቢ ርዕሱን ሰሌዳ ላይ ልትጽፊ ይገባሽ ነበር፡፡ ደግሞኮ ኖት ብታዘጋጅ ኖሮ ጥሩ ነበር፡፡ |
| የተማሪ አስተማሪ | አዘጋጅቻለሁ፡፡ |
| ሱፐርቫይዘር | ብታዘጋጅማ መጽሐፉን ብቻ ተመርኩዘሽ አታስተምሪም ነበር፡፡ በመጽሐፍ ላይ ብቻ መመረኮዝ የለብሽም አሁን ለምሳሌ ስለዝናብ ስርጭት በምታስተምሪበት ጊዜ የተጠየቅሽውን ጥያቄ ታስታውሻለሽ≡ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታዎች ዝናብ መቼ እንደሚያገኙ ከገለጽሽላቸው በኋላ የጠረፍ አካባቢዎች ዝናብ የሚያገኙት መቼ ነው ስትባይ መቼ እንደሚያገኙ አይታወቅም በማለት ነበር የመለስሽው፡፡ ይህ ደግሞ ጥሩ አይደለም፡፡ ተማሪዎች ከመምህራን የሚጠብቁት ትክክለኛ ምላሽን ነው፡፡ ኖት ብታዘጋጁ ኖሮ እዚያው መጽሐፉ ላይ ጠረፋማ አንባቢዎች መቼ ዝናብ ሊያገኙ እንደሚችሉ ታገኝው ነበር፡፡ ለመሆኑ ስለአቅጣጫ የምታስተምሪ ከሆነ አቅጣጫ ጠቋሚ መርጃ መሳሪያ ወይም ካርታ ለምን |

አልተጠቀምሽም? ወይም ስሌዳ ላይ ለማሳየት ሳትሞክሪ ለምን ቀረሽ? ይህን ብታደርጊ ጥሩ ነበር፡፡

**የተማሪ አስተማሪ** ገባኝ ካርታ ላመጣ ወደ ት/ቤቱ ማዕከል ሄጄ ነበር ይሁን እንጂ ካርታው ተቀዳዶ አልቋል ስለአሉኝ ነው፡፡

**ሱፐርቫይዘር** ሌላውና ከምንም በላይ ጎልቶ የታየው ችግር ጊዜሽን በአግባቡ መጠቀም አለመቻልሽ ነው፡፡ ቀድም እንደገለጽኩልሽ ከሰላሳ ደቂቃ በላይ ባለፈው ክፍለ ጊዜ የተማሩትን ትምህርት በመከለስ ጨርሰሽዋል፡፡ ክለሳ አይኑር ማለቴ አይደለም ነገር ግን በጥቂት ደቂቃ ውስጥ በመከለስ ወደ ዕለቱ ትምህርት መሸጋገር ይገባሽ ነበር፡፡ ጊዜሽን እያሰብሽ ብታስተምሪ ጥሩ ይሆናል፡፡

**የተማሪ አስተማሪ** እዚህ ላይ . . .

**ሱፐርቫይዘር** ይገባኛል ምንም አይደል ሁሉንም ወደፊት ታሻሽይዋለሽ በተረፈ ጥሩ ነው አንድ ጊዜ ተመልሼ ላይሽ እችላለሁ፡፡ ደህና ዋይ፡፡

## ውይይት 2

**ሱፐርቫይዘር** እሺ የዕለታዊ ዕቅድ ዝግጅትሽ በጣም ጥሩ ነው፡፡ በምታስተምርበት ጊዜ ያየኋቸውን አንዳንድ ነጥቦች ልገልጽልህ፡፡ የስልጣኔን ጥቅም አንስተህ ስታስረዳ አውቶቡስ የስልጣኔ ውጤት እንደሆነ ገልፀሐል ጥሩ ነው፡፡ የሰጠኸው ምሳሌ ላይ የከተማ አወቶቡስ በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ እንደሚያገለግል ነው፡፡ ይሁን እንጂ የከተማ አወቶቡስ ያለው አ/አ ከተማ ብቻ አይደለም ለምሳሌ ጅማ እንዳለ አውቃለሁ፡፡ ሌላው አምፑል ስልጣኔ ያስገኘው እንደሆነ ካስረዳሃቸው በኋላ እንዴት ሊሰራ እንደሚችል ለተጠየቅከው ጥያቄ የሰጠኸውን መልስ ታስታውሳለህ?

**የተማሪ አስተማሪ** አዎን

**ሱፐርቫይዘር** ምን ብለህ ነበር የመለስክለት፧

**የተማሪ አስተማሪ** እንዴት ሊሰራ እንደሚችል አይታወቅም ብዬ

**ሱፐርቫይዘር** ለተማሪ እንዲህ ተብሎ መመለስ የለበትም እነሱ መምህር ሁሉን ነገር ያውቃል ብለው ነው የሚያስቡት፡፡ የማታውቀው ቢሆን እንኳን ዛሬ የምንማረው ስልጣኔ ስላስገኛቸው ነገሮችና ጥቅማቸው ነው፡፡ አሰራራቸውን በሚመለከት አሁን አንስተን መነጋገሩ ይከብዳል፡፡ ወደፊት እናንተም እያደጋችሁ ስትሄዱ በላይኞቹ የክፍል ደረጃዎች ትማሩዋቸዋላችሁ፡፡ እንዲያውም የሚሰሩበት ቦታ ድረስ ሄዳችሁ ታያላችሁ በማለት መግለጽ ይኖርብሃል፡፡

| | |
|---|---|
| የተማሪ አስተማሪ | ለወደፊቱ እንዲህ ዓይነት ጉዳይ ሲገጥመኝ ለመስተካከል እሞክራለሁ:: |
| ሱፐርቫይዘር | ጥሩ በተረፈ ለምታስተምረው ትምህርት መርጃ መሳሪያ ቢኖርህ መልካም ነው:: ክፍሉ ጠባብ በመሆኑና የተማሪዎች ቁጥር በጣም አነስተኛ ስለሆነ ይመስለኛል የክፍል ቁጥጥርህ በጣም ጥሩ ነው:: ልጆችን መቅጣት ተገቢ እንዳልሆነ ተገቢ ቢሆንም እንዲህ እንዳንተ በሚረብሹበት ጊዜ ዝም በሉ ማለትና Control ማድረጉ ጠቃሚ ነው:: በዕለቱ ሊሰጥ የታሰበውን ትምህርት ለማስተማር ምቹ ሁኔታ ይፈጠራልና:: በተረፈ በዚሁ ቀጥል በርታ:: |

## ሱፐርቫይዘር "16"

### ውይይት 1

| | |
|---|---|
| ሱፐርቫይዘር | እኔ አስተያየት ልሰጥህ የምፈልገው ከዕለታዊ ዕቅድህ በመጀመር ይሆናል:: በዕለታዊ ዕቅድ ዓላማ ስትነደፍ አጠቃላይነት ባይኖረው ተመራጭነት ይኖረዋል:: ለምሳሌ መስራት ይችላሉ የሚለውን ብናይ ይህን ለመለካት አስቸጋሪ ነው:: ይሰራሉ መባል አለበት:: ይችላሉ የሚለው ሌላ መለኪያ ያስፈልገዋልና:: ለምሳሌ ስለማባዛት ለማስተማር ባቀድከው መሠረት ዓላማህ መሆን ያነበረበት የመልመጃ ጥቅምን ይለያሉ ሳይሆን የማባዛት ምልክትን ተጠቅመው ቁጥሮችን ያሰላሉ /ያባዛሉ/ ተብሎ ዓላማው መቀመጥ ይኖርበታል:: ምክንያቱም የምታስተምራቸው ስለ መልመጃ ጥቅም አይደለም::<br>The other thing-well በጥሩ ሁኔታ እንትን ብለሃል ተማሪዎችን ለማነቃቃት ያደረከው ሙከራ ጥሩ ነበር:: መርጃ መሳሪያን በተገቢው መንገድ ተገልግለሃል:: ሌላ ያየሁት ጠንካራ ጎን ምን መሰለህ የተማሪዎችን ተሳትፎና የጥቁር ሰሌዳ አጠቃቀምህን ነው:: ማሻሻል ያለብህ የክፍል ቁጥጥርህን ነው:: |
| የተማሪ አስተማሪ | አዎ እሱ ነገር በጣም አስቸጋሪ ነው:: |
| ሱፐርቫይዘር | ምንም አስቸጋሪ አይደለም በጣም ቀላል ነው በክፍል ውስጥ አንተ የራስህን ስራ ብቻ መስራት የለብህም:: በተቻለ መጠን ወደ ተማሪዎቹ መለስ እያልክ eye contact ማድረግ አለብህ:: አንዳንድ ጊዜ ወደ ተማሪዎቹ መካከል በመግባት መቆጣጠርም ይጠበቅብሃል:: ሌላው ተማሪዎችህ በጋራ መልስ ባይመልሱ ጥሩ ነው ምክንያቱም በጋራ በሚመልሱበት ጊዜ የትኞቹ እንዳወቁና የትኞቹ እንዳላወቁ ለመለየት ያስቸግራል:: ከዚሁ ጋር በተያያዘ መንገድ ተማሪዎችን በምታሳትፍበት |

ጊዜ እጅ ለሚያወጡ ብቻ እድል አትስጥ። እጅ የማያወጡትንም መጠየቅ ያስፈልግሃል። ምክንያቱም እጇን ባወም ባላወጣም መጠየቄ አይቀርም በማለት እንዲሞክሩ ያደርጋቸዋል። ወደ ጥቁር ሰሌዳው በመውጣት እንዲጽፉ ማድረግም መልካም ነው። መልስ በሚሰጡበት ጊዜ ዝም ብሎ ከመቀበል ይልቅ ለምን≅ እንዴት≅ የሚሉ ጥያቄዎችን በማስከተል ማብራሪያ እንዲሰጡ ማድረግ ያሻል። ጨርሻለሁ።

## ውይይት 2

ሱፐርቫይዘር ዕለታዊ ዕቅድህን ሳየው ብዙም ችግር ያለበት ሆኖ አላገኘሁትም። የዓላማ አነዳደፍህ በጣም ጥሩ ነው። ሌሎችም ጠንካራ ጎኖች አሉህ። ለምሳሌ የትምህርት አቀራረብህና የጥቁር ሰሌዳ አጠቃቀምህ መልካም ነበር። ሌላው በጣም ትልቅ ስህተት ነው አካፋይ እና ተካፋይ የሚለው ሐሳብ ለአንተም ግልጽ የሆነልህ አልመሰለኝም። መጽሐፉ ላይ እንኳን የተፃፈውን በሚገባ አንብበህና ተዘጋጅተህ የምታስተምረውን ትምህርት አውቀህ መገኘት ይኖርብሃል። ከአቅምህ በላይ ቢሆን እንኳን ነባር መምህራንን በመጠየቅ ለመረዳት ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። ልጅቷ እጇን አውጥታ ስህተት መሆኑን ባትጠቁምህ ኖሮ ተማሪዎችህን አሳስተሃቸው ነበር እኮ። ሌላው ተማሪዎቹ ያወቁትንና ያላወቁትን ለመለየት ትችል ዘንድ በጋራ እንዲመልሱ ከማድረግ ይልቅ በተናጠል መጠየቁ የተሻለ ነው። 1 × 1 ስንት ነው? በማለት ከጠየቅክ በኋላ መልስ ሲሰጡህ ለምን? የሚል ጥያቄ ብታስከትል ጥሩ ነው። ይህ አይነት አካሄድ ተማሪዎች በግምት ብቻ መልስ ከመስጠት ይልቅ አስበው አውጥተውና አውርደው እንዲመልሱ ያበረታታቸዋል።

የተማሪ አስተማሪ እህ አስተያየተዎን ተቀብያለሁ።

ሱፐርቫይዘር ሌላው ደህና ነው እንደገና መጥቼ አይሃለሁ።

## ሱፐርቫይዘር “19”

## ውይይት 1

ሱፐርቫይዘር እሺ . . . እስኪ አንዳንድ ነገር እንነጋገር። መጀመሪያ አንተ ስለማስተማር ልምምዱ ምን አስተያየት አለህ? እዚህ ላይ ጥሩ ነበር ይህ ደግሞ ጥሩ አልነበረም የምትለው ነገር ይኖርሃል?

| | |
|---|---|
| የተማሪ አስተማሪ | የማስተማር ልምምድ ስናደርግ ከጓደኞቻችን ጋር እንተያይ ነበር እና . . . በዚያን ወቅት ልናስተካክላቸው የሚገቡ ነጥቦችን ተጠቋቁመናል:: |
| ሱፐርቫይዘር | ለምሳሌ አንተ ስታስተምር ካዩ በኋላ ምን Comment ሰጡህ? |
| የተማሪ አስተማሪ | አትፍጠን፣ አትኮሳተር ነው ያሉኝ:: |
| ሱፐርቫይዘር | በሰጡህ አስተያየት መሠረት ያሻሻልክ ይመስልሃልን? |
| የተማሪ አስተማሪ | ማሻሻል አልፈለኩም:: የምኮሳተርበት የራሴ የሆነ ምክንያት አለኝ ሳቅ እያልኩ የማስተምር ከሆነ ተማሪዎች ይረብሹኛል:: |
| ሱፐርቫይዘር | ተማሪዎችን እንዳይረብሹ ለማድረግ መኮሳተር አያስፈልግም:: የተማሪዎቹን ፍላጎት በመረዳት ጥሩ የማስተማር ዘዴ ተጠቅመን ብናስተምራቸው ሊረብሹ አይችሉም:: አትኮሳተር ሲሉህ እኮ እየሳቅክ አስተምር ማለታቸው አይመስለኝም:: ሌላው Inactive የሆኑ ተማሪዎችን ለመርዳት ምን የምታደርገው ጥረት አለ? |
| የተማሪ አስተማሪ | አዎን አለ:: ምን አደርጋለሁ መሰለሽ እርስ በርሳችሁ እየተረዳዳችሁ ተማማሩ ከዚያ ያልገባችሁንም እኔን ጠይቁኝ ያለበለዚያ ፈተና ላይ ዜሮ ታገኛላችሁ እላቸዋለሁ:: በተለይ የማውቃቸውን ሰነፍና ጎበዝ ተማሪዎች አንድ ላይ እንዲቀመጡ ለማድረግም ሞክሬያለሁ:: |
| ሱፐርቫይዘር | ጥሩ ነው:: በምታስተምርበት ጊዜ ኖት ትይዙልኛላችሁ ስትል ሰምቼሃለሁ:: ኖቱን የሚይዙልህ ላንተ አይደለም አይደል? |
| የተማሪ አስተማሪ | ለራሳቸው ነው እንጂ |
| ሱፐርቫይዘር | እኮ እኔም የምልህ እሱን ነው:: ደብተራችሁን አውጥታችሁ ይህንን ኖት ፃፉ ብትላቸው ጥሩ አይመስልህም:: |
| የተማሪ አስተማሪ | በጣም እስማማለሁ:: |
| ሱፐርቫይዘር | ለመሆኑ የእንግሊዝኛና የአማርኛ አፃፃፍ ልዩነት ያለው ይመስልሃልን? |
| የተማሪ አስተማሪ | እኔ ልዩነቱ አይታየኝም:: |
| ሱፐርቫይዘር | ቢያንስ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ልዩነት ያለው አይመስልህም? |
| የተማሪ አስተማሪ | እሺ ስጽፍ የተሳሳትኩት ነገር ነበርን? |
| ሱፐርቫይዘር | አማርኛ ስትጽፍ ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ እየተጠቀምክ ቢሆን ጥሩ ይሆናል:: ስለስርዓተ ነጥብ ተምረሃል አይደል:: ከተማሩ ደግሞ አገልግሎቱን በጽሁፋችን ውስጥ በመጠቀም ማሳየት ይጠበቅብናል ማለት ነው:: እስኪ ና ወደዚህ "ዲ" የምትለዋን ሆሄ ፃፍልኝ ጥሩ ነው አሁን ደህና አድርገህ ፃፍካት ክፍል ውስጥ ስታስተምር ደጋግመህ ስትጽፍ |

በትክክል አላስቀመጥካትም። ተመልሰህ ስትገባ ጥቁር ሰሌዳ ላይ የፃፍካትን "ዲ" ታያታለህ።

የተማሪ አስተማሪ እሺ አያታለሁ።

ሱፐርቫይዘር ሌላው አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ ማለት ምን ማለት ነው ተብለህ ለተጠየቅከው ጥያቄ ምን የሚልመልስ ነበር የሰጠኸው?

የተማሪ አስተማሪ አንተ ትበልጥ አንተ ትበልጥ ብዬ

ሱፐርቫይዘር እኔ አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ ማለት አንተ ያልከው ፍቺ ያለው አይመስለኝም። መተዛዘንን የሚገልፅ ነው የሚመስለኝ እርግጠኛ ያልሆንበትን መልስ ለተማሪዎች መስጠት ተገቢ አይሆንም። ምናልባት ለጊዜው ከከበደን አንብበንና ሰው ጠይቀን በመምጣት መልሱን መንገር እንደለብን መገንዘብ ያስፈልጋል።

የተማሪ አስተማሪ እሺ አስተያየትሽን ተቀብያለሁ።

ሱፐርቫይዘር በጣም ጎበዝ በተረፈ ከዚህ በበለጠ ልታሻሽል እንደበትችል አምናለሁ። በርታ።

## ውይይት 2

ሱፐርቫይዘር ክፍሉን በደንብ ተቆጣጥረሽዋል ይሁን እንጂ የምታስተምሪውን ነገር በደንብ ተዘጋጅተሽበት የመጣሽ አይመስለኝም። እስኪ ለማንኛውም አንዳንድ አስተያየቶችን ልስጥሽ። በመጀመሪያ እኔ ወደክፍል ስገባ መርጃ መሳሪያ ለማምጣት ወጣሽ። የእኔ መምጣት አይደለም መርጃ መሳሪያ እንድትጠቀሚ የሚያደርግሽ። በዕለታዊ ዕቅድሽ መጠቀም ያለብሽ መሆኑን ከጠቆምሽ ብቻ ነው ልትጠቀሚ ይገባሽ የነበረው። ገና ካርታውን አምጥተሽ ስትሰቅይው ስለቅኝ ግዛት ልታስተምሪ መስሎኝ ነበር። ነገር ግን ስለ ካርታ ምንነትና ጥቅም ነበር ያስተማርሽው አይደል?

የተማሪ አስተማሪ አዎን።

ሱፐርቫይዘር ታዲያ ስለካርታ ምንነትና ጥቅም ለማስተማሪያነት ባመጣሽው ካርታ ተጠቅመሽ ለመግለጽ የሞከርሽው ምን ምን እንደነበር ትዝ ይልሻል Subject Matterun በቅድሚያ ማወቅ ይጠበቅብሻል።

ሌላው ድምጽሽን ከፍ አድርገሽ ለማስተማር ሞክሪ ምክንያቱም ወደፊት በጣም በርካታ ተማሪዎችን በምታስተምሪበት ወቅት በዚህ መልኩ የምታስተምሪ ከሆነ ሊያዳምጡሽ አይችሉም። ጥያቄ በምትጠይቂበት ጊዜ ከኋላ የተቀመጡትንም ይሁን የምትሰጭው ምሳሌ ግልጽና የማያሻማ መሆን ይጠበቅበታል።

ዛሬ እንዳየሁሽ ሁሉ ነገር የተምታታ ትምህርት ነው ያስተማርሽው ተማሪዎች መምህራን የተናገሩት ሁሉ ልክ ነው ብለው ያስባሉ፡፡ ስለዚህ mislead ባታደርጊያቸው መልካም ይመስለኛል፡፡ ለመሆኑ የክፍል መምህርቷ እዚህ ግቢ የለችምን፧ ነበረች፡፡

የተማሪ አስተማሪ ሱፐርቫይዘር

በጣም የሚያስቸግርሽ ነገር ካለ እኮ እሷንም መጠየቅ ትችይ ነበር፡፡ ለማንኛውም ወደ ክፍል ከመግባትሽ በፊት ኖት ብታዘጋጅና ደጋግመሽ በማንበብ ስለምታስተምሪው ትምህርት በቂ ግንዛቤ ቢኖርሽ መልካም ነውና ልታስቢበት ይገባሻል፡፡ ጨርሻለሁ ወደ ክፍልሽ ልትገቢ ትችያለሽ፡፡

## አባሪ ፬

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## ድህረ ምረቃ ት/ቤት

## በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሰርተፍኬት /10+1/ መርሃ ግብር ዕጩ መምህራን የሚሞላ መጠይቅ

## /ሚያዚያ 1997 ዓ.ም/

ውድ ዕጩ መምህራን!

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ በኮ.መ.ት.ኮ የሰርተፍኬት /10+1/ መርሃ ግብር የፕራክቲከም፣የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥን አተገባበርን በተመለከተ የእናንተን አስተያየት ማሰባሰብ ነው:: ጥናቱ ይዞት የተነሳውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ይችል ዘንድ እናንተ በመጠይቁ ለቀረቡላችሁ ጥያቄዎች የምትሰጡት መልስ እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው:: ስለዚህ በሁለት ክፍል ተለይተው የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና አንብባችሁ ተገቢውን መልስና አስተያየት በመስጠት የበኩላችሁን አስተዋፅኦ ታደርጉ ዘንድ በትህትና ትጠየቃላችሁ::

የትምህርት ጊዜያችሁን በመውሰድ ይህንን መጠይቅ በመሙላት ከተባበራችሁኝ ከልብ ላመሰግናችሁ እወዳለሁ::

በመጠይቁ ላይ ስምን መፃፍ አስፈላጊ አይደለም::

ክፍል አንድ:- አጠቃላይ መረጃ

ከተራ ቁጥር 1-3 ለተሰጡት ጥያቄዎች ተገቢ የሆኑ መረጃዎችን በባዶ ቦታዎች ላይ በፅሁፍ አስፍሩ:: ለጥያቄ 4 ደግሞ የምትመርጡትን መልስ በማክበር አመልክቱ

1. ዕድሜ
2. ፆታ
3. የ10ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ውጤት ________
4. ወደ ኮሌጅ የገባሁት ሀ. ተወዳድሬ ለ. ተመድቤ ሐ. መርጬ

 መ. በኮታ ሠ. አማራጭ አጥቼ

ክፍል ሁለት:- ፕራክቲከምን የማስተማር ልምምድና ሱፐርቪዥንን በተመለከተ

በ"ሀ"፣ በ"ለ" እና "ሐ" ስር ለቀረቡት ጥያቄዎች አማራጮች ተሰጥተዋል:: በጣም እስማማለሁ =5፣እስማማለሁ፣ለመወሰን እቸገራለሁ=3፣አልስማማም=2፣ ፈጽሞ አልስማማም=1 ነጥብ ዋጋ ይይዛሉ::

በዚሁ መሠረት በመረጣችሁት መልስ ትይዩ የ"✓" ምልክት በማድረግ አመልክቱ::

ሀ. ፕራክቲከም በተመለከተ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | ለፕራክቲከም ወደ ት/ቤቶች ከመሔዳችን በፊት ስለፕራክቲከም ምንነት በቂ ገለፃ ተደርጎልናል:: | | | | | |
| 2 | ከፕራክቲከም መልስ የምናቀርበውን ሪፖርት እንዴት ማዘጋጀት እንዳለብን ተገልፆልናል:: | | | | | |
| 3 | ሱፐርቫይዘሬን የማገኘው ያዘጋጀሁትን ሪፖርት ለሰጠው ብቻ ነው:: | | | | | |
| 4 | ሱፐርቫይዘሬ ያዘጋጀሁትን የፅሁፍ ሪፖርት በሚገባ በማንበብ ገንቢ የሆኑ አስተያየቶችን ሰጥቶኛል:: | | | | | |
| 5 | ከሱፐርቫይዘሬ ጋር በየዙሩ በመገናኘት ባቀረብኩት ሪፖርት ላይ ውይይት አድርገናል:: | | | | | |
| 6 | ለፕራክቲከም ወደ ተመደብኩበት ት/ቤት በመጀመሪያ ቀን ይዞኝ የሄደው ሱበርቫይዘሬ ነው:: | | | | | |
| 7 | ሱፐርቫይዘሬ በየጊዜው በቅርብ እየተገኘ ይረዳኛል:: | | | | | |
| 8 | ሱፐርቫይዘሬ ለእኔ ያለው ግምት ዝቅተኛ ነው:: | | | | | |
| 9 | ሱፐርቫይዘሬ ወደ ተመደብኩበት ት/ቤት ብቅ ብሎ አያውቅም | | | | | |
| 10 | ሱፐርቫይዘሬን በፕራክቲከም ወቅት በአካል አግኝቼው አላውቅም:: | | | | | |
| 11 | ሱፐርቫይዘሬን በፕራክቲከም ውጤቴን ለቢሮ ከማስተላለፍ በፊት አሳይቶኛል ተወያይተንበታል:: | | | | | |
| 12 | ከመጀመሪያው፣ ሁለተኛው፣ ሦስተኛውና አራተኛው ዙር የፕራክቲከም ምልከታዬ በኋላ ከሱፐርቫይዘሬ ጋር ውይይት አድርጌያለሁ:: | | | | | |
| 13 | ከሱፐርቫይዘሬ ጋር በምወያይበት ጊዜ የፍርሐት ስሜት ተሰምቶኝ ነበር:: | | | | | |
| 14 | በክፍል ውስጥ የቀሰምኩት ንድፈ ሐሳብና በፕራክቲክም ወቅት የተመለከትኩት ነገር ፈፅሞ የሚጣጣም አይደለም:: | | | | | |
| 15 | በክፍል ውስጥ ከሚሰጥ ንድፈ ሐሳብ ትምህርት ይልቅ ፕራክቲከም በቂ ግንዛቤ ያስጨብጣል:: | | | | | |
| 16 | ለፕራክቲከም የተመደብኩበት ት/ቤት ርዕስ መምህር አስፈላጊውን ትብብር አድርጎልኛል:: | | | | | |
| 17 | መደበኛ መምሕራን እኔን ለመርዳት ፈቃደኛ አይደሉም:: | | | | | |

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 18 | የተመደብኩበት ት/ቤት ማህበረሰብ በሙሉ ለእኔ ያለው ግምት ዝቅተኛ ነው:: | | | | | |
| 19 | መደበኛ መምህራን ኮሌጁ ባዘጋጀው የመገምገሚያ መስፈርት መሠረት ከገመገመኝ በኋላ በድክመትና ጥንካሬዬ ዙሪያ አወያይተውኛል:: | | | | | |
| 20 | ለፕራክቲከም በተመደብኩበት ት/ቤት በርካታ ችግሮች ገጥመውኛል:: | | | | | |
| 21 | የገጠሙኝን ችግሮች በመፍታት ሂደት ሱፐርቫይዘሬና ት/ቤቱ ማህበረሰብ ያደረጉልኝ የነበረው እገዛ ከፍተኛ ነው:: | | | | | |
| 22 | ለፕራክቲከም ወደ ተባባሪ ት/ቤት በሄድኩ ጊዜ ሁሉንም የክፍል ደረጃዎች የመጎብኘት ዕድል ገጥሞኛል:: | | | | | |
| 23 | ሱፐርቫይዘሬና መደበኛ /ነባር/ መምህራን በአንድ ላይ ሆነው በነበረኝ የፕራክቲከም ቆይታ ዙሪያ አወያይተውኛል:: | | | | | |
| 24 | በአራቱም ፕራክቲከም ከሱፐርቫይዘሬ በተሰጠኝ ውጤት ተደስቻለሁ:: | | | | | |
| 25 | በአጠቃላይ ከፕራክቲከም ምልከታዬ ከመደበኛ ተማሪዎች ባህሪያት ከመምህሩ የማስተማር ዘዴና የዕለታዊ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት ጋር ተዋውቄያለሁ:: | | | | | |
| 26 | ፕራክቲከሙን በተመለከተ ሌላ ለመግለፅ የምትፈልገው ነገር አለን? ካለ በአጭሩ በፅሁፍ ግለፅ:: | | | | | |

ለ. የማስተማር ልምምድን በተመለከተ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1. | ለማስተማር ልምምዱ የተመደበው 4 ሳምንት በቂ ነበር:: | | | | | |
| 2. | የማስተማር ልምምዱ በጣም አስፈላጊ ነው:: | | | | | |
| 3. | ፕራክቲከሙና የማስተማር ልምምዱ ተደጋጋፊዎች በመሆናቸው ጠቀሜታቸው የጎላ ነው:: | | | | | |
| 4. | በፕራክቲከም ወቅት ያደረኩት ምልከታ ለማስተማር ልምምድ በሚደረግበት ጊዜ ትልቅ እገዛ አድርጎልኛል:: | | | | | |
| 5. | በማስተማር ልምምድ ወቀት ሱፐርቫይዘሬ በዕቅድና በፕሮግራም እየተመራ ለሦስት ጊዜ ያህል ጎብኝቶኛል:: | | | | | |
| 6. | ነባር መምህራን በማስተማር ልምምድ ወቅት በክፍል ውስጥ በመገኘት እገዛ አላደረጉልኝም:: | | | | | |
| 7. | በማስተማር ልምምድ ወቅት የተባባሪ ት/ቤቱ መምህር እገዛ የጎላ ነበር:: | | | | | |
| 8. | በክፍል ውስጥ የቀሰምነው ንድፈ ሐሳብ የማስተማር ልምምዱን በአግባቡ ለማከናወን ረድቶኛል:: | | | | | |
| 9. | የማስተማር ልምምድ ንድፈ ሐሳብን ወደ ተግባር ለመለወጥ አያስችልም:: | | | | | |

10. የማስተማር ልምምዱን በተመለከተ ሌላ መግለጽ የምትፈልገው አስተያየት ካለ በአጭሩ ፃፍ::

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------

ሐ. ሱፐርቪዥኑን በተመለከተ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1. | በድህረ ማስተማር ውይይት ወቀት ሱፐርቫይዘር ከሚገባው በላይ ትኩረት የሰጠው ለጠንካራ ጎኔ ነበር:: | | | | | |
| 2. | ሱፐርቫይዘሬ ከፕራክቲከምና ከማስተማር ልምምድ በኋላ የሚያቀርብልኝ ሐሳብ ተቀባይነት አልነበረውም:: | | | | | |
| 3. | ሱፐርቫይዘሬ ሊጎበኘኝ እንደሚመጣ በቅድሚያ ያሳውቀኛል:: | | | | | |
| 4. | ከሱፐርቫይዘሬ ጋር በቂ የመወያያ ጊዜ አልነበረኝም:: | | | | | |
| 5. | ሱፐርቫይዘሬ የማስተማር ልምምድ ወደማደርግበት ት/ቤት የሚመጣው እኔን ለመደገፍና ለማበረታታት ሳይሆን ለመገምገመ | | | | | |
| 6. | ከሱፐርቫይዘሬ ያገኘሁት ምግበ መረጃ የማስተማር ብቃቴን እንዳሻሽል ትልቅ እገዛ አድርጎልኛል:: | | | | | |
| 7. | የተማሪ አስተማሪዎች የሚገመገሙት አንድ የትምህርት ይዘትን መሠረት በማድረግ ነው:: | | | | | |
| 8. | በድህረ ማስተማር ውይይት ወቅት ሱፐርቫይዘሬ ተናጋሪ እኔ አድማጭ ነበርኩ:: | | | | | |
| 9. | ሱፐርቫይዘሬ አማራጭ የማስተማር ዘዴዎችን እንድፈጽም አበረታቶኛል:: | | | | | |
| 10. | ሱፐርቫይዘሬን እንደጓደኛና የሥራ ባልደረባዬ አየዋለሁ:: | | | | | |

11. ስለነበረው የሱፐርቪዥን አተገባበር ሌላ ለመግለጽ የምትፈልገው ነገር ካለ በአጭሩ በጽሁፍ ግለጽ::

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

አመሰግናለሁ::

# አባሪ ፩

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
## ድህረ ምረቃ ት/ቤት
## በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሰርተፍኬት /10+1/
## መርሃ ግብር ሱፐርቫይዘሮች የሚሞላ መጠይቅ
## /ሚያዝያ 1997 ዓ.ም/

ውድ ሱፐርቫይዘሮች!

የዚህ ጥናት ዓላማ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የፕራክቲከም፣የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥን አተገባበርን በመፈተሽ ጠንካራና ደካማ ጎኑን ለመጠቆም የሚያስችሉ መረጃዎችን ማሰባሰብ ነው:: ስለዚህ ቀጥሎ በሶስት ክፍል ተለይተው የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥንቃቄ በማንበብ ተገቢውን ምላሽ በመስጠት ትተባበሩኝ ዘንድ በአክብሮት እጠይቃለሁ::

ውድ ጊዜአችሁን በመስዋት ስላደረጋችሁልኝ ትብብር ከልብ አመሰግናለሁ::

በመጠይቁ ላይ ስምን መፃፍ አያስፈልግም::

ክፍል አንድ:- አጠቃላይ መረጃ

ከተራ ቁጥር 1-5 ለተሰጡት ጥያቄዎች ተገቢ የሆኑ መረጃዎችን በባዶ ቦታዎቹ ላይ በጽሁፍ አስፍሩ::

1. የትምህርት ደረጃ ______________
2. የስልጠና መስክ ______________
3. የአገልግሎት ዘመን ______________
4. ስለፕራክቲከም ወይም ሱፐርቪዥን ስልጠና ወስደዋልን? ______________
5. ከፕራክቲከም በተጨማሪ የሚያስተምሩት "ክሬዲት ሐወር" ብዛት ______

ክፍል ሁለት:- ቀጥሎ ፕራክቲከምን፣ የማስተማር ልምምድንና ሱፐርቪዥንን

በተመለከተ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ይሆናሉ ተብለው አምስት አምስት አማራጮች ተሰጥተዋል:: እነሱም:- በጣም እስማማለሁ=5፣ እስማማለሁ=4፣ ለመወሰን እቸገራለሁ =3፣ አልስማማም=2 እና ፈጽሞ አልስማማም=1 ነጥብ ይይዛሉ:: በዚሁ መሠረት በመረጣችሁት መልስ ትይዩ የ"✓" ምልክት በማድረግ አመልክቱ::

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | ያለብኝ የሥራ ጫና የፕራክቲከሙንና የማስተማር ልምምድ አተገባበሩን በአግባቡ ለመከታተል እንዳልችል አድርጎኛል:: | | | | | |
| 2 | የተማሪ አስተማሪዎች ለፕራክቲከም/ለማስተማር ልምምድ ከመውጣታቸው በፊት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ገለፃ አደርጌላቸዋለሁ:: | | | | | |
| 3 | የተማሪ አስተማሪዎች በፕራክቲከም ወቅት የተገነዘቡትን ነገር በጽሁፍ እንዴት ማቅረብ እንዳለባቸው ገልጨላቸዋለሁ:: | | | | | |
| 4 | በአራቱም ዙር ፕራክቲከም መጨረሻ ላይ ከተማሪ አስተማሪዎች ጋር ውይይት አላደረኩም:: | | | | | |
| 5 | በዕቅድና በፕሮግራም እየተመራሁ የእያንዳንዱን ተማሪ የማስተማር ልምምድ ለሶስት ጊዜ ያህል ጎብኝቻለሁ:: | | | | | |
| 6 | የተማሪ አስተማሪዎች በየዘ□ሩ የሚያቀርቡትን የጽሁፍ ሪፖርት በማንበብ ተገቢውን ምግበ መረጃ ሰጥቻለሁ:: | | | | | |
| 7 | የማስተማር ልምምዱን ለመጎብኘት እመጣበት የነበረውን ጊዜ ለተማሪ አስተማሪዎች በቅድሚያ አላሳውቅም:: | | | | | |
| 8 | የተማሪ አስተማሪዎች ለፕራክቲከም ወደ ተመደቡበት ት/ቤት ይገኑ በመሄድ ከት/ቤቱ ማህበረሰብ ጋር አስተዋውቄያለሁ:: | | | | | |
| 9 | የተማሪ አስተማሪዎችን የፕራክቲከምና የማስተማር ልምምድ ውጤት ለሬጅስትራር ከማስረከቤ በፊት እንዲያዩት አድርጌያለሁ:: | | | | | |
| 10 | የተማሪ አስተማሪዎች በፕራክቲከም ወቅት የተገነዘቡትን ነገር በቃል ካቀረቡ በኋላ አስተያየት ሰጥቻቸዋለሁ:: | | | | | |
| 11 | ከማስተማር ልምምድ በኋላ በሚደረግ ውይይት ወቅት የተማሪ አስተማሪዎች ፎግዴታ ከእኔ መመሪያና ምክር ሊያገኙ ይገባል ብዬ አላምንም:: | | | | | |
| 12 | በድህረ ማስተማር ልምምድ ወቅት በሚደረግ ውይይት የተማሪ አስተማሪዎች ዘና እንዳ>ሉ አደርግ ነበር:: | | | | | |
| 13 | ለፕራክቲከምና ማስተማር ልምምድ መሳካት ከት/ቤቱ ነባር መምህራን ጋር በመመካከር ሰርቻለሁ:: | | | | | |
| 14 | ኮሌጁ ካዘጋጀው የመገምገሚያ ቅጽ ውጭ አልጠቀምም:: | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 15 | በድህረ ማስተማር ልምምድ ውይይት ወቅት የተማሪ አስተማሪዎችን ስብዕና ላለመንካት ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርጌአለሁ:: | | | | | |

ክፍል ሦስት፣ <u>በጽሁፍ የሚመለሱ ጥያቄዎች</u>

16. በሱፐርቪዥን ሂደት ውስጥ ምን አይነት የመገምገሚያና የመከታተያ መንገድ ይከተሉ ነበር?

17. ሌላ ፕራክቲከሙንና የማስተማር ልምምዱን በተመለከተ መግለጽ የሚፈልጉት ሐሳብ ካለ በጽሁፍ ይግለጹ::

አመሰግናለሁ::

# አባሪ ፮

## የክፍል ምልከታ መከታተያ ቅጽ ናሙና

ክፍል ______________ ሴክሽን ______________

የተማሪ አስተማሪው ስም ______________ የተማሪ ቁጥር ______________

የሱፐርቫይዘር ስም ______________ ቀን ______________

አማራጭ መልሶች የሚይዙት ውጤት 4=በጣም ጥሩ፣ 3=ጥሩ፣ 2=በቂ፣ 1=ዝቅተኛ

| ተ.ቁ | መመዘኛ ነጥቦች | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሀ. ዝግጅት | | | | |
| 1 | የተማሪ አስተማሪው የዕለት ትምህርት ዕቅድ አዘጋጅቷል:: | | | | |
| 2 | ዝግ ያልሆኑና ተግባቦታዊ ተግባራትን አመጣጥኖ በተገቢው ሁኔታ አዘጋጅቷል:: | | | | |
| 3 | መልመጃዎቹና ተግባራቱን በአውድ ለማቅረብ ሞክሯል | | | | |
| 4 | ዕቅዱ ነባራዊ የቋንቋ አጠቃቀም ይታይበታል:: | | | | |
| | ለ. የቋንቋ አጠቃቀም | | | | |
| 1 | የተማሪ አስተማሪው ታላሚውን ቋንቋ በተገቢው መንገድ ይጠቀማል:: | | | | |
| 2 | የቋንቋ አጠቃቀሙን ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር ለማጣጣም ይሞክራል:: | | | | |
| | ሐ. የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት | | | | |
| 1 | የትምህርት ዕቅድ በግልጽና በጥሩ ሁኔታ አዘጋጅቶ አቅርቧል:: | | | | |
| 2 | የመረጣቸው የትምህርት ይዘቶችና መልመጃዎች ዓላማውን ለመተግበር አስችለውታል:: | | | | |
| 3 | ከአንዱ መልመጃ ወደ ሌላው መልመጃ ግልጽ በሆነ መንገድ ይሸጋገራል:: | | | | |
| 4 | ያዘጋጀውን የትምህርት ይዘት በተሰጠው ሰዓት ውስጥ አቅርቧል:: | | | | |
| 5 | የተማሪ አስተማሪውና የተማሪው ንግግር ተመጣጣኝ ነው:: | | | | |
| 6 | ለተማሪዎቹ የሚሰጠው ምግበ መረጃ ዓይነትና መጠን በቂ ነው:: | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 7 | ባህላዊ ሁኔታዎችን ከትምህርቱ ጋር አቀናጅቶ አቅርቧል። | | | | |
| | **መ. የክፍል ቁጥጥር** | | | | |
| 1 | መልመጃዎችን በትናንሽ ቡድኖች/በብጤ ለማሰራት ሙከራ አድርጓል። | | | | |
| 2 | የተማሪዎች አቀማመጥ ለመማር ማስተማሩ እንቅስቃሴ የተመቸ አድርጎታል። | | | | |
| 3 | የመርጃ መሣሪያዎችን በአግባቡ ይጠቀማል። | | | | |
| 4 | ለሁሉም ተማሪዎች እኩል ትኩረት ይሰጣል። | | | | |
| 5 | ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያደርጋል። | | | | |
| | **ሠ. የክፍል አውድ** | | | | |
| 1 | ተማሪዎች በንቃት ይሳተፋሉ። | | | | |
| 2 | የመማሪያ ክፍሉ ሞቅ ያለ ውይይት ይታይበት ነበር። | | | | |
| 3 | ውይይቱ ለተማሪዎች ክፍት ሆኖ የተማሪዎቹ ሐሳብ ተቀባይነት ነበረው። | | | | |
| 4 | የተማሪዎችን ችግር የመፍታት ልዩ ስሜት ይታየበት ነበር። | | | | |
| | **ረ. ቴክኖሎጂን መጠቀም** | | | | |
| 1 | ትምህርቱን በቴክኖሎጂ (በቪዲዮ፣ በቴፕ፣ በፕሮጀክተር) ለማቅረብ ይጥራል። | | | | |
| 2 | ቴክኖሎጂዎችን የማያገኝ ከሆነ ሌሎች አማራጮችን ይጠቀማል። | | | | |
| 3 | ቴክኖሎጂዎችን በክፍል ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከክፍል ውጭ ጭምር ይጠቀማል። | | | | |

## አስተያየቶች

ጠንካራ ጎኖች ..............................................................................................

ደንማ ጎኖችን ለማሻሻል መደረግ ያለባቸው ነጥቦች ..........................................

..............................................................................................................

ምንጭ:- **Haroldfs (2001) Language Classroom Observation Form**.

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናት የራሴ ሥራ መሆኑንና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ምንጮ
የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡

ስም ተሰጠ አሰፋ

ፊርማ __________

ቦታ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም